# የሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙሃን

## እና

# የሥነ ሕዝብ መረጃ፣ ትምህርት፣ መገናኛና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ማስተዋወቂ ዓውደ ጥናቶች ስንኝቶች

ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

## የ"ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙሃን" ዓውደ ጥናት ስንኝቶች (Proceedings)

ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት

*ቀይ መስቀል ማሰልጠኛ ማዕከል*
*ከየካቲት 7-9 ቀን 1992 ዓ.ም.*
*<u>አዲስ አበባ</u>*

# ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ ........ 1
1.1 ዳራዊ መረጃ ........ 1
1.2 የዓውደ ጥናቱ ዓላማዎች ........ 1
1.3 ተሳታፊዎች ........ 2
1.4 የዓውደ ጥናቱ መርሃ-ግብር ........ 2

2. የዓውደ ጥናቱ ስንኝቶች (Proceedings)........ 3
2.1 የመክፈቻ ንግግሮች ዐበይት ነጥቦች........ 3
2.2 የጥናት ወረቀቶች ጥቅል ሀሳብና በውይይቱ ወቅት የተነሱ ነጥቦች........ 5
ጉባዔ (Session) አንድ ........ 6
ጉባዔ ሁለት ........ 9
ጉባዔ ሦስት........ 11
ጉባዔ አራት........ 15
ጉባዔ አምስት........ 18
ጉባዔ ስድስት........ 20
ጉባዔ ሰባት........ 23
ጉባዔ ስምንት........ 27
ጉባዔ ዘጠኝ........ 31

2.3 የቡድን ውይይት የመነጋገሪያ ሀሳቦችና ሪፖርቶች........ 33
2.3.1 የቡድን ውይይቱ ዓላማ........ 33
2.3.1 የቡድን ውይይቱ የመነጋገሪያ ሀሳብ........ 34
2.3.3 ቡድኖች ያቀረቧቸው ሪፖርቶች........ 34

2.4 የመዝጊያ ንግግር ........ 40

3. አባሪዎች........ 41
3.1 የመክፈቻ ንግግሮች........ 43
3.2 የጥናት ጽሑፎች........ 49
3.3 የዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ዝርዝር........ 167
3.4 የዓውደ ጥናቱ መርሃ-ግብር........ 174
3.5 የመዝጊያ ንግግር........ 176

# 1. መግቢያ

## 1.1 ዳራዊ መረጃ

የሥነሕዝብ ጉዳይ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዳለው በመታመኑ ከ1985 ወዲህ ብሔራዊ የሥነሕዝብ ፖሊሲ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ፖሊሲው የሕዝብ ብዛትን ከኢኮኖሚ እድገት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ዋና ዓላማው ነው። ዓላማውን ለመቀዳጀት የተካተቱትን ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች በአጠቃላይ ሕዝቡ፣ በተለይ ደግሞ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲገነዘቧቸውና እንዲያውቋቸው፣ ብሎም እንዲተገብሯቸው፣ ከቁሳዊ ሀብት አቅርቦትና ሥርጭት ጐን ለጐን፣ የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን (ኢትኮ) ፕሮግራም የላቀ ድርሻ አለው።

ለኢትኮ እንቅስቃሴዎች በኮሙኒኬሽን፣ በመገናኛ ብዙኃንና በኪነጥበብ መስኮች የተሠማሩ ባለሙያዎች ዋነኛ ተዋንያን ናቸው። ሕዝቡን በማሳወቅ፣ በማስተማርና በማዝናናት ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱና ሙያዊ ትስስር ያላቸው ጋዜጠኞችና የሥነጥበብ ባለሙያዎች ተልእኳቸውን በአግባቡ ለመወጣት ተከታታይ ሥልጠናና የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮችን መፍጠር ያስፈልጋል። እነዚህም በየጊዜው ያሉትን ዘመናዊ የባሕሪ ሳይንስ አስተሳሰቦችና ግኝቶች ለማወቅ፣ ቀደም ብለው የተሠሩ ሥራዎችን ለመገምገምና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ከተፈለገው ግብ ለመድረስ መልካም ዘዴዎች በመሆናቸው በሕዝቡ ዘንድ የሚፈለገውን ግንዛቤ ለመፍጠር፣ የአመለካከትና የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት እንደሚያግዙ ይታመናል።

በዚሁ መሠረት ብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት «ሥነሕዝብና መገናኛ ብዙኃን» (Population and Mass Media) በሚል ርእስ በትያትር ጥበብ (ጸሐፊ ተውኔት፣ ተዋናይና አዘጋጅ፣...)፣ በመገናኛ ብዙኃን አውታሮች በኅትመት፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ጋዜጠኝነት ለተሠማሩና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ለሚሠሩ ባለሙያዎች የሦስት ቀን ዐውደ ጥናት ሰጥቷል። ዐውደ ጥናቱ ከየካቲት 7 እስከ 9 ቀን 1992 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ማሠልጠኛ ተቋም ተካሂዷል።

## 1.2 የዐውደ ጥናቱ ዓላማዎች

ለሦስት ቀናት የተካሄደው ዐውደ ጥናት ዋና ዓላማ በሥነሕዝብ ጉዳይ ውስጥ ስለተካተቱት እሳቤዎች በጋዜጠኝነትና በትያትር ጥበብ የተሠማሩ ባለሙያዎችን ግንዛቤ

የበለጠ በማጐልበት በየተሠማሩበት የሙያ መስክ ሕዝቡን በአግባቡ እያዝናኑ እንዲያሳውቁና እንዲያስተምሩ ለማድረግ ነው።

ዝርዝር ዓላማዎችም፡-

1. የመገናኛ ብዙኃንና የትያትር ጥበብ ሙያተኞች የሥነሕዝብ ኮሙኒኬሽን (Population Communication) (ፅንሰ ሐሳብ) ግንዛቤያቸውን ይበልጥ በማሳደግ ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት/ለመሥራት እንዲችሉ ማነሣሣት፣
2. የሥነሕዝብ ጉዳዮችን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙኃንና በትያትር ጥበብ መስኮች የተሠሩ ሥራዎችን በመገምገም ጠንካራና ደካማ ጐኖቻቸውን መፈተሽ፣
3. ባለሙያዎች የልምድ ልውውጥ በማድረግ የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ለመፍጠር እንዲቻል ጠቃሚ ሐሳቦችን እንዲያፈልቁ ማመቻቸት፣ እና
4. በጋዜጠኝነትና በትያትር ጥበብ የተሠማሩ ባለሙያዎች ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን ለሕዝቡ ለማስተማርና ለማሳወቅ ባደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለይቶ በማውጣት የመፍትሔ ሐሳቦች መጠቆም ናቸው።

## 1.3 ተሳታፊዎች

በዐውደጥናቱ ላይ ከ75 በላይ ተሳታፊዎች ተካፍለዋል። ተሳታፊዎቹ በማእከልና በክልሎች ከሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች፣ የትያትር ጥበብ ተቋሞች፣ የሥነሕዝብ ጽ/ቤቶች እና ከግል ድርጅቶች የተውጣጡ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ናቸው (የተሳታፊዎችን ዝርዝር በአባሪ 3 ይመልከቱ)።

## 1.4 የዐውደ ጥናቱ መርሐ ግብር

ለሦስት ቀናት የተካሄደው ዐውደ ጥናት የተለያዩ ጉዳዮችን ያስተናገደ ነበር። የመርሐግብሩ የመጀመሪያ ክፍል የመክፈቻ ሥነሥርዓትን ይመለከታል። በሁለተኛው ክፍል በሥነሕዝብ፣ ልማትና የአካባቢ ትስስር፣ በተዋልዶ ጤና፣ በሥነሕዝብና ኮሙኒኬሽን፣ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና በማኅበራዊ ግብይት (Social Marketing)፣ በትያትር ጥበብ (በኪነ ጥበብ) መስኮች ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች ያዘጋጇቸው ዘጠኝ የጥናት ጽሑፎች ተስተናግደዋል። እያንዳንዱ የጥናት ጽሑፍ ቀርቦ እንዳለቀ ተሳታፊዎች በጥናታዊ ጽሑፉ ላይ በመመሥረት ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ አስተያየት እንዲሰጡና አጠቃላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መድረኩ ክፍት ሆኗል። በዚህ

ወቅት የተለያዩ ሐሳቦች እየተነሡ ሰፊ ውይይት የተካሄደና ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፣ በዚህም የጋራ ግንዛቤ ለመጨበጥ ተችሏል።

ጥናታዊ ጽሑፎች በዚህ መልክ ከተጠናቀቁ በኋላ የሦስተኛው ቀን የከሰዓት በኋላ ጊዜ የቡድን ውይይት የተደረገበት ነው። ተሳታፊዎች በኅትመት መገናኛ ብዙኃን፣ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃንና በትያትር ጥበብ ሦስት ቡድኖች ተከፍለው ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን ለሕዝቡ እያዝናኑ ለማሳወቅና ለማስተማር ያከናወኗቸውን ተግባራዊ ሥራዎችና ያጋጠሙ ችግሮችን በመመርመር የተሻለ ሥራ ለማካሄድ እንዲቻል የመፍትሔ ሐሳቦችን ለአጠቃላዩ ውይይት አቅርበዋል። በመጨረሻም የጽ/ቤቱ ኃላፊ የመዝጊያ ንግግር አድርገዋል። መርሐ ግብሩ ተሳታፊዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚጋብዝ ነበር ማለት ይቻላል (መርሐ ግብሩ በአባሪ 3 ተያይዟል)።

## 2. የዐውደ ጥናቱ ስንኝቶች (Proceedings)

### 2.1 የመክፈቻ ንግግሮች ዐበይት ነጥቦች

በዐውደጥናቱ መክፈቻ ሥነሥርዓት ላይ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ንግግር አድርገዋል። አቶ ኀኑይ ምትኩ፣ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ የመግቢያ ንግግር አድርገዋል።

አቶ ኀኑይ የመገናኛ ብዙኃን፣ በተለይ የሥነሕዝብ ፖሊሲ ከታወጀ ወዲህ ሥነሕዝብ ነክ መልእክቶችን፣ በቂ ነው ባይባልም፣ አልፎ አልፎ እንደሚያስተላልፉና በሥነጥበብ መስክ ግን በቁጥር ከሚታወቁት እንቅስቃሴዎች በስተቀር ፕሮግራም ተይዞላቸው ወደተፈለገው ታዳሚ ያነጣጠሩ ተከታታይ ሥራዎች እንዳልተሠሩ ገልጸዋል። ከዚህ አንጻር ዐውደ ጥናቱ ጋዜጠኞችንና የትያትር ጥበብ ባለሙያዎችን ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያግዝ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

ዐውደ ጥናቱን በይፋ የከፈቱት ክብርት ወ/ሮ ብሥራት ጋሻውጠና፣ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ናቸው። ወ/ሮ ብሥራት በትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠው የሥነሕዝብና የቤተሰብ ኑሮ ትምህርት ተተኪውን ትውልድ በሥነሕዝብ ተግባራት እየኮተኮተ ለማሳደግ እንደሚያስችልና የነገይቱን ኢትዮጵያ የልማትና የእድገት ተስፋ የሚያለመልም

እንደሆነ አስታውቀዋል። ይሁን እንጂ በትምህርት፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በሌሎችም ተግባራት ላይ የተሠማራውን ሕዝብ ስለሥነሕዝብና ልማት ቅንጅት በማስገንዘብ ለስኬታማነቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ለማነሣሣት የጋዜጠኞችና የሥነጥበብ ባለሙያዎች ግዴታቸውን በወጉ መወጣት እንዳለባቸው ም/ሚኒስትሯ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥነሕዝብ ፖሊሲን በማስፈጸም ባከናወኗቸው ተግባራት ለዓለም አቀፍ ሽልማትና አድናቆት መብቃታቸውን ወ/ሮ ብሥራት በመጥቀስ የመንግሥትና የግል፣ የፌደራልና የክልል፣ እንዲሁም የትምህርት የመገናኛ ብዙኃን ለሥነሕዝብ ጉዳዮች የሚሰጡት ትኩረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።

ምክትል ሚኒስትሯ በትያትር ድርሰትና ትወና ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ኤድስንና የመሳሰሉ አሳሳቢ ጉዳዮችን፣ እንዲሁም ሥነሕዝብን ከልማትና አካባቢ ጋር እንዲያጣጥም ሕዝቡን እያዝናኑ የማስተማሩንና የማሳወቁን ተግባር ልዩ ትኩረት እንዲሰጡትና የመገናኛ ብዙኃንም እንዲተባበሯቸው ጥሪ አቅርበዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ፣ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ የሥነሕዝብ ፖሊሲ ይፋ ከተደረገበት ከ1985 ዓ.ም. ወዲህ በሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች ሕዝቡን በማስተማርና ግንዘቤ በመፍጠር የተደረጉ ጥረቶችን፣ የተገኙ ውጤቶችና ወደፊት ትኩረት የሚሰጣቸውን አቅጣጫዎች በሚመለከት ሰፊ ንግግር አድርገዋል። ዶ/ር ንጉሤ የሕዝብ እድገት በአገራችን የልማት ጥረትና ጥቅም ላይ ከሚውለው ሃብት ጋር ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዳለበት በመጠቆም፣ ሕዝቡ በማእከልም ሆነ በክልል ደረጃ ያለው ግንዛቤ ፖሊሲው ሲወጣ ከነበረው ከፍ ያለ እንደሆነ አሳውቀዋል። ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት የተካሄዱት የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን (IEC) ተግባራት አጠቃላይ ግንዛቤ ከመፍጠር አልፈው በሕዝቡ ዘንድ ትክክለኛ የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት ለወደፊቱ የተለየ ስልትና አሠራር ይዞ መጓዝ እንደሚያስፈልግ ካለፈው ተሞክሮ ለማወቅ መቻሉን ገልጸዋል።

ዶ/ር ንጉሤ ከዚህ ጋር በማያያዝ በሥነሕዝብ ጉዳይም ሆነ በሌሎች፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው እንቅስቃሴ *የምናስተምረው ማንን ነው? የምናስተምረውስ ምንድነው? የምናስተምረውስ እንዴት ነው?*

የሚያስተምረውስ ማነው? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ከመነሻው አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ካልተቻለ ድካማችን ሁሉ ውጤት አልባ እንደሚሆን አሳስበዋል። በዚህ መነሻነት የተቀየሰው ብሔራዊ የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራተጂ የታሰበውን ውጤት ሊያስገኝ እንዲችል፡-

- ማናቸውም የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ተግባራት በጋዜጠኝነትም ሆነ በሥነጥበባት መስክ በጥናት ላይ ተመሥርተው መዘጋጀት፣
- የአቀራረብ ስልታቸውም ሆነ የመልእክት ዝግጅታቸው ከአጠቃላይ ቅስቀሳና ግንዛቤ ይልቅ አድማጩን ወይም ተመልካቾቹን ለያይተው ለምሳሌ ለወጣቶች፤ ለሴቶች፤ ለባሎች በማለት እንደአስፈላጊነቱ በመነጣጠል ላይ ማነጣጠር፣ እና
- መልእክቶች ቀጥታ ጽሑፍ ከማንበብ ወይም በተለመደው የቅስቀሳ መንገድ ከመለፈፍና ከማዘጋጀት ይልቅ ስሜትን በሚስብ መልክ በጭውውትና በማዝናናት ማስተማር (Entertainment Education) መልክ መሠራጨት

እንደሚኖርባቸው አብራርተዋል። በመጨረሻም የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በጋዜጠኝነትና በትያትር ጥበብ ሙያ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ያካባቱ መሆናቸውን በመግለጽ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የሚያቀርቡት አስተያየት ለወደፊቱ ሥራ እጅግ ጠቀሜታ እንደሚኖረውና ትኩረትም እንደሚሰጠው አረጋግጠዋል።

## 2.2 <u>የጥናት ወረቀቶች ጥቅል ሐሳብና በውይይቱ ወቅት የተነሡ ነጥቦች</u>

ለሦስት ቀናት በተካሄደው ዐውደጥናት ላይ ከፍተኛ ባለሙያዎች በሙያ መስካቸው ዘጠኝ ጥናታዊ ጽሑፎች አቅርበዋል። ጥናታዊ ጽሑፎች ሥነሕዝብ፣ በልማትና በአካባቢ ሁኔታ ትስስር፣ ኮሙኒኬሽን የሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር የሚኖረው ሚና፣ በተዋልዶ ጤና፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በጐጂ ልማዳዊ ተግባሮች ረገድ የመገናኛ ብዙኃን ድርሻ፣ በማኅበራዊ ግብይት (Social Marketing)፣ ሥነጥበብ፣ ትያትር እና ድራማዎች ለሥነሕዝብ ጉዳዮች ባላቸው ፋይዳ ላይ ያተኮሩ ናቸው። በአብዛኞዎቹ ጽሑፎች ጽንሰ ሐሳብ ያመዘነ ቢሆንም አንዳንዶቹ በተግባር በመካሄድ ላይ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ለመዳሰስ ሞክረዋል። ጥናታዊ ጽሑፎች የጋዜጠኞችና የትያትር ጥበብ ባለሙያዎች በሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች አኳያ ሕዝብ ተገንዝቧቸውና ዕውቋቸው የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ እንዲያመጣ በሚያደርጓቸው የኢንፎርሜሽንና የትምህርት ፕሮግራም ወይም የኢንተርቬንሽን ጥረት አጋዥና ጠቃሚ እንደሆኑ

ታስበው የተመረጡ ናቸው:: የጥናት ወረቀቶቹ አጠቃላይ ሐሳብና በውይይቱ ላይ የተነሡ ዐበይት ነጥቦች ቀጥሎ በዘጠኝ ጉባኤ (Session) ተከፍለው ቀርበዋል::

## ጉባኤ (Session) አንድ

### 1.1 <u>የጥናታዊ ጽሑፉ ጥቅል ሐሳብ</u>

### ሥነሕዝብ፣ ልማትና አካባቢ በኢትዮጵያ

*አቶ ሲሳይ ወርቁ፣ በብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የፕላን ዝግጅት፣ ሥልጠና፣ ክትትልና ግምገማ ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ*

ጥናታዊ ጽሑፎች መቅረብ የጀመሩት አቶ ሲሳይ ባዘጋጁት ጥናት ጽሑፍ ነው:: የአቶ ሲሳይ ጽሑፍ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕዝብ እድገት የታየበት እንደሆነ በመግለጽ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሕዝብ እድገት ፈጽሞ አይታይም? እድገት ይቀንሳል? ወይስ እስካሁን ያልታየ ከፍተኛ እድገት ይታያል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሣት ይጀምራል:: ይህን መነሻ በማድረግ ጽሑፉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት ላይ ተጽእኖ እንደሚኖረው ቢታሰብም በተወሰነ መጠን የሚኖረው የሕዝብ እድገት ከልማት ጥረቶች ጋር ስለማይመጣጠንና ሕዝብና ልማትም የተቆራኙ ስለሆኑ የኢኮኖሚ እድገትን በማፋጠን ዘለቄታ ያለው ልማት ለማምጣት የሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የሕዝብ ጉዳይን ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው:: ጽሑፉ አሁን ያለው 62 ሚሊዮን የሕዝብ ብዛት በአማካኝ በዓመት ቢያንስ 1.8 ሚሊዮን በመጨመር እ.ኤ.አ በ2030 129 ሚሊዮን እንደሚደርስ በመገመቱ ይህንን ሕዝብ ለመመገብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ፣ የሥራ እድል ለመፍጠር እንደማይቻል ይተነትናል::

የጥናት ጽሑፉ በሕዝብና በልማት መካከል ያለው ቁርኝትና ትስስር የሚጀምረው ከመሠረታዊ የዲሞግራፊ ባሕርያት (ወሊድ፣ ሞትና ፍልሰት) እና እነዚህም ባሕርያት የሕዝብ ብዛትና የሕዝብ ቅንብር እና ሥርጭት እንደሚያስከትሉ ያብራራል:: የዲሞግራፊ ውጤቶችም በተለያየ መንገድ በልማት ሂደትና ውጤቶች ላይ፣ ማለትም በነፍስ ወከፍ የገቢ መጠን፣ በሥራ እድል፣ በትምህርት ተሳትፎ፣ በጤና ሽፋንና በአመጋገብ ደረጃ፣ እና በተፈጥሮ ሀብት ላይ አወንታዊ/አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ::

ጥናታዊ ጽሑፉ ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን እንዳልቻለች፣ የምግብ ዋስትናው ያልተረጋገጠ ከ30 ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብ እንዳላት፣ ጥራትና ብቃት ከግምት ውስጥ ሳይገባ የትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ፣ የጤና ሽፋን ከ45 በመቶ እንደማይበልጥ፣ ከሚገባ በላይ የታረሰ፣ የተጋጠ የእርሻና የግጦሽ መሬት እንዳላት በመዘርዘር ይህንንም ችግር ለመቅረፍ የተደረገው ጥረት አነስተኛ እንደሆነ ይተነትናል። ከዚህ አኳያ በአገሪቷ ዘላቂ ልማትን ለማስፈን በየደረጃው ያሉትን የፖሊሲ፣ የእቅድ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች፣ እንዲሁም ሕዝቡን በቅንጅት ሊያሳትፍ የሚችል ሥነሕዝብን፣ ልማትንና አካባቢን ያዋሐደ አንድ ወጥ አገር አቀፍ መርሐ ግብር ነድፎ በአስቸኳይ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ በማሳሰብ አጠቃሏል።

## 1.2 ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች

### ሥነሕዝብና አካባቢ

በሥነሕዝብ፣ በልማትና በአካባቢ መካከል ያለው ቁርኝነት ጥብቅ ቢሆንም በሥነሕዝብ፣ በአካባቢና በተፈጥሮ ሃብት (Environment and Natural Resources) መካከል ያለው ከፍተኛ ትስስር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ሐሳብ ተሰንዝሯል። አካባቢና የተፈጥሮ ሃብት ለሁሉም መሠረቶች ስለሆኑ በሕዝብ እድገት፣ በድህነት፣ በአካባቢ መራቆትና መበከል፣ እንዲሁም በተፈጥሮ ሃብት መሸርሸር መካከል ያለው ትስስር በወጉ መፈተሽና የሚወሰደውም እርምጃ ይህንኑ መሠረት ማድረግ እንዳለበት ተገልጿል።

### ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሕዝብ እድገት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዓለም ላይም ሆነ በአገራችን ብዙ ሕዝብ መጨረሱን ከቀጠለ የሕዝብ እድገትን ስለሚቀንስ ስለሕዝብ እድገት መጨነቅና ማሰብ እንደማያስፈልግ የሚያስቡ ወገኖች ስላሉ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ማብራሪያ ተጠይቋል። 20ኛው ምእተ ዓመት ካወረሰን ጠንቀኛ ችግር አንዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንደሆነና በኢትዮጵያ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዲሞግራፊያዊ ባሕርያትና በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ተጽኢኖ እንደሚያሳድር በማብራራት በተለይ ከዲሞግራፊ ባሕርያት አንጻር የሚያሳድረው ተጽእኖ በኢትዮጵያ ባይጠናም በ13 የአፍሪካ አገሮች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ደረጃው ቢለያይም ቫይረሱ በሞት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ከፍተኛ ቢሆንም በወሊድ ላይም ተጽእኖ ስለሚኖረው የሕዝብ እድገትንና የተፈጥሮ እድገትን (Natural Increase) ይቀንሳል። በኢትዮጵያ በዚህ ረገድ

የተጠና ጥናት ባይኖርም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የመራቢያ ጊዜ ከ8-10 ዓመት እና አንዲት ሴት የምትወልዳቸው ሕፃናት መጠን ወደ 6.7 ስለሆነ በሞትና በወሊድ መጠን ላይ ተጽእኖ ቢኖረውም የሕዝብ እድገት ጨርሶ አይኖርም፣ ወደሚል መደምደሚያ ስለማያደርስ የሕዝብ እድገት እንደሚኖር ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ተወስቷል። የሥነሕዝብ ፖሊሲ አስፈላጊነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥረቶች ከሕዝብ እድገት ጋር ማጣጣምን ግቡ ያደረገ እንደመሆኑ መጠን ይህም ሁኔታ በኤድስ አሉታዊ ተጽእኖ ይቀረፋል፣ ማለት እንደማይሆን ተጠቅሷል።

ስለዚህም ኤድስ ዲሞግራፊያዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን የሚያሳድር እንደመሆኑ የሥነሕዝብ ፖሊሲን አስፈላጊነት ቦታ የሚያሳጣ ሊሆን እንደማይችል ግንዛቤ ተገኝቷል። በሥነሕዝብ ረገድ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ኤድስ ቢሆንም ሕዝብን በማሳወቅ ሂደት ውስጥ ሁለቱ ራሳቸውን ችለው በወጉ እንዲታዩ የማድረግ ኃላፊነት የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች መሆኑ ተገልጿል።

<u>ሥነሕዝብን በረጅም ጊዜ ብቻ ለመፍታት ማሰብ</u>

የሥነሕዝብን ጉዳይ ጨምሮ በአገሪቷ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት የሚሰጠው ትኩረት በወጉ የተጤነ እንዳልሆነ ሐሳብ ቀርቧል። ለዚህም ትኩረት የሚሰጣቸውን ችግሮች በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ከፋፍሎ ማየት ያስፈልጋል። አንዳንዶቹ በአጭር ጊዜ ብቻ ይፈታሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በረጅም ጊዜ የሚፈቱ ይሆናሉ። ይህ ማለት ግን አንገብጋቢ ችግሮች ብቻ ቅድሚያ እየተሰጣቸው የረጅም ጊዜዎቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ አይፈተሹም፣ ማለት አይደለም። ከዚህ አንጻር የሥነሕዝብ ጉዳይን የረጅም ጊዜ ጥረትና በረጅም ጊዜ ብቻ እንደሚፈታ በማሰብ የመተው አዝማሚያ በተለያዩ አካላት ስለሚታይ የሥነሕዝብ ጉዳይ የረጅም ጊዜ ችግር ቢሆንም የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ መርሐግብሮች ተቀይሰው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊኖር እንደሚገባ ተብራርቷል።

## ጉባኤ ሁለት

### 2.1 የጥናት ጽሑፉ ጥቅል ሐሳብ

#### የሥነሕዝብ ኮሙኒኬሽን

*አቶ አስረስ ከበደ፣ በብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ አማካሪ*

በአቶ አስረስ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ሁለት ዋና ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያው ክፍል ስለሥነሕዝብ ኮሙኒኬሽን ምንነትና ትኩረት የሚሰጣቸው አላባውያን፣ ስለባሕሪ ለውጥ ምንነትና ደረጃዎች፣ ስለታላሚ ታዳሚ፣ ስለመገናኛ ዘዴዎች አይነቶች አመራረጥ ዐበይት ነጥቦች ተተንትነዋል። የሥነሕዝብ ኮሙኒኬሽን (Population Communication) በታለሙ ታዳሚዎች ዘንድ የባሕርይ ወይም የአመለካከት ለውጦች ማምጣትን ወይም ማግኘትን ዓላማ በማድረግ የኮሙኒኬሽን ቴክኒኮችን፣ አቅጣጫዎችንና ሂደቶችን አመቺና አሳታፊ በሆነ መልክ አዋሕዶ የሚጠቀምና ሥርዓት ባለውና በጥናት ላይ ተመሥርቶ የሚተገበር የአንድ አገር የልማት መርሐግብር አካል ነው፤ የሚለው ብያኔ የተሻለ እንደሆነ ይገልጻል።

ሁለተኛው ክፍል የብሔራዊ ሥነሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር ከሥነሕዝብና ኮሙኒኬሽን ጋር በተያያዘ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ይዘረዝራል። ፖሊሲውን ለማስፈጸም የተነደፈውን የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ለማካሄድ የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ያለመኖር፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ ሥራን አስከኖና ትኩረት ሰጥቶ ያለመሥራት፣ የምርምር እጥረት፣ የተወሰኑ ቢሆኑም የተሠሩት ያለመሠራጨት፣ የክትትልና የግምገማ ያለመኖር ዋና ችግሮች እንደሆኑ ተብራርቷል። በሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች የሚሰጠው ትምህርትና ኢንፎርሜሽንም በተዋልዶ መብት፣ በወጣቶች ተዋልዶ ጤና፣ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በተዋልዶ ጤና የወንዶች ተሳትፎ እና የሥነሕዝብ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን እንዲደግፉ በማነሣሣት ላይ እንዲያተኩሩ በአራተኛ አገራዊ ፕሮግራም መታሰቡን ጥናቱ ይጠቅሳል።

### 2.2 ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች

#### ኢትኮ ምን ምን አከናወነ?

የሥነሕዝብ ፖሊሲ ይፋ ከሆነ ካለፉት ዓመታት ወዲህ ፖሊሲውን ለመተግበር የሥነሕዝብ ኢትኮ (POP/IEC) ትኩረት ተሰጥቶት ነበር። ከዚህ አኳያ የጥናት ጽሑፉ «የሥነሕዝብ ኮሙኒኬሽን በኢትዮጵያ» በሚል አይነት በኢትኮ የተሠሩ ሥራዎችን፣

ያስገኘውን ውጤትና ፋይዳ በመፈተሽ ስለጥንካሬና ስለድክመት ፍንጭ ይገኝ እንደነበር አስተያየት ተሰጥቷል።

## የአገልግሎት አቅርቦትና ሥርጭት

በሥነሕዝብ ጉዳዮች ረገድ ባለፉት ዓመታት የወሊድ መከላከያዎችን ስለመጠቀም ግንዛቤ ለመፍጠር በተደረገው እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ መስተዳድር አንዳንድ ክሊኒኮች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ የወሊድ መከላከያዎችን ለመውሰድ ቢመጣም የአገልግሎት አቅርቦትና ሥርጭት ውሱንነትና እጥረት ስላለ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዳልተቻለና ኢንፎርሜሽን ጥራትና ብቃት ያለው አገልግሎት ከመስጠት ጋር እንዲጣጣም እንዲደረግ አስተያየት ቀርቧል። በመሠረቱ ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የሕዝብን እድገት ለመቀነስ የወሊድ መከላከያዎች መጠቀምን ዋና ግብ አድርጎ መታየት እንደሌለበትና ሌሎች አማራጭ መንገዶችም እንደ ጋብቻ ዕድሜ፣ ከወሲብ መታቀብና የመሳሰሉት በተጓዳኝ እንዲታዩ መረጃ መስጠት እንደሚያስፈልግ አስተያየት ተሰንዝሯል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በታዕታይ የአስተዳደር መዋቅር ስለሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች ትምህርትና መረጃ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ለመስጠት የሚመደቡት ሠራተኞች ከችሎታ፣ በሕዝብ ዘንድ ካላቸው ተቀባይነት፣ ተሰሚነትና አርአያነት አንጻር ተፈትሸው መሠማራት እንዳለባቸው ተጠቅሷል።

## የባሕሪን ለውጥ በቀላሉ ማምጣት ይቻላል?

በዓለም ላይም ሆነ በእኛ አገር በተፈለገው ታዳሚ ዘንድ የባሕሪ ለውጥ ማምጣት አስቸጋሪ ተግባር እንደሆነ በመጥቀስ የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት የመገናኛ ብዙኃን ሚና ምንድን ነው? ባህላዊ መገናኛ (Folk Media) ምን ሚና ይጫወታል? የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት ተመራጭ ሞዴል የቱ ነው? የሚሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በኢትኮ ግንዛቤን ከመፍጠር ባሻገር ዋና ተልእኮው የባሕሪ ለውጥ ማምጣት እንደመሆኑ መጠን ትልቁ ፈተናም የባሕሪ ለውጥ በታዳሚው ዘንድ ማምጣት እንደሆነና የባሕሪ ለውጥንም ለማምጣት ይህን ሞዴል በብቸኛነት ተጠቀም ብሎ የሚገድብ ድንጋጌ ባይኖርም በምርምር ላይ የተመሠረተ የድርጊት መርሐ ግብር የተነደፈለትና ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ፕሮግራም ጠቀሜታ እንዳለው ተብራርቷል። የባሕሪ ለውጥ ለማምጣም ብቻውን ተነጥሎ እንደማይካሄድና ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች ጋር ጐን ለጐን ተጣጥሞ መካሄድ እንደሚኖርበት ተጠ

ቅሷል። አንድ የመገናኛ ዘዴ ብቻ ውጤታማ ነው ለማለት ስለማይቻል ከመልእክቱ ይዘት፣ ከታዳሚ ባሕሪና ዐቅም፣ እንዲሁም ሊገኝ ከታሰበው ዓላማ አንጻር የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በተደጋጋሚና በቀጣይነት መጠቀም ተመራጭነት እንዳለውና ሆኖም የቁሳዊ ሀብት እጥረት ባለበት ሁኔታ ኢንፎርሜሽንና ትምህርት ብቻውን የባሕሪ ለውጥ ያመጣሉ፣ ማለት እንዳልሆነ ተዘርዝሯል። በአንዳንድ አገሮች ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱት ባህላዊ መገናኛዎች በኢትዮጵያ ገና ያልተነኩ ስለሆነ የትኛው ዘዴ ለየትኛው አካባቢ ኅብረተሰብ እንደሚመረጥ በማጥናት መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ተጠቁሟል።

## ለኮንዶምና ፒልስ ማስታወቂያዎች ትኩረት ይሰጥ

በመገናኛ ብዙኃን ስለወሊድ መከላከያዎች በተለይም ስለኮንዶምና ፒልስ የሚሰራጩት ማስታወቂያዎች ልቅነትን የሚጋብዙና ለችግሩ አይነኛ መፍትሔ መሆናቸውን የሚያመላክቱ መልእክት ያዘሉ በመሆናቸው ትኩረት እንዲሰጣቸው ሐሳብ ቀርቧል። ስለዚህም ከጤና ጋር የተያያዙ ማስታወቂያዎች ለሕዝብ ይፋ ከመሆናቸው በፊት በጥንቃቄ የተጠኑ፣ በቅድመ ፍተሻ (Pretest) የተሞከሩ፣ የኅብረተሰቡን ባህልና የጤና ንቃተኅሊና ያገናዘቡ፣ የመልእክቶች ትክክለኛነት የተረጋገጠ፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚዳስሱ (የሚነኩ)ና ጐጂ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ የማያስከትሉ ሆነው መቅረብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ተገኝቷል። በዚሁ መንፈስ የማስታወቂያ ድርጅቶች፣ የማስታወቂያው ባለቤቶችና የመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች ኃላፊነት ተሰምቷቸው ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ተጠቁሟል።

# ጉባኤ ሦስት

## 3.1 የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ

## የጤና ፕሮግራሞችና የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት

*አቶ ገብረመድኅን ኪዳነማርያም፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማእከል ዋና ሥራ አስኪያጅ*

ጽሑፉ በኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት በመጨመሩ፣ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ባለመጠናከራቸው፣ ኅብረተሰቡ ስለጤና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ ባለመዳበሩ፣ የሚቋቋሙት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከችግሩ ስፋት ጋር ባለመመጣጠናቸው የጤና ችግሮች ከጊዜ ወደጊዜ

በአይነትም ሆነ በሥርጭት ረገድ እየተባበሱ መሄዳቸውን መረጃዎችን ከማጣቀስ ያብራራል፡፡

የጤና መረጃና ትምህርት ኅብረተሰቡ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአስተሳሰብና የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጣ በማድረግ ጤንነቱን እንዲጠብቅና በተዘረጉለት የጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግና ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በጤና ዘርፍ የኢትኮን ሥራ በተጠቀላጠፈ መልኩ ለማከናወን የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማእከል ተቋቁም በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የጥናት ጽሑፉም የሀገራችንን የጤና ችግሮች ለማቃለል ከሚካሄደው የማከም አገልግሎት ጐን ለጐን አስቀድሞ የመከላከልን ዕውቀትና ብልሃት በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽ የሚደረጉ የጤና ትምህርትና መረጃ ጥረቶች፦

- ተከታታይነት ባለው መልክ ባለመካሄዳቸው፣
- የሕዝቡን ዋናኛ የጤና ችግሮች በመመርመርና በማጥናት ላይ ተመሥርቶ የባሕሪ ለውጥ ሊያመጡ እንዲችሉ ሆነው ባለመከናወናቸው፣
- በመገናኛ ብዙኃንና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው ክፍሎች መካከል የጋራ እቅድና መርሐግብር በመንደፍ በቅንጅት የሚሠራት ሁኔታ ባለመመቻቸቱ ምክንያት የተፈለገውን ያህል እንዳልተሠራና ያስገኙትም ለውጥ ጠንካራ እንዳልሆኑ ይተነትናል፡፡

ስለዚህም የሚደረጉ የጤና ነክ ትምህርቶች እነዚህን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው የጥናት ጽሑፉ ይጠቁማል፡፡ የጤናና ጤናነክ ትምህርቶችንና መልእክቶችን ለሕዝቡ ለማዳረስ የመገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው በመጥቀስ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ፋና፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ አብዮታዊ ዲሞክራሲና *አዲስ ዘመን* እቅድ እንዳላቸው ይጠቅሳል፡፡

ማኅበራዊ ግብይትንም በተመለከተ ጽሑፉ በማኅበራዊ ግብይት ውስጥ በዋናነት ተጠቃሾች ኤድስን ለመከላከል፣ በሚል የኮንዶምና ለተዋልዶም የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን የማስተዋወቅ ሥራዎች ሕዝቡን ከጉዳት ለመጠበቅ መልእክቶች በጥንቃቄ መመረጥ፣ መቀነባበር፣ መፈተሽና መሠራጨት እንዳለባቸው ያስገንዝባል፡፡

## 3.2 ውይይትና የተነሡ ሀበይት ነጥቦች

### ማኅበራዊ ግብይት

ማኅበራዊ ግብይትን በተመለከተ በገበያ ላይ የቀረቡ የወሊድ መከላከያ ምርቶችን ኅብረተሰቡ እንዲያውቃቸው "DKT" እያደረገ ስላለው እንቅስቃሴ አንድ ተሳታፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ድርጅቱ ማስታወቂያዎችን ከማሠራጨት በተጨማሪ ስለጤና፣ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሕዝቡን ለማሳወቅና ለማስተማር ከሬዲዮ ፋና ጋር በመተባበር «ሐኪምዎን ያማክሩ» የተሰኘ ፕሮግራም እንዳለው፣ በመላው ኢትዮጵያም በመንቀሳቀስ ስለኤድስ በሽታ ትምህርት እንደሚሰጥ፣ "ABC of HIV/AIDS" በሚል ርዕስ ባለቀለም ፖስተር በማሳተም እንዳሠራጨ ተገልጿል። ከሚተላለፉ ማስታወቂያዎች በተጨማሪ ትምህርት ለመስጠት ጥረት እንደተደረገና አልፎ አልፎ ስህተት ሊሠራ ስለሚችል ስሕተትን ለማረም ጥረት እንደሚደረግ ተጠቅሷል።

### በመገናኛ ብዙኃን ስለተደረጉ የጤና ሽፋኖች

የመገናኛ ብዙኃን ለጤናነክ ጉዳዮች የሰጡትን ሽፋን በተመለከተ በርካታ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው በጥናቱ ውስጥ በማእከል ደረጃ ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎችም እንደ ኢትዮጵያ ሬዲዮ የአፋርኛና የሶማሊኛ ፕሮግራሞች ያሉት የመገናኛ ብዙኃን የሰጡት የጤና ሽፋንና በየክልሎች የሚታተሙ እንደ«ወይን» ዓይነት ጋዜጦችና እንደ«ድምፀ ወያኔ» ዓይነት የሬዲዮ ጣቢያዎች ለጤና የሰጡት ሽፋን በጥናቱ ውስጥ መካተት እንደነበረባቸው ተጠቅሷል።

የክልሎች መገናኛ ብዙኃን የሚሰጡትን ሽፋን አለማወቁ ወይም ዝቅተኛ ግምት መስጠት ተገቢ እንዳልሆነ፣ ከዚህም በላይ የመገናኛ ብዙኃን ስለሚኖራቸው ሚና ንድፈ ሐሳብ ከማብራራት ይልቅ በየሚዲያው የተላለፉ የጤና ጉዳዮች ጥንካሬና ድክመት በመፈተሽ ላይ ቢተኮር ኖሮ የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች ሥራዎቻቸውን ለመገምገም ያስችላቸው እንደነበር ሐሳብ ተሰንዝሯል።

### ቅንጅታዊ አሠራር

በሌላም በኩል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተለይም የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማእከል ከመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች ጋር ያለው ቅንጅት ምን ይመስላል? በመገናኛ

ብዙኃን በሚተላለፉ ፕሮግራሞች ወይም ዐምዶች ላይ የማእከሉ ሚና ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ተነሥተዋል።

ሕዝቡን ስለጤና ጉዳዮች በማስተማርና በማሳወቅ ረገድ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማእከል ከመገናኛ ብዙኃንና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሠራር ለመፍጠር ጥረት ያለ ቢሆንም በይበልጥ በማጠናከር ቅልጥፍናና ሥርዓት እንዲኖረው በጤናና በመረጃ ረገድ ወደፊት በሚደረግ ዐውደ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚታይ የጥናት ጽሑፉ አቅራቢ ገልጸዋል። በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስተባባሪነት በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ የጤና ፕሮግራሞችና ዐምዶች ብቃትና ጥንካሬ በሚመለከት ከሚዲያው ድርጅት ጐን ለጐን የጤና ጥበቃም አሠሪ አካል በመሆኑ ኃላፊነት ስላለበት የክትትልና የግምገማ ዘዴ (Monitoring and Evaluation Mechanism) በመፍጠር ሊቃኛቸው እንደሚገባ መልስ ተሰጥቷል።

ጤናን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፕሮግራም ከግቡ ለማድረስ የሚያስችል የኢትኮ ተግባር ለማከናወን በምርምርና ጥናት ላይ በመመሥረት ታዳሚን መለየትና መምረጥ፣ መልእክትን ማዘጋጀትና ማቀነባበር፣ የማስተላለፊያ ዘዴዎችን መለየትና መምረጥ፣ የተሠራውን ሥራ መከታተልና መገምገም፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ የድርጊት መረሐ ግብር መንደፍና መተግበር ጠቀሜታ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አፅንኦት ተሰጥቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኢንፎርሜሽንና ትምህርት ዝግጅትና ሥርጭት ዙሪያ በጥናት ላይ መመሥረት (Research Based)፣ ታዳሚን ማጥናት (Audience Research) እና የመሳሰሉ መርሆዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች ይቻላል? የሚል ጥያቄ ቀርቧል። የፋይናንስ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የጊዜ እጥረት ሊኖር ቢችልም ዐቅም እስከፈቀደ ድረስ ደረጃው ቢለያይም ገና ከመነሻው ጀምሮ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተብራርቷል።

## የተማረ የሰው ኃይል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መጠቃት

በአገራችን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኤድስ እየተጠቁና እየተጐዱ እንደሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይም የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል «ምሁሩ» በቫይረሱ እየተጠቃ ስለመሆኑ ተሳታፊዎችን አነጋግሯል። መልስ ያላገኙ በርካታ ጥያቄዎች እንዲነሡ አድርጓል። ጥያቄዎቹ ምሁር ማለት ምንድን ነው? ማነው ምሁሩ? ከሚሉት ይጀምራሉ። የተማረ የሰው ኃይል ለኤድስ ጥቃት የመጋለጡ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ማስተላለፊያ መንገዳቸውን ካለማወቅ? ካለመገንዘብ? ወይስ ሌላ?

የተማረው የሰው ኃይል ኤድስን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የለውጥ አራማጅነቱን እንዴት ይወጣል?

<u>ለገበሬዎች የሬዲዮ አውታር መድረክ መፍጠር</u>

የመገናኛ ብዙኃን ሚና ቢኖራቸውም በገጠር ያሉ ሴቶች ቀርቶ በከተማ ያሉት ጋዜጦችን ለማንበብና ሬዲዮና ቴሌቪዥን በመከታተል በሚተላለፉ መልእክቶች ተጠቃሚ ለመሆን ልምድ እንደሌለ ተገልጿል:: በተለይ ሴቶች ከሥራ መልስ በቤት ውስጥ የሴትነት ሚናቸውን ለመወጣት የሚንደፋደፉ በመሆናቸው ሴቶችን ለመድረስ የሚያስችል መድረክ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ሐሳብ ተጠቁሟል::

አንዳንድ አገሮች የገበሬዎች የሬዲዮ አውታር (Farmers Radio Network) በመጠቀም ውጤታማ ስለሆኑ በኢትዮጵያም ለዕድር፣ ለማኅበር፣ ለገበያና ለመሳሰሉ ጉዳዮች የሚሰባሰቡትን የኅብረተሰብ ክፍሎች የጤና፣ የቤተሰብ አያያዝ፣ የተዋልዶ፣ የአካባቢ ጥበቃና የመሳሰሉ መረጃዎችን ለማስተላለፍ የሚያግዙ መድረኮችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተወስቷል:: ከዚህ አንፃር ያሉትን ሚዲያዎች በወጉ መጠቀም እንደሚያስፈልግና በአራተኛው አገራዊ የሥነሕዝብ ፕሮግራም ውስጥ እንደሚታይ መታሰቡ ተጠቁሟል::

## ጉባኤ አራት

### 4.1 <u>የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ</u>

### በእናቶችና በሕፃናት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

*ወ/ሮ ቢጋለች ዓለሙ፣ በግብርና ሚኒስቴር*
*የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ*

ጥናታዊ ጽሑፉ በኢትዮጵያ፣ በተለይም በሴቶችና በሕፃናት ጤና፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርሱና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች (ጉልድ) እና አመለካከቶች በየብሔረሰቦች ባህል ውስጥ እንደሚገኙና እነዚህንም ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ በብሔራዊና በክልል ደረጃ ጉጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ እንደተቋቋመ በመግለጽ ይጀምራል::

የጥናት ጽሑፉ ሁለት ዋና ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያው ክፍል በኢትዮጵያ ያሉት ዋና ዋና ጠቃሚና ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተዘርዝረዋል። በተለይም በርካታ ጉልድ ያሉ ቢሆንም የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ ሰውነትን በስለታማ ነገር መቁረጥ፣ የተመጣጠነ ምግብ ለሕፃናትና ለእናቶች መከልከል፣ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሥራ ጫና መብዛት በዋናነት እንደሚታዩ በጥናቱ ተጠቅሷል። እነዚህም ድርጊቶቸ የሚካሄዱባቸው ምክንያቶችና የሚያስከትሏቸው ችግሮች ተተንትነዋል።

የጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ጠቃሚውን ልማድ ለማዳበርና ጐጂ ልማዶችን ለማስወገድ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያብራራል። ከዚህ አንፃር፡–

- ጐጂና ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት ለይቶ ማውጣት፣
- በተለያዩ መድረኮችንና መገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ኅብረተሰቡን በየደረጃው ማሳወቅና ማስተማር፣
- ደንቦች፣ ሕጐችንና ፖሊሲዎችን ማውጣት (ማሻሻል)ና ተግባራዊ ማድረግ፣
- መገናኛ ብዙኃንን ከባህላዊ መገናኛ (Folk Media) ጋር አቀናጅቶ መጠቀም፣
- ጐጂ ባህል ፈጻሚ ግለሰቦችን ማስተማርና በሌላ የሥራ መስክ እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የድርጊት መርሐግብሮችን በቅንጅት በመንደፍ መተግበር እንደሚያስፈለግ ያስረዳል።

## 4.2 <u>ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች</u>

## <u>የጉልድ ምንጮችንና አራማጆችን መለየት</u>

የተለያዩ ብሔረሰቦች የራሳቸው ባህል ልማድና ወግ እንዳላቸው ሁሉ የማንን ባህልና ልማድ ማንም፣ መጥፎ/ጐጂ ባህል/ልማድ፣ በማለት መፈረጅና ማእከል ተቀምጦ በክልል ያለውን ባህልና ልማድ ማውገዝ አግባብ እንዳልሆነ አስተያየት ተሰጥቷል። በዚህ ሐሳብ ላይ ያለዕድሜ ጋብቻን፣ የሴት ልጅን ግርዛት፣ ጠለፋንና የመሳሰሉትን ድርጊቶች ጐጂ ባህላዊ ድርጊቶች፣ ከማለት ይልቅ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የሚለው ስያሜ የእንግሊዝኛውን "Harmful Traditional Practices" እሳቤ በተቀራራቢ አቻነት እንደሚተካው ተጠቁሟል። በማያያዝም ሁሉም ባህልና ልማድ ጥሩ የሚባል ብቻ ሳይሆን ጥሩም መጥፎ ተብሎ ስለሚፈረጅ ጥሩውን ከመጥፎ ለይቶ በማውጣት ጉዳት

እንዳይደርስ መከላከል ተገቢ እንደሆነ ተብራርቷል። ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልም፣ አንድን ችግር ለመፍታት የችግሩን ምክንያት/ምንጭ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ በቀጥታ የሚመለከተው ሕዝብ/ኅብረተሰብ ድረስ ዘልቆ በመግባት ድርጊቶችን ለመከወን አነሣሽ ምክንያቶችንና አራማጅ ኃይሎችን ለይቶ በማወቅ ላይ መመሥረት እንዳለበት ግንዛቤ ተገኝቷል።

ከዚህ አኳያ የጐልድ አነሣሽ ምክንያቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይስ ልማዳዊ? ብሎ መለየት፣ ድርጊቶች እንዲቀጥሉ አስተዋፅኦ የሚያደርጉት ወላጆች፣ አረጋዊያን፣ ሴቶች/ወንዶች ወይስ ድረጊቱን መተዳደሪያቸው ያደረጉት ሰዎች ናቸው? የሚለውን በመፈተሽ ዘመቻ የማካሄድ አስፈላጊነት ትኩረት እንዲሰጠው ተገልጿል።

## ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

በእናቶችና በሕፃናት ላይ የሚደርሱትን ጐጂ ልማዳዊ ተግባሮችና አመለካከቶች ለማስቀረት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር የባህል መምሪያና በብሔራዊ ጐጂ ባህላዊ አስወጋጅ ኮሚቴ መካከል ስላለው ቅንጅታዊ አሠራር ጥያቄ ቀርቧል። በሁለቱ መ/ቤቶች መካከል በብሔራዊና በክልል ደረጃ በተቋቋመው የጐጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ ውስጥ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር አባል ስለሆነ የጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን አስመልክቶ የሚነደፉና የሚተገበሩ ሥራዎችን በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የአወቃቀር ሥርዓት መዘርጋቱ ተብራርቷል።

## የባህላዊ መገናኛ (Folk Media) ሚናና አወቃቀር

ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አዳጊ አገሮች የመገናኛ ብዙኃን ያልተስፋፉ ስለሆኑ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለሕዝቡ በማሳወቅና በማስተማር ረገድ የላቀ ሚና እንደሚጫወቱ ይታመናል። ነገር ግን በወደፊቱ ላይ የትኛው የባህላዊ መገናኛ ለየትኛው አካባቢ የበለጠ ፋይዳ አለው? በማን ይዋቀሩ? ከመገናኛ ብዙኃን ጋር እንዴት ይቀናጁ? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽና ምርምር የሚያሻቸው ሆነዋል።

# ጉባኤ አምስት

## 5.1 የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ

### የወጣቶች ተዋልዶ ጤና

*ወ/ሮ ገነት መንግሥቱ፣ በብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የተዋልዶ ጤና፣ የሴቶችና የወጣቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ*

የወ/ሮ ገነት ጥናታዊ ጽሑፍ በካይሮው ዓለም አቀፍ የሥነሕዝብና ልማት ጉባኤ (ICPD) የተዋልዶ ጤናን አስመልክቶ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በሆነው የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ላይ ያነጣጠረ ነው።

ጥናታዊ ጽሑፉ እንደሌሎች አዳጊ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ በወጣትነት ዕድሜ ክልል (ከ10–24 ዓመት) ውስጥ የሚገኙት 33 በመቶ ወይም 21 ሚሊዮን (እ.ኤ.አ. 1998) ስለሚሸፍን ለወጣቱ ትውልድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ኃይል እንደሆነ ያስረዳል። በተለይም አብዛኛው ወጣት እንደ ሕዝቡ ሁሉ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ አገልግሎት ባልተስፋፋባቸው የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ በመሆናቸው የወጣቶች የተዋልዶ ጤና በቀላሉ እንደማይታይ ተጠቁሟል።

የጥናት ወረቀቱ ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት። በአንደኛው ክፍል በወጣቶች የተዋልዶ ጤና ሥር የሚካተቱ የወጣቶች ወሲባዊነት (Sexuality)፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ያልተፈለገ እርግዝና፣ አስተማማኝነት የሌለው ውርጃ (Unsafe Abortion)፣ የአባለዘር በሽታዎችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ፆታዊ ጥቃት (Sexual Violence)፣ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ በአኃዛዊ መረጃዎች ተደግፈው ቀርበዋል። ከዚህም ሌላ አብዛኞዎቹ ወጣቶች ስለተዋልዶና ስለወሊድ መከላከያ መሠረታዊና ትክክለኛ መረጃ ሳይኖራቸው ወሲብ ስለሚፈጽሙ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለአባለዘር በሽታና ኤድስ፣ በልጅነት በመውለድና አስተማማኝ ባልሆነ ውርጃ ምክንያት የወጣት ሴቶች ጤና መጓዳል፣ ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውሶች እንደሚጋለጡ ጥናቱ ያብራራል።

የጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ወጣቶች ስለተዋልዶ ጤና ኢንፎርሜሽንና አገልግሎቶችን ለማግኘት እንዲችሉ የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የተቀናጀ ጥረትና ሙሉ ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክታል። በዚሁ መሠረት የተለያዩ ታዳሚዎችን ለማሳወቅና

ለማስተማር ልዩ ልዩ አማራጮችን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ማስተላለፍ እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ያብራራል። ከዚህ አኳያ የመገናኛ ብዙኃን፡-

1. ስለወጣቶች ተዋልዶ ጉዳዮች ትክክለኛና ተገቢ ኢንፎርሜሽን ለወጣቶች፣ ለወላጆችና ለፖሊሲ አውጪዎች መስጠት እንዳለበት፣ እና
2. በተዋልዶ ጤና ላይ የሚቀርቡ ዘገባዎችንና ሽፋኖችን ማራኪና ሳቢ ለማድረግ መጣር እንደሚኖርባቸው ያሳስባል።

## 5.2 <u>ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች</u>

### <u>የሴት ልጅ ግርዛት ጐጂ ልማዳዊ ድርጊት ወይንስ ፆታዊ ጥቃት?</u>

የሴት ልጅ ግርዛት ከተዋልዶ ጤና አንፃር የሚታይ ሊሆን ቢችልም በፆታዊ ጥቃት ሥር ሳይሆን በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሥር መመደብ እንደነበረበትና ለምን በፆታዊ ጥቃት ሥር እንደተካተተ እንዲብራራ ተጠይቋል። የሴት ልጅ ግርዛት የግድ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሥር መካተት እንደሌለበትና በተለያዩ ምክንያቶችና ውጤቶች ሲባል በሴቶች ላይ ገና በጨቅላነታቸው፣ በአንዳንዶችም በወጣትነታቸው ጊዜ ያለእነርሱ ፍላጐትና ምክር ስለሚደረግ ከፆታዊ ጥቃት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የግድ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሥር መካተት እንደሌለበት ተብራርቷል።

### <u>የተዋልዶ ጤና ጉዳዮችን ስለማስተማር</u>

በየክልሉ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተዋልዶ ጤና ጋር ተዛማጅ ስለሆኑ ጉዳዮች ትምህርት በመስጠት ላይ ነው። ይሁን እንጂ በገጠራቱ የአገሪቷ ክፍል የሚገኙ ኅብረተሰቦች አንዳንድ ጉዳዮችን እንደባህል ቆጥረው በሚተገብሯቸው አካባቢዎች፣ ለምሳሌ በአፋር ክልል የሴት ልጅ ግርዛት እንደባህል ይወሰዳል፣ በተለይ መምህራን ከሙያ ብቃትና ከማስተማር ዘዴ ጋር በተያያዘ እነዚህን ጉዳዮች ለማስተማር ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው በመጥቀስ የሚቃለሉባቸው መንገዶች እንዲቀየሱ አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

### <u>አስገድዶ መድፈርና ሕጋዊ ውሳኔ</u>

አስገድዶ በመድፈር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሁነው በተገኙ ግለሰቦች ላይ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ፣ ለምሳሌ አንድ ጐልማሳ የዘጠኝ ዓመት ሕፃን ልጅ በመድፈሩ የሚተላለፍበት የቅጣት ውሳኔ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር፣ በተለይም ከኤድስ ሥርጭት አንፃር፣ የማይጣጣም ስለሆነ ጥፋተኞች እንዲታረሙ ተፅዕኖ እንደማያደርግ

ተገልጿል። ከዚህ ጋር የተያያዙ የወንጀለኛና የፍትሐብሔር ሕጐች እንዲሻሻሉ የውሳኔ ሐሳቦች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለቀረቡ ይሻሻሉ፣ ተብሎ እንደሚጠበቅ ተወስቷል።

## ጠለፋና ኢኮኖሚ

ጠለፋ በአገሪቷ የተለያዩ አካባቢዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቢካሄድም በአርሲ፣ በባሌና በሸዋ ግን ጠለፋ ኢኮኖሚያዊ ምስጢር እንዳለው ተገልጿል። በተጠቀሱት አካባቢዎች ወንዶች ትዳር ለመመሥረት፣ ሠርግ ለመሠረግ፣ ለልጅቷ ቤተሰቦች ጥሎሽ ለመጣልና መደገሻ ለመስጠት ስለሚገደዱ ይህን ለማድረግ ዐቅሙ የሌላቸው ማግባትም ግድ ሲሆንባቸው እንደሚጠልፉ ተብራርቷል። ስለሆነም ጠለፋን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን የጠለፋን ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ገጽታዎች እየፈተሹ ለመፍታት ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስተያየት ተሰጥቷል።

## የመገናኛ ብዙኃን ሽፋንና ወጣቶች

መገናኛ ብዙኃን ኅብረተሰቡን እንደወጣቶች ያሉ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለማስተማር፣ ለማሳወቅና ለማዝናናት የሚያቀርቧቸው የተለያዩ ፕሮግራሞች መጥፎ ጐናቸውን ወይም አሉታዊ ገጽታቸውን (Negative Image) ብቻ ከማንፀባረቅ ይልቅ ጥሩ ጐናቸውን ወይም አወንታዊ ገጽታን (Positive Image) በማሳየት ላይ ማዘንበል እንደሚያስፈልግ ተገልጿል። መጥፎ ድርጊት የሚፈጽሙ ወጣቶች እንዳሉ ሁሉ ጥሩ ፈጻሚዎች ስላሉ የመጥፎን ነገር አስከፊነት በማሳየት ብቻ መጥፎ ነገር እንዳይሠሩ ለመምከር ከመሞከር ይልቅ ጥሩ ሥራ የሚሠሩትንም በማሳየት መጥፎ ነገር እንዳይሠሩ ለማድረግ ስለሚቻል በዚህ ረገድ ብዙ መሠራት እንዳለበት ሐሳብ ቀርቧል።

# ጉባኤ ስድስት

## 6.1 የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ

### ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የመገናኛ ብዙኃን

*ዶ/ር ኃይሉ ነጋሳ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኤፒደሞሎጂና የኤድስ መምሪያ ቡድን መሪ፣*

የዶ/ር ኃይሉ ጥናት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ በኢትዮጵያ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝና በሽታውን ለመከላከል የመገናኛ ብዙኃን ሚና ምን እንደሆነ ማብራሪያ

የሚሰጥ ነው። በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያ ኤች.አይ.ቬ/ኤድስ መኖሩ ሪፖርት ከተደረገበት ከ1978 ጀምሮ እየተስፋፋ በመምጣት እስከ መስከረም 1992 ዓ.ም. ድረስ ሪፖርት ያደረጉ የኤድስ ሕሙማን 73,216 ሲሆኑ፣ ሊኖሩ ይችላሉ፣ ተብለው የሚገመቱት ግን ከ400,000 በላይ እንደሆኑ ተገልጿል። ጥናቱ የኤድስ ስርጭት በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ምን እንደሚመስል አኀዛዊ መረጃ ይሰጣል። በተደረገው ቅኝትም በሴተኛ አዳሪዎች የኤድስ ሥርጭት እየጨመረ በመምጣት በ1990 ዓ.ም. በመቱ 37%፣ በናዝሬት 53%፣ በባሕር ዳር 55% እና በአዲስ አበባ 73.3% እንደነበር ገልጿል። በቪዛ አመልካቾች ላይ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭት አዲስ አበባ እ.ኤ.አ. በ1992 ዓ.ም. 10.8 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ ከሐጂና ኡምራ ተጓዦችም ውስጥ 11.2 በመቶ በሽታው እንዳለባቸው ተጠቅሷል። ከሰባት ዓመት በፊት በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች በተደረገው ጥናት መጠኑ አነስተኛ የነበረ ቢሆንም ወረርሽኙ ገጠር እንደገባ በዕውን ይጠቁማል። ለሌሎች ጥናቶች ተሰብስበው ከተቀመጡ 3,853 የደም ናሙናዎች ላይ እ.ኤ.አ. በ1996/97 በተደረገው ደም ምርመራ ወንዶች 6 በሙቶ እና ሴቶች 6.9 በመቶ ቫይረሱ ተገኝቶባቸዋል። ኤድስ በአምራች ሰው ኃይል፣ በደህንነት፣ በቤተሰብ፣ በትምህርት፣ በግብርና፣ በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በኢኮኖሚና በጤና ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያሳድር በጥናቱ ተገልጿል።

በዚህ ረገድ የመገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተም በአንድ በኩል የኤች.አይ.ቬ/ኤድስ ወረርሽኝ በፍጥነት መሠራጨት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በግንዛቤውና በአመለካከት ለውጡ ዘገምተኛነት መካከል ያለው ጣምራ ክፍተት ሰፊ ስለሆነ ለማጣጣም እንዳልተቻለ ጥናቱ ያመለክታል። ከዚህ አኳያ የመገናኛ ብዙኃን:-

- ለሕዝቡ ስለ ኤች.አይ.ቬ/ኤድስ ኢንፎርሜሽን በመስጠት ለማሳወቅ፣
- ሕዝቡ ከበሽታው ራሱን እንዴት መከላከል እንደሚችል ለማስተማርና የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት፣ እና
- ሌሎች በርካታ ተግባራት እንዳላቸው ወረቀቱ ዘርዝሯል።

ከዚህም ሌላ ጥናቱ በኤድስ ቫይረስ ከፍተኛ የሕዝብ እልቂት የደረሰባትን ዩጋንዳን በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ ውጤቶች ለማስመዝገብ ያስቻሏትን መላዎች ይጠቅሳል። ከእነዚህም ውስጥ የመንግሥት ቁርጠኝነት መኖር፣ ኤድስ የሁሉም የልማትና የአገልግሎት ዘርፎች ዋነኛ አጀንዳ መሆን፣ በብዙ ተቋሞች መካከል የቅንጅት ሥርዓት መዘርጋት፣ ማኅበረሰቡን ማሳተፍ፣ የመገናኛ ብዙኃን የላቀ ሚና መጫወት ይገኙበታል።

## 6.2 ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች

### ደም ለጋሾችና ኤድስ

በተለያዩ ምክንያቶች ደም ለመለገስ ወደቀይ መስቀል በመምጣት የሚለገሠው ደም በተለይም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ ለሦስት ወራት ሳይታወቅ በደም ውስጥ ሊቆይ ስለሚችል፣ የተለገሠው ደም ከቫይረሱ ነፃ ነው፣ ብሎ እርግጠኛ መሆን እንደማይቻልና ይህም ደም የሚሰጣቸው ሰዎች ሊበከሉ ስለሚችሉ መወሰድ ባለበት ጥንቃቄ ላይ አስተያየት ተሰጥቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ደም ከሰጡት/ከለገሡት ውስጥ ቫይረሱ የተገኘባቸው ሰዎች ሁኔታቸውን የሚያውቁበትና የምክር አገልግሎት የሚያገኙበት አሠራር እንደሌለ ተገልጿል። ይህ ደግሞ ለቫይረሱ ሥርጭት የሚያደርገው አስተዋፅኦ በቀላሉ መታየት እንደሌለበትና ዐቅምና ችሎታን በመፍጠር ታማሚዎች ይዞታቸውን እንዲያውቁና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል።

### የዩጋንዳ ተሞክሮ ለኢትዮጵያ ያለው ፋይዳ

ዩጋንዳ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት በመግታት ውጤታማ ለውጥ ለማምጣት ሥራ ላይ ያዋላቸው ስልት ለኢትዮጵያ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ማብራሪያ ተጠይቋል። በዚሁ መሠረት አንድን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኀበራዊ መርሐ ግብር ተግባራዊ ለማድረግ በዩጋንዳ ውጤት ያስገኙት አላባዎች በታሳቢነት እንዲወሰዱ ተጠቁሟል። እንዲሁም ሁለቱ አገሮች ተቀራራቢ ባሕርያት ስላሏቸው በዩጋንዳ የተወሰዱት ዋና ዋና እርምጃዎች ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመጣጣም የምንከተላቸው እንደሆኑና ኢትዮጵያ ከዩጋንዳ ብዙ ለመማርና ልምድ ለመቅሰም እንደምትችል ተወስቷል።

### የሃይማኖት ድርጅቶች ሚና

ሕዝቡን ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለማስተማርና ለማሳወቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሃይማኖት ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ድርሻ ውይይት ተካሂዷል። የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ሃይማኖቱ ከሚያራምደው እምነታዊ መርህ አንፃር፣ የኤድስን ሥርጭት ለመከላከል፣ የቫይረሱን ታማሚዎች ለመንከባከብና በአጠቃላይ የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል ድርሻ ስላላቸው በተቀናጀ መልክ እንዲሠሩ ትኩረት እንደሚሰጣቸውና አንዳንዶቹም የሃይማኖት ድርጅቶች በየደረጃው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሆኑ ተወስቷል።

## የኮንዶም ማስታወቂያዎች

በመገናኛ ብዙኃን ኮንዶምን አንዱ ብቸኛ መድኃኒት አድርጐ ማስተዋወቅ ወጣቶችንም ሆነ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ወሲብ እንዲያመሩ ስለሚገፋፋ ይህን ለማስተካከል የተደረገ ጥረት አለ? የሚል ጥያቄ ከተሳታፊዎች ቀርቧል። በኮንዶምና በመሳሰሉ ምርቶች ላይ የሚደረገውን ማስታወቂያ ለመከታተል አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራውን ለመጀመር በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆነ መልስ ተሰጥቷል። ከዚህም ሌላ ስለኮንዶምና ስለመሳሰሉ የመከላከያ ዘዴዎች የሚሰጡ ትምህርቶች የታዳሚውን የዕውቀትና የመቀበል ዐቅምን ከግምት ውስጥ ማስገባትና ሊረዳው በሚችለው መልክ ሊሆን እንደሚገባ ግንዛቤ ተገኝቷል።

## የባለብዙ ዘርፋዊ አደረጃጀት ስጋት

ኤድስን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት የሚያስተባብረውን አካል በዘርፈነጠላ ከማደራጀት (Unisectoral Organization) ይልቅ በዘርፈብዙ ማደራጀት (Multi Sectoral Organization) የጉዳዩን ዋና ባለቤት በማሳጣት፣ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን በማደብዘዝ ውጤት አልባ እንደሚያደርግ አስተያየት ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ የበሽታውን ባሕሪና ሥርጭት መግታት የሁሉንም ዘርፎች በጐ ፈቃድና ሙሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ በአንድ ድርጅት አስተባባሪነት ከመንቀሳቀስ ይልቅ የዘርፈብዙ ቅንጅታዊ አሠራር አስተባባሪነት የተሻለ ውጤት እንደተገኘ የብዙ አገሮች ተሞክሮ ስለሚያስረዳ ተመራጭነት እንዳለው ተጠቅሷል። ለዚህም አስፈላጊውን በጀትና የሰው ኃይል በመመደብ የሥራ ኃላፊነትንና ተጠሪነትን በግልጽ ማስፈር ያስፈልጋል።

# ጉባኤ ሰባት

## 7.1 የቀረበው የጥናት ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ

### ማኅበራዊ ግብይት

*አቶ ደምሰው በቀለ፣ የትምህርት መገናኛ*
*ዘዴዎች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ*

የጥናት ጽሑፉ የአንዳንድ በሽታዎች ምንጭ ሰዎች በሚያደርጓቸውና በማያደርጓቸው ነገሮች ላይ የተመሠረተና በአንድ በኩል በልምድና በባሕሪ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በበሽታና በጤና መካከል ጥብቅ ትሥሥር ያለ በመሆኑ ከደረቅ ሕክምና ጋር ባሕርያዊ ሕክምና መስጠት ለማኅበራዊ ግብይት (Social Marketing) መጀመር

የነበረውን ሚና በመጥቀስ ይንደረደራል። ማኅበራዊ ግብይት ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ ፕሮግራሞችን፣ ሐሳቦችንና ባሕሪዎችን መሸጥ የሚቻልበትን ስልትና ተግባር ማካሄድን የሚመለከት እንደሆነ ጥናቱ ያስረዳል። ይህም የሸቀጥ ግብይት ስልት/ሂደት (ስለገበያው መረዳት፣ ኅብረሰቡን/ሸማቹን ማወቅ፣ የሚመረተውን ሸቀጥ ማዘጋጀትና መተመን፣ እቅድ በመንደፍ መተግበር፣ አጠቃላይ ግምገማ ማካሄድ፣ ምገባ [feed back]) ከንግድና አገልግሎት አቅራቢ ውጪም ለሆነ ማኅበራዊ ግብይት ሊያገለግል እንደሚችል ፊልፕ ካትለር (እ.ኤ.አ. 1971) የሰነዘረውን ሐሳብ በመከተል ሥራ ላይ እንደዋለ ጥናቱ ይተነትናል።

ጥናቱ አንድን ነገር ከግለሰብ ደረጃ አልፎ ማኅበረሰቡ ተቀብሎት የሚፈለገውን ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ማኅበራዊ ግብይት ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወትና ተልእኮውንም ለማሳካት አራት ስልቶች፣ ማለትም ሕጋዊ መንገድ፣ ቴክኖሎጂያዊ አቀራረብ፣ ኢኮኖሚያዊ አቀራረብና የሐሳብ መረጃ ዘዴ፣ እንደተቀየሱ ያብራራል።

በዚህ መንፈስ ጥናታዊ ጽሑፉ ማኅበራዊ ግብይትን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን እቅድ ለማውጣት ችግሩን ከመረዳት (Problem Identification) ጀምሮ ተግበራና ግምገማ (Implementation and Evaluation) እስከ ማካሄድ ያሉትን ሰባት ዋና ዋና ደረጃዎች ይተነትናል።

የማኅበራዊ ግብይት መልእክቶችም የአልቀበሌነትን ድንበር የሚጥሱ፣ ሊተገበሩ የሚችሉ፣ አነጣጣሪ ተኳሽ፣ ቀልብ ሳቢ፣ ባንድ ነጥብ ላይ ያተኮሩ፣ ፈጥኖ ደራሽና የመሳሰሉ መሆን እንዳለባቸው ጥናቱ ይዘረዝራል። ከዚህ አኳያ ማኅበራዊ ግብይት የመገናኛ ብዙኃንንና የሰው ለሰው ግንኙነትን አቀናጅቶ በመጠቀም በኅብረሰቡ ዘንድ የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት፣ የኮንዶም ምርት ሽያጭን ከፍ ለማድረግ ፣ የክትባት አገልግሎት በሮችን ለመክፈት እንደሚያገለግል ጥናቱ ያስረዳል።

## 7.2 <u>ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች</u>

### <u>ማኅበራዊ ግብይትና ማስታወቂያ</u>

በማኅበራዊ ግብይትና በማስታወቂያ መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምንድን ነው? አልፎ አልፎ ይህ ምርት በማኅበራዊ ግብይት ስለተመረተ እንጂ ይህ ባይሆን ኑሮ የምርቱ ዋጋ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል፣ የሚነገረው ምን ለማለት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ማስታወቂያና ማኅበራዊ ግብይት ሐሳብን/ምርትንና አገልግሎትን ለሕዝብ በማሳወቅ በኩል ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም የማስታወቂያ አይነተኛ ተልእኮ

አይነተኛ ተልእኮ በመሸጥ ትርፍ/ገንዘብ ማግኘት ነው። ማኅበራዊ ግብይት ግን ኮንዶምን፣ ኪኒንን፣ ቅባቶችን፣... ሕዝቡ እንዲጠቀምባቸው/ለሕዝቡ አገልግሎት ለመስጠት እንጂ ለትርፍ ተብለው የሚቀርቡ አለመሆናቸው እንደሆነ ግንዛቤ ተገኝቷል።

## የመልእክት ማስተላለፊያ መገናኛዎች መረጣ

መልእክቶች የሚተላለፉባቸው የመገናኛ ዘዴዎች ከታዳሚው፣ በተለይም በገጠር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዐቅምና ችሎታ ጋር የተጣጣመ እንዳልሆነ ሐሳብ ቀርቧል። በአንዳንድ አካባቢዎች ገበሬዎች ጋዜጦችን እንዲገዙ እንደሚገደዱና ለገበሬው የተሻለ ጥቅም ይሰጣል፤ የሚባለው የሬዲዮ ሥርጭት ደግሞ የድምፅ ጥራት እንደሌለው ተገልጿል። በዚህ ጉዳይ ላይ የጋዜጦች የቅጅ ብዛትና የሥርጭት አድማስ በጥናት ላይ ተመሥርቶ መወሰን እንጂ ጋዜጣ ወደገጠር መላክ የለበትም፤ የሚል አይነት ማጠቃለያ አግባብነት እንደሌለው ምላሽ ተሰጥቷል። የመገናኛ ዘዴ መረጣንም በተመለከተ የትኛው የመገናኛ ዘዴ ለየትኛው ሕዝብ/አካባቢ የበለጠ አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚችል በወጉ መጠናት እንዳለበት ተገልጿል። ዘላቂና አስተማማኝ የሬዲዮ ሥርጭት እንዲኖር፣ የመነሻ ካፒታሉ ውድ ቢሆንም፣ የሳተላይት ሬዲዮ ለመጀመር ሐሳብ እንዳለ ተጠቅሷል።

## መልእክቶች በተግባር ደረጃ ምን ይመስላሉ?

ለማኅበራዊ ግብይት ሲባል የሚተላለፉ መልእክቶች በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ምን መሆን እንዳለባቸው በወጉ ተገልጿል። ይሁን እንጂ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የተላለፉት መልእክቶች በተግባር ደረጃ ምን እንደሚመስሉ ቢፈተሹ ኑሮ የበለጠ ግንዛቤን ለማዳበርና የተሻለ ሥራ ለመሥራት እንደሚረዱ ሐሳብ ቀርቧል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዛሬ በኢትዮጵያ ባለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርህ መሠረት በርካታ የግል ባለሃብቶች ወደ ንግድና ኢንዱስትሪ (ቢዝነስ) ዓለም በዓይነትና በብዛት እየገቡ ባሉበት ወቅት ምርትንና አገልግሎትን በማስተዋወቅ ያለው የሽቀጥ ግብይት በተግባር/በዕውን ምን እንደሚመስል ጠንካራና ደካማ ጎኑ ቢፈተሽ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደነበረው አስተያየት ተሰንዝሯል።

የጥናት ወረቀቱ በአመዛኙ በንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮች ላይ ቢያተኩርም ወረቀቱ ሲቀርብ አልፎ አልፎ አንዳንድ የማኅበራዊ ግብይት ውጤቶች መጠቃቀሳቸው

(ስለኮንዶም፣ ስለሲጋራ፣...) የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ የጥናት ጽሑፉ አቅራቢ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

## ከሥርጭት በፊት መረጃን ማጣራት

በመገናኛ ብዙኃንና በኪነጥበብ መድረኮች ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ይተላለፋሉ። በዚህ ወቅት አልፎ አልፎ በጤና፣ በትምህርትና በሥነሕዝብ ጉዳዮች የተዛቡ መረጃዎች ይተላለፋሉ። የተዛቡ መረጃዎች ለሕዝብ ከመሠራጨታቸው በፊት በማን ይመረጡ? አንድ መ/ቤት በተናጠል ለማካሄድ ዐቅም አለው? ምን ያህልስ ገለልተኛ ይሆናል? መልእክቶች በተለያዩ የማሠራጫ ዘዴዎች ለሕዝብ ይፋ ከሆኑ በኋላ ስሕተት ሲገኝ ከማረም ይልቅ ቅድመ ሙከራ (Pre-test) በማድረግ አጣርቶ ማሠራጨት አይመረጥም? የሚሉ ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል።

በወረቀቱ ላይ ዐቅምና ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ መልእክቶችን ማስተላለፍ፣ ለሕዝብ ከማሠራጨት በፊትም ቅድመ ሙከራ ማካሄድ፣ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ የሌለው የማጣራት ሥራ በተቀናጁ አካላት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ ተወስቷል።

## የመረጃ እጥረትና የምርምር ዩኒት አስፈላጊነት

የተለያዩ ድርጅቶች ኤድስን፣ ተዋልዶንና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ቢያከናውኑም ማን ምን እየሠራ? እንዴት እየሠራ? እንደሆነ የሚያመላክት መረጃ የለም። ለዚህም የአሠራር ቅንጅት ሥርዓት አለመዘርጋት ዋና ምክንያት ነው፣ ማለት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ማን ምን ሠርቶ ምን ውጤት አመጣ? የተላለፉ መልእክቶች ምን ተፅዕኖ/ውጤት (Impact/Effect) አስገኙ? ሰዎችን ያለምንም ፍራቻና ሥጋት እንዴት ማነጋገር ይቻላል? ላለመናገር ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልሶች የሉም።

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በየደረጃው የምርምር አሐድ (Research Unit) በመፍጠር ተከታታይነት ያለው ምርምር ማካሄድ፣ ለዩኒቱም አስፈላጊውን በጀት፣ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ መመደብ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባው በአፅንኦት ተገልጿል። የመረጃን እጥረት ምርምር በተከታታይ በማካሄድ መፍታት እንደሚቻል ይታመናል።

# ጉባኤ ስምንት

## 8.1 <u>የቀረበው የጥናት ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ</u>

### በመገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ድራ ማዎች ለሥነሕዝብ ያላቸው ጠቀሜታ

*አቶ በላይነህ አቡኔ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል መምህር*

ጥናታዊ ጽሑፉ «በአፍሪካ ውስጥ ትያትር ወደሕዝቡ መሄድ አለበት እንጂ ሕዝቡ ወደትያትር እንዲመጣ መጠበቅ የለብንም» የተሰኘውን የካቤዌ ካስማን አባባል በማራመድ ትያትር ስለሥነሕዝብ ጉዳዮች ሕዝብን በማስታወቅና በማስተማር የሚኖረውን ሚና የሚፈትሽ ነው። ጥናታዊ ጽሑፉ ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል በኢትዮጵያ ከሥነሕዝብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን የሚያብራራ ሲሆን በየጊዜው በከፍተኛ መጠን እየጨመረ የመጣው የሕዝብ እድገት ከልማትና ከማኅበራዊ አገልግሎት ደረጃዎች ጋር ስለማይጣጣም ሕዝቡ ለድህነት፣ ለረሃብ፣ ለሞትና ለስደት እንደተጋለጠ ይተነትናል። ከችግር ለመላቀቅ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማስፈን፣ ሕዝቡን ማስተማር፣ ማሳወቅና የመሳሰሉ የመፍትሔ ሐሳቦች ሠፍረዋል።

የጥናት ወረቀቱ ሁለተኛ ክፍል የተለያዩ ትያትሮች ሕዝቡን ስለሥነሕዝብ ጉዳዮች ለማሳወቅና ለማስተማር ስለሚኖራቸው ጠቀሜታ የሚያብራራ ነው። ጥናቱ ሕዝብንና አካባቢን መሠረት አድርገው የሚታዩ ትያትሮች እንደየቦታውና እንደትያትሩ አትኩሮት የተለያዩ ስያሜዎች እንደሚሰጣቸው በመጥቀስ፣ በአጠቃላይ ግን ሕዝባዊ ቲያትር (Popular Theater) እና ትያትር ለልማት (Theater for Development) ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ ይገልጻል። ጽሑፉ ከዚህም ጋር በማያያዝ ተመልካችን የሚያሳትፍ ትያትርን፣ ማለትም የተሳትፎአዊ ትያትር፣ (Participatory Theater) አስፈላጊነትና አይነቶች ይተነትናል። የተለያዩ የትያትር እንቅስቃሴዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የገጠርና የከተማ ነዋሪዎች ስለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ልማት ነክ ጉዳዮች ሰፊ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ በችግሮቻቸው ላይ እንዲወያዩ መንገድ ለመጥረግ፣ መፍትሔ ለመፈለግ ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለማድረግና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ተጠቅሷል።

ሦስተኛው ክፍል የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎችን በሥነሕዝብ ጉዳዮች ላይ የሚያቀርቡ የትያትር ባለሙያዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ ነጥቦችን የሚዘረዝር ነው። በዚሁ መሠረት የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎችን በመጻፍ፣ በማዘጋጀትና በመተወን የሚሳተፉ ባለሙያዎች ስለሚጽፉባቸው ርእስ ጉዳዮችና ጭብጥ በሚገባ ማወቅ፣ ስለተደራሲው ማኅበረሰባዊ ዳራ በቂ ዕውቀት መጨበጥ፣ ስለሬዲዮና ቴሌቪዥን ድራማዎች የአጻጻፍ፣ የአዘገጃጀትና የመተወን ጥበባዊ ክሂሎትን ማዳበር እንደሚያስፈልግ በመጥቀስ ምንነታቸው ተዘርዝሯል።

## 8.2 ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች

<u>ባህላዊ የችግር አፈታት መንገዶችን ማወቅ</u>

በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የሚገኙ ኅብረተሰቦች የሚያጋጥሟቸውን ማኅበራዊ ችግሮችና እንቅፋቶች ለመፍታትና ለማቃለል ባህላዊ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ስርቆት፣ ወንጀል የመሳሰሉ ጥፋቶች ቢፈጸሙ አጥፊውን ለመለየት አፈርሳታ አውጫጭኝ ወዘተ. የሚጠቀስ ነው። ይህን የመሳሰሉ ባህላዊ የችግር መፍቻ ዘዴዎች ከትያትርና ከመሳሰሉት ጋር ተጣጥመው ለሥነሕዝብ ጉዳዮች ሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ መፈለግ ጠቃሚ እንደሆነ አስተያየት ተሰጥቷል።

<u>ጥናታዊ ጽሑፎች በሥራ ጨ</u>

ትያትር በመድረስ፣ በማዘጋጀትና በመተወን ሙያ የተሠማሩ ባለሙያዎች ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን ከሕዝቡ በላይ በመሄድ እያዝናኑ ለማስተማርና ለማሳወቅ ትክክለኛው ሙያዊ ዕውቀት የሚገኝባቸውን መድረኮች ሊፈጥሩ እንደሚገባና በዚህ ዐውደ ጥናትና በሌሎች የሚቀርቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ጠቃሚ ማጣቀሻዎች ስለሆኑ በሙያው ለተሠማሩ ሰዎች ቢላኩ በደመነፍስ/ከመሬት ተነሥተው እንዳይሠሩ እንደሚያግዝ ጥያቄ አዘል አስተያየትም ቀርቧል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲህ ያሉ ዐውደ ጥናቶችን በተለያዩ ጊዜያት የሚያዘጋጅ ሙያዊ ዐቅምን ለማሳደግ ካለው እምነት እንደሆነና ጥናታዊ ጽሑፎችን አባዝቶ እንደሚሰጥ ተገልጿል።

## የ«ጋብቻና ፍቅር» ድራማዎች ከየት ይመደቡ?

ከተጠቀሱት ሦስት የተሳትፎአዊ ትያትር ዓይነቶች ውስጥ ሥውር ትያትር እና ሸንጐ ትያትር ያላቸው ልዩነትና አንድነት ምንድን ነው? በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «ጋብቻና ፍቺ» እና «ጠለፋ» በሚል ርእስ የቀረቡት ድራማዎች ከየት ይመደባሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል። ሁለቱ ትያትሮች ልዩነት ቢኖራቸውም ተመሳሳይነታቸው የጐላ እንደሆነ ተብራርቷል። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተጠቀሱት ድራማዎች ታዳሚውን በማሳተፍ ረገድ የተሳትፎአዊ ትያትርን ገጽታ የሚያንፀባርቁ ቢመስሉም ስሜታዊ እንዲሆን ያደረጉ ናቸው። የተሳትፎአዊ ትያትር ተልእኮ ሕዝቡን ስሜታዊ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን ስለጉዳዩ ቆም ብሎ እንዲያስብ መፍትሔ እንዲፈልግና እንዲወስን የማድረግ ሚና እንዳለው ተብራርቷል። ድራማዎቹ ግን ይህን የሚያሟሉ እንዳልሆኑ ተጠቅሷል።

## የመገናኛ ዘዴ መረጣ

የችግሩ ሰለባዎች መልእክቶች አይደርሷቸውም። ትያትርን ወደሕዝቡ ለማድረስ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጠቀሜታ ቢኖራቸውም ስለሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችና ችግሮች በሬዲዮና በቴሌቪዥን መልእክቶች ቢተላለፉም የችግሩ ሰለባዎች በተለይ ቴሌቪዥን የሌላቸው ስለሆኑ የሚተላለፉትን መልእክቶች ለመከታተል ስለማይችሉ በመገናኛ ዘዴ መረጣ ላይ ትኩረት እንዲደረግ አስተያየት ተሰጥቷል። በዚህ ረገድ ድራማዎችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን ብቻ ማቅረብ ብቸኛ አማራጭ ተደርጐ መወሰድ እንደሌለበትና ኅብረተሰቡ በሚገኝበት አካባቢ ባሉት መድረኮች ድራማዎችን ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ተገልጿል። እንዲሁም ሁሉም ሕዝብ የመገናኛ ብዙኃን መከታተያ (ሬዲዮና ቴሌቪዥን) ስለሌለውና ድራማዎችንም የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ይከታተላቸዋል፣ ተብሎ ስለሚታሰብ የሚተላለፉት ድራማዎች የማኅበረሰቡን ችግሮች የሚነኩ፣ ሳቢና ማራኪ ከሆኑ በቤት ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን መከታተያ ባይኖርም ወደጐረቤት በመሄድ ሊከታተሉ ስለሚችሉ መልእክቶች ለተፈላጊ ታዳሚዎች አይደርሱም፣ ለማለት እንደሚያዳግት ተገልጿል።

## የትያትር ባለሙያዎችን የጋጠማቸው ማነቆ

የትያትር ባለሙያዎች ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን ለሕዝብ ለማሳወቅና ለማስተማር የሚያዘጋጇቸው የቴሌቪዥን ድራማዎች በተለያዩ «ጥቃቅን ምክንያቶች» በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዳይሠራጩ በመታገዳቸው ሙያዊ ተልእኳቸውን ለመወጣት እንደተቸገሩ

የዐውደ ጥናቱ አንዳንድ ተሳታፊዎች በምሬት ገልጸዋል። ለምሳሌም የኢትዮጵያ ሕዝብ በ2016 ምን እንደሚመስል የሚያመለክተው ድራማ ለተወሰነ ጊዜ ተላልፎ መታገዱ፣ ሌሎች ድራማዎችም የሕዝብን ባህል ይነካሉ፤ የሴቶችን የበታችነት ያንፀባርቃሉ፣ በሚል ሰበብ በመታገዳቸው ባለሙያዎችን ከቴሌቪዥን የማራቅ አዝማሚያ ስላለ ብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት በጉዳዩ እስካመነበት ድረስ ኃላፊነት ሊወስድና መከታ ሊሆን እንደሚገባ አስተያየት ቀርቧል።

በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል። ጐጂ ልማዶችንና ሴቶችን የበታች አድርጐ የማየትን ጨምሮ ሌሎች ማኅበራዊና ልማዳዊ ችግሮችን ባለሙያዎች በወጉ በመፈተሽ፣ ችግሮች ሊያማቸውና ሊቆጠቁጣቸው እንደሚገባና የአፈታት መላውንም ከውስጣቸው ማመንጨት እንደሚኖርባቸው ተብራርቷል። ያሉትን ችግሮች ለኅብረተሰቡ ማሳየት፣ ለለውጥ ማነሣሣት፣ ወደመፍትሔ እንዲያመራ የሚገፋፉ ጭብጥ ማስተጋባት፣ አፈጻጸሙን በማሳመር ማስተላለፍ የተሻሉ እንደሆኑ ተወስቷል። በተጨማሪም በአንድ ድራማም ሆነ መልእክት ላይ ሁሉም ሰው ወይም አካል በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ዓይነት አቋም ወይም ምላሽ እንደማይኖረውና በመገናኛ ብዙኃንም በርካታ ቃፊሮች (Gatekeepers) እንዳሉ በማሰብ የትያትር ባለሙያዎች በሚያጋጥሟቸው አንዳንድ ችግሮች ተስፋ በመቁረጥ ከሙያው ለመራቅ ማሰባቸው ተገቢ እንዳልሆነ ተወስቷል። የመገናኛ ብዙኃን ድርጅቱም ግልጽና ቀጥተኛ አስተያየት/ግምገማ ለመስጠት የሚያስችል አንድ ወጥ የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ችግሩን ለማቃለል እንደሚረዳ በውይይቱ ላይ ተጠቅሷል።

<u>ለምን የትያትር አይነቶች አልተስፋፉም?</u>

ትያትር ለልማት፣ ሕዝባዊ ትያትር፣ ተሳትፎአዊ ትያትርና የመሳሰሉት በኢትዮጵያ ለምን አልተስፋፉም? ኬንያና ዩጋንዳ ከደረሱበት ደረጃ አንፃር በአገራችን የሚቀርቡት ድራማዎች/ትያትሮች ማኅበራዊ ችግሮችንና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችን ለመፍታት ዓላማና ግብ ያላቸው ናቸው? የሕዝቡን ችግሮች ምን ያህል ይፈታሉ? የትያትር አማተሮችም ሆኑ ባለሙያዎች ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ? የሚሉ ጠንካራ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የተጠቀሱት ዓይነት ትያትሮች በአገራችን ላለመለመዳቸው ከሥልጠና መርሐ ግብር፣ ከሠልጣኞች ሙያዊ ብቃት፣ ከትያትር ቤቶችና ከማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር/ቢሮዎች በጐ ፈቃደኝነትና ከተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች አንፃር በጥልቀት መፈተሽ እንዳለባቸው ተጠቁሟል።

### ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት መፍጠር

በሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች አኳያ የሚቀረጸውን የኢትኮ መርሐ ግብር ከዳር ለማድረስ በሥነሕዝብ፣ በመገናኛ ብዙኃንና በትያትር ጥበብ ባለሙያዎች መካከል ጥብቅ የሥራ ግንኙነት መኖር እንዳለበት ይታመናል። ይሁን እንጂ ጥብቅ ግንኙነት ስለሌለ የሚጠበቀውን ያህል ሥራ በቅንጅት ለመሥራት ስላልተቻለ ወደፊት ጠንካራ ሙያዊ ግንኙነት ለመፍጠር ትኩረት እንደሚሰጠው በውይይቱ ላይ የተነሣ ነጥብ ነው።

## ጉባኤ ዘጠኝ

### 9.1 የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቅል ሐሳብ

ኪነጥበብና ማኅበራዊ ጠቀሜታው

*ልጅ ወንድሜ ላእከማርያም፣ የሐበሻ የትያትርና ሙዚቃ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አስኪያጅ*

ጥናታዊ ጽሑፉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ ኪነጥበብ (ትያትርና ሙዚቃ) ለማኅበራዊ ችግሮች መቀረፍ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የሚቃኝ ነው። የጥናቱ የመጀመሪያ ክፍል ማኅበራዊ ችግሮች ብዙና ሰፊ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮች፣ የሴቶች ፆታዊ በደሎች፣ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንደሆኑ በመጥቀስ ምንነታቸውን ያብራራል። በሁለተኛው ክፍል ማኅበራዊ ኑሮ፣ ልማድ፣ አስተሳሰብና አስተዳደግ በቤተሰብም ሆነ በት/ቤት ደረጃ በተፈለገው መንገድ አለመዳበሩና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት መጫጫቱ ለማኅበራዊ ችግሮች መበራከት መንሥኤዎች እንደሆኑ ተገልጿል።

በሦስተኛው ክፍል ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ተብለው የሚዘጋጁት ትያትሮችና ሙዚቃዎች ከታለመው ኅብረተሰብ ዘንድ ደርሰው ተገቢውን ግንዛቤ ሊያስጨብጡ እንዲችሉ «ወግና ደርዝ ኖሯቸው ጥበባዊ ምልዓታቸው በሚስብ መልክ» መቅረብ እንዳለበት ተተንትኗል። እንዲህ ያሉ ትያትሮችና ሙዚቃዎችም በታላላቅ መድረኮች፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ሥርጭት ብቻ፣ ከመወሰን ይልቅ በጥናት ላይ ተመሥርተው ባህላዊ መገናኛን (Folk Media)፣ በርካታ ሕዝብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚሰባሰብባቸው መድረኮችና ት/ቤቶች መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ተገልጿል።

የጥናቱ አራተኛ ክፍል ሐበሻ የትያትርና ሙዚቃ ኢንተርፕራይዝ መሠረታዊ ዓላማዎችና ድርጅቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት ለመግታት ያደረገውን እንቅስቃሴ («ኪነጥበብና ኤድስ» በሚል ርእስ ስላዘጋጀው ዐውደ ጥናት) ያብራራል።

## 9.2 ውይይትና የተነሡ ዐበይት ነጥቦች

### በሕፃናት መደፈር ላይ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን

በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ጥቃቶች አንዱ አስገድዶ መድፈር ነው። ሕፃናት ሴቶች በቅርብ ዘመዶቻቸው (አባት፣ ወንድም፣...) እንደተደፈሩ የሚገልጽ ዜና በመገናኛ ብዙኃን ይተላለፋል። እንዲህ ያሉ ወንጀሎች በመገናኛ ብዙኃን እስከምን ድረስ መዘገብ (ሽፋን ማግኘት) እንዳለባቸው ጥያቄ ቀርቧል። በጉዳዩ ላይ ሁለት የመከራከሪያ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል። አንደኛው ሐሳብ እንዲህ ያሉ ወንጀሎች፦

- ለሕዝብ ይፋ ሲሆኑ ኅሊናን ስለሚያቆስሉና ስለሚዘገንኑ፣
- ወንጀል ይፋ ሲሆን የወንጀል ቴክኒኩም አብሮ እንዲስፋፋና እንዲበራከት አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ፣
- የኅብረተሰቡ ንቃተ ኅሊና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ስለሆነ በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን መሰጠት የለበትም፣ የሚል ነው።

ሁለተኛው ሐሳብ ደግሞ፦

- ሕዝቡ መረጃ የማግኘትና የማወቅ መብት ስላለው፣
- በሕዝብ ውስጥ ያለን ችግር ከመደበቅ ይልቅ ይፋ ማድረግ ስለሚመረጥ፣
- ኅብረተሰቡ የራሱን ማኅበራዊ ችግር በራሱ እንዲማማርና መፍትሔ እንዲፈልግ ስለሚያግዝ ሕፃናትን የመድፈርና የመሳሰሉት ወንጀሎች በመገናኛ ብዙኃን ይፋ መሆን አለባቸው፤ ይፋ ሲሆኑ ግን ጥንቃቄ ይደረግ፣ የሚል ነው።

ለዚህም የመገናኛ ብዙኃን ሙያዊ ተልእኳቸውን ሲወጡ የወርቃማውን አማካኝ መርህ (The Principle of Golden Mean) ተከትለው ቢሠሩ የተሻለ እንደሆነ አስተያየት ተሰጥቷል።

### ተከታታይ ሥልጠና ለአማተር ከያኒያን

አልፎ አልፎ በክልል ደረጃ ለአማተር የኪነጥበብ ሰዎች የአጭር ጊዜ ሥልጠና በተለያዩ አካላት ይሰጣል። ነገር ግን ከሥልጠናው በኋላ ሥራዎቻቸውን

የሚገመግምላቸውም ሆነ የሚከታተልላቸው ስለሌለና ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ሥልጠና ስለማይሰጥ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት እንዳልተቻለ አስተያየት ተሰጥቷል። በተለይም ማኅበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው እንቅስቃሴ መማር፣ ማወቅና የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጣ የሚጠበቀው ሕዝብ በክልልና በታዕታይ መስተዳድር መዋቅሮች (Grassroot Levels) ስለሚገኙና የተጠቀሱት ባለሙያዎችም የላቀ ሚና ሊጫወቱ ስለሚችሉ ለተከታታይ ሥልጠና ትኩረት ለምን አይሰጥም? ማነው ኃላፊነት መውሰድ ያለበት? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

በዚሁ መንፈስ በኅብረተሰቡ ዘንድ የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት ከሁሉ በፊት የለውጥ አራማጅ ኃይሎች ሙያዊ ብቃት ሊኖራቸው እንደሚገባና ለዚህም ሙያዊ ሥልጠና በተከታታይ መስጠትና ኢንፎርሜሽኑ ወይም ትምህርቱ የተሰጠው፣ ኅብረተሰብም ስለደረሰበት ደረጃ በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ግንዛቤ ተገኝቷል።

<u>ለባለሙያዎች የመሥራ ት ነፃነት/መብት</u>

የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ የመሥራት ነፃነት/መብት ሊኖራቸውና ምቹ ሁኔታዎች ሊፈጠሩላቸው እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል። በፍርሃትና በጥርጣሬ መንፈስ ውስጥ ተዘፍቆ ፈጠራዊ ሥራዎችን ለማመንጨት አዳጋች ስለሆነ ያሉትን ማኅበራዊ ችግሮችና ጎፀዎች ለሕዝቡ ለማስተማርና ለማሳወቅ ቀና መንፈስ በሁሉም አካላት ሊኖር እንደሚገባ ተጠቅሷል።

## 2.3 <u>የቡድን ውይይት</u>

የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሠሩባቸውን መሥሪያ ቤቶች/ድርጅቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሦስት ቡድኖች ማለትም በኅትመት መገናኛ ብዙኃን፣ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃንና በትያትር ጥበብ ዘርፍ ተከፍለው ውይይት አካሂደዋል።

### 2.3.1 <u>የቡድን ውይይቱ ዓላማ</u>

ብሔራዊ የሥነሕዝብ ፖሊሲ ዓላማዎቹንና ግቦቹን ለመቀዳጀት እንዲችል በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች የተዋልዶ መብት፣ የወጣቶች ተዋልዶ ጤና፣ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና በተዋልዶ የወንዶች ሚና ናቸው። ስለዚህም የቡድን ውይይቱ ዓላማ እነዚህንና ሌሎች ሥነሕዝብ ነክ ጉዳዮችን ሕዝቦች ወይም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲያውቋቸው፣ እንዲገነዘቧቸው፣

የአመለካከት፣ የእምነትና የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጡና ተግባራዊ እንዲያደርጉ [Knowledge, Attitude, Belief, Behaviour, Practice, (KABBP)] ጋዜጠኞችና የትያትር ጥበብ ባለሙያዎች በሚኖራቸው ሚና ላይ መወያየት፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮች መለየትና የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆም ነው።

## 2.3.2 የቡድን ውይይቱ የመነጋገሪያ ሐሳብ

የቡድኑ ውይይት የመነጋገሪያ ሐሳብ ሁለት ዋና ነጥቦች ነበሩት። የመጀመሪያው የሥነሕዝብ ፖሊሲውን ጨምሮ ማንኛውም የልማት ወይም የማኅበራዊ ፕሮግራም ስኬታማ እንዲሆን መሟላት ባለባቸው መሠረታዊ አላባውያን ላይ በመወያየት ግንዛቤን ማዳበር ነው። መሠረታዊ አላባውያን የሚባሉት፦

1. የመንግሥት ቁርጠኝነት/ሙሉ ፈቃደኝነት (Political Will/Commitment)
2. ቴክኒካዊ ድጋፍ (Technical Support)
   - 2.1 ኃላፊነት የተሰጠው ድርጅት/መሥሪያ ቤት መኖር፣
   - 2.2 መ/ቤቱ ከማእከል እስከ ታዕታይ የመስተዳድር መዋቅር ድረስ መዘርጋት፣
   - 2.3 የተቀናጀ አሠራር ማካሄድ (ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር)
   - 2.4 የአስፈላጊው ቁሳዊ ሃብት መሟላት፣
   - 2.5 በመስኩ የሠለጠነ የሰው ኃይል መኖር፣
   - 2.6 ተስማሚ የኢትኮ ስትራቴጂና መርሐግብር መቅረጽና መተግበር፣
   - 2.7 የማኅበረሰቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎ መኖር ናቸው።

ሁለተኛው ነጥብ ቡድኖች ከኅትመት መገናኛ ብዙኃን፣ ከኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን ወይም ከትያትር ጥበብ አኳያ የሥነሕዝብ ጉዳዮችን በሚመለከት እየተደረጉ ያሉ ሥራዎችንና እንቅስቃሴዎችን በመዳሰስ ያጋጠሙ ችግሮችን መዘርዘርና ችግሮችንም ለማቃለል የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆም ነው። በዚሁ መሠረት ሦስቱ ቡድኖች ያቀረቧቸው ሪፖርቶች ቀጥሎ ቀርበዋል።

## 2.3.3 ቡድኖች ያቀረቧቸው ሪፖርቶች

### 2.3.3.1 የሥነሕዝብና የኅትመት መገናኛ ብዙኃን ቡድን ሪፖርት

ሀ. ያጋጠሙ ችግሮች

1. በሙያው የተሠማሩ ስለ ሥነሕዝብ በቂ ዕውቀት አለመኖር፣

2. በኅትመት ለሚወጡ ጉዳዮች የጋዜጠኛው ብቻ ተጠያቂ መሆን፣

3. የሚተላለፉ መልእክቶች ግልጽነት አለመኖር፣

4. ብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ እንዲወጣ ተገቢው ሁሉ አለሟላት፣

5. የቅንጅት አሠራር ችግር

6. ለሥነሕዝብ ጉዳይ የኅትመት መገናኛ ብዙኃን ተገቢውን ቦታና ዓምድ አለመስጠት፣

7. ኅብረተሰብ ስለሥነሕዝብ በቂ ዕውቀት እንዲኖረው አለማደረግ፣

8. የጋዜጦችን ሥርጭት በተመለከተ የክትትል ሥራ አለመሠራት።

ለ. <u>የመፍትሔ ሐሳቦች</u>

1. በሙያው ለተሠማሩ ጋዜጠኞች ተከታታይ ሥልጠና መስጠት አለበት፣

2. ሙሉ መረጃዎችን የማግኘት መብት እንዲረጋገጥ ማድረግ ያስፈልጋል፣

3. ከሥርጭት በኋላ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የጋራ ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፣

4. ለባሙያዎች ሥነሕዝብን በተመለከተ መመሪያ ጽሑፍ (Handbook) መዘጋጀት አለበት፣

5. በኅትመት መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፈው መልእክት ተጨባጭ ዓላማና ግብ (Smart Objective) ሊኖረው ይገባል፣

6. የመ/ቤቶች ቅንጅታዊ አሠራር መፈጠር ይኖርበታል።

2.3.3.2 ሥነሕዝብና የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን ቡድን ሪፖርት

ሀ. <u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>

1. ፕሮግራም ሲነደፍ የመነሻ ጥናትና ተከታታይ ፍተሻ አለመኖር፤
2. ገና ከመነሻው ታዳሚን ለይቶ አለመምረጥ፤ ፕሮግራሙ ከተላለፈ በኋላም የታዳሚ ጥናት ባለመኖሩ የአሠራርን ጥንካሬና ድክመት አለመመዘን፤
3. የፕሮግራሞች ተከታታይነት አለመኖር፤
4. መረጃዎችን ከሚመለከታቸው ክፍሎች በበቂ ሁኔታ አለማግኘት፤
5. የውሎ አበልና የመጓጓዣ እጥረት ስለሚያጋጥም ገጠሩን መድረስ አለመቻል፤

6. የመልእክትን ይዘት አለመመዘን፤
7. ከሚመለከታቸው ክፍሎች የሚገኙ ዕውነታዎችና አኀዛዊ መረጃዎች አንድወጥ አለመሆን፤
8. የኅብረተሰቡ አለመሳተፍ፤
9. የቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር (የሚዲያ ዘርፍ ከሚዲያ ዘርፍ፣ ከአስፈጻሚ መ/ቤቶችና ቢሮዎች፣ ወዘተ.)
10. የሥነጥበብ ሰዎችና ጋዜጠኞች ስለሥነሕዝብ ጉዳይ ያላቸው ግንዛቤና ዕውቀት አናሳነት፤
11. ለሚዲያ የሚቀርቡ ጭውውቶች ተደጋጋሚ መሆን፣ ግልጽነት ማጣት፤
12. ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክፍሎች (በሚዲያ ውሳኔ ሰጪዎች፣ በፕሮራም አስፈጻሚዎች) ትኩረት አለማግኘት፤
13. በሚዲያ የሚተላለፈው መልእክትና የአገልግሎት አቅርቦትና ሥርጭት ስለማይመጣጠን ተአማኒነትን ማጣት፣
14. የሥነሕዝብ ፕሮግራም ራሱን ችሎ አለመኖር፤
15. ከጤናና ከተዋልዶ ጤና ጋር የተዛመዱ ማስታወቂያዎች መልእክቶች የተፋለሱ መሆን ( ኮንዶም፣ ፒልስ ወዘተ. ወዘተ. )

ለ. <u>የመፍትሔ ሐሳቦች</u>

1. የመገናኛ ብዙኃን ለሥነሕዝብ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት፣
   - መደበኛ የአየር ጊዜ መስጠት፣
   - በተከታታይነት የሚያካሂዱበትን መንገድ መፍጠር ይኖርባቸዋል፤

2. ሥራዎች በጥናትና በምርምር፤ በእቅድ፣ በክትትልና ግምገማ (Monitoring & Evaluation) መታገዝ ይገባቸዋል።
3. የሥነሕዝብ ጉዳይ ትምህርት በአገልግሎት መደገፍ ስላለበት ስልት መቀየስ ይኖርበታል።
4. የሥነሕዝብ ጉዳይ ፕሮግራሞች ከብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት በሚገኙ ኢንፎርሜሽን፣ ግብዓቶችና ሥልጠና መደገፍ አለባቸው።
5. የሥነሕዝብ ጉዳዮችን ተፈጻሚና ውጤታማ ለማድረግ ብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ መገናኛ ብዙኃንና የክልል ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤቶች በቅንጅት የሚሠሩበት መንገድ መቀየስ አለበት።

6. በሥነሕዝብ ጉዳዮች ላይ ለሚሠሩ ጋዜጠኞች፣ የፈጠራ ባለሙያዎች (ኪነጥበብ ወዘተ.) ስለልማት ኮሙኒኬሽን፣ ስትራቴጂያዊ ፕላን (እቅድ አነዳደፍ)፣ የሙያ ወዘተ. ተከታታይ ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፤
7. ማንኛውም የንግድ ማስታወቂያ፣ በተለይም ከሥነሕዝብና ከጤና ጋር የተጎዳኙ ማስታወቂያዎች ከመቅረባቸው በፊት የሚያጠናና የሚቆጣጠር አካል መኖር አለበት፤ ጋዜጠኛው ተነሣሽነት ሊኖረው ይገባል።

## 2.3.3.3 የሥነሕዝብና የትያትር ጥበብ ቡድን ሪፖርት

### ሀ. ያጋጠሙ ችግሮች

1. የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በተጠናከረ መልክ ባለመደራጀታቸው ከመካከላቸው በሥነ ሕዝብና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ባለሙያዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥረው የተፈለገውን ያህል ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያለመቻል፤

2. በተናጠልና በራሳቸው ተነሣሽነት የሚያዘጋጁትን ሥነ ሕዝብ ነክ ተውኔቶች ለሕዝብ የሚያቀርቡበት መድረክ እንደልብ ለማግኘት ያለመቻልና አግኝተው ማቅረብ ከጀመሩ በኋላ ሥራዎቻቸው መታገዳቸው፤

3. በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ድራማዎችን ገምግሞ ለአየር ሥርጭት መዋል ወይም ያለመዋል የሚወስን አካል ያለመኖር፤

4. ፍላጐትና ተሰጥኦ ያላቸው የሥነ ጥበብ ሠራተኞች ሙያዊ ብቃታቸውን የሚያሳድጉበት የሥልጠና እድል ያለመኖር፤

5. በሀገሪቱ ውስጥ በየአካባቢው የሚገኙ የቲያትር ጥበብን የሚያራምዱ ትውፊታዊ ሀብቶች፣ ልማዳዊ ወጐች በአግባቡ ያለመጠናታቸው፣ ባህላዊ የመገናኛ ዘዴዎችን ለሥነ ሕዝብና ተዛማጅ ጉዳዮች መጠቀም ያለመቻል፤

6. በተለያዩ የትያትር ዓይነቶች ሕዝቡን በይፋና ይፋ ባልሆነ መንገድ (ስውር፣ ሽንጐ፣ ምስላዊ) የሚያሳትፉና፣ በጉዳዩ ላይ፦ ማለትም በሥነ ሕዝብ ችግሮች ላይ እየተወያየ ራሱ መፍትሔ እንዲያመነጭ የሚያስችሉት የጥበብ ሙከራዎች ሥራ ላይ በማዋል ፈንታ የተወሰኑ የአጻጻፍና የትወና ቴክኒኮችን ብቻ መጠቀም ናቸው።

እኛ የዚህ ዐውደ ጥናት ተሳታፊ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ድራማንና ሌሎች የኪነጥበብ ሥራዎችን አስፈሪና አስከፊ በሆነ ሁኔታ እየተባባሰ የመጣውን የኢትዮጵያን የሥነ ሕዝብ እድገት ሁኔታ ለመቆጣጠር በሚቻልበት ሁኔታ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በመድረክና በኦዲዮቪዥዋል ሚዲያዎች መጠቀም እንዲቻል የሚከተለውን ስልት በአጭርና በረጅም ጊዜ መርሐግብር በመክፈል ተግባራዊ እንዲሆን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ሐሳብ እናቀርባለን። ይኸውም ከታች የተቀመጡትን ሥነ ሕዝባዊ የኪነጥበብ ሥራዎች በመሥራትና በኅብረተሰቡ ውስጥ የአስተሳሰብና የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት፣

ሀ/ ከተለያዩ ሕዝባዊ የኪነጥበባት ቡድኖች (ከኪነጥበባት ኢንተርፕራይዞች፣ ከክበባት፣ በግል ከሚንቀሳቀሱ ሙያተኞች እሚወከሉ)፦ ከሥርዓተ ትምህርትና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የዲሞግራፊ ሥልጠናና ምርምር ማእከል፣ እና ከትያትር ጥበባት ክፍል፣ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ፣ ከብሔራዊ ትያትርና ከኮፋፕ የተውጣጣ አንድ ኮሚቴ ማቋቋም፣

ለ/ ለቴአትር ጥበባት ባለሙያዎች በሙያው (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በተሳትፎአዊ ቴአትሮች) እና በሥነሕዝብ ጉዳዮች ላይ የአጭርና የረዥም ጊዜ የሥልጠና እቅድ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣ የሚሉት ዐበይት ተግባራት ናቸው።

ሉ. <u>የመፍትሔ ሐሳቦች</u>

1. ድራማ እንደሬዲዮና ቴሌቪዥን ሁሉ ከመገናኛ ዘዴ አውታሮች አንዱ መሆኑ ታውቆ ዘላቂነትና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ፦
   - በትያትር ቤቶች፣
   - በሬዲዮና በቴሌቪዥን /በተከታታይ «በሲሪያል»/
   - በማእከልና በክልል የገበያ ሥፍራዎች
   - በሌሎች የሕዝብ መሰብሰቢያ ሥፍራዎች (በአደባባዮች፣ በአውቶቡሶችና በባቡሮች ላይ፣ በእድሮች፣ በጠጅና በጠላ ቤቶች ወዘተ.)

- በሕዝብ በዓላት ማክበሪያ ሥፍራዎች /በሃይማኖት በዓላት፣ በጥምቀተ ባሕሮች፣ በታቦት ንግሥ ቀናት፣ በኢድና በአረፋ ወዘተ.)
- በብሔራዊ በዓላት ቀናት (የካቲት 12፣ 23፣ ግንቦት 20፣....)
- በሌሎች ልዩ ልዩ ቀናት (በዓለም የኤድስ፣ የሥነ ሕዝብ፣ የቱሪዝም፣ የአካባቢ ወዘተ.)

የብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን ዓላማዎችና ግቦች በሚያራምዱበት መንገድ በብሔራዊ ቋንቋችንና በተለያዩ ሀገርኛ ቋንቋዎች በመላ ሀገሪቱ በሚታይበት መንገድ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ አለበት፤

2. በግል የሚንቀሳቀሱና የመንግሥት ተቀጣሪ የትያትር ባለሙያዎች (ጸሐፌ ተውኔት፣ ተዋንያንና አዘጋጆች) በአጫጭር የትምህርት ሥልጠናና የሥራ ጉብኝት መልክ «ትያትር ለልማት» ወደዋለባቸው አዳጊ ሀገሮች እየተላኩ የሙያ ክሂሎታቸውን የሚያዳብሩበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፤

3. የሕዝቡ ወደትያትር የመምጣት ዐቅምና ግንዛቤ ያልዳበረ መሆኑ ታውቆ በየቀበሌው (በከተማና በገጠር) የወጣት የትያትር፣ የኪነት ቡድኖች ተደራጅተው በሕዝባዊ ትያትር አማካይነት የሥነ ሕዝብንና የሌሎች ተጓዳኝ የልማት ተግባራትን ዓላማና ግቦች የሚያስፈጽሙበት መንገድ ሊቀየስ ይገባል፤

4. በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሥነ ሕዝብ፣ የኤድስ፣ የአካባቢ ልማት ጥበቃ ክበባት አባላትን ማንቀሳቀስና በት/ቤቶች ያለውን አሠራርና አደረጃጀት ከቀበሌዎች ወጣቶች ክበባትና የኪነት ቡድኖች ጋር ማስተባበር የሚቻልበት መንገድ ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆን አለበት፤

5. አንድ የ'Audio - visual' ማእከል ተቋቁሞ የተሠሩትን ሥራዎች እየቀረጸ ለሕዝብ እንዲያሠራጭና፤ የወጣት ክበባትና የኪነት ቡድኖች የሬዲዮና ቴሌቪዥን ድራማዎች የሚከታተሉባቸው ሬዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች በእርዳታ የሚያገኙበት መንገድ ቢመቻች፤ በተጨማሪም የቴሌቪዥን ሥርጭት በሚዳረስባቸው የከተማና የገጠር ቀበሌ ጽ/ቤቶች ለሕዝብ አገልግሎት የሚውሉበት መንገድ መመቻቸት ይኖርበታል፤

6. ባህላዊ ሚዲያዎች (አፈርሳታ፣ ጉማ፣ እግዚአታ፣ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎች፣ ተረቶች ወዘተ.) ተጠንተው የሥነ ሕዝብ ዓላማዎችን ለማራመድ የሚውሉበት መንገድ ከወዲሁ እንዲታሰብበት ጥረት መደረግ ይስፈልጋል፤

7. የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በሥነ ሕዝብና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ሕዝብን ያስተምራሉ፣ ያዝናናሉ፣ ያሳውቃሉ ብለው የሚያዘጋጁቸውን የጥበብ ውጤቶች ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ በመገናኛ ብዙኃንና በሌሎች የጥበብ መድረኮች በመጠቀም ሥራቸውን የሚያስተላልፉበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል።

## 2.4 የመዝጊያ ንግግር

ለሦስት ቀናት በተካሄደው ዐውደ ጥናት ማጠቃለያ ላይ ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ፣ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ የመዝጊያ ንግግር አድርገዋል።

ዶ/ር ንጉሤ ባደረጉት ንግግር የቀረቡት የጥናት ጽሑፎችና የተደረጉት ውይይቶች ጋዜጠኞችንና የኪነት ባለሙያዎችን በሥነሕዝብ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ከማስጨበጥ በሻገር እስካሁን ሕዝብን ለማስተማርና ግንዛቤ ለመፍጠር የተደረጉ ሥራዎችን ለመገምገም በመቻሉ ዐውደ ጥናቱ ፍሬያማ እንደሆነ አስታውቀዋል። በዐወደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የተዘረዘሩት ችግሮችና የተጠቆሙት የመፍትሔ ሐሳቦች ለዐውደ ጥናቱ ዓለማዎች ግብ መምታትና ውጤታማ መሆን ማረጋገጫዎች መሆናቸውን የጽ/ቤቱ ኃላፊ አብራርተዋል።

ዶ/ር ንጉሤ የተጠቀሱት የመፍትሔ ሐሳቦች ጽ/ቤቱንና ሌሎችንም መ/ቤቶች የሚመለከቱ እንደሆኑ በመግለጽ፣ ጽ/ቤቱ ዋና ነጥቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ ለመሥራት የሚቻለውን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል።

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

# የመክፈቻ ንግግሮች

በ"ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን" ዐውደ ጥናት መክፈቻ ላይ

አቶ ጎኑይ ምትኩ ፣

የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ የትምህርትና
የኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ ያደረጉት

የመግቢያ ንግግር

ክብርት ወ/ሮ ብሥራት ጋሻው ጠና – የማስታወቂያና ባህል ምክትል ሚኒስትር
ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ – የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ

ክቡራትና ክቡራን

በቅድሚያ በዚህ ዐውደ ጥናት ላይ ለመሳተፍ ጥሪያችንን አክብራችሁ በመምጣታችሁ በብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤትና በራሴ ስም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የኢትዮጵያ ሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በሚያዝያ 1985 ዓ/ም ከታወጀ ጀምሮ መገናኛ ብዙኃን "ሥነ ሕዝብና ልማት" በሚል ርእስ በልዩ ልዩ የአገርኛ ቋንቋዎች ሳምንታዊ ፕሮግራሞችን ከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ተከታታይነት ባይኖረውም፣ በድራማ ሥነ ሕዝብ ነክ መልእክቶች በመገናኛ ብዙኃን አልፎ አልፎ ይተላለፋሉ።

የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ከመውጣቱም በፊት ቢሆን ማለትም ከ1980 ዓ/ም ጀምሮ መገናኛ ብዙኃን ከተባበሩት መንግሥታት የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ጋር በመተባበርና በፕሮጀክት በመታቀፍ አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበር ይታወቃል።

በኪነ ጥበብና በሥነ ጥበብ መስክ ግን በቁጥር ከሚታወቁት ሥራዎች በስተቀር ፕሮግራም ተይዞላቸው ተከታታይነት ባለው መልክና ወደ ተፈላጊው ታዳሚ (Target Audeince) ያነጣጠሩ ሥራዎች እንዳልተሠሩ ግልጽ ነው።

የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በዚህ መስክ ግንዛቤያቸውን በይበልጥ በማሳደግ ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ፣

"ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን" በሚል ርእስ ይህ ዐውደ ጥናት ተዘጋጅቷል። በዚህ ዐውደ ጥናት፦

- ሥነ ሕዝብ፣ ልማትና የአካባቢ ሁኔታ፤
- ሥነ ሕዝብና ኮሙኒኬሽን፤
- የጤና ፕሮግራሞችና የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት፤
- የወጣቶች ተዋልዶ ጤና፤
- በእናቶችና ሕፃናት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፤
- ማኅበራዊ ግብይትና የሚዲያ ሚና፤ (social marketing and the role of mass media)

* በመገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ድራማዎች ለሥነ ሕዝብ ጉዳይ ያላቸው ጠቀሜታ፣

* ኪነጥበብና ማኅበራዊ ጠቀሜታው፣

በሚሉ ርእሶች ጥናታዊ ጽሑፎች ይቀርባሉ። በነዚህም ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ በመመሥረት በሚደረጉት ውይይቶች የዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የልምድ ልውውጥ በዚህ መስክ የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍተኛ እንደሚሆን እምነታችን ነው።

ይህንን ዐውደ ጥናት በንግግር እንዲከፍቱልን ክብርት ወ/ሮ ብሥራት ጋሻውጠናን በትሕትና እጠይቃለሁ።

*አመሰግናለሁ።*

## ክብርት ወ/ሮ ብሥራት ጋሻውጠና፣ የማስታወቂያና ባህል ም/ሚኒስትር ከየካቲት 7 እስከ 9 ቀን 1992 ዓ.ም. ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት «ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን» በሚል ርእስ ያካሄደውን ዐውደጥናት ሲከፍቱ ያደረጉት ንግግር

*የተከበራችሁ እንግዶች!*

*የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሆናችሁ የመገናኛ ብዙኃንና የሥነ ጥበባት ሙያተኞች!*

*ክቡራትና ክቡራን!*

ከሁሉ አስቀድሜ ይህንን «ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን» በተሰኘ ርእስ ለጋዜጠኞችና የቲያትር ባለሙያዎች የተዘጋጀውን ዐውደጥናት ለመክፈት እድል በማግኘቴ የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ።

የሥነ ሕዝብ ጉዳይ በኢትዮጵያ ልማት ሂደት ትልቅ ትኩረት የሚያሻው መሆኑን በማመን የኢፌዲሪ መንግሥት በ1985 ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ፖሊሲው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛቱ ከልማቱ ጋር እንዲጣመር ስለጉዳዩ ምንነት የማሳወቅና የማስተማሩ አስፈላጊነት አስምሮበታል። በዚህ ረገድ ስለ ሥነ ሕዝብና ልማት ቅንጅት ለማስገንዘብ፣ ለማስተማርና ለማነሣሣት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ቢጠበቅበትም በመገናኛ ብዙኃንና በሥነ ጥበባት ተግባራት ላይ የተሠማሩ ጋዜጠኞች፣ ደራስያንና ተዋንያን ግምባር ቀደም ግዴታ አለባቸው።

*ክቡራትና ክቡራን!*

የሥነ ሕዝብን ፖሊሲ በማስፈጸም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባከናወኗቸው ተግባራት ለዓለም አቀፍ ሽልማትና አድናቆት መብቃታቸው በእዚህ አጋጣሚ መጠቀስ ያለበት አርአያነት ያለው አኩሪ ተግባር ነው። የክልል የማስታወቂያና የባህል ቢሮዎችና የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤቶች በሬዲዮ፣ በመጽሔቶች፣ በጋዜጦች፣ በፖስተሮችና በበራሪ ጽሑፎች አማካይነት የሥነ ሕዝብን መልእክቶች በማስተላለፍ ረገድ እያከናወኑት ያለው ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ሬዲዮ ፋና በሚያስተላልፏቸው ሳምንታዊ የሥነ ሕዝብ ፕሮግራሞች ሕዝቡን ስለጉዳዩ ምንነትና ስለጠቀሜታቸው በማሳወቅና በማስተማር የተያያዙት ተግባር አበረታች ነው።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም ከብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት በመቀናጀት አልፎ አልፎ እንደአመችነቱ ሳይሆን ቢቻል እንደሌሎቹ የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች የሥነ ሕዝብን ጉዳይ በየቋንቋ ክፍሎቹ ማሠራጨት የሚጀምርበትን ሁኔታ በማጥናት ተግባራዊ የሚያደርግበት ዘዴ አስፈላጊ ይሆናል።

የግል የኅትመት መገናኛ ብዙኃንም አልፎ አልፎ ከሚያሠራጯቸው የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ዜናዎች በስተቀር ይህን ጉዳይ ትኩረት ያልሰጡት በመሆኑ በዚያ አኳያ በብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት በኩል ጠንካራ ሥራ መሠራት ይኖርበታል።

በተመሳሳይ መልኩም የኪነ ጥበብ ሙያተኞች ከማስታወቂያና ባህል ሚ/ርና ከብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር ካቀረቧቸው ጥቂት ቲያትሮች በስተቀር የሥነ ሕዝብን መልእክት የሚያስተላልፍ ቲያትርም ሆነ ጭውውት እምብዛም አይተኮርበትም። በሙያተኞችም በኩል ዝግጅት ቢኖርም ለመድረክ ለማብቃት የሚያስፈልገው የሀብት ቅንጅት በበቂ ሁኔታ አይገኝም። ስለሆነም በትያትር ድርሰትና ትወና ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ሥነ ሕዝብን በተመለከተ በተለይም ጐጂ ልማዶችንና ቀሳፊውን ኤድስ የመሳሰሉ አደገኛ ማኅበራዊ ችግሮችን፣ በጠቅላላውም የሥነ ሕዝብንና ተዋልዶ ጤናን ጉዳዮች ከሥነ ሕዝብና ልማት፣ እንዲሁም ከተፈጥሮ አካባቢ ጋር በማገናዘብ እያዝናኑ የማያስተምሩበትንና የሚያሳውቁበትን ቀና መንገድ ለመዘርጋት የሁሉም አካላት ቅንጅትና ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ ብሔራዊ ቅንጅታዊ አሠራሩን የበለጠ የሚዳብርበትን ሁኔታ መሻት ይኖርበታል። ከዚሁ ጐን ለጐን ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮም ሆነ ከሀገራችን ሁኔታ በመነሣት ለሕዝቦች ባህላዊ መገናኛዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት እነዚህ የመገናኛ ስልቶች ዳብረው ተፈላጊውን መልእክት ለማድረስ እንዲችሉ አስፈላጊው ሥራ ሁሉ መከናወን ይኖርበትል። ለማጠቃለም የዐውደጥናቱ ተሳታፊ ጋዜጠኞችና የቲያትር ባለሙያዎች በተሠማራችሁባቸው ሙያዎች የሕዝባችንን ባህል ከሥነ ሕዝብ ተልእኮ ጋር በማጣጣም የሕዝብ ብዛትና ምርት ካልተጣመሩ አገራችን ለረሃብ፣ ለእርዛት፣ ለጤና መጓደል በጠቅላላውም ለባሰ ኋቀርነት መዳረጓ እየተባባሰ መሄዱ አይቀሬ መሆኑን ማስገንዘብ ይጠበቅባችኋል። ከዐውደጥናቱ በምታገኙት ግንዛቤ የሙያ መስካችሁ ለሥነ ሕዝብ ተግባራት የምትሰጡትን ትኩረት እንደምታጐለብቱም አምናለው። የተሳካና ፍሬያማ ዐውደጥናት እንዲሆን እመኝላችኋለሁ።

አመሰግናለሁ።

## አባሪ ሁለት

# የጥናት ጽሑፎች

# ስነ ህዝብ፣ ልማትና አካባቢ በኢትዮጵያ

በሲሳይ ወርቁ

## 1. መግቢያ :-

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የነበረው 1.65 ቢሊዮን የዓለም ህዘብ በክፍለ ዘመኑ መገባደጃ ላይ ከ 6 ቢሊዮን በላይ ተመዝግቧል። ኢትዮጵያ ሃያኛው ክፍለ ዘመንን ( ማለትም እ.ኤ.አ. 1900 ) የተቀበለችው በግምት በ 11 ሚሊዮን ህዝብ ሲሆን፣ ክፍለ ዘመኑን ያጠናቀቀችው ( ማለትም እ.ኤ.አ January 1, 2000 ) በ 62.6 ሚሊዮን ህዝብ ነው። ሀያኛው ክፍለ ዘመን በአለምም ሆነ በሀገራችን ከፍተኛ የህዝብ ዕድገት የተመዘገበበት ብቸኛ ክፍለ ዘመን ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሊታይ የሚችለው የህዝብ ዕድገት ምን ሊመስል ይችላል?

የሕዝብ ዕድገት ፈጽሞ አይታይም?
ዕድገት ይቀንሳል? ወይስ
በ20ኛው ክፍለ ዘመን ያልታየ ከፍተኛ ዕድገት ይታያል?

ከሦስቱ አንዱ ሊከሰት ይችላል። ሆኖም ጥያቄዎን በአግባቡ ለመመለስ የህዝብ ዕድገት ምክንያቶቹን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በጥልቅ መመርመር ያስፈልጋል። ለህዝብ ለውጥ ወይም ዕድገት ዋና ምክንያቶች ወሊድና ሞት ናቸው። የሞት መጠን በ ኤች አይቪ ኤድስ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ልዩ ትኩረት አግኝቷል። ኤች አይቪ ኤድስ በሞት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ቢሆንም በወሊድ ላይም ተጽዕኖ በማሳደር የሀገሪቱን የህዝብ ዕድገት ሁኔታ ሊለውጡት እንደሚችሉ ይገመታል። ሆኖም በምን ያህል የሚለውን ለመመለስ የሚያስችል የተደራጀ መረጃ የለም። ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ ህዝብ በአማካኝ በአመት ቢያንስ በ 1.8 ሚሊዮን ሰዎች እንደሚያድግ የጠቅላይ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አመልክቷል። የጠቅላይ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለህዝብ ዕድገት ምክንያት ለሆኑት የወሊድ ና የሞት ሁኔታ የወሰዳቸው ታሳቢዎች ዕውን ቢሆን፣ ከ30 ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት አሁን ባለው ላይ 67 ሚሊዮን በመጨመር በ 2030፣129 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። ሊከሰት የሚችለው ዕድገት ይብዛም ይነስ፣ ከወደፊት የሀገሪቱ የህዝብ ዕድገት አካሄድ አንፃር ሊነሱ እና ሁሉንም ሊያወያዩ ከሚገባ የልማት ጥያቄዎች የተወሰኑትን ለመጥቀስ፣

- ለሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ከሆኑት አንዱ ምግብ ነው። አሁን ላለው ህዝብ በበቂ መጠንና ጥራት የሚፈለገውን ምግብ ሚሟላት ባልቻልንበት ሁኔታ ቢያንስ በየዓመቱ በ 1.8 ሚሊዮን

ለሚጨመረው የኢትዮጵያ ህዝብ የምግብ አቅርቦትን እንዴት ማሟላት ይቻላል?

- ዛሬ ለሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ማዳረስ ባልተቻለበት ሁኔታ እያደገ ለሚመጣው ህዝብ እንዴት ማዳረስ ይቻላል?
- በአሁኑ ወቅት ስራ ፈላጊ ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ስራ መስጠት ባልተቻለበት ሁኔታ ቢያንስ በየአመቱ በአማካኝ በአንድ ሚሊዮን ለሚጨምረው የሰው ኃይል እንዴት ስራ ማዳረስ ይቻላል?
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ ባልተቻለበት ሁኔታ ውስጥ በአማካኝ በአመት በ140 ሺህ እያደገ ለሚመጣው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፈላጊ ወጣት እንዴት ትምህርት ለሁሉም የሚለው ግብ ላይ ይደረሳል?
- የመጠጥ ውሃ፣ መጠለያና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ባልተሟሉበት ደረጃ ላይ እያለን እያደገ የሚመጣውን ህዝብ ፍላጐት እንዴት ማሟላት ይቻላል?
- የመጪውን ትውልድ ሕይወት ጉዳት ላይ ላለመጣል በህዝብና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለውን ሚዛን እንዴት ጤናማ ማድረግ ይቻላል?

ከላይ ከተነሱት መሠረታዊ የልማት ጥያቄዎች አንፃር የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያመለክተው የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ስነ ህዝብና ልማት ላይ እኩል ክብደት ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ነው።

## 2. ህዝብና ልማት

ህዝብና ልማት ፍፁም ሊነጣጠሉ የማይችሉ የተሳሰሩ ጉዳዮች ናቸው። ለዚህም ነው የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን ዘለቄታዊነት ያለው ልማት ለማምጣት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሕዝብ ጉዳይን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው የሚባለው። ተለዋዋጭ የሆኑ የዲሞግራፊ ባህርያትን ያላገናዘበ

የልማት ጥረት ሊያስከትል ከሚችላቸው ችግሮች መካከል የተወሰኑትን ለመጥቀስ ፡-

- የተፈለገውን የልማት ግብ / አላማ / አለማስመዝገብ፣
- ውስን የሆነው የሰው ኃይል፣ የተፈጥሮ ሀብት ና የገንዘብ ሀብት ላይ ብክነት መድረስ፣
- ድህነትን ማባባስ ናቸው ።

በተለይ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ማንኛውም የልማት ጥረት የህዝብ ጉዳዮችን ማገናዘበ አለባቸው የሚባለው ከሚከተሉት ዕውነታዎች በመነሳት ነው ፡-

ሀ/ ህዝብ ልማትን አካሄጅ ዋናው ኃይል እና ከልማት የሚገኘውንም ውጤት ዋናው ተጠቃሚ ስለሆነ፣

ለ/ ህዝብ በልማት ላይ አውንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርስ የሚችል፣ መልሶም ልማት በህዝብ ላይ ይህንን ተጽዕኖ ስለሚያደርስ፣

ሐ/ ማንኛውም የልማት ችግር ውስብስብና የብዙ ጉዳዮች ጥርቅም ውጤት ነው። ማለትም የአንድ የልማት ችግር ምክንያቶች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ፣ ፖለቲካዊ ና ዲሞክራፊያዊ ይዘት ሊኖረው ስለሚችል፣

መ/ እነዚህን ከላይ የተመለከቱትን እውነታዎች ትኩረት ያልሰጠ የልማት አካሄድ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በአካባቢው ህዝብ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ አላስፈላጊ የሆኑ ተጾዕኖዎች በማድረስ ውስን ሀብትን በአግባቡ ና ለተፈለገው ህዝብ ጥቅም ላይ እንዳይውልና ምናልባትም የመጪውን ትውልድ ህይወት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል።

ስለ ህዝብ ና ልማት ትስስር ሲወራ ብዙ ጊዜ የተሳሳተ ትርጉም ይሰጣል። ይኸውም ህዝብን «ቁጥር» አድርጐ የመውሰድ። ህዝብ ግን ከቁጥር ባሻገር ከተለያዩ

የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነው ። በእርግጥ ስለ ህዝብ ሲነሳ ስለ ህዝብ ቁጥር ወይም ዕድገት ማውሳት አንዱ ጉዳይ ነው። ሆኖም የህዝብ ቁጥር ወይም ዕድገት ውጤት መንስኤዎቹ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከኢኮኖሚ፣ ከምግብ፣ ከባህላዊና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ግንኙነት ስላለው በስፋት መዳሰስ ይኖርበታል።

በቻርት 1 ላይ እንደተመለከተው በህዝብና በልማት መካከል ያለው ትስስር የሚጀምረው መሰረታዊ ከሆነው የዲሞግራፊ ባህርያት / ወሊድ፣ ሞትና ፍልሰት/ ነው። የእነዚህ ባህርያት ውጤት የህዝብ ብዛት፣ የህዝብ ቅንብር በዕድሜና በፆታ፣ እንዲሁም የህዝብ ስርጭት/ አሰፋፈር/ ሲሆኑ ፣ እነዚህ የዲሞግራፊ ውጤቶች በተለያየ መንገድ የልማት ሂደትን ማለትም መሠረታዊ የአገልግሎትና ምርት ፍላጐቶች / ምግብ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ውኃ፣ መጠለያ ወዘተ../፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንት፣ የሰው ኃይል አጠቃ ም፣ የመሬት፣ ካፒታልና ቴክኖሎጂ አጠ ቃቀ ም፣የአካባቢ ልማት እና የመንግሥት በጀት አጠቃም ላ ይ ተጽዕኖ ያደርሳሉ። ለምሳሌ የትምህርት ሽፋንን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የተማሪው ቁጥር በየአመቱ እየጨመረ መምጣት መንግሥት ለትምህርት የሚመድበውን በጀት እንዲጨመር ሊገደድ ይችላል። ምናልባትም ይህ ገንዘብ ለኢንቨስትመንት ቢውል የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ ጉልህ ሚና ሊጫወት ይችላል።

የዲሞግራፊ ውጤቶች የልማት ሂደት ላይ ተጽዕኖ በማድረግ የልማት ውጤ ቶች ላይ ማለትም የነፍስ ወከፍ የገቢ መጠን ፣ የስራ ዕድል፣ የትምህርት ተሳትፎ፣ የጤና ሽፋን፣ የአመጋገብ ደረጃ ( Nutritional Status ) ፣ እና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ተጽዕኖ ያደርሳሉ። እነዚህ የልማት ውጤቶች መልሰው የዲሞግራፊ ባህርያት ማለትም ወሊድ፣ሞትና ፍልሰት ላይ አሉታዊ ወይም አውንታዊ ተጽእኖ ያደርሳሉ። ለምሳሌ የጤና ሁኔታ መለኪያ የሆነውን የህፃናት ሞት መጠን እንውሰድ። ከሚወለዱ አንድ ሺህ ሕፃናት ውስጥ አንድ አመታቸውን ሳያከብሩ የሚ ሞቱት ሕፃናት ብዛት 110 ነው ። ለዚህ ችግር አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ምክንያቶች ብዙ ናቸው። የጤና አገልግሎት ማነስ እንደ አንዱ ብቸኛ ምክንያት ተቆጥሮ ሆስፒታልና ክሊኒክ መገንባት ችግሩን ሙሉ በሙሉ ይቀርፈዋል ብለን ልንደመድም እንችል ይሆናል። ግን ለችግሩ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉት ችግሮች መካከል ጥቂቱን ለመጥቀስ:-

• ወሊድ ( Fertility)

አራርቀው የማይወልዱ ና ብዙ ህፃን ያላቸው እናቶች የራሳቸውን እና የልጆቻቸውን ጤና ጥያቄ ውስጥ ይከቱታል። ይህ ሁኔታ ለህፃናት ሞት አንዱ ምክንያት እንደሆነ ብዙ ጥናቶች ዘግበዋል።

• ያልተመጣጠነ ምግብ

የእናቶችም ሆነ የህፃናት የአመጋገብ ሁኔታ በሚወለደው ልጅ ጤና ላይ ተጽእኖ በማሳደር የህመም ወይም የሞት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

• የአካባቢ ሁኔታ

የተበከለ አካባቢ ወይም የንፁህ ውኃ እጥረት ሌላው አንዱ ምክንያት ነው ።

• ትምህርት

በተለይ የእናቶች የትምህርት ደረጃ ዝቅተኛ ሲሆን ሌላው ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ይህ በአጠቃላይ የሚያመለክተው በህዝብና በልማት መካከል ከፍተኛ ትስስር እንዳለ እና የሚከሰቱትም የልማት ችግሮች የእነዚህ ትስስር ነፀብራቅ እንደሆኑ ነው። የእነዚህ ትስስር ውጤት የሆኑት የልማት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የሚተገበሩትም ተለዋዋጭ በሆነው በእዚሁ የህዝብና የልማት ትስስር ሁኔታ (environment) ውስጥ ስለሆነ፣ ከጥንስሳቸው ጀምሮ ፖሊሲዎች ወይም ፕሮግራሞች ይህንን ትስስር ትኩረት የሰጡ መሆን ይገባቸዋል።

ቻርት 1 በተጨማሪ የሚያመለክተው ዕውነታ፣ የስነ ህዝብ ፖሊሲ አንዱ የልማት ፖሊሲ እንደሆነ እና የሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች አፈፃፀምን ስኬታማ ለማድረግ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ እንደሆነ ነው። በመሰረቱ ማንኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተደጋጋፊነት አላቸው። ለምሳሌ የትምህርትና የጤና ፖሊሲ ለስነ ህዝብ ፖሊሲ ግብ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከዚህ ጋር መዛንጋት የሌለበት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የሚደጋገፉበት መንገድ እንዳለ ሁሉ የሚቃኑበትም ሁኔታና አጋጣሚዎች ስላሉ፣ ይህንን በአግባቡ ተከታትሎ በማስወገድ፣ የልማት ፖሊሲዎች የጋራ አላማ የሆነውን የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ከግብ ማድረስ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ነው።

ቻርት 1

በህዝብና ልማት መካከል ያለውን ትስስር የሚያሳይ ማዕቀፍ




ምንጭ ፡ Herrin ( 1987 )

## 3. የኢትዮጵያ ህዝብ ሁኔታ

የህዝብ ዕድገት ወይም ቅነሳ ማለት በአንድ ዓመት ውስጥ ከሚወለዱ ህፃናት ላይ የሚሞቱት ሰዎች ተቀንሶ፣ በሰደት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ተደምሮ እና በስደት ከሀገር የሚወጡት ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት ነው ፡፡ ከኢትዮ ጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትም ሆነ የሚወጡት ስደተኞች ቁጥር የሀገሪቱን የህዝብ ሁኔታ በመለወጥ ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ የሚገባ አልነበረም፡፡ በአብዛኛው ለሀገሪቱ ሕዝብ ዕድገት ለውጥ ምክንያቶች የነበሩት በፍጥነት እያደገ የመጣው የወሊድ ሁኔታ እና በአዝጋሚ ሁኔታ እየቀነሰ የመጣው የሞት መጠን ነው፡፡ ስለዚህ በሚወለዱ ህፃናትና በሚሞቱ ሰዎች መካከል ያለው ሚዛን ማለትም የተፈጥሮ ዕድገት ወይም በእንግሊዝኛ Natural Increase ለሀገሪቱ ህዝብ ዕድገት ዋናው ምክንያት ነበሩ፡

እ. ኤ.አ በ1999 የኢትዮ ጵያ ህዝብ ብዛት 63.5 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከአፍሪካ 8 ከመቶ፣ ከአለም አንድ ከመቶ ድርሻ አለው፡፡ የሀገሪቱ ህዝብ አመታዊ ዕድገት 2.92 በመቶ ወይም በ1.8 ሚሊዮን ሰዎች ነው፡፡

ለሀገሪቱ ፈጣን የህዝብ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረገው ዋናው ምክንያት ወሊድ ነው፡፡ አንድ ሴት በወሊድ ዘመኗ ( 15-49 ዓመት ) የምትወልደው አማካኝ የልጆች ብዛት 6.52 ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ 1.2 በጣሊያን ና በስፔን ሲሆን፣ ከፍተኛው 7.6 በየመን ነው፡፡ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የወሊድ መጠን አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ምክንያቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ የሴቶች የማህበራዊ ና የኢኮኖሚያዊ ዝቅተኛነት፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዝቅተኛነት፣ ባህላዊ እና ወዘተ ናቸው፡፡

የሞት ሁኔታ በኢትዮ ጵያ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮ ጵያ አጠቃላይ የሞት መጠን (CDR ) ከአንድ ሺህ ሰዎች 15 ሲሆን፣ ከሚወለዱ አንድ ሺህ ህፃናት፣ አንድ ዓመታቸውን ሳያከበሩ የሚሞቱት 110፣ 5 ዓመታቸውን ሳያከብሩ የሚሞቱት 161 ሲሆን አማካኝ ዕድሜ ለሴቶች 53 ዓመት፣ ለወንዶች ደግሞ 51 ዓመት እንደሆነ ተገምቷል፡፡

የህዝብ ሥርጭትን በተመለከተ አብዛኛው በገጠር የሚኖር ሲሆን፣ የከተማው ድርሻ 15 በመቶ ( 14 ሚሊዮን ህዝብ ) ብቻ ነው፡፡ ወደፊት በከተማ የሚኖረው ህዝብ እያደገ በመምጣት በ2030፣ 22 ከመቶ ድርሻ በመያዝ 30 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

## 4. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ኢኮኖሚ

### የሀገር ውስጥ ምርት

አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በ1991/92 እና 1977/98 መካከል በአማካኝ በአመት 5.8 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ሆኖም የነፍስ ወከፍ ምርት ያሳየው አመታዊ ዕድገት 2.8 በመቶ ነው። ይህ የሆነው በአማካኝ በአመት በ2.9 በመቶ ያደገው የኢትዮጵያ ህዝብ የተመዘገበውን የምርት እድገት ስለተሻማው ነው።

አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ና የነፍስ ወከፍ ምርት፣
1991/92 - 1977/98

| ዓ/ም | አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት( GDP) በሚሊዮን ብር | የነፍስ ወከፍ ድርሻ በብር | ሕዝብ በሚሊዮን |
|---|---|---|---|
| 1991/92 | 10471.56 | 215.00 | 48.8 |
| 1992/93 | 11724.42 | 234.00 | 50.2 |
| 1993/94 | 11910.33 | 231.00 | 51.6 |
| 1994/95 | 12644.30 | 238.00 | 53.1 |
| 1995/96 | 13990.30 | 256.00 | 54.6 |
| 1996/97 | 14767.80 | 262.00 | 56.4 |
| 1997/98 | 14834.50 | 255.00 | 58.1 |

ምንጭ፡ MEDAC, 1999 እና CSA (1999)

### ግብርና፣

የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት 50 በመቶ፣ ከጠቅላላ የውጭ ምንዛሪ 90 በመቶ ድርሻ ያለው እና 85 ከመቶ ለሚሆነው የሀገሪቱ ህዘብ የሥራ መስክ ነው። መሬት ዋናው መሠረታዊ የሀገሪቱ ሀብት ሲሆን፣ ለእርሻ ተስማሚ ነው ተብሎ ከሚገመተው 66 ከመቶ / 73.6 ሚሊዮን ሄክታር/ ውስጥ ለእርሻ የዋለው 16.5 ሚሊዮን ሄክታር / 22 ከመቶው/ ነው ።

ከሀገሪቱ ጠቅላላ መሬት 36 ከመቶ ድርሻ ያለው የደጋው ክፍል፣ 88 ከመቶ የሚያህለው ደሀገሪቱ ህዝብ የሚኖርበት ሲሆን፣ 70 በመቶው የሀገሪቱ የእንስሳት ሀብት እዚህ በደጋው ክፍል ይገኛል። በሰብል ከሚሸፈነው የሀገሪቱ መሬት ውስጥ 90 በመቶው በደጋው ክፍል ይገኛል። ሆኖም ሰውና እንስሳት ባደረሱት ጫና የሀገሪቱ የእርሻ መሬት እየተሸረሸረ መጥቶ ለምነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

መስኖ ለሀገሪቱ ግብርና ልማት ያለው ድርሻ ውስን ነው። ሀገሪቱ 3.7 ሚሊዮን ሄክታር የሚያለማ የውሀ ሀብት ቢኖራትም፣ በመስኖ የለማው 4.4 ከመቶ ብቻ ነው። መስኖ ለአመታዊ የምግብ ሰብል ምርት ያለው ድርሻ ከ3 ከመቶ ያልበለጠ መሆኑ የሚያሳየው ምርቱ በዝናብ ላይ ተወስኖ የቀረ እንደሆነ ነው። በእንሰሳት ሀብት ከፍተኛ ድርሻ የያዘች ሀገር ብትሆንም በመኖ እጥረትና በበሽታ ምክንያት የእንስሳቱ ምርታማነት በጣም ዝቅተኛ ነው።

ኢትዮጵያ ካላት ወንዞችና ሀይቆች በአመት ልታመረት ከምትችለው ዓሳ 15 ከመቶውን ብቻ ነው የምትጠቀመው። የማርና ሰም ምርት ደረጃም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ግብርና ለሀገሪቱ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚጫወተው ሚና የተጠበቀውን ያህል አይደለም። ለዚህ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ዋናዎቹ በህዝብ ዕድገት እየተባባሰ የመጣው የአካባቢ መሸርሸር፣ ድርቅ፣ ኋቀር የአመራረት ዘዴ፣ ደካማ መሰረተ ልማትና ተስማሚ የሆኑ ፖሊሲዎች አለመኖር ናቸው።

ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን አልቻለችም። በሀገር ውስጥ ምርትና የምግብ ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት በየአመቱ እየሰፋ የመጣ ሲሆን፣ ይህም ልዩነት ሲሞላ የነበረው በግዥ ወይም በእርዳታ ከውጭ በሚገባ እህል ነው። በእርዳታ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው የእህል መጠን ከሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ያለው ድርሻ በ1985፣ 2.3በመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ1996፣ 26 በመቶ ደርሷል። ይህ የሚያስከትለው ችግርም ለኢንቨስትመንት ሊውል የሚችለውን የውጭ ምንዛሪ መቆጣትና የውጭ ጥገኝነትን ማባባስ ናቸው።

## የሰብል ምርት

97 ከመቶ ያህሉ የሀገሪቱ የሰብል ምርት አነስተኛና የተበጣጠሰ የእርሻ መሬት ይዞታ ባላቸው የግል ገበሬዎች የሚመረት ነው። በእነዚህ ገበሬዎች ይዞታ ሥር ካለው መሬት የተመረተው የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬ ና የቅባት እህል ምርት ከ1991/92 እስከ 1977/98 በአማካኝ የ3.3 በመቶ አመታዊ ዕድገት በማሳየት ከ68 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 83 ሚሊዮን ኩንታል አድጓል። ሆኖም በዚሁ የስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የነፍስ ወከፍ ምርት ከ 1.5 ኩንታል የበለጠ አልነበረም። የዚህም ምክንያት የተመዘገበው የምርት ዕድገት ከሕዝብ ዕድገት ጋር የተጣጣመ ስላልነበር ነው። ከምግብ ፍላጎት አንፃር፣ የተመዘገበው 1.5

ኩንታል የነፍስ ወከፍ ምርት በ20 ከመቶ ያነሰ ነው። ይህንን አነስተኛና ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ የነፍስ ወከፍ ምርት እያደገ ለሚመጣው ህዝብ እንዳለ ለማቆየት ቢያንስ የሀገር ውስጥ ምርት በአመት በ3.0 ከመቶ / በ2.5 ሚሊዮን ኩንታል/ ማደግ አለበት። ለምሳሌ ከ30 አመታት በኋላ 129 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ለተገመተው ህዝብ 1.5 ኩንታል የነፍስ ወከፍ ምርትን እንዳለ ለማቆየት ከ180 ሚሊዮን ኩንታል ያላነሰ የሰብል ምርት መመረት ይኖርበታል። ማለትም በ1997/98 የተመዘገበው 83.5 ሚሊዮን ኩንታል ላይ የ97 ሚሊዮን ኩንታል የምርት ዕድገት መታየት አለበት ማለት ነው።

## የእርሻ መሬት

አማካኝ የአንድ ቤተሰብ የእርሻ መሬት ይዞታ ከግማሽ ሄክታር እንደማይበልጥ ይገመታል። የነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት ይዞታ ከ 0.1 ሄክታር በላይ እምብዛም ከፍ ብሎ አያውቅም። በዋና ዋና የምግብ ሰብሎች /ብርዕ፣አገዳ፣ጥራጥሬና የቅባት እህሎች/ የተሸፈነው መሬት ለበርካታ አመት ከ6 ሚሊዮን ሄክታር የበለጠ አልነበረም። ይህ ማለት የነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት እየቀነሰ እንጂ እየጨመረ አልመጣም ማለት ነው ። በመጠን መቀነስ ብቻ ሳይሆን በለምነትም እየቀነሰ መጥቷል።

በገጠር የሚኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት በአሁኑ ጊዘ 52 ሚሊዮን እንደሚደርስ ሲገመት ከ30 አመታት በኋላ 99 ሚሊዮን እንደሚሆን የጠቅላይ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ትንበያ ያመለክታል። አሁን ካለው ውስን የእርሻ መሬት ሁኔታ እያደገ የሚመጣው የገጠር ህዝብ ሊያጋጥመው የሚችለው የእርሻ መሬት እጥረት ቀላል አይሆንም።

በአሁኑ ጊዜ የምግብ ዋስትናው ያልተረጋገጠ ህዝብ ከ30 ሚሊዮን አያንስም። እያደገ ከሚመጣው ህዝብ አንፃር ይህንን ሁኔታ ለመቀየር በሁሉም መስክ በቅንጅት መረባረብን ይጠይቋል።

## ትምህርት

ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ና ፖለቲካዊ ሂደቶችን ለማፋጠን ትምህርት ቁልፍ መሳሪያ ነው። በተለይ የስነ ሕዝብ ፖሊሲ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ጉልህ ሚና ይጫወታል። ትምህርት በኢትዮጵያ ለማስፋፋት መንግሥት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም አጠቃላይ የትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በትምህርት ልማት መርሃ ግብር ( 1998 -2002 ) ላይ የተጣለው ግብ

የትምህርት ተሳትፎን አሁን ካለበት ደረጃ በ2000 ወደ 50 ከመቶ ለማሳደግ ነው::

የትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆን ብቻ ሳይሆን ጥራቱም እያሽቆለቆለ መጥቷል:: የሚወድቀውና የሚደግመው ከፍተኛ ግምት ያለው ስለሆነ ይህም በሀብት አጠቃቅ ም ላይ ብክነትን ያስከትላል:: የደጋሚዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆን የትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረትም ያኮስሰዋል::ደጋሚዎች ባይኖሩ ወደ አንደኛ ደረጃ የሚገቡ ተማሪዎችን ከ 15 እስከ 20 በመቶ ማሳደግ እንደሚቻል ጥናቶች ይጠቁማሉ::

ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎ / ከ1-6/ በ1993/94 ፣ 23 ከመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ1995/96፣ 34.6 ከመቶ እንደደረሰ ነው:: የሴቶች ድርሻ ከጠቅላላው ተሳትፎ 37 ከመቶ ነው::

የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎ እያደገ ቢመጣም፣ ከትምህርት ውጪ ያሉት የህፃናት ብዛት ከፍተኛ ነው:: በ1995/96 ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ውጪ የነበሩት ህፃናት 6 ሚሊዮን ይጠጋል:: ዕድሜአቸው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት የደረሱ ህፃናት / 7-12 ዓመት/ ወደፊት እያደገ በመምጣት በ2000፣ 9.8 ሚሊዮን፣ በ2030 ደግሞ 17 ሚሊዮን ይደርሳል::

በሀገሪቱ የትምህርት ስትራቴጅ የተነደፈው የትምህርት ተሳትፎ ማለትም በ2000፣ 50 ከመቶን ለመተግበር አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ ለ1.7 ሚሊዮን አዲስ ገቢዎች ቦታ መገኘት አለበት:: ይህም ሆኖ ከትምህርት ቤት ውጪ ሊሆኑ የሚችሉት ህፃናት ብዛት 5 ሚሊዮን ይጠጋል:: ለ1.7 ሚሊዮን አዲስ ገቢዎች የሚያስፈልገው ት/ቤት፣ አስተማሪዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች ወዘተ... ቀላል ሊሆን አይችልም:: መንግሥት የትምህርት ሴክተሩን ለማሳደግ እየመደበ ያለው በጀት ባለፉት አመታት ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል:: በ1990/91 እና 1995/96 መካከል ለትምህርት የተመደበው የካፒታል በጀት ከ43 ሚሊዮን ብር ወደ 442 ሚሊዮን ብር አድጓል:: ከአጠቃላይ የካፒታል በጀት የትምህርት ድርሻ በዚሁ ዓመታት ውስጥ ከ4 በመቶ ወደ 12.4 በመቶ አድጓል::

## ጤና

የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ግንባታ ሲነሳ የሰዉ ኃይል የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል:: በትምህርት የታነፀና ጤናማ ዜጋ የመፍጠር ጉዳይ በልማት ጥረት ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው::

አጠቃላይ የህዝቡ የጤና ደረጃ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል:: ለዚህ ችግር አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ምክንያቶች የምግብ እጥረት፣ተላላፊ በሽታዎች፣የአካባቢ ሁኔታ፣ንፁህ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ እና የጤና አገልግሎት በአግባቡ አለመጠቀም፣ዲሞግራፊያዊና ሌሎች ምክንያቶች ናቸው:: የእናቶች፣ የህፃናት ህመም እና ሞት በሀገራችን ከፍተኛ ነው:: በኢትዮጵያ ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚሞቱት እናቶች ከ 560 እስከ 850 ከሚወለዱ 1000, 000 ህፃናት ውስጥ ይደርሳል:: ዕድሜአቸው አንድ ዓመት ሣይደርስ የሚሞቱት 110 ከአንድ ሺህ ውልደት ውስጥ ሲሆን፣ 5 አመታቸውን ሳያከብሩ የሚሞቱት 161 ይገመታል:: በበለፀጉ ሀገሮች የተመዘገበው የህፃናትም ሆነ የእናቶች ሞት መጠን ከ10 በታች ነው:: በኢትዮጵያ በአመት ውስጥ ከሚከሰቱት አጠቃላይ ሞቶች 65 ከመቶው የሚከሰተው በእናቶች ና በህፃናት ላይ ነው ::

በወሊድ ዕድሜ ( 15-49) ላይ ያሉ ሴቶች ቁጥር በአሁኑ ጊዜ 12 ሚሊዮን ሲገመት ከ30 አመታት በኋላ ወደ 34 ሚሊዮን ያድጋል:: ከዕድሜ 0 እስከ 5 አመት ያሉትም ህፃናት ቁጥር አሁን ካለበተ 11 ሚሊዮን በ2030 ወደ 15 ሚሊዮን ያድጋል:: ከዚህ አንፃር ልንገነዘበው የምንችለው ምን ያህል በጤናው መስክ ሊኖር የሚችለው ጫና ቀላል እንዳልሆነ ነው ::

አጠቃላይ የጤና ሽፋን ለብዙ ዓመታት ከ 45 ከመቶ አልበለጠም:: ይህ ማለት ለጤና ተቋማት ግንባታና የጤና ባለሙያዎች ለማፍራት ጥረት አልተደረገም ማለት አይደለም:: ሆኖም የተደረገው ጥረት ከህዝብ ዕድገት ጋር ሊመጣጠን ስላልተቻለ ነው:: በ1995 አንድ ሆስፒታል ለ 584, 414 ይደርሳል:: ይህ ከአጠቃላይ የህዝብ ሁኔታ ነው እንጂ አብዛኛው የጤና ተቋማት በከተማ ውስጥ ይገኛሉ::

ለህዝቡ የጤና አገልግሎት ለማዳረስ መንግሥት የሚመድበው በጀት ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል። የጤናው መስክ ከአጠቃይ የሀገሪቱ በጀት የነበረው ድርሻ ከ 3.3 በመቶ ወደ 6.2 በመቶ በ1990/91 እና 1977/98 መካከል አድጓል። በ1990/91 ለጤና የተመደበው መደበኛ በጀት 128.4 ሚሊዮን ብር፣ የካፒታል በጀት 32.1 ሚሊዮን ብር ሲሆን በ1997/98 መደበኛ በጀት ወደ 397.8 ሚሊዮን ብር፣ ካፒታል በጀት ደግሞ 354.2 ሚሊዮን ብር ደርሷል። ሆኖም ወደፊት እያደገ ከሚመጣው ህዝብ በተለይ ከህፃናትና እናቶች ጤና አጠ ባበቅ አንፃር ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

## የአካባቢ ሁኔታ

ስነ ህዝብ፣ ልማትና አካባቢ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተላዋዋጭ የሆነ ዝምድና አላቸው። ህዝብ የልማትም ሆነ የአካባቢ ዋናው ማዕከል ሲሆን፣ አካባቢና ልማት ከህዝብ ጋር የተቆራኘ ግንኙነት አላቸው። ሰው የራሱን መሰረታዊ ፍላጐቶች ለማሟላት በሚያደርገው የልማት ሂደት ውስጥ የአካባቢውን ሚዛን አዛብቷል። አሁን በደረስንበት የዕድገት ደረጃ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለው ሚዛን ተዛብቶ ድርቅና በረሃማነት እየተስፋፋ ይገኛል። በተለይ የኢትዮጵያ የአካባቢ ሁኔታ ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ የሚገባው ከሁለት በኩል ነው። በአንድ በኩል ፈጣን የህዝብ ዕድገት በሌላው በኩል ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት መሸረሸር እየተባባሰ መምጣት ነው። ፈጣን የህዝብ ዕድገት ና የተፈጥሮ ሀብት መሸርሸር ድህነትን እያባባሱ የሚገኙ ሲሆን፣ ድህነትም መልሶ ፈጣን የህዝብ ዕድገትንና የአካባቢ መሸርሸርን (Eniviromental Degradtion) እያባባሰው ይገኛል። ድህነትን ለመቅረፍ በአካባቢ ልማትና በስነ ህዝብ ጉዳይ ላይ የሚደረገው ጥረት ጊዜ የማይሰጥ ነው፣ ሆኖም እርምጃው ሲዘገይ ወደፊት የሚጠይቀው ዋጋ ከፍተኛ እና ችግሩም የከፋ ደረጃ ላይ በመድረስ ሊወገድ የማይችል ሁኔታ ላይ ይደርሳል።

በኢትዮጵያ የደጋው ክፍል ከፍተኛ የአፈር መሸርሸር የተከሰተበት ነው። ፈጣን የህዝብ ዕድገት ያስከተለውን ተጨማሪ ከፍተኛ የምግብ ፍላጐት ለማሟላት፣ ለእርሻ ምቹ ያልሆኑ መሬቶች ታርሰው ለአፈር መሸርሸር እንዲጋለጡ ተደርጓል። ምናልባት ገበሬው ይህን ለምን ያደርጋል ብለን ብንጠይቅ በገጠር ህዝብና በከተማ ህዝብ መካከል ያለው የወሊድ ና የሞት ልዩነት በተዘዋዋሪ መልስ ሊሆን ይችላል። የጤና፣ የትምህርት፣ የስነ ተዋልዶ አገልግሎት፣ የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ የጤና ሽፋን፣ የገቢ መጠን፣ ወዘተ ፣ አብዛኛው የገጠር ህዝብ ባለበት እጅግ በጣም አነስተኛ ነው።

በኢትዮጵያ የእርሻ መሬት ከሚገባው በላይ ታርሷል፣ የግጦሽ መሬት ከሚገባው በላይ ተግጧል፣ ደን ከሚገባው በላይ ተጨፍጭፏል። ለዚህ አስተዋጽኦ ከአደረጉት ምክንያቶች አንዱ ፈጣን የህዝብ ዕድገት ነው። ይህንን እንደ ችግር ተቀብለን የሚመለከተን ሁሉ ምን ያህል ተንቀሳቅሰን እርምጃ እየወሰድን ነው? በየመድረኩ ስለችግሩ አሳሳቢነት የሚወራው፣ ችግሩን ለመቅረፍ ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር የማይገናኝ ነው። በዘገየን ቁጥር ለልጆቻችን የምናስረክበው፣ ሀብት ሳይሆን ሊገፉት የማይችሉት የችግር አለት ነው።

## 5. ማጠቃለያ

ስነ ህዝብ፣ ልማትና የአካባቢ ሁኔታ የተሳሰሩ ጉዳዮች ስለሆኑ፣ ማንኛውም የልማት ፖሊሲና ፕሮግራም ይህንን ትስስር ትርጉም ያለው ግንዛቤ በመስጠት ዘላቂ ልማትን ማስፈን፣ አንዱ የኢትዮጲያ መሠረታዊ የልማት ስልት መሆን ይገባዋል።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ፣ በየደረጃው ያሉትን የፖሊሲ፣ የዕቅድ አውጪዎችና አስፈፃሚዎችን እንዲሁም በአጠቃይ ህዝቡን በቅንጅት ሊያራምድ የሚችል አንድ ወጥ ሀገር አቀፍ መርሃ ግብር ነድፎ በአስቸኳይ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው።

## I. መግቢያ

መረጃ የሰው ልጅ የአእምሮ ወይም የተግባር ውጤት ሲሆን በተለያየ ክፍለ ኢኮኖሚ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማቀናጀትና ወደ አንድ ግብ ለማምጣት ዓይነተኛ መሣሪያችን ሆኖ ያገለግላል። መረጃ ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበትን በመቆጠብ የአንድን አገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተማማኝ ያደርጋል።

በጤናው ዘርፍ መረጃና ትምህርት ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት የጤና ጥበቃ ሚ/ር የሚያደረገውን እንቅስቃሴ ከዳር ለማድረስ የጎላ ጠቀሜታ አለው። የጤና መረጃና ትምህርት ህብረተሰቡ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የባህርይና የአካባቢ ለውጥ እንዲያመጣ በማድረግ ጤንነቱን እንዲጠብቅና በጤናማነት እንዲቀጥል ብሎም በተዘረጉለት የጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በአዲሱ የጤና ፖሊሲ ትኩረት ከሰጠባቸው ዘርፎች መካከል መረጃና ትምህርትን የሚያጠቃልለው IEC አንዱና ተቀዳሚው ነው። ዛሬ የIEC ስራን በተቀላጠፈ መልኩ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማዕከል በቦርድ ተዋቅሮ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማዕከል የጤና ትምህርቶችና መልዕክቶች በተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ቋንቋዎች ለህብረተሰቡ እንዲሰራጩ ለማድረግ እንደ ኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ሬዲዮ ፋና፣ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን፣ አዲስ ዘመን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲና ወጋገን ያሉትን የመገናኛ ብዙኃን በመጠቀም ላይ ይገኛል። እንዲሁም የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን በበራሪ ፅሁፍ፣ ቡክሌት፣ ሥዕላዊ መግለጫ፣ በኦዲዮና ቪዲዮ ካሴቶች፣ በፊልም መልክ እያዘጋጀ ለህብረተሰቡ ያሰራጫል።

ማዕከሉ እስከአሁን ድረስ እነዚህን የመገናኛ ብዙኃን በመጠቀም የጤና ግንዛቤ ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰርፅ በማድረግ በኩል ከፍተኛ የሥርጭት ሽፋን ማግኘት የቻለ ቢሆንም የጤና አጠባበቅ ትምህርት አድማስን የበለጠ ለማስፋትና ለማጥራት ገና ብዙ ይጠበቅበታል።

በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ መልዕክቶች ከፍተኛ ተአማኒነት ያላቸው፣ ለበርካታ ህብረተሰብ ጆሮ ሊደርሱ የሚችሉና አንዴ ከተሠራጩ በኋላ ወዲያውኑ ማስተካከያ ሊደረግላቸው የማይቻሉ በመሆናቸው ጥንቃቄ ያሻቸዋል።

ስለሆነም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያንፀባርቁ መረጃዎች በግልፅነትና ሃቀኝነት ላይ ተመስርተውእንዲሠራጩ ለማድረግና የሚሰጡትም የጤና ትምህርቶችና መልዕክቶች የታለመላቸውን የባህርይ ለውጥ ማስገኘት እንዲችሉ የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ፈር እንዲይዝ ማድረግ ተገቢ ነው። ለዚህም ዓላማ ተፈፃሚነት የጤና መረጃዎችና ትምህርቶችን ለማሠራጨት ውክልና የተሰጣቸው አካላት ያላቸውን ሃላፊነትና ተግባራት ለይቶ ለማስቀመጥ መረጃዎችና ትምህርቶች በአግባቡ የሚያሰራጩበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል።

በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ በጤና ፕሮግራም ዝግጅት የመገናኛ ብዙሃን ሚና ምን መሆን እንደሚገባው ለመጠቆም የተሞከረ ሲሆን፣ ስራው የማዕከሉ ብቻ ሳይሆን የጋራ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነውና በቀረበው ጽሁፍ ላይ የሁሉም አስተያየት ታክሎበት ሊዳብር እንደሚገባው እሙን ነው።

## II. የጤና አገልግሎት ሽፋን

የሀገራችን የጤና ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትም ሆነ በስርጭት ረገድ እየተባባሱ መሄዳቸው የታወቀ ነው።

- ወባ ከቆላማና ሞቃት አካባቢዎች አልፎ ደጋና ወይና ደጋማ አካባቢዎችም እየተከሠተና በርካታ ህዝብን እያጠቃ ነው
- በኤድስ ምክንያት ከሚረግፈው ህዝብ በተጨማሪ ያለተንከባካቢ የሚቀሩ አራጋውያን ያለአሳዳጊ የሚቀሩ ህፃናት ቁጥር በአስፈሪ መጠን እየጨመረ ነው
- በውሃና ቆሻሻ ወለድ ተላላፊ በሽታዎች ጤናው የሚቃወሰው ህዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም

ለዚህ ሁኔታም

- ድህነታችን
- የህዝባችን ቁጥር ከተጠበቀው በላይ በፍጥነት መጨመር
- የከተሞች መስፋፋትና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ያለመጠናከር
- ህብረተሰቡ ስለጤና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ ያለመዳበርና
- ከአለፉት ስርዕቶች በተሻለ መልኩ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ቁጥር የጨመረ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ከችግሩ ስፋት ጋር በተመጣጠነ መልኩ አገልግሎቱ ያለመጠናከሩ አጋዥ ሆነዋል።

የሀገራችንን የጤና አገልግሎት ደረጃ አመልካች ከሆኑት መካከል የተወሰኑትን እንኳን ብናይ

## Vital Statistics Ethiopia (1999/2000)

| | |
|---|---|
| • Infant mortality rate | 110/1000 |
| • Under 5 mortality rate | 161/1000 |
| • Maternal mortality rate | 560-850/100,000 |
| • Fertility rate | 6.5% |
| • Contraceptive prevalence (1999) | 11% |
| • Growth rate | 2.9% |
| • Health service coverage | 48.5% |

Source: Central Statistics Authority 1998

ሲሆን ይህም የሚያመለክተው የጤና አገልግሎት ደረጃችን በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው::

ይህንንም ሁኔታ በኢኮኖሚም ሆነ በመልክአ ምድር አቀማመጥ ከሚቀርቡት ሀገሮች ጋር ስናነጻጽረው የሚከተለውን ይመስላል::

## Comparative Indicators for East Africa 1998

| | | Eth. | Ken. | Tan. | Uga. |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. Life expectancy at birth | M | 49.7 | 57 | 49 | 43 |
| | F | 52.4 | 60 | 52 | 43 |
| 2. Infant mortality rate | | 110 | 57 | 86 | 99 |
| 3. Total fertility rate | | 6.5 | 4.6 | 5.6 | 6.7 |
| 4. Maternal M/R | | 560-850 | 650 | 530 | 550 |
| 5. Under 5 mortality rate | | 161 | 90 | 141 | 144 |
| 6. Prevalence of child malnutrition | | 48 | 23 | 26 | 29 |

Source: World Development Report 1998/99

- Central Statistics Authority 1999

ከዚህ አንፃር ስናየው የሀገራችን ሁኔታ ከቀረቡት ሃገሮች በባሰ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው።

ምንም እንኳን የሀገራችንን የጤና ችግሮች ለማቃለል ከሚካሄደው የማከም አገልግሎት ጎን ለጎን አስቀድሞ የመከላከልን እውቀትና ብልሀት በህብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም አሁንም የተፈለገውን ያህል ያልተሠራና ያመጣው ለውጥም ጠንካራ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል።

- የጤና ትምህርቱ ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመካሄዱ
- በምርምርና የህዝብን ዋነኛ የጤና ችግሮች መሠረት ባደረገ ጥናት ላይ ተመስርቶ የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ የሚካሄድ አለመሆኑ
- በመገናኛ ብዙሃንና በጤና ጥበቃ ሚ/ር የሚመለከታቸው ክፍሎች መካከል የጋራ የሆነ እቅድና መርሃ ግብር የሚሠራበት ሁኔታ ያለመመቻቸቱ ለሚታዩት ችግሮች መባባስ ወይም ፈጣን ለውጥ ላለመገኘቱ ምክንያት ሆኗል።

## III. የመገናኛ ብዙሃን ድርሻ

በተደጋጋሚ እንደተገለፀውና እንደሚታወቀውም መገናኛ ብዙሃን ህዝብን በመቀስቀስና በማስተማር የሚፈለገውን ለውጥ በማምጣቱ በኩል ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ለአንድ ሀገር እድገት መሠረት ለሆኑት

- ለምርት ተግባሮች መጎልበት
- ለህዝብ የአኗኗር ደረጃ መለወጥ

- ለኋላቀር አስተሳሰቦች መቀየር
- ስለጤና ግንዛቤ ለማስገኘት፣ ህዝብ የበሽታ መንስኤዎችንና መከላከያቸውን አውቆ ራሱን ለመጠበቅ መገናኛ ብዙሃን የጎላ አስተዋጽኦ አላቸው።

በተለይ

- ካለማወቅ የተነሳ በርካቶች እግዜር የሰጠኝን ያህል እወልዳለሁ በሚሉባት ሀገር
- በጎጂ ባህላዊ ልምዶችና ድርጊቶች የተነሳ በርካታ ሴት ህፃናት ለዕድሜ ልክ ስቃይ በሚደረጉባት
- በተላላፊ በሽታዎች ምክንያት በርካታ ህዝብ በሚረግፍባት
- በክትባት ያለመዳረስ ምክንያት በርካታ ህፃናት የዕድሜ ልክ አካለስንኩልነት በሚዳረጉባት
- በአጠቃላይ በአኗኗር ዘይቤ ረገድ ኋላቀርና አሳዛኝ ህይወት በሚገፋባት ሀገራችን መገናኛ ብዙሃን ከማዝናናቱና ከመቀስቀሱም በላይ ለማስተማሩ ቅድሚያ መስጠታቸው የግድ ነው።

ከዚህ በመነሳት መገናኛ ብዙሃን ይህን ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ምን ያህል ተንቀሳቅሰዋል? ምን ውጤትስ አምጥተዋል? የሚለው መታየት አለበት። በዚህ ረገድ ጥረቶችና ጀምሮች ቢታዩም ገና ብዙ በጣም ብዙ ይጠበቃል።

## IV. በጤና ትምህርት የመገናኛ ብዙሃን እንቅስቃሴ

በጥናት የተደገፈ መረጃ ባይኖርም የጤናና ጤናነክ ትምህርቶችንና መልዕክቶችን ለህብረተሰቡ ለማዳረስ በዕቅድ ካስቀመጡ የመገናኛ ብዙሃን መካከል የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

የመገናኛ ፕሮግራሞች ሽፋን በመገናኛ ብዙሃን

| የድርጅቱ ስም | የማተላለፍበት ቋንቋ | መጠን በወር | |
|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ ሬድዮ | | | |
| | አማርኛ | 4 ጊዜ | አርብ |
| | ትግርኛ | 4 ጊዜ | ማክሰኞ |
| | ኦሮምኛ | 4 ጊዜ | ሀሙስ |
| ሬዲዮ ፋና | | | |
| | አማርኛ | 4 ጊዜ | ረቡዕ አሙስ |
| | ኦሮምኛ | 4 ጊዜ | ሰኞ ረቡዕ |
| | አፋርኛ | 4 ጊዜ | ረቡዕ |
| | ሱማልኛ | 4 ጊዜ | ማክሰኞ |
| ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን | | | |
| | አማርኛ | 2 ጊዜ | ሐሙስ |
| | ኦሮምኛ | 2 ጊዜ | ረቡዕ |
| | ትግርኛ | 2 ጊዜ | ማክሰኞ |
| አብዮታዊ ዴሞክራሲ | | 4 ጊዜ | ሀሙስ (2 ኮለም) |
| አዲስ ዘመን | | 4 ጊዜ | ሀሙስ (2 ኮለም) |

እነዚህ በዕቅዱ ላይ የተመለከቱት ሲሆኑ በታቀደው መሠረት ሁሉም አይካሄዱም

ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን የህዝባችንን የጤና ችግሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይነካኩት እንጂ ተከታታይነት ባለው መልኩ የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ስልት የማቅረብ ድክመት አለባቸው።

የመገናኛ ብዙሃን ስለጤና አጠባበቅ ትምህርት በኢንፎርሜሽን መልክ መስጠት የመጀመሪያው ስራ (እርምጃ) ሆኖ ወሬውን ሰምተው ለሚመጡ ወይም መወሰን ላልቻሉ ሰዎች ተከታታይ የሆነ ትምህርት በመስጠት ትምህርቱን እንዲቀበሉት ወይም የተባለውን እንዲተገብሩት ማድረግ ያስፈልጋል።

እየተጀመረ የሚቋረጥ፣ ወይም ተከታታይነት የሚጎድለው ከሆነ ግን ተቀባይ የማግኘቱና የሚፈለገውን ውጤት የማምጣቱ ዕድል ጠባብ ይሆናል። ውጤት ላያመጣም ይችላል።

በመሆኑም የጤና ትምህርት ሲሰጥ የትኞቹን ለመለወጥና ለማግኘት እንደፈለግን መወሰን ያስፈልጋል።

ለዚህ ለመብቃት ደግሞ ትምህርቱን

- በተከታታይ
- በቀላል መንገድና
- በሚስብ አቀራረብ ማዘጋጀትን ይጠይቃል። ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ አመርቂ ላይሆን ይችላል።

የጤና ትምህርትን በተጠናከረ መልኩ ለማካሄድና የታሰበውን ግብ ለመምታት ደግሞ በጥናትና ምርምር ላይ በመመስረት ዋነኛ የህዝቡን ችግሮች በመለየትና ሁነኛ ተጠቃሚዎችን Target Audience መለየት ያስፈልጋል። ይህም ሲባል

የተመልካችን (አንባቢን/አድማጭን)

1. ፍላጎት
2. እድሜ
3. ፆታ
4. የትምህርት ደረጃ
5. ባህል
6. ሃይማኖትና የመሳሰሉትን መለየትና ማወቅ ተገቢ ነው።

የሚተላለፈው መረጃ ወይም ትምህርት

- ምን?
- እንዴት?
- ለማን?
- በምን? እንደምናስተላልፍ መምረጥ ለስራችን ውጤታማነት መሠረቶች ናቸው።

ይህ ብቻ አይደለም በሚተላለፈው የጤና መልዕክት ውስጥ አፍራሽ መልዕክት ያላቸው ሃሣቦች እንዳይተላለፉ መጠንቀቅም ያስፈልጋል።

## V. ማህበራዊ ግብይት

በአገራችን የማህበራዊ ግብይት ሥልትን በመከተል ጤናን ለማራመድ የተለያዩ ፕሮግራሞች ይሰራሚሉ። ከነዚህም ውስጥ ተጠቃሾቹ የኤድስ በሽታን ለመከላከል የኮንዶም ሽያጭን የማራመድና የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን የማስተዋወቅ ሥራዎች ናቸው።

በተለይም የኮንዶምን ሽያጭ ለማሳደግ የሚደረገው የማስተዋወቅ ተግባር የኤድስ በሽታ የመተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን በማሳወቅ በኤድስ ላይ ተከታታይ ሽፋን ለመስጠት እንደሚያግዝ ይታመናል።

ሆኖም ግን የማህበራዊ ግብይት ማስታወቂያዎችን በጥንቃቄ ካለመጠቀም የተነሳ ለመጥፎና አከራካሪ ዜናዎች ትኩረት መስጠትና ትክክለኛ ላልሆኑ፣ አሳሳችና ሚዛናዊነት ለጎደላቸው መረጃዎች መሠራጨት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከዚህም አልፎ ለጤና አጠባበቅ ትምህርት ዓላማ ግብ መምታትና ተግባራዊነት እንቅፋት መፍጠር አጠያያቂ አይሆንም።

ስለዚህ ማህበራዊ ግብይትን ለማሳደግ በመገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያዎች ከመቅረባቸው በፊት የመልዕክቶቹ ይዘት ከሚከተሉት ነጥቦች አንፃር መገምገምና መመርመር አለበት።

- መልዕክቱ የታለመለትን አድማጭ፣ ተመልካች ወይም አንባቢን መለየቱን፣
- የመልዕክቱ አስፈላጊነትና ትክክለኛነትን ፣
- ተግባራዊነቱንና ከህብረተሰቡ አቅም ጋር የተገናዘበ መሆኑን ፣
- ከጤና አጠባበቅ አኳያ ጉዳት የማያስከትል መሆኑ ፣
- በህብረተሰቡ ዘንድ ሊያመጣ የሚችለው የአስተሳሰብ ለውጥ ጤናማ መሆኑንና
- የመልዕክቱ ይዘት መስህብ ያለው፣ በማያሻማና ግልጽ በሆነ ቋንቋና አቀራረብ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

የሁላችንም አላማ ህዝብን ከጉዳት ለመጠበቅ በመሆኑ በጋራ ተነጋግሮ መስራት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ያግዛል። ይህን በማድረጉና ህዝብን ከጉዳት በመጠበቁ ላይ የመገናኛ ብዙሃንም ሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ታላቅ ሃላፊነት አለባቸው።

## VI. ከመገናኛ ብዙሃን ምን ይጠበቃል

*ሀ/ መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች*

1. ቋሚ የሆነ የአየር ጊዜ ወይም አምድ ለጤና ፕሮግራሞች መመደብ
2. በተመደበው የአየር ጊዜ ወይም አምድ ተከታታይ በሆነ መልኩ የጤና ትምህርቶች እንዲተላለፉ ማድረግ
3. በዜናና በሌሎች የንግድ ማስታወቂያዎች አማካይነት የሚተላለፉ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ህዝብን የሚያዘናጉና የሚያሳስቱ መልዕክቶችን መቆጣጠር። ቢቻል ከሚመለከተው አካል ጋር መነጋገር (ጤና ጥበቃ)
4. ከጤና ጥበቃ ጋር የጋራ የአሠራር ስልት በመቀየስ በቅንጅት መስረት

*ለ/ ጋዜጠኞች*

1. የአድማጭ (ተመልካች) አንባቢን ፍላጎት፣ የዕድሜ፣ የፆታና የዕውቀት ደረጃ ግምት ውስጥ ያስገባ በጥናት ላይ የተመሠረተ ስራ መስራት
2. በሚሠሯቸው ሥራዎች ውስጥ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲጋጥሙ የሚመለከተውን ክፍል ማነጋገር
3. ቢቻል ተከታታይነት ያለው አድማጭን ከመቀስቀስ አልፎ ሊያሳውቅ (ሊያስተምር) የሚችልና ወደ ተግባር የሚያደርስ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

*ሐ/ ከኪነጥበብ ባለሙያዎች*

1. በተለይ 80% በላይ ያልተማረና በገጠር የሚኖር ህዝብ ላላት ሀገራችን
   - ይህንን አታድርግ
   - ይህንን አድርግ በሚል የትዕዛዝ መልክ ባለው መልዕክት ሳይሆን ከህይወቱ ገጠመኝና ከችግሩ በመነሳት ፍላጎቱን በመሳብ በሚማርበት መልክ የፈጠራ ስራዎችን ማቅረብ

2. የሚቀርቡት የፈጠራ ስራዎች
   - ባህልን የማያንቋሽሽ
   - ሰውን በዘሩ፣ በሀብቱ፣ የማያበላልጡ
   - ወደ አልተፈለገ ሱስ ወይም ድርጊት የማይገፋፉ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል

## VII. ማጠቃለያ

የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት ማለት የህብርተሰቡን የባህሪ ለውጥ በማምጣት ከችግሩ ማላቀቅና ወደ ተሻሻለ የኑሮ ደረጃ ማሸጋገር ነው።

ህብረተሰብን ወደ ተሻሻለ ኑሮ በማሸጋገር ሂደት እንደ ጤና ጥበቃ ሚ/ር ሁሉ በርካታ ተቋማትም ኃላፊነት አለባቸው። ይህን ተግባራቸውን ለማሳካት ሁሉም የመገናኛ ብዙሃንን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀማሉ። ይሁንና ግቡ አንድ ሆኖ ሳለ አጠቃቀሙ በተናጠል መሆኑ የምንጠብቀውን ለውጥ ለማምጣት አላስቻለንም።

ምንም እንኳን በማስተማር የሚገኝ የባህሪ ለውጥን መለካት አስቸጋሪና ውጤቱም በአጭር ጊዜ የሚታይ ባለመሆኑ የማይደረስበት ሊመስል ይችላል። ይሁንና የምንጓዝበትን አቅጣጫና የምናልመውን ግብ አውቀን በጋራ ከተንቀሳቀስን ውጤታችን ያማረ ይሆናል።

# በእናቶችና ሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

በወ/ሮ ቦጋለች ዓለሙ
ከግብርና ሚኒስቴር

## መግቢያ

በአገራችን በተለይም በሴቶችና ሕፃናት አሉታዊ ተፅዕኖ በተለይም በጤና፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ሕይወታቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ እንዲሁም ለሴቶች ኋላቀርነት፣ ጎስቋላና የበታችነት ኑሮ የሚያበቁ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና አመለካከቶች በየብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ ይገኛሉ።

እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጊቶችን በማስወገድ ሴቶችና ወንዶች በአገሪቱ የልማት ሂደት እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ የሚሆኑበት ሥርዓት ለመዘርጋት የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል። ከእነዚህ እርምጃዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ሕጎች፣ ደንቦችና ፖሊሲዎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ለአብነት ያህል የፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የኢትዮጵያ ባህል ፖሊሲ፣ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ፣ የብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ እና የጤናና ማኅበራዊ ደህንነት ፖሊሲዎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ ለሴቶችና ሕፃናት ደህንነት መሠረታዊ እርምጃ መውሰድ እንደለበት አስቀምጠዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ በሴቶችና ሕፃናት ላይ ጉዳት የሚያመጡትን እንዲሁም ጎልተው የሚታዩትን ልማዳዊ ድርጊቶችና አመለካከቶች ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ በብሔራዊና በክልል ደረጃ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ይህ ኮሚቴ በአፍሪካ ደረጃ ከተቋቋመው የኢንተር አፍሪካ የጎጂ ባህል አስወጋጅ ጽ/ቤት 26 የአፍሪካ አገሮች አባል የሆኑበት አህጉራዊ ኮሚቴ አባል በመሆንና ልምድን በመቅሰም ጠቃሚ ባህሎችን እንዲጠበቁና እንዲጎለብቱ በማድረግ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ለማድረግ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

የልማዳዊ አመለካከትና ድርጊት መሠረቱ የግንዛቤ፣ የትምህርትና እንዲሁም መረጃ አለማግኘት በመሆኑ ጎጂ ልማዳዊ አመለካከቶችን ለመከላከል ኅብረተሰቡን ማስተማርና በጠቃሚና ጎጂ ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጊቶች ላይ ያተኮረ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህን ትምህርትና መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችን ለምሳሌ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸውን የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች (Media Personnel) በትምህርት ቤት ተማሪዎችና

መምህራን የተደራጁ የሴቶች ማህበራትን ወዘተ ለመድረስ የተለያዩ የማስተማሪያ መድረኮችን (Channel) በስብሰባ ፊልም በበራሪ ጽሑፍ በፖስተሮች በውይይት በጋዜጣ ወዘተ መረጃን ሕብረተሰቡ በማድረስ የሕብረተሰቡ ግንዛቤ ማዳበርና አመለካከት ለመለወጥ ጥረት ተደርጓል።

በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የሚገኙትንና በሴቶችና ሕጻናት ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን እንዲሁም ጠቃሚ የሆኑና ሊጠበቁ የሚገባቸውን ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጊቶችን ለይቶ በማወቅ ሕብረተሰቡ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ መረጃን እንዲያገኝ ለማድረግ በየደረጃው ጥናቶችን ሲያካሂድ ቆይቷል።

## ጠቃሚና ጎጂ ባሕላዊ ድርጊቶች በኢትዮጵያ

ባህል በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሲሆን ቋንቋውን፤ አለባበሱን፤ አመጋገቡን፤ የሥራ ልምዱንና የማህበራዊ ህይወቱን የሚያንጸባርቁና ከሌሎች ተለይቶ እንዲታወቅ ያደርገው መታወቂያው ነው። በመሆኑም የነበረውን ሥርዓትና ልምድ ጉዳትና ጥቅሙ ሣይመረመር እንዳለ በመበቀበል ተግባራዊ ሲሆን በመቆየቱ በጤናውም ሆነ በማህበራዊ ህይወቱ በባህል ተጽዕኖ የሚደርሰውን ችግር ለማስወገድ ሣይቻል ቆይቷል። ሆኖም የጤናና የማህበራዊ ችግሩ ከዓመት ወደ ዓመት እየተወሳሰበና በህይወት ላይ ችግር እያስከተለ በመምጣቱ መሻሻል እንዳለበት በብዙዎች የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እየታመነ መጥቷል።

ባህል የተለያየ ገጽታ ቢኖረውም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንደሚከተለውበ ሁለት ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል።

### ጠቃሚ ባህሎች

ሕብረተሰቡ ሊያቆያቸውና ሊጠብቃቸው የሚገቡ ጠቃሚ አመለካከቶችና ድርጊቶች በየብሔረሰቡ ዘንድ ይገኛሉ። እነዚህ በሴቶችና ሕጻናት ጤንነት የሚጠቅሙና ማህበራዊ ኑሮን ለማጎልበት የምንጠቀምባቸውን ባህሎች ማበረታታትና ማጠናከር ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብዙ

ጠቃሚ ባህሎች በየብሔር ብሔረሰቡ መኖራቸው ቢታወቅም ዋና ዋናዎቹ ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝርዋል።

ሀ. ጡት ማጥባት፤

ለ. ለወላድ እንክብካቤ ማድረግ፤

ሐ. የተጣላን ማስታረቅ፤

መ. ሀብትን በጋራ መጠቀም፤

ሠ. ዕድርና ዕቁብ በማቋቋም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መፍታት፤

ረ. ሌሎች

## ጎጂ ባህላዊ ልምዶች

በኢትዮጵያ ውስጥ ልናዳብራቸው የማገቡ ጠቃሚ ባህሎች የመኖራቸውን ያህል የጤና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠንቅ የሆኑና ለሕብረተሰቡ እድገት እንቅፋት የሆኑ የተለያዩ ጎጂ ባህሎች ይገኛሉ። በአገራችን ውስጥ እንደየብሔረሰቡና ቋንቋው የተለያዩና ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ጎጂ ባህሎች የሚገኙ ሲሆን የሴት ልጅ ግርዛት፤ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፤ ጠለፋ፤ ለሕክምና ይረዳል በማለት ሰውነትን በስለታማ ነገር መቁረጥ፤ የተመጣጠነ ምግብ ለሕጻናትና እናቶች መከልከል፤ መጠኑ ያልተጠበቀ የባህል መድሀኒት መውሰድ በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሥራ ጫና መብዛት የመሳሰሉት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ጎጂ ባህሎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ማንኛውንም የእድሜ ክልልና ጾታ የሚዳስስ ሲሆን ከዚህ በመቀጠል በተለይ በእናቶችና በሕጻናት በአጠቃላይ ደግሞ ሕብረተሰቡን የሚያጠቁትን በሶስት በመክፈል ለማቅረብ ተሞክሯል።

### በእናቶች ላይ የሚደርሱ ጎጂ ልምዶች

- የሴት ልጅ ግርዛት፤
- ያለዕድሜ ጋብቻ/
- የእርጉዝ ሴትን ሆድ በቅቤ ማሸት፤
- እንግዴ ልጅ እንዲወርድ በምጥ ላይ ያለች እናትን መነቅነቅ፤

- እንግዴ ልጅ እንዲወርድ በወስፌ ቅቤ እያስነኩ የእናቲቱን ጉሮሮ መውጋት፤
- ነፍስ ጡሮችን በተደጋጋሚ ኮሶ ማጠጣት፤
- ራስ በራስ መውለድ፤
- ሴት ሙሽራን ጥፍሯን መንቀልና በፈላ ቅቤ መንከር፤
- ምጥ ሲቆይ ፍየል አርዶ ፈርሱን ማጠጣት፤
- በሴቶች ላይ የሥራ ጫና መብዛትና ፍትሃዊ የሥራ ክፍፍል አለመኖር፤
- በሃብት ላይ የመወሰንና አጠቃቀም በወንዶችና በሴቶች መሃከል እኩል መብት አለመኖር
- ሴቶችን ከወንዶች ዝቅ አድርጎ መመልከት፤
- የአመጋገብ ልዩነት፤
- አስገድዶ መድፈር
- ሌሎች፤

<u>በሕጻናት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ጎጂ ልምዶች</u>

- እትብትን ንጽህናው ባልተጠበቀ መሣሪያ መቁረጥና እበትና አመድ መቀባት፤
- እንጥል መቁረጥ፤
- ጉሮሮ ማስቧጠጥ፤
- የሴት ልጅ ግርዛት፤
- ግግ ማስፈልፈል፤
- ጣጣቴ መተኮስ፤
- ያልተመጣጠነ ምግብ መስጠት
- ለጎሳ መለያና ለውበት ሲባል ሰውነትን መተልተል፤
- የፊት ጥርስን መንቀስ/መንቀል፤
- ለወንድ ልጅ ማድላት
- አስገድዶ መድፈር፤

*በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ጉዳት የሚያደርሱ*

- ለጎሣ መለያና ውበት ሲባል በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ቆዳን መተልተል፤
- ቆዳን ቆርጦ ደም ማፍሰስ፤
- መጠኑ ያልተጠበቀ የባህል መድሀኒት መውሰድ፤
- ጣጣቴ መተኮስ
- ንቅሣት፤
- ቀግምት
- ጠለፋ
- ያለዕድሜ ጋብቻ፤
- ለማሳደግ ከሚቻለው በላይ ብዙ ልጆችን መውለድ ፤
- ሌሎች

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሴቶችና በሕጻናት ስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በየብሔር ብሔረሰቦች መሀከል የተለያዩ ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጊቶች ይታያሉ። ከእነዚህም መሀከል ያለዕድሜ ጋብቻ ፤ ጠለፋ፤ አስገድዶ መድፈር፤ ብዙ ልጆችን የመውለድ ፍላጎት፤ በወንድና በሴት ልጅ መሃከል ማበላለጥና ወንድን ልጅ ለመውለድ መጓጓት፤ ግርዛት፤ መቼና ምን ያህል ልጆችን ለመውለድ ወንዶችና ሴቶች እኩል ለመወሰን አለመቻል (Reproductive Right) ልጅን በመንከባከብና በማሳደግ ሂደት እናቶችና የአባቶች የሥራ ድርሻ አለመመጣጠን ለሴት ልጅ ትምህርት ድጋፍና ትኩረት አለመስጠት ጥቂቱ ናቸው። በመሆኑም እላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ ልማዳዊ ድርጊቶች መሀከል በስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ከፍተኛ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉትን የሚከተሉትን ልማዳዊ ድርጊቶች እንመልከት፤

*የሴት ልጅ ግርዛት*

የሴት ልጅ ግርዛት የተጀመረበት ጊዜና ቦታ በትክክል አይታወቅም። አንዳንድ የአፈ ታሪክ ተናጋሪዎች በግብጽ አገር በፈርኦን ዘመነ መንግስት ተጀመረ ይላሉ። በብዙ ቦታ የሴትን ልጅ ግርዛት ከሀይማኖት ጋር ለማያያዝ

ይሞክራል። ሆኖም ከሀይማኖት ጋር ላለመያያዙ የሚከተሉት በማስረጃነት መቅረብ ይችላሉ።

- በሁሉም የእስልምና ተከታይ አገሮች አይካሄድም። ለምሳሌ በኢራን፤ በኢራቅ የሴት ልጅ ግርዛት አይካሄድም።

- በሁሉም ክርስትና ተከታይ አገሮች አይካሄድም፤

- መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርዓን ሴት ልጅ እንድትገረዝ አያዝም፤

## የሴት ልጅ ግርዛት ሥርጭቱ

የሴት ልጅ ግርዛት በአብዞኛው የአፍሪካ አገሮች፤ በየመን፤ እንዲሁም የእስልምና ሀይማኖት በሚከተሉት የኢንዶኔዥያና ማሊዥያ በመሳሰሉ አገሮች ይካሄዳል። በአውሮፓና በአሜሪካ ውስጥ ከአፍሪካ በስደት መልክ በሄዱ ቤተሰቦችም ይካሄዳል።

በዓለም ዘንድ ከ80 ሚሊዮን የሚበልጡ ሕጻናትና ሴቶች ለግርዛት የተጋለጡ ሲሆኑ በአብዛኛው የሚገኙት በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ በብዙ አገሮች የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰቦች የሴት ልጅ ግርዛትን የሚፈጽሙ ሲሆን ጥቂት ብሔረሰቦች ይህን ግርዛት አያካሄዱም። ኢኖ ጎሣ በኬንያ ዶርዜ በኢትዮጵያ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። በብዙ አፍሪካ አገሮች በአብዛኛው የሚካሄደው የግርዛት ዓይነት ኤክቴንሽን ይባላል።

## የሴት ልጅ ግርዛት የሚካሄደቡት ምክንያት

- ሕጓን ትጠብቃለች፤
- ወላድ ለመሆን፤
- ባል ለማግኘት፤

- የወሲብ ስሜት ለመቀነስ ወይም እንዳትባልግ፤
- ንጽህና ለመጠበቅ፤
- ሀይማኖት ስለሚያዝ
- በአንዳንዳንድ ጎሣ ግዳጅ
- ዕቃ ትሰብራሪለች በማበለት
- ጤናን ለመጠበቅ
- ኃይለኛ እንዳትሆን
- የሀይማኖት ትዕዛዝ ነው በማለት
- ሌሎች

ሀ. <u>የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች</u>

- ሱና
- ክሊተሪዶክቶሚ
- ኢክሲዥን
- ኢንፊቡሌሽን

ለ. <u>የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለው ችግር</u>

ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች የተሳሳቱ መሆናቸውና ምንም ሳይንሳዊ መነሻ እንደሌላቸው በየአገሩ የተካሄዱ የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ። የሴት ልጅ ግርዛት እጅግ ዘግናኝና ለጎዳት የሚያደርስ መሆኑን እንደሚከተለው እንመልከት፤

የሴት ልጅ ግርዛት በጤና ላይ የሚያስከትለውን ችግሮች በሁለት በመለየት ወዲያው የሚታይና ዘግይቶ የሚመጣ ችግር ተብሎ ሊከፈል ይችላል።

1. <u>ወዲያውኑ የሚታዩ ችግሮች</u>
   - የደም መፍሰስ
   - ራስ መሳት

- መንጋጋ ቆልፍ
- የደም መመረዝ
- ሽንት ለመሽናት መቸገር
- ሞት

2. <u>ዘግይተው የሚመጡ ችግሮች</u>
   - የወር አበባ በደንብ አለመፍሰስና ከፍተኛ ህመም መኖር፤
   - መካንነት፤
   - የጠባሳ መፈጠር
   - በጠባሳ መፈጠር በተለይ በወሊድ ጊዜ ብልቱ የመለጠጥ ባህርይ ስለማይኖረው ሊቀደድ በመቻሉ ሽንትና ሰገራ በተገቢው መንገድ ባለመምጣቱ የፌስቱላ ችግር መከሰት፤
   - የመሽናት ችግር በዚህ የተነሳ የሽንት መጠራቀም የኩላሊት ጠጠር መፈጠር፤
   - የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት መሰቃየትና ደም መፍሰስ፤
   - የምጥ መራዘምና የሕጻኑ መሞት፤
   - ለአስከፊ የHIV/AID በሽታና መሞት መጋለጥ፤

## <u>ያለእድሜ ጋብቻ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በገጠር አካባቢ የሚፈጸሙ ጋብቻዎች እንደየብሔረሰቡ ይለያያሉ። በአንዳንድ አካባቢ ወንዱ ሴቷን በማስገደድ በጠለፋ መልክ ሲያገባ ይታያል። በሌላ ቦታ አንዲት ሴት በምታገባበት ወቅት ክብረ ንጽህናዋን /ሕጓን/ ጠብቃ መገኘት ይኖርባታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች በጋብቻ ወቅት ክብረንጽህናዋ ካልኖረ ባል የመግረፍና ለቤተሰቦቿ የመመለስ መብት ይኖረዋል።

በጋብቻ መልክ በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚፈጸሙት በደሎች በጣም የተለያየ መልክ ያላቸውና ብዙ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ በተለይ በአማራ በትግራይና

በቤንሻንጉል ጉምዝ አካባቢ በስፋት የሚካሄደው ያለ እድሜ ጋብቻ ነው። በአንዳንድ ቦታ የሚዳሩት ከ7 እስከ 8 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን እስከ 12 ዓመት ድረስ የግብረስጋ ግንኙነት ሣያደርጉ ይቆያሉ። በአንዳንድ ቦታ ጋብቻው የሚፈጸምበት ጊዜ ሴት ልጅ ከ11-13 ዓመት ዕድሜ ስትደርስ ይሆናል።

ያለ ዕድሜ ጋብቻ በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚካሄድ በኢትዮጵያ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ በተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች ተለይቷል። ከእነዚህም ውስጥ፤

- ወላጆች ከማርጀታቸውና ከመሞታቸው በፊት ልጆቻቸውን ድረው ራሳቸውን ለማስቻል፤
- ከሃብታም ቤተሰብ ጋር በመጋባት የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል፤
- በቤተሰቦች መሃከል ዝምድናና ትስስርን ለማጠንከር፤
- የሴቷን ክብረ ንጽህናን ለማስጠበቅ፤
- በተለይም ሴቷ ልጅ በወቅቱ በመዳር ቆሞ ቀር እንዳትሆን

የተጠቀሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

ያለ ዕድሜ ጋብቻ በኢኮኖሚ በስነ ልቦና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያስከትለው የተለያዩ ችግሮች ሲኖሩት በተለይ በእርግዝናና በወሊድ ወቅት በጤና ላይ የሚያስከትለው ችግር በቀላሉ ሊታይ የማይቻልና የማይታለፍ ነው። በፊስቱላ ሆስፒታል ለሕክምና ከሚመጡ እህቶቻችን መሀከል በብዛት ችግር የደረሰባቸው ያለ እድሜ ጋብቻ በተፈጸመባቸውላይ ነው። የ12 ዓመት ሕጻን ማህጸን በእርግዝና ወቅት ችሎ መሸከም ካለመቻሉም ሌላ በወሊድ ወቅት ሊከሰት የሚችለውም ሌላ ችግር መገመት አያዳግትም። ስለዚህ ከምንዋጋቸው ዋነኛ ጎጂ ባህሎች አንዱ ያለ እድሜ ጋብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ያለ ዕድሜ ጋብቻ ሴት ልጅ በትምህርት እንዳታድግና ራሷን እንዳትችል ያደርጋል። ከትምህርት ቤት ታቋርጣለች ወይም የሴት መሃይማንን ቁጥር እንዲጨምር ያደርጋል።

* ሴቷን ለኢኮኖሚ ጥገኝነትና የስነ ልቡና ጫና ያበቃል፤
* የቤተሰብን ኃላፊነት መሸከም በማትችልበት ዕድሜ ትዳር በመያዝ ለስነ ልቦና ጭንቀት ይዳርጓታል
* መውለድን በልጅነት ስለምትጀምር ብዙ ልጆችን እንድትወልድና ከመውለድ ጋር ለተያያዙ ችግሮች /እንደ ፌስቱላ/ እንድትጋለጥ ያደርጋታል፤

<u>ጠለፋ</u>

ጠለፋ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የሚታዩ ቢሆንም በስፋት የሚከሄደው በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት እንደሆነ በጥናት የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

* ጠለፋ የሚፈጸምበት ምክንያት

* ልጅቷ ወይም ቤተሰቧ ለጋብቻ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀር፤

* የሠርግ ወጪን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ፤

* የጥሎሽ ዋጋን ወይም የጋብቻ ወጪን ለመሸፈን አቅም ሲያንስ፤

* ልጅቷ ብዙ ፈላጊ ካላት ሌላው ሳይቀድም እኔ ልቅደም በማለት፤

* ሀብታም ወላጆች ልጆቹ እንዳይገቡ ሲፈልጉ፤

## ጠለፋ የሚያስከትለው ችግር

- በተለይ ልጅቷ ፈቃደኛ ካልሆነች በጠለፋ ሂደት ብዙ መንገላታት ይደርስባታል።

- በጠለፋ ምክንያት የቤተሰቦችና የጎሣ ግጭት ሊያስከትል ይችላል፤

- ፈቃደኝነት ከሌለው ደስተኛ ያልሆነ ቤተሰብ እንዲፈጠር ወይም ፍችን የሚያስከትል ይሆናል፤

## ሌሎች ጎጂ ባህሎች ባህላዊ ልምዶች

በሕክምናና ውበት ለማሳመር ሲባል ሰውነትን በስለታማ ነገር መተልተል ትኩረት ለስጥባቸው የሚሹ ጎጂ ባህላዊ ልምዶች ናቸው። በእነዚህ ውስጥ እንጥል ማስቆረጥ፤ ጎሮሮ ማስቧጠጥ፤ ግግ ማስፈልፈል፤ ለጎሣ ምልክት በማለት ሰውነትን መተልተል ንቅሣት/ ሰውነትን መብጣት እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ሰውነትን ከመቁረጥ ጋር የተገናኙ ጎጂ ባህሎች ብዙ ደም በመፍሰስ፤ የሚቆረጥበት መሣሪያ የዛገ ከሆነ ለቴታነስ መጋለጥ፤ ባሻገር ለአስከፊው የHIV/AID በመጋለጥ የሞት አደጋ ይደርሳል። አንዱ የተቆረጠበት ሌላው ከተደገመበት የተለያዩ በሽታዎች በሕጻናትና በሴቶች ላይ የሥራ ጫናን ማብዛት ለእናቶችና ሕጻናት ጠቃሚ የሆኑ ምግቦችን መከልከል የመሳሰሉት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሊወገዱ ይገባል።

## ጠቃሚውን ለማዳበርና ጎጂ ባህሎችን ለማስወገድ መወሰድ ያለበት እርምጃ

የኢትዮጵያ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ብሔራዊ ኮሚቴ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ አውደ ጥናቶችን፤ የአሰልጣኞች ስልጠና የሚካሄድ ሲሆን የትምህርቱን ቅስቀሳ በሰፊው ለማዳረስ በሁሉም ክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቋቁሟል።

ብሔራዊ ኮሚቴው ትምህርቱን በበለጠ ለሕብረተሰቡ ለማድረስ በክልል ቅርንጫፍ ኮሚቴዎች በኩል በሕብረተሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸውን ግለሰቦችና የተለያዩ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ እንዲቻል ጥናት በተከታታይ በትምህርትና ቅስቀሳ ፕሮግራም መከናወን ይኖርበታል።

ሀ. <u>መደራጀት ፤</u>
በየደረጃው የሚገኙ የተለያዩ መንግሥታዊና መነግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚወክሉ ባለሙያዎችና ከህብርተሰቡ የተውጣጡ አካላትን በየሕብረተሰቡ ጎልተው ስለማገኙ ባህላዊ ልምዶች በተመለከተ ስለሚያስወግዱበት ዘዴ በመወያየት ዕቅድና ስልትን በመንደፍ መንቀሳቀስ።

ለ. <u>ጎጂና ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶችን መለየት</u>
እያንዳንዱ የሕብረተሰብ አካል በሥሩ የሚገኙትን ጠቃሚና ጎጂ ባህሎች በጥናት ለይቶ ማውጣት ያስፈልገዋል።

ሐ. <u>ማስተማር</u>
ሕብረተሰቡን ማስተማር ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል። ሕብረተሰቡን በሚያስተምሩበት ወቅት፤

* እራሳቸው ተለውጠው ጎጂ ድርጊቶች በመተው አርአያ መሆን ይኖርባቸል።

* ለዘመናት የቆየን ልማድና ባህል ለማላቀቅ ጊዜ ስለሚጠይቅ በአንድ ጊዜ ትምህርት ብቻ ሕብረተሰብን መለወጥ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ተስፋ ባለመቁረጥ ደጋግመው ማስተማር ይገባቸዋል።

* የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት፤ ብዙ ጥረትና ቀንጅታዊ እንቅስቃሴን እንደሚጠይቅ መረዳ፤

* ፍላጎትና ሙሉ ፈቃደኝነት እንዲኖር ያስፈልጋል፤

* የትምህርቱ ሃገደት ሕብረተሰቡን በሚገባ እንዲሳተፍ ማድረግ፤

* ለትምህርቱ ላይ በቂ ዝግጅት በማድረግ፤ የተለያዩ የማስተማሪያ መድረኮችን መጠቀም ያስፈልጋል።

* የትምህርቱን ውጤት በማገባ መከታተልና በየጊዜው ወቅታዊ መረጃዎችን በማግኘት ውጤቱን ማየትና መከታተል፤

መ <u>ፖሊሲ፤</u>

በመንግሥት የወጡትን የሴቶች የሥነ ሕዝብ ማህበራዊ ጉዳይና ሌለች ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ትኩረት የሰጡ ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተገቢው ድጋፍ መስጠትና ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

ሠ. *ገራዦችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ፈጻሚዎችን መመዝገብና በሌላ የሥራ መስክ እንዲተዳደሩ በማስተማርና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት፤*

ሴቶች ልጅ ግርዛትም ላይ ሆነ በሌሎች ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ለይቶ መመዝገብ። ከሌላው በተለይ ሁኔታ በተደጋጋሚ የሚሠሩት ሥራ ለሕብረተሰቡ ጤና አደገኛ መሆኑን በማስረዳት ሥራውን እንዲተው ማድረግ። የገቢ ምንጫቸው እንዳይቋረጥ ሌላ ሥራ ሠርተው እንዲኖሩ ማደራጀት ተገቢ ይሆናል።

ረ *የሕብረተሰቡ ተደማጭ ክፍሎች*

የሀይማኖት መሪዎች፤ የአገር ሽማግሌዎች፤ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፤ መምህራን፤ የግብርና ሠራተኞች፤ የጤና ባለሙያዎች፤ የልምድ አዋላጆችና ሌሎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ትምህርቱን እንዲያስተላልፉ ሀላፊነትና አደራ መስጠት፤

ሸ *መገናኛ ብዙሀን*

በአገሪቱም ውስጥ ሆነ በየክልሉ የሚገኙትን መገናኛ ብዙሀን እንደ ቴሌቪዥን ሬዲዮ ጋዜጣ የመሳሰሉትን ሕዝብ በሚረዳው ቋንቋ እንዲያስተላልፉ ትብብር መጠየቅ። የትምህርት ማሠራጫ ጣቢያዎች ብዙ ተማሪዎች ከመዳሰሳቸውም ባሻገር ሌላው የሕብረተሰቡ ክፍልም ስለሚያዳምጥ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ስለ ጎጂ ባህል ትምህርት መስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በመሆኑም የብዙሃን መገናኛ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች ስለጎጂ ባህል ግንዛቤአቸው ዳብሮና አመለካከታቸው ተለውጦ ሕብረተሰቡን ሊያስተምሩ ይገባል።

ቀ *የስብሰባ ቦታዎችና ባህላዊ የመገናኛ መድረኮች*

በባሕላዊ የመገናኛ መድረኮችና እንደ ስብሰባዎች እድር፤ እቁብ፤ ክለብ የመሣሠሉትን በመጠለቀም ጊዜ ወስዶ ስለ ጎጂ ባህል ትምህርት ለመስጠት ብዙ ሰዎችን ማግኘት ይቻላል።

በ *ክትትል*

ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች በሕብረተሰቡ እየተወገዱ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ ክትትል ማድረግ ይጠቅማል።ከተማሪው ውስጥ መጠነኛ የሆነ የህብረተሰቡ ክፍል እንኳን ከተለወጠ ማበረታታት ያስፈልጋል። የተለወጡትም በምሳሌነት ሌሎችን እንዲያስተምሩ በማስረዳት አርአያ እንደሆኑ እውቅናና ድጋፍ መስጠት።

ተ *ቅንጅት*

የጎጂ ባህል ማስወገድ ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀረፍ እንዲቻል ተከታታይነት እንዲኖርው በሕብረተሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸው ክፍሎች በማስተማር ከራሳቸው የዕለት ዕለት ሥራ ጋር አቀናጅተው እንዲያሠሩት ይጠበቃል። መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት ትንሽ ደቂቃ ወስዶ ለተማሪዎቹ እንዲያስረዳ፤ ጤና ባለሙያው ለህሙማን፤ የሀይማኖት መሪዎች ለምዕመናን እንዲያስተምሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሕብረተሰቡ ጋር በቅንጅት በመሥራት እንዲሁም የብዙሃን መገናኛ ባለሙያዎች በየመድረኮቻቸው ስለጎጂ ባህል በማካተት በአጭር ጊዜ የአመለካከትና የግንዛቤ ለውጥ ለማምጣት ይረዳል።

ቸ *የማስተማሪያ መርጃ መሣሪዎች*

የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በራሪ ጽሁፍ፤ ፊልም ፤ ድራማ፤ በመሳሰሉት በየብሔረሰቦች ባህልና ቋንቋ ላይ ተመስርቶ አቅም በፈቀደ መጠን ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ በየደረጃው መጠቀም ትምህርቱና መረጃው ውጤታማ እንዲሆን ይረዳል።

ነ    ልምድ ልውውጥ

በተለያዩ ጊዜ እየተገናኙ ልምድ መለዋወጥ ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል። በመሆም በኢትዮጵያ የሚገኙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቀነስ ብሎም ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ዋነኛው መፍትሄ ሕብረተሰቡን ማስተማር መሆኑ የሚታወቅ ነው። ትምህርቱን ለሁሉም ለማዳረስ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸው ግለሰቦች ትምህርቱን በሚሠጡበት ወቀት ያስትማሩትን መልዕክት ለሌሎች እንዲያስትላልፉ ማስገንዘብ ለጎረቤቶቻቸው፤ ለሚያገኙአቸው ሁሉ እንዲያሳውቁ ማድረግ መልዕክቱ ለብዙሃኑ እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል። ጎጂ ባህላዊ ልምድን ለማጥፋት በየዘርፉ የሚገኙ ባለሙያዎች የተጠናከረ የቅንጅት ሥራን ይጠይቃል። በመሆኑም መምህራን፤ ጋዜጠኞች፤ ተማሪዎች፤ የሀይማኖት መሪዎች፤ ያገር ሽማግሌዎች፤ ሴቶች ራሳቸው ጎጂና ጠቃሚ ባህሎችን በተመለከተ መረጃን አግኝተው የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ሌሎችን ሊለውጡ ይገባል። በተለይም የመገናኛ ብዙሃን የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በመለወጥ ሂደት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ስለሚችሉ የእነሱን ግንዛቤ አዳብሮ ትኩረት እንዲሰጡት ማመቻቸት ፈጣን የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ይረዳል።

# ማኅበራዊ ግብይት

*ከደምሰው በቀለ*

አጀማመሩ - በሃያኛው ክፍለ ዘመን የታየው የሰው ልጅ ዕድሜ እርዝማኔ የተገኘው በሽታን በመከላከል በተደረገው እንቅስቃሴ ነው ። ወባን፣ ፖሊዮን ኮሌራን፣ ፈንጣጣን የመሳሰሉትን ለመከላከል የተወሰዱት ዘመቻዎች አጥጋቢ ውጤት አስገኝተዋል ። ይህ በዚህ እንዳለ የአንዳንድ በሽታዎች ምንጭ ከባህሪያችን ጋር የተያያዙ ናቸው ። ይህ ማለት ሰው በሚያደርጋቸውና በማያደርጋቸው ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው ።

በልምድና በባህሪ ባንድ በኩል በሌላ በኩል በጤናና በበሽታ መካከል ያለው ጥብቅ ትስስር ሐኪሞችን፣ የሥነ ልቦና ተመራማሪዎችን፣ ፀሐፊዎችንና ፈላስፋዎችን ይበልጥ መስኩ ላይ እንዲሠሩ አተጋግቷቸዋል ። በ375 – 351 ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲርካ በተባለው ጽሑፍ፣ ሒፖክሪቲዝ በየቀኑ የምንወስደው ምግብ በጤንነታችንና በሕመማችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይናገራል ። ስለዚህ ሒፖክሪቲዝ ማንኛውም የጤና ባለሙያ በምርምርና በሕክምና ወቅት የባህሪ ሁኔታን በጥንቃቄ እንዲያስተውሉ ይጠይቃል ።

> "እያንዳንዱ የሕክምና ባለሙያ ተግባሩን ለመወጣት ከፈለገ፣
> በተፈጥሮ ላይ ብቃት ያለው ሆኖ መገኘት አስፈላጊ ሆኖ
> ይታያል ። ሰውን ከምግብና ከመጠጡ እንዲሁም ከሥራው
> ጋር እያንዳንዱ ከሌሎቹ ጋር ሲሆኑ የሚያመጡትን መከ
> ታተል ተገቢ ነው ።" (ሒፖክሪቲዝ)

ኤልሳቤጥ ብላክዌል የተባለችውን የሕክምና አዋቂም በጣም ያስጨንቃት የነበረው ጉዳይ ምንም እንኳ ዜጎቿ ለኅብረተሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ቢገኙም ከአኗኗራቸው በመነጨ ምክንያት ጤንነታቸውን አደጋ ላይ እየጣሉ የመሄዳቸው ነገር ነው ። በ1860 በጻፈችው ጽሑፍ ውስጥ የየቀን ተግባራችን ከጤና ሕግ ጋር መጣጣም እንዳለበትና ሥልጣኔን ለማስገኘት ብለን ብቻ አካላዊና መንፈሳዊ ተፈጥሮአችንን አሳልፈን እንዳንሰጥ ጥንቃቄ እንድናደርግ ትመክራለች ።

አብዛኛውን የበሽታ መንስኤዎች ከባህሪያችን ጋር የተቆላለፉ ናቸው፤ ከመቶ በሽታ መነሻዎች ውስጥ 70ው ቀን ተቀን ከምናደርገው እንቅስቃሴዎች ጋር የተገናኙ እንደሆኑ ብዙ ጥናቶች አረጋግጠዋል ።

## ባህሪያዊ ሕክምና

የባህሪና ጤንነት ውኅደት በሥነ ልቦና መስክ፣ በመድኃኒት፣ በጤና አጠባበቅ ሰዎች የሚያርጉት እንቅስቃሴ ከሰውነታቸው ጋር ግንኙነት መኖሩ በታወቁ ባህራዊ ሕክምና ሕልውና እያገኘ መጣ ። ይህ የሕክምና ዘርፍ በአካልና በሕመም መካከል ያለውን ግንኙነት በመረዳት ይህንኑ እውቀት ሕመምን ለመከላከልና ለመመርመር፣ ለመታከም በተግባር ማዋል የሚቻልበት መንገድ ነው ።

ጤንነትን ለመጠበቅ ከሚያስፈልጉ ልምዶች ዋና ዋናዎቹ አመጋገብን መቆጣጠር፣ ማጨስን መከላከል፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ማዘውተር፣ ልቅ የመጠጥ ተገዥነትን መከላከል፣ ካለሐኪም ትእዛዝ የሚወሰድ መድኃኒትን ማቆም ናቸው ።

እነዚህን ባለማስተዋል ከሚመጡ ሕመሞች የተነሳ ዕድሜያቸው ባጭር የሚቀጨው ቁጥር ከፍተኛ ነው ። በልብ ሕመም 4.3 ሚሊዮን ዓመቶች ባክነዋል፤ በስትሮክ 833,944 ዓመቶች፣ እራስን በማጥፋት 814,517 ዓመቶች እና ከመጠጥ በሚመጣ የጉበት በሽታ 478,473 ዓመቶች ባክነዋል ። የሰው ልጅ ባህሪውን ቢያስተካክል ለጤንነት የሚፈሰው ገንዘብ ለብዙ የልማት ሥራዎች ሊውል በቻለም ነበር ።

የባህሪና ጤንነት መዛመድ ከታወቀ ወዲህ ከደረቅ ሕክምና ጋር የባህሪ ለውጥ ትምህርት መካሄድ እንዳለበት ታምኗል ።

## የማኅበራዊ ግብይት ፅንሰ - ሐሳብ

ወደ ማኅበራዊ ግብይት ፅንሰ - ሐሳብ ከመግባታችን በፊት የሸቀጥ ግብይቶችን በተመ ለከተ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት የሚያስፈልግበት ለማኅበራዊ ግብይት መሠረቱ በመሆኑ ነው ። ገበያ ችግርን ለመፍታት የሚደረግ ሂደት ሲሆን ሥርዓት ባለው መንገድ እንድንጓዝ ያደርገናል ።

### የግብይት ሂደት

የግብይት ሂደት ክብነት ያለው ሆኖ የመጨረሻው የግብይት ደረጃ መልሶ የመጀመሪያውን ደረጃው በመመገብ እንደገና ለማቀድና ለማሻሻልም ቦታ ይሰጣል።

1. ገበያ

ማንኛውም ገበያ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ስለገበያው፣ ስለተጠቃሚው ገበያውን ተቋም ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል ። ኅብረተሰብን በበቂ ሁኔታ የሚያገለግል ገበያ ባለበት ቦታ ለመክሰር ካልተፈለገ በስተቀር እዛ ቦታ ተመሳሳይ ገበያ መጀመሩ አያዋጣም ። ነገር ግን ከዛ ኅብረተሰብ የግብይት አገልግሎት ለማግኘት ያልቻለ ክፍል ካለ ያንን ክፍል ለማገልገል ከተፈለገ ሊያዋጣ የሚችል ነው ። እዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ምን ዓይነት ሸቀጥ እንደሚፈለግ ቀድም ብሎ ማወቅን ይጠይቃል ።

2. ኅብረተሰቡ

እላይ "እንደሚፈለግ" ስንል ኅብረተሰቡ ምን ይፈልጋል የሚለውን አካቶ የያዘ ነው ። ብዙ ጉዳዮችን እንደ ዕድሜ፣ ገቢ፣ ፆታ፣ ትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ መጠን፣ ቦታ፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከቱን፣ ሥራውን፣ ሃይማኖቱን፣ ዘሩን፣ የመገናኛ ዘዴ አጠቃቀም ባህሉን፣ የመሳሰሉትን ሁሉ ማወቅ ጠቀሜታ አለው ። እነዚህ ትኩረቶች ዕቅድ፣ ዓላማን፣ የገበያ ስልትን፣ እንቅስቃሴን ለመቀየስ መንገድ ይከፍታሉ ።

3. ምርት

የሚያመርተውን ሸቀጥ፣ ሥርጭቱን፣ ዋጋውን፣ የመገናኛ ስልቱንና መልዕክቱን፣ ሙከራውን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ።

4. ትግበራ

በዚህ ወቅት በእቅድ የተያዘ ሁሉ ተግባራዊ የሚሆንበት ወቅት ነው እንዲሁም የሂደት ግምገማ፣ የአሠራር ግምገማ ወቅታዊ የሆኑ እርምቶችን እያስተካከሉ መንቀሳቀስ ውጤታማ ያደርገዋል ።

5. አጠቃላይ ግምገማ

የተጠቃሚውን፣ የቸርቻሪውን፣ መገናኛ ዘዴውን፣ ሥርጭቱን፣ ተቋሙን ገቢና ወጪውን በመለየት ለቀጣይ ተግባር ያመቻቻል ።

6. ምገባ

ይህ ለመጀመሪያው ደረጃ ግብአት በመሆን ያገለግላሉ ። አጠቃላይ የሸቀጥ ገበያ ይህን ከመሰለ "ሳሙናን መሸጥ ከቻልን ለምን ወንድማማችነትን መሸጥ አልቻልንም" ሳሙና ሻጮች ከማኅበራዊ ጉዳይ ሻጮች የበለጠ ሻጮች ናቸው ። ጥናቶች እንደሚ ያሳዩት የሸቀጥ ግብይት ስልትን ከተጠቀሙ ማኅበራዊ ግብይትን ውጤታማ ይሆናል የሚል እምነት አለ ። ብዙ ሰዎች ተገቢውን ባህሪዊ የጤና አጠባበቅን ለመከተል የሚችሉት እኛ እነዚህን ነገሮች መሸጥ ስንችል ብቻ ነው ። የግብይት ስልትን ከባህሪ ለውጥ ስልቶች ጋር በደንብ ካቀናጀን ከባህሪ የሚመጡ የጤና ችግሮችን ማስወገድ እንችላለን ።

ፊሊፕ ኮትለር ( በ1971 ) የሸቀጥ ግብይት ስልት ከንግድና አገልግሎት አቅራቢ ውጭ ለሆኑ ነገሮችም ጭምር ሊያገለግል ይችላል የሚለውን ሐሳብ መነሻው አደረገው ። በዚህ መሠረት ማኅበራዊ ግብይት ለማኅበረሰብ ጠቃሚ የሆኑ ፕሮግራሞችን ሐሳቦችን ባህሪ ዎችን መሸጥ የሚቻልበትን ስልትና ትግበራ ለማካሄድ ለሚሸጠው ነገር እቅድ፣ ዋጋው፣ መገናኛው፣ ስርጭትና የገበያ ምርምርናጥናት መካሄድ አለበት ።

ስለዚህ ማኅበራዊ ግብይት፣

1. ጥሩ ስልቶችን ለመቀየስ እንዲቻል ግልጽ እቅድና ዓላማ መንደፍን ይጠይቃል ።
2. ገበያተኛን በመተንተን የኛን የአሁኑን ገበያተኞችና የወደፊት ገበያተኞችን መለየት፣
3. ገበያተኛውን በመግዛት የሚያገኘውን ጥቅምና ማስረጃ ማዘጋጀት፣
4. የሚሸጠውን በተለያዩ ዘዴ ማስተዋወቅ፣

<u>የገበያ ምርምና ጥናት</u>

– ችግሩን መረዳት (Problem identification) – ችግሩ ሊመዘንና ሊፈተሽ በሚችል መልኩ መቅረብ ይኖርበታል ።

- የጥናትና ምርምር ዝግጅት (Research design) – የሚያስፈልጉ መረጃዎች (data) ማሰባሰብ ዘዴ፣ ጥያቄዎቹን፣ የመሳሰሉትን ማዘጋጀት፣
- መረጃዎችን መተንተን (Data analysis) – ጠቃሚ የሆኑ ሐሳቦችን ከመረጃዎቹ ማጠናቀርን፣

## ገበያተኛው ጠቀሜታ (Consumer Benefit)

ግብይት ሻጩ ለተጠቃሚው የሚቀርበውን በጥንቃቄ በመመርመር ከተጠቃሚው ፍላጎት አንፃር እንጂ ከራሱ ፍላጎት መነሳት የለበትም ። ገበያተኛው ከዚህ አዲስ ከሚቀርብለት ምን ጠቀሜታ እንዲያገኝ ማየት መቻል አለበት ። ይህን ለማድረግ ግን በቅድሚያ አንዳንድ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል ። አንድ ሰው አንድ ነገር ለመቀበል በአራት የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ማለፍ አለበት ።

1. ቀልብ መሳብ ( Attention getting ) – ይህ የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን ግለሰቡ ከሚገዛው ጋር መተዋወቅ የሚችልበት መድረክ ነው ። ይህን አዲስ ነገር በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች እንበትናለን ። በዚህ ደረጃ ግንባር ቀደም የቅስቀሳ መሣሪያዎቻችን መገናኛ ዘዴዎች ናቸው ። ተጠቃሚው በቂ የቅስቀ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ሊሆን ይገባዋል ።
2. ፍላጎት ማሳደር ( Develop Interest) – ተጠቃሚ በቂ የቅስቀሳ ፕሮግራሞችን ማግኘት ከቻለ ከጊዜ በኋላ እርሱ ራሱ የበለጠ ሐሳብ ለማግኘት የራሱ ጥረት ይታከልበታል ።

3. መመዘን መጀመር ( Evaluation ) – ይህ ደረጃ ወሳኝ ከሆኑት ደረጃዎች ሁሉ ዋንኛው ነው ። በዚህ ደረጃ ልምዱን (attitude) የሚለወጥበትና አዲሱን ልምድ የሚቀበልበት ደረጃ ነው ።

- ጠቀሚታ (Relative Advantage) ጠቀሚታውን ይገመግማል ። ተጠቃሚው አዲሱን ነገር ካለው ጋር የማነፃፀርና የማመዛዘን ደረጃ ላይ ይደርሳል ።
- መጣጣም (Compatability) ይህ ካለው ሁኔታ፣ ባህሉ ጋር ይሄዳል ወይ ብሎ ያመዛዝናል ።
- ውስብስብነቱ (Complexity) ይህ አዲሱ ነገር አጠቃቀሙ ውስብስብ ነው ወይስ ቀለል ብሎ የሚገመገምበት ሁኔታ አለ?
- ተሞካሪነቱ (Trialability) በመጠኑም ቢሆን ሀሳቡን ይሞክራል ።
- እይታ (Observability) የዚህን አዲስ ነገር ጠቀሚታ ማየት ይቻላል ወይ? ውጤቱ ቅርብ ነው ወይ?አንድ ሰው በዚህ ደረጃ ካለፈና ሀሳቡ ጥሩ ሆኖ ካገኘው ልምድ (attitude) አዳብሯል ብለን የምንቀበልበት ነው ። በአነጋገሩም ሆነ በአመለካከቱ ተቀባይነቱን የሚገልጽበት ደረጃ ደርሷል ማለት ነው ። በዚህ ወቅት ከመገናኛ ብዙሃን ይበልጥ የሰው ለሰው ግንኙነት ከፍተኛ ውጤት አለው ። ሌሎች ምን ውጤት እንዳገኙ ለማወቅ ይፈልጋል ። መገናኛ ብዙሃን ሀሳቡን ይበልጥ መሠረት እንዲይዝ ሊረዳ ይችላል።

4. ትግበራ (Action) – በዚህ ወቅት ግለሰቡ ሀሳቡን መቀበሉን የሚለይበትና ተግባራዊ የሚያደርግበት ደረጃ እንደደረሰ መረዳት ይቻላል ። ቢሆንም አሁንም አጠናካሪ መልእክቶችን ማግኘት አለበት ።

በአጠቃላይ አጫጭር መልእክቶች በሁለቱ በሀሳብ መሳቢያና ፍላጎት ማሳደር ደረጃ ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው ። ረዘም ያለና ትምህርታዊ መልእክቶችን ያዘሉ ፍላጎት ካደረ በኋላ የሚሰጡት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ። ትግበራ ደረጃ ከደረሰ በኋላ የተለያዩ ደጋፊና በሙከራዊ ውጤት ላይ ያተኮሩ መልእክቶች ማስተላለፍ ውህደቱን ያጠናክራል ።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው አንድ ሀሳብ አንድ ሰው ወዲያው አይቀበለውም ጊዜ ይፈጃል ። ብዙ መረጃዎች መሰጠት አለባቸው ። ይህም ሆኖ አንዳንድ ሰዎች አንድን ልምድ ላለመተው ብዙ ስልቶች ( selectivity ) አሏቸው ። በማስታወቂያና በሬድዮ ብቻ የሚካሄድ ማኅበራዊ ግብይት ውጤቱ አጥጋቢ ባለመሆኑ የሰው ለሰው ግንኙነት ( Social Communication) መሠረት ይዞ መጣ ። ይህም ጠለቅ ያለ የገበያ ጥናት ባለማካተቱ ማኅበራዊ ግብይትን አስከተለ ። ማኅበራዊ ኮሚኒኬተር (Social Communicator) ከሶሻል ግብይት ኮሚኒኬተርም (Social Market Communicator) የሚለይበት ቁልጭ ብሎ ታየ ። ማኅበራዊ ኮሚኒኬተር ዕቃው፣ የዕቃው ዋጋ፣ እቅድና አሠረጫጨቱ ላይ አይሳተፉም ። ነገር ግን የማኅበራዊ ግብይት ባለሙያ ከእቅድ ጀምሮ ስለሚኖር ምክር ይሰጣል፤ ማበረታቻ ዓይነቶችን ይቀይሳል፤ የዕቃው (ሀሳቡን) ዓይነቱንና ሥርጭቱን አብሮ ይመክራል ።

ማኅበራዊ ለውጥ ከግለሰብ ደረጃ አልፎ ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ብዙና ሰፋ ያሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋሉ ። ማኅበራዊ ግብይትም ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ይረዳል ። አራት ስልቶች ተቀይሰዋል ።

1. ሕጋዊ መንገድ – ይህ ሕግ በማውጣት አንድ ነገር እንዴት መከተልእንዳለብን የሚመራ መንገድ ነው ።
2. ቴክኖሎጂያዊ አቀራረብ – አንድን መጥፎን ባህሪ በአዲስ ፈጠራ መተካት የሚቻልበት ዘዴ ነው ።
3. ኤኮኖሚያዊ አቀራረብ – የመጥፎውን ባህሪ ዋጋ ከፍ በማድረግ የአዲሱን በቀላሉ የሚገኝበትን መቀየስ ነው ።
4. የሀሳብ መረጃ ዘዴ – አሳማኝ መልእክቶችን በማስተላለፍ ኅብረተሰቡን መቀስቀስ ነው ።

## የግብይት ሂደት

1. ጥናት (Analysis) ማካሄድ – ገበያ ማወቅ፣ ተጠቃሚውን መለየትና ማወቅ፣ የሚያንቀሳቅሰው ተቋም ደረጃና ግንኙነት መለየት አስፈላጊ ነው ።
2. እቅድ መንደፍ (Planning) – በግብይት ላይ ያተኮረ እቅድ መንደፍ ያስፈልጋል ።
3. ፕሮግራም ዝግጅትና ሙከራ (Testing) – ሸቀጡን ዋጋውን መወሰን፣ ሥርጭቱን መቀየስ ይይዛል ።
4. ትግበራ (Implementation) – ሥርጭትና ግምገማን አጠናክሮ መነሳት ።
5. ግምገማ (Evluation) – አጠቃላይ ግምገማ የቀጣዩን ሥራ ያመቻቻል ።
6. ምገባ (Feedback) – ይህ ለማንኛውም የሸቀጥ ግብይት ሲሆን የማኅበራዊ ግብይትም ከዚሁ አይለይም ። ሆኖም የሸቀጥ ግብይት ከማኅበራዊ ግብይት የሚለይበት ሁኔታ አለ።

| የሸቀጥ ግብይት | ማኅበራዊ ግብይት |
| --- | --- |
| ሸቀጥ ለመግዛት ጊዜ አይፈጅም | ጊዜ ይፈጃል |
| ሸቀጡን መግዛት ድካም የለውም | ብዙ ድካም አለበት |

## የማኅበራዊ ግብይት ሂደት

ማኅበራዊ ግብይት ቅስቀሳን ለማካሄድ የሚያስፈልገው እቅድ ለማውጣት 7 ዋና ዋና ደረጃዎች አሉ ። እነሱም ችግሩን መረዳት (problem identification) ፣ ግብን ማስቀመጥ (goal setting)፣ የታለመ ገበያን መተንተን (target market segmentation) ተጠቃሚን መተንተን (consumer analysis)፣ በመገናኛ መስመር የሚያገለግሉትን መዘርዘር (channel analysis)፣ የግብይት ስልት ቀየሳ (marketing strategy) እና ትግበራና ግምገማ (implementation & evaluation) ናቸው ።

# በማኅበራዊ ግብይት የመገናኛ ብዙኃን ሚና

የማኅበራዊ ግብይት የመገናኛ ስልት የሚገኙትን የኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች በመጠቀም የባህሪ ለውጥ ለማምጣት፣ የምርት ሽያጭን ከፍ ለማድረግ (ኮንዶም)፣ የአገልግሎት በሮችን ለመክፈት (ክትባት)፣ ያገለግላሉ ።

ኮሙኒኬሽን →
- የባህሪ ለውጥ ለማምጣት
- የምርት ሽያጭን ከፍ ማድረግ
- የአገልግሎት በሮችን መክፈት

ሆኖም ይህን ግብ ለመምታት የማኅበራዊ ግብይት ባለሙያዎች በደንብ የተቀናጀ መልእክት ለመልእክቱ ደጋፊ ነገሮች ማዘጋጀትና በርቀትና በቀጣይነት ማሠራጨት አለባቸው ። ብዙ ጊዜ የኮሙኒኬሽን ተግባር ኅብረተሰቡን ስላለው ችግር ማንቃት ሲሆን የባህሪ ለውጥ የሚገኘው ደግሞ በመገናኛ ብዙኃን ብቻ ሳይወሰን ከሰው ለሰው ግንኙነት ጋር ተቀናጅቶ የችግሩን አሳሳቢነት ኅብረተሰቡ ትኩረት ሲሰጠው ነው ።

ውጤታማ የሆነ የማኅበራዊ ግብይት ቅስቀሳዎች (Campaigns) የታለሙትን የኅብረተሰብ ክፍል ለመድረስ ሰፋ ያለ የመገናኛ ዘዴዎችን የተጠቀሙ ናቸው ።

ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች →
- የአካባቢ የጤና ሠራተኞች፣
- የለውጥ ወኪሎችን

በማኅበራዊ ግብይት የመገናኛ ብዙኃን ሚና

| | |
|---|---|
| መገናኛ ብዙኃን ብቻ | • ንቃት ይፈጥራል ፡፡<br>• በባህሪ ለውጥ መሠረት ይጥላል ፡፡<br>• የምርት ሽያጭን ከፍ ያደርጋል ፡፡<br>• የአገልግሎት በሮች ይከፍታል ፡፡ |
| መገናኛ ብዙኃን ከሰው ለሰው ግንኙነት ጋር | • የባህሪ ለውጥ ያመጣል ፡፡ |

## ጥሩ የማኅበራዊ ግብይት መልእክቶች ምን ዓይነት መሆን አለባቸው?

* የአልቀበሌነትን ድንበር የሚጥስ መሆን አለበት ፡፡ (overcome resistance) ይህን ለማግኘት፣
  – መልእክቱ ምን የጤና ችግር ለመወጣት እንደሚዘጋጅ በትክክል መረዳት አለበት ፡፡
  – የሚፈለገው የማኅበራዊ ግብይቱ ወይም የባህሪ ለውጡ ምን እንደሆን መለየት አለበት ፡፡
  – የታለመው የኅብረተሰብ ክፍል የቱ እንደሆን ጥርት ባለመልኩ መለየት አለበት ፡፡
  – ሀሳቡን ላለመቀበል የሚያደርገው መሰናክል መታወቅ አለበት ፡፡

* ጥሩ መልእክት ጤፍ ቆይ ብቻ መሆን የለበትም ፡፡
  – ጥሩ መልእክት ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው (Doable)
  – ኅብረተሰቡ ሊቀበል ከሚችለው የባህሪ ለውጥ ዓላማ አንፃር መልእክታችን ቁልጭ ብሎ ከተቀመጠ ሊተገበር ይችላል ፡፡
  – ለምሳሌ ከማኅበራዊ ኢኮኖሚ አቅሙ በላይ ከሆን አዲሱን ሀሳብ መቀበሉ ይቸግረዋል ፡፡

* ጥሩ መልእክት አቤቱ ጌታዬ መባል መቻል አለበት ፡፡
  – ጥሩ መልእክት ታአማኒ መሆን መቻል አለበት ፡፡ (Believable)
  – መልእክት ከባህልና ከኤኮኖሚ ጋር መጣጣም አለበት ፡፡

* ጥሩ መልእክት አቤቱ ጌታዬ መባል መቻል አለበት ፡፡
  - ጥሩ መልእክት ታአማኒ መሆን መቻል አለበት ፡፡ (Believable)
  - መልእክት ከባህልና ከኤኮኖሚ ጋር መጣጣም አለበት ፡፡

* ጥሩ መልእክት አንድ አፍቃሪ በአንድ ለአንድ የሚያምን መሆን አለበት ፡፡
  - ጥሩ መልእክት ባንድ ነጥብ (ጽንሰ - ሐሳብ) ላይ ያተኮረ እንደሆነ ነው ፡፡ (Single concept)
  - አንድን የባህሪ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል መልእክት መሆን አለበት ፡፡
  - መተው –አንድ ላንድ – ኮንዶም (ሁሉም ለአንድ ሰው አያገለግልም)
  - በተለይ በመገናኛ ብዙኃን ካንድ በላይ መልእክት ይቸግራል ፡፡
  - መልእክቱ ሊደጋገም ይችላል ፡፡
  - መልእክቱ የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል ፡፡

* ጥሩ መልእክት እየኮረኮረ እያሳቀ ቀልብ ሳቢ መሆን አለበት
  - ፍላጎታቸውን የሚያቆይ (የሚጠብቅ) መሆን ይገባዋል ፡፡
  - ከአዲሱ ምርት (ሀሳብ) የሚያገኙትን ጠቀሜታ በውስጣቸው ማስረፅ አለበት ፡፡
  - እነዚህ ጠቀሜታዎችን በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ድጋፍ መስጠት አለበት ፡፡

* ጥሩ መልእክት አነጣጥሮ ተኳሽ መሆን አለበት ፡፡
  - ተጠቃሚውን ለይቶ የሚያነጋግር መሆን አለበት ፡፡
  - መልእክቶቹ በተጠቃሚዎቹ ልክ ተለክተው መሰፋት አለባቸው ፡፡
  - በጣም የጠበበ ወይም በጣም የሰፋ መልእክት ለሱ ተብሎ ያልተሰፋ ስለሆነአይረባውም ፡፡

* ጥሩ መልእክት ምቹ መንገዱን ያውቃል ፡፡
  - የትኛው መልእክት በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጽሑፍ፣ በሰው፣ ወዘተ. ቢሄድ ከመድረሻ ቦታው ሳይመሽበት ይገባል ፡፡

* ጥሩ መልእክት ዘረኛ ነው ።
  - የወፍ ቋንቋ ልጠቀም አይልም ።
  - የትኛውን አባባል ለማን ላውል ይላል ።

* ጥሩ መልእክት ፈጥኖ ደራሽ ነው ።
  - ችግር ሲደርስ ችግርን ይፈታል ።
  - ለአከራካሪ ችግር ዘላቂ መፍትሔ ያወርሳሉ ።

# በገመናኛ ብዙሃን የሚቀርቡ ድራማዎች ለሥነ ሕዝብ ጠቀሜታ

በበላይነህ አቡኔ
ከአ.አ. ዩኒቨርሲቲ

## መግቢያ

በመልማት ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች በመገናኛ ብዙሃን የሚቀርብላቸው ልዩ ልዩ ፕሮግራም የእነርሱን ሕይወት ያላገናዘበ፣ የዘመኑን ቋንቋና ፍልስፍና ተከትሎ የሚጓዝ በመሆኑም ጭምር በእነርሱ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። የሰሙትንና ያዩትን ለማድረግ ቢፈልጉም ምኞታቸው እንዲህ በቀላሉ ስለማይሳካ አላስፈላጊ ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ።

ማኀበራዊ ለውጥ የተሟላ ትምህርትና ዋስትና ያለው ገቢ፣ የቤተሰብ ምጣኔና ዕቅድ፣ ጥሩ ምግብና የተሟላ ጤና ለሥራ የሚኖር አዎንታዊ አመለካከትና እንከን የሌለበት ሕይወት ለመምራት በጥቂት ከተሞች ውስጥ የሚደረግ አካላዊ ለውጥ ብቻ አይበቃም። ከሁሉም በላይ የሕዝቡን አመለካከትና የባሕርይ ለውጥ አብሮ ማምጣትን ይጠይቃል። ወሳኙ ሕዝቡ ለአጠቃላይ ማኀበራዊ ለውጥ የሚኖረው ተሳትፎና ተነሳሽነት ነው። ለማኀበራዊ እድገት የሚቀየሱ ፕሮግራሞች ግባቸውን እንዲመቱ ለሕዝቡ የሚገባው ቋንቋ ግንኙነት መፍጠር አስፈላጊ ነው። የመድረክ፣ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ድራማዎች የሕዝቡን ስሜት በመያዝና አትኩሮቱን በመሳብ ተፈላጊውን መልዕክት በማስተላለፍ በኩል ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

በዚህ አነስተኛ ጥናት በሕዝብ መገናኛ የሚቀርቡ ድራማዎች ለሥነ ሕዝብ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል። በድራማው ዙሪያ የሚሳተፉ ሙያተኞች ስለሥነ ሕዝብ ችግሮች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በመጀመሪያው ክፍል ይህንኑ ጉዳይ በመጠኑ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል። በማስከተል፣ ትያትርም ከሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አንዱ ነውና በልማት ዙሪያ ስለሚሠሩ ቲያትሮች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተሞክሯል። በመጨረሻው ክፍል የሬዲዮና የቴሊቪዥን ድራማዎችን በሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ማቅረብ የሚሹ የትያትር ባለሙያዎች ማወቅ ስለሚኖርባቸው ነጥቦች በዝርዝር ለማስቀመጥ ጥናት አቅራቢው ጥረት አድርጓል።

## 1. የሥነ ሕዝብ ችግሮች

ዛሬ እንደኢትዮጵያ ያሉ አዳጊ አገሮች ከሥነ ሕዝብ (Population) እና ስነ ተዋልዶ ጤና (Reproductive Health) ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የልማትና የእድገት እንቅስቃሴያቸውን ገድበውት ይገኛሉ። በየጊዜው እየጨመረ የሚመጠውን የሕዝብ እድገት፣ አገሪቱ ካላት የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የልማት ሥርጭት ጋር በማጣጣም በሂደት የሕዝቡን አጠቃላይ ደህንነት የሚጠብቅ የተቀናጀ አሠራር መንደፍ ተገቢ ነው።

በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች በከፍተኛ ቁጥር እያደገ የሚሄደው ይህ የሕዝብ ቁጥር መጠን ለከፍተኛ ድህነት፣ ረሃብ፣ ሞትና ስደት እያጋለጣቸው ይገኛል። በዚህም ምክንያት ለከፍተኛ የውጭ ዕዳ ጫናና ልመና ተጋልጠዋል።

በሀገራችን በኢትዮጵያም ይህ ከሥነ ሕዝብ ጋር የተያያዘ ችግር በጣም በአሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል። የሕዝቡ ብዛትና ሀገሪቱ ያለችበት የልማት ደረጃ በፍጹም ተመጣጣኝ አይደለም። በብዙ የሀገራችን ክፍሎች ለእርሻ የሚሆነው መሬት እየጠበበ በመምጣቱ አብዛኛው ወጣት የኅብረተሰብ ክፍል የተሻለ ነገር ለማግኘት ወደከተሞች የሚያደርገው ስደት ቀላል አይደለም። ደኖች የእርሻ መሬት ለማግኘትም ሆነ ለማገዶ በየጊዜው ይጨፈጨፋሉ። በዚህ የተነሣ ድርቅ ይከተላል። ነዋሪው ለረሃብና ለተረጂነት ይጋለጣል። በዚህ የሕዝብ ብዛት ሳቢያና በሌሎችም ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ችግሮች የሀገሪቱ የኤኮኖሚ ዐቅም ውሱን በመሆኑ ለአብዛኛው የገጠር ነዋሪ መሠረታዊ የጤናና የትምህርት አገልግሎት ማዳረስ አስቸጋሪ ሆኗል።

በሀገሪቱ ትላልቅ ከተሞች የሚስተዋለው የሕዝብ ክምችት መንሥኤው የተሻለ ሕይወትና የሥራ ዕድል ለማግኘት ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው የገጠሩ ኅብረተሰብና በከተሚው መጥኖ ያለመውለድ የመጣ ችግር ነው። በመሆኑም ዛሬ የትላልቅ ከተሞች መለዮ የሆነው ሥራ አጥነት፣ ሴትኛ አዳሪነት፣ ዝርፊያና የወንጀለኛ መበራከት፣ የአባለ ዘርና የኤድስ በሽታ መስፋፋት፣ የሐሺሽና የሌሎችም ዕፆች ተጠቃሚነት፣ ወደተለያዩ የዐረብ ሀገሮች የሚደረግ ስደት፣ በአካባቢ ብክለት የተነሣ የሚመጣ የእናቶች፣ የአባወራዎች ሞትና እንዲሁም የልጆች ያለዕድሜ መቀጠፍና የመሳሰሉት ሁሉ ምክንያቱ ሀገሪቱ የምትገኝበት የእድገት ደረጃና በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣው የሕዝብ ቁጥር እድገት ሊጣጣም ያለመቻሉ ነው። ኤ.ኤስ.ኦቤራይ (1993) የተባለ የሥነ ሕዝብ ኤክስፐርት እንደሚለው በከተሞች ውስጥ ለሚታየው ድህነት መሠረታዊው መንሥኤ የአካባቢ የምርት እድገትና የሠለጠነ የሰው ኃይል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት፣ በምርት ውጤቶች የሚስተዋለው ያልተመጣጠነ ክፍፍል ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ ያለው ውሱን ዐቅም፣ ከፍተኛ የሕዝብ መራባት፣ (በተለይ በዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል) የከተሞችን እድገት ለማፋጠን ብዛት ያለው የሰው ኃይል ያስፈልጋል፣ በሚል የሚነደፍ ስትራተጂ የሚፈጥረው አድሎአዊነት ናቸው። በሌላ በኩልም በአነስተኛና እዚህ ግባ በማይባል የገቢ ምንጭ በሚተዳደሩ ቤተሰቦች ላይ የሚስተዋለው ድህነት መንሥኤ:-

1. ከቤተሰቡ በዕድሜ ከፍ ያሉት ሥራ ለማግኘት ያላቸው ዕድል አናሳነት፣
2. የሥራ ዕድል በአጋጣሚ ቢገኝ እንኳን በትምህርት የገፉ ስላልሆኑ የሚከፈላቸው ክፍያ በጣም ዝቅተኛነት፣

3. አጠቃላይ የቤተሰቡ ገቢ በመጠኑ ሚዛን የደፋ እንኳን ቢሆን የልጆች መብዛትና የሌላ ዘመድ አዝማድ ጥገኝነት በቤተሰቡ ኑሮ ላይ ጫና መፍጠሩ የማይቀር በመሆኑ ነው።

ሌሎች ተጨማሪ ሕፃናት ወደቤተሰቡ በተቀላቀሉ ቁጥር የቤተሰቡ አባላት የሚኖራቸው የምግብም ሆነ የሌሎች መሠረታዊ ፍላጐቶች ፍጆታ መጠን እየቀነሰ ይሄዳል። ቀስ በቀስም የቤተሰቡ አባላት በፊት ከነበሩበት «የተሻለ» የኑሮ ደረጃ ወደከፋ የድህነት አዘቅት ይሽቀነጠራሉ። በቤተሰቡ አባላት መካከል ንዝንዝና ጭቅጭቅ ይፈጠራል። አባወራው በብስጭት ከጭቅጭቅ ለመራቅ ሲል እስከ እኩለ ሌሊት አምሽቶ መግባቱን ይያያዘዋል። እናት እየዘመመ የመጣውን ቤት ለማቃናት ስትል በዕዳ መዘፈቅ ትጀምራለች። ቀስ በቀስ የቤተሰቡ ኑሮ እየተናጋ እስከነአካቴው ይፈርሳል። ልጆቹም ከ«መሞት መሰንበት» ነውና ለጐዳና ተዳዳሪነት ለዝሙት አዳሪነትና ለልመና ይዳረጋሉ። ቤተሰቡ የመፍረስ ዕጣ ባይገጥመው እንኳን ቤተሰቡ ከገባበት የኢኮኖሚ ቀውስና ብድር ለመውጣት አባወራው በሙስና ተግባር መዘፈቁ አይቀሬ ነው። ዛሬ በየጊዜው በፖሊስ ፕሮግራም (በቴሌቪዥንና በሬዲዮ) የምናዳምጠውና የምንሰማው የየመሥሪያ ቤቱ ዘበኞች በሙስና መዘፈቅና ከሌቦች ጋር መሻረክ ምንጩ ይህ ሳይሆን ይቀራል?

በአብዛኛው የሀገራችን ክፍሎች የሚዘወተረው ሴቶችን በዝቅተኛ ዕድሜ መዳር ለሕዝብ ቁጥር መጨመር የሚያደርገው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። በ14 እና በ15 ዓመታቸው ለጋብቻ የሚዳረጉ ሴት ልጆች ዕድሜያቸው ወደ 25 ወይም 30 ሲደርስ ስንት ልጆች እንደሚወልዱ (ያውም አራርቆ መውለድ ባልተለመደበት ሁኔታ ውስጥ) ለማወቅ የሒሳብ ሊቅ መሆንን አይጠይቅም። በሌላ በኩል ካለፍላጐታቸው ለማያውቁት ሰው በመዳራቸውና፣ በጋብቻ ሕግ መላላት የተነሣ የህብት (የንብረት) ባለቤትነት መብት መዛባት በሴቶቹ ላይ በሚያስከትለው ተፅእኖ ትዳራቸውን አፍርሰው ወደከተማ የሚኰበልሉ ሴቶች ቁጥር ቀላል አይደለም። ከተማም ቢገቡ ሥራ ለማግኘት ያላቸው ዕድል በእጅጉ የመነመነ ነው። ስለዚህ ሳይወዱ በግድ ወደዝሙት አዳሪነት ይሰማራሉ። እንግዲህ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት ከዚህ ይጀምራል እነዚህም።

1. ከሴተኛ አዳሪዎች የሚወለዱ ሕፃናት ለተለያየ ተላላፊ በሽታ መጋለጣቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአጋጣሚ ቢያድጉም የመልካም ዜጋ ባሕርይና ስሜት የሌላቸው ቦዘኔዎች ይሆናሉ። ማጅራት መቺዎችና ኪስ አውላቂዎች ሆነው ጤናማውን የኅብረተሰብ ክፍል ዕረፍት ይነሳሉ።
2. የሴትኛ አዳሪዎችና መጠጥ ቤቶች መብዛት ለቤተሰብ መናጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። በሁለቱ ሱስ የተጠመደ አባወራ ለቤተሰቡ ፍቅር አይኖረውም። ገቢውም ስለሚዳከም ቀስ በቀስ ትዳሩ ይናጋል።

3. ዛሬ ሕዝብ እየጨረሰ ያለው ኤድስም ሆነ ሌሎች የአባለዘር በሽታዎች በሴትኛ አዳሪዎች አካባቢ የመስፋፋትም ሆነ የመተላለፍ ባሕሪያቸው ከፍተኛ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ የኅብረተሰብ ጤና ዲፓርትመንት አባል ዶ/ር ማትያስ አክሊሉ በአዲስ አበባ ለሕክምና በሄዱ 372 ሴትኛ አዳሪዎች ላይ ለ3 ወራት ባካሄዱት ጥናት፡-

- 98% ስለኤድስ ምንነትና መተላለፊያ መንገድ ጠንቅቀው አያውቁም።
- ብዙዎቹ በዝቅተኛ ኑሮ ላይ የነበሩና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከጠር ወደከተማ የመጡ ናቸው።
- ኑሮን ለማሸነፍ በሴትኛ አዳሪነት ከተሠማሩት ከእነዚህ 372 ሴቶች ውስጥ 35% ፊደል ያልቆጠሩ ናቸው።
- ከተጠቀሱት ሴትኛ አዳሪዎች ውስጥ 30% በእያንዳንዷ ጠባብ ክፍል ውስጥ 8 ሆነው የሚተኙ ናቸው።
- በተጨማሪም ብዙዎቹ የቂጥኝ ውርዴነት ሲኖርባቸው 74% የሚሆኑት በኤድስ ቫይረስ ተይዘዋል።

እንግዲህ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ችግሮች ለመቅረፍ በተጠናና በተማከለ አሠራር፤ የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮጀክቶችና እቅዶች ሲነደፉ የሥነ ሕዝብ ችግሮችንና ምንጮችን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው። እ.ኤ.አ. በ1994 ግንቦት ውስጥ በተካሄደው <u>የሥነ ሕዝብና የልማት እቅዶችን ማጣጣም</u> ብሔራዊ ጉባዔ ላይ ኔልሰን ኦ.አይ. ባቀረቡት ጥናት ስለ ሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ስፋትና ጥልቀት እንዲህ ብለዋል፡- «የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ቀደም ሲል ከቤተሰብ ምጣኔ ፖሊሲና ፕሮግራም ጋር ተመሳሳይነት ነበረው። አሁን ግን ልማትና ሥነ ሕዝብ ባላቸው ሁለትዮሽ ተፅእኖ የተለያየ ጣልቃ ገብነትን (መፍትሔ) የሚሹ ጉዳዮች አሉ» በማለት በሁለት ከፍለው ጉዳዮቹን ዘርዝረዋቸዋል። እነዚህም በሥነ ሕዝብ ላይ ቀጥተኛ ተፅእኖ ያላቸው እንደቤተሰብ ምጣኔ፣ ፣ የጋብቻ ዕድሜ፣ የሞት ዐይነትና ሁኔታ፣ የሕዝብ መልክአምድራዊ ሥርጭት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩልም ለሥነ ሕዝብ ችግር ምላሽ የሚያስገኙ ጉዳዮች ሲዘረዝሩ፣ ምግብና የምግብ አጠቃቀም ዘዴ፣ የመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ የትምህርት ስርጭት፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ጤናን የማሻሻልና ማኅበራዊ ደህንነት ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ በሥነ ሕዝብ ከታቀፉት ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ የሴቶችንና የወጣቶችን ደህንነት መከታተል፣ ለዐቅመ ደካሞች እንክብካቤ ማድረግ፣ አካባቢን መጠበቅና የኤድስ ጉዳይ ናቸው።

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰውና መሰል ጉዳዮች ላይ የሥነ ሕዝብ ባለሙያዎችና ሌሎችም በጉዳዩ ላይ አግባብ ያላቸው ባለሙያዎች የሚጠቁሙትን የመፍትሔ ሐሳብ መመልከቱ በተለይ

ትያትርን (ለመድረክ፣ ለሬዲዮና ለቴሌቪዥን) ለሥነ ሕዝብ ጠቀሜታ ለሚያውሉ ባለሙያዎች ይጠቅማል። በዚህ ረገድ እኔ የደረስኩባቸው (ሌሎችም ሊኖሩ ስለሚችሉ) የሚከተሉት ናቸው።

1- ከሁሉም በፊት በአንድ ሀገር የዲሞክራሲ መስፈን አስፈላጊ ስለሆነ በሕዝብ ተመርጦ ለሕዝብ የቆመ፤ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን መሠረት ያደረገ መንግሥት መኖር፣

2- ሕዝቡ በራሱ ጉዳይ ራሱ ወሳኝ የሚሆንበትን በሁሉም (ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ) ዘርፎች ላይ ተሳታፊ ሆኖ የሚወያይበትን (Dialogue) ሁኔታ ማመቻቸት፣

3- በከተሞች የሕዝብ መጨናነቅ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስ በገጠር የተመጣጠነ የልማት አውታሮችን (ከእርሻ ውጪ ትናንሽ የንግድ፣ የኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ማእከላት) በመዘርጋት አማራጭ ሰጥቶ ፍልሰቱን መቀነስ፣

4- አርሶ አደሩ ኋላ ቀር የአመራረት ዘይቤውን እንዲለውጥና የኑሮ ደረጃውን እንዲያሳድግ እርሱ የሚሳተፍበት የልማት እቅድ መዘርጋትና የብድር አገልግሎት ማስፋፋት፣

5- ሕዝቡ የቤተሰብ ዕቅድና ምጣኔ እንዲለምድ፣ ከገቢ ጋር ባልተመጣጠነ ሁኔታ ብዙ ልጆች መውለድ ስለሚፈጥረው ችግር፣ ስለአካባቢና ግል ጤንነት፣ ስለደን ጥቅም፣ ስለመሠረተ ትምህርት አስፈላጊነት ወዘተ. ትምህርት መረጃና መልእክት በተለያዩ ዘዴዎች እንዲደርሰው ያስፈልጋል።

## 2. የ'ትያትር ለልማት' እንቅስቃሴ ለሥነ ሕዝብ ያለው ጠቀሜታ

ትያትር ከአነሣሡም ሆነ ከእድገቱ ማኅበረሰባዊ ጠባይና ጠቀሜታ እንደነበረው በመስኩ የተሠማሩ ምሁራን ብዙ ጥናታዊ ዘገባዎችን አቅርበውበታል። ጥንታዊው ማኅበረሰብ በነበረው ውሱን ዕውቀት ራሱንና አካባቢውን ለማወቅና የተፈጥሮን ምሥጢር ለመረዳት በሚደረገው ጥረት የተለያዩ ትውፊታዊ ክንዋኔዎች ነበሩት። በዚህ ሃይማኖታዊ ይዘት በነበረው ትውፊታዊ ክንዋኔ አማካይነት የአካባቢው ማኅበረሰብ ሥነልቡናዊ እርካታን ከመጐናጸፉም በላይ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎችን ያገኝባቸው እንደነበር ጥናቶች ያስረዳሉ።

በመሆኑም የወቅትን መፈራረቅ፣ የምርትን መበራከት፣ የአካባቢን ፍትህ መጓደል አስመልክቶና ማኅበራዊ አንድነታቸውን ለማጠናከር በሚከበሩት የማኅበረሰቡ ትውፊታዊ ክብረ

በዓሎች ውስጥ ዛሬ የምናየው የተዋናይና የተመልካች ሚና ክፍፍል አልነበረም:: የተሳትፎው ደረጃና መጠን ይለያይ እንጂ ለክንዋኔው ተግባራዊ ጠቀሜታ በአካልና በመንፈስ የሚደረገው ተመስጦአዊ ተራክቦና ጥምረት የሁሉንም ተሳትፎ በእጅጉ የሚጠይቅ ነበር::

ዛሬ የአፍሪካ፣ የላቲን አሜሪካና የእስያ መንግሥታት የልማት ድርጅቶችና የትያትር ባለሙያዎች ይህን ከሕዝብ ለሕዝብ የሚቀርብና የሕዝብን ተሳትፎ መሠረት ያደረገ የትያትር ለልማት እንቅስቃሴ በሰፊው እያካሄዱበት ይገኛሉ:: ይህ ላለፉት ዓሥርት ዓመታት መሠረት በመጣል ላይ የሚገኝ ትያትራዊ እንቅስቃሴ ለሰፊው ሕዝብ ፖለቲካዊ ንቃት፣ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት አካባቢያዊ ባህሎችንና ልምዶችን በመንተራስ ሕዝቡ በራሱ ጉዳይ ራሱ ወሳኝ የሚሆንበትን ሁኔታ በማመቻቸት ይህ ነው፣ የማይባል ጠቀሜታ አስገኝቷል::

በብዙ ምዕራባውያን ሀገሮች እንደሚስተዋለውና አንዳንድ የጥበቡ ባለሙያዎች እንደሚሰብኩት ጥበብን ለጥበብነቱ ብቻ መከወን እንጂ ለትምህርትና ለሌሎች ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ከዋለ ጥበብነቱን እንደሚያስቀረው ይከራከራሉ:: የትያትር ጥበብ በራሱ እንደግብ እንጂ እንደመሣሪያ መዋል የለበትም፣ ባይ ናቸው:: ምናልባት ይህ አስተሳሰብ ሀገሮቹ ከደረሱበት የረቀቀ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገት አንፃር የሕዝቡም አስተሳሰብና ግንዛቤ በዚያው ልክ በዳበረበት ሁኔታ የትያትርን ጥበብ እንደሸቀጥ (commodity) ለትርፍ ማጋበሻ ብቻ መጠቀማቸው ለምን? የሚል ጥያቄ እንዳናነሣ ሊያደርገን ይችላል:: በመልማት ላይ በሚገኙ አዳጊ ሀገሮች ግን፣ ካብዌ ካስማ የተባለ አፍሪካዊ የትያትር ባለሙያ እንደሚለው «በአፍሪካ ውስጥ ትያትር ወደሕዝቡ መሄድ አለበት እንጂ ሕዝቡ ወደትያትር እንዲመጣ መጠበቅ የለብንም»:: ስለሆነም የሕዝቡን ችግርና ብሶት የሚያንፀባርቁ አመለካከቱንና ግንዛቤውን በማስፋት ለተሻለ ልማትና ዕድገት የሚያነሣሡ ትያትሮችን መሥራትና ሕዝቡን ማሳተፍ የተለመደ ሆኗል::

እነዚህ ሕዝብንና አካባቢን መሠረት አድርገው የሚታዩ ትያትሮች እንደየቦታውና እንደትያትሩ አትኩሮት የተለያየ ስያሜ ሲሰጣቸው እናያለን:: እነዚህም ትያትር ለልማት (Theatre for Development)፣ ተሳትፎአዊ ትያትር (Participatory Theatre)፣ ሕዝባዊ ትያትር (Popular Theatre)፣ አካባቢያዊ (ማኅበረሰባዊ) ትያትር (Community Theatre)፣ ትምህርታዊ ትያትር (Educational Theatre)፣ ናቸው:: ይሁንና ሁሉም የትያትር ዓይነት በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኘውን ዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍል ማኅበራዊ ለውጥ፣ ብሎም ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው የማሳተፍ ዐይነተኛ ዓላማቸው ነው::

2.1 *ሕዝባዊ ትያትር*- በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች በመዘውተር ላይ ያለው ይህ የትያትር እንቅስቃሴ አማተር ከያንያንና የአካባቢው ማኅበረሰብ በጋራ ሆነው በሕዝቡ

መሠረታዊ ችግሮች ላይ የሚሳተፉበት ነው። በችግሮቹ ላይ በግልና በጋራ (በቡድን) ውይይት ሰፊ ትንተና ከተደረገበት በኋላ ለአካባቢው ሕዝብ ቅርብ በሆኑ ጥበባዊ ክንዋኔዎች ቅርጽ ይዞ በቴአትር መልክ ለሕዝቡ ይቀርባል። በመድረክ ለሕዝቡ የቀረበው ትያትር የሚያንፀባርቀው ችግሮቹን ብቻ ስለሆነ ለመፍትሔው ማኅበረሰቡን ለውይይት ይጋብዛል። በድኅረ ትወናው ላይ ተመልካቾችና ተዋናዮቹ በሚሳተፉበት ወይይት የአካባቢው ኅብረተሰብ ችግሮቹን ለመቅረፍ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በቅደም ተከተል ያስቀምጣል። ይህን የትያትር ዐይነት ከሌላው ለየት የሚያደርገው ለዓላማው መሳካት ሕዝባዊነት ባላቸው ትውፊታዊ ክንዋኔዎች የትያትር ቅርጽ መጠቀሙ ነው።

2.2 ***ትያትር ለልማት***– ይህም የትያትር እንቅስቃሴ ልክ እንደሕዝባዊ ትያትር ሀገርኛ ጥበባዊ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። የዚህ የትያትር ለልማት አንቀሳቃሾች የትያትር ኤክስፐርቶች ናቸው። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ የልማት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራሉ። እነዚህን የልማት ድርጅቶች እንደተሰለፉበት መስክ ዓይነት፣ ማለትም በዘመናዊ የእርሻ አጠቃቀም፣ በመሠረተ ትምህርት፣ በአካባቢ ንጽህና፣ በደን እንክብካቤ፣ በቤተሰብ እቅድና ምጣኔ፣ በኤድስና በመሳሰሉት ላይ ትያትሮችን በማዘጋጀት ተፈላጊው መልእክት ለተቀባዩ ወገን በትክክል የሚደርስበትን መንገድ የትያትር ባለሙያዎቹ በማዘጋጀት ይረዷቸዋል። ትያትሩ በድራማ አቀራረብ ብቻ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ዘፈኖችንና ውዝዋዜዎችን በማቀላቀል ሊቀርብ ይችላል። በተለይ ዘፈኖቹ ቀለል ያሉ፣ ዜማቸው የሚስብና ስሜትን የሚማርኩ፣ ግልጽ መልእክት ያዘሉ መሆን አለባቸው። ዘፈኖቹን የትያትር ተሳታፊዎቹና ሕዝቡ በጋራ ያዜሟቸዋል። የዚህ ትያትር ቁርጥ ያለ ዓላማ ከኅብረተሰቡ ጋር ቀጥታ ግንኙነት መፍጠር፣ ማስተማርና ችግሮችን አንሥቶ ከኅብረሰቡ ጋር መፍትሔ መፈለግ፣ ብሎም ወደድርጊት እንዲሸጋገሩ ብልጭታ መጫር ናቸው።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለቱ የትያትር ዐይነቶችም ሆኑ ሌሎቹ (ተሳትፎአዊ፣ አካባቢያዊና ትምህርታዊ) የትያትር እንቅስቃሴዎች ዋነኛ ዓላማ በገጠሩ አርሶ አደርም ሆነ በከተማ ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ በሚገኙት ነዋሪዎች ዘንድ ስለ ተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እንዲሁም ልማት ነክ ጉዳዮች ሰፊ ግንዛቤ መፍጠርን ነው። በችግሮቻቸው ላይ እንዲወያዩ (Dialogue) መንገድ መጥረግ ነው። ለመፍትሔውም ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ሆነው የድህነትን ቀንበር አሽቀንጥረው የሚጥሉበትን መድረክ ማመቻቸት ነው።

ብራዚሊያዊው የትያትር ዳይሬክተር[1] አውጉስቶ ቦል በትያትርና በተመልካች መካከል ያለውን የበላይና የበታች – ያለቃና የምንዝር ዓይነት የተዋረድ ግንኙነት (top-down communication) ሰብሮ ተሳትፎአዊ ትያትር እንዲኖር ጥረት አድርጓል፡፡ በአውጉስቶ ቦል «የተጨቋኞች ትያትር» ፅንሰ ሐሳብ መሠረት የመድረክ ላይ ትወና ለፕሮፌሽናሎች ብቻ መተው እንደሌለበትና ማንም ሰው መተወን እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ይሁንና መሠረታዊ የትወና ስልቶችን ማወቅ እንደሚገባ ግን ያሠምርበታል፡፡ የቦል ተሳትፎአዊ ትያትር ሦስት ዐይነት መንገዶች አሉት፡፡

1. ምስላዊ ትያትር (Image Theatre)፡– ይህ ተዋናዮቹ ስለኅብረተሰቡና ስለአጠቃላይ ባህሉ ትክክል ናቸው፣ የሚሏቸውን ዕውነታዎች ካለንግግር በምስል ብቻ (አስፈላጊ ሲሆን አንዳንድ ቃላት እየተጠቀሙ) ለማውጣት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ልምምዶች ናቸው፡፤ በምስላዊ ትያትር የሚሳተፉ ተዋናዮች ስለኑሮአቸው ስለሚሰማቸው ስሜት፣ ስለገጠመኛቸው፣ ስለተጨቆኑበት ጉዳይ በቡድን ወይም በግል ምስል ይሠራሉ፡፡ ይህ ምስል አንድ ርእስ ተሰጥቶት (ከሌሎቹ ተሳታፊዎች) አስተያየት ይሰጥበታል፡፡ ትልቁ ቁም ነገር ከቋንቋ ይልቅ ምስል በውስጣችን የሚሰማንን ዕውነት መግለጹ ወይም «አንድ ምስል የሺ ቃላት ያህል ኃይል አለው» የሚባለው ሐቅ ነው፡፡ ምስል የቋንቋም ሆነ የባህል ግርዶሽን ይሰብራል፡፡ በዚህም ከአካባቢ ወጣ ብሎ ሀገር አቀፍ አልፎ ተርፎም ዓለም አቀፍ ጠባይ ሊይዝ ይችላል፡፡ ለሚቀጥሉት ሁለት የትያትር ዐይነቶች መሠረት በመጣልም ያገለግላል፡፡
2. ስውር ትያትር (Invisible Theatre)፡– ይህ ሕዝቡን ራሱ ሳያውቅ እርሱኑ በማሳተፍ የሚሠራ የትያትር ዐይነት ነው፡፡ ሕዝቡ ተመልካችም ተዋናይም (Spect-actors) የሚሆንበት ነው፡፡ ይሁንና ድርጊቱ ሲካሄድም ሆነ በኋላ «ዕውነተኛ ድርጊት» መሆኑን እንጂ ሕዝቡ ትያትር መሆኑን አያውቅም፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ ሲካሄድ የሚያያቸው ሰዎች ዕውነተኛ ሰዎች፣ ድርጊቱ ዕውነት፣ በድርጊቱ ላይ የሚታየው እንቅስቃሴ ሁሉ ዕውነት ሆኖ ስለሚያገኘው ነው፡፡

   የዚህ ዐይነት ትያትር የሚሠራው በተለመደው ቤተ ትያትር ወይም የትያትር ዝግጅት በሚካሄድበት ቦታ ሳይሆን ሕዝብ በብዛት በሚገኝበት ገበያ መንገድ ላይ፣ ፌርማታ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ በዛ ያሉ ተዋናዮች በአንድ ጭብጥ ላይ በመመርኮዝ ቀደም ሲል ልምምድ የደርጋሉ፡፡ እናም የወከሏቸውን ገፀባሕርያት መስለው ሕዝቡ ውስጥ ገብተው ይተውናሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ለዚህ ዐይነት ትያትር

---

[1] ቦል ጸሐፊና የትያትር ፅንሰ ሐሳብ ቀማሪ ነው፡፡ ትያትር ኦቭ ዘ ኦፕሬስድ የሚለው መጽሐፍ በ25 ቋንቋዎች ተተርጉሟል፡፡

የሚመረጠው ትዕይንት ማኅበረሰቡ በልማድ «መልካምና ትክክል» አድርጐ የሚወስዳቸውን የሕይወት እንቅስቃሴዎች «ማደፍረስ» ወይም በእነርሱ ላይ «ማመጽ» ነው:: የተወሰኑት ተዋንናዮች ድርጊቱን ተቃውመው ምላሽ ይሰጣሉ:: ሕዝቡ ሳያውቅ በክርክሩ መሳተፉ አይቀሬ ነው አንዱን ወገን ደግፎ ስለሆነም በስውር ትያትር ሕዝቡ ነገሮችን እንዲጠይቅ፣ እንዲከራከር መንገድ ይከፍታል:: በአንድ ወገን የሚሰጥ ሰበካ ስለሌለበት፣ በጋራ ውይይት የመማርን ባህል ያዳብራል:: ተመልካቾቹ በሚቀርቡት ጉዳዮች ላይ ከተዋናዮቹ በላይ ዕውቀት እንደሚኖራቸው ከመጀመሪያውም ግንዛቤ ይኖራል::

3. የ«ሸንጐ ትያትር» (Forum Theatre):– ይህ ደግሞ የአንድ ማኅበረሰብ (ኮሚኒቲ) አባል ነዋሪዎችና ተዋንናዮች የሚሳተፉበት ሲሆን፣ ለተመልካቹ የመተወን ዕድል ይሰጣል:: አንድን ችግር ያለመፍትሔው በመድረክ ማቅረብና «ተመልካቾቹ» (Spect-actors) የመፍትሔ ሐሳብ እንዲሰጡ ዕድል የሚሰጥ ነው:: ይህ ላቲን አሜሪካውያን የጭቆናቸውን ምንጭ የሚፈትሹበት ትያትር ነው:: በመድረክ ላይ የሚቀርቡት ገፀባኅርያት ሲጨቆኑና ሲረገጡ ያሳያል:: ተመልካቹ ገፀባሕርያቱ ከገቡበት ጭቆና የሚወጡበትን አማራጮች በመጠቆም ወይም ራሱ ወደመድረክ በመውጣትና የገፀባሕርያቱን ቦታ በመውሰድ መፍትሔ ነው የሚለውን ድርጊት ይተውናል:: ይሁንና የጨቋኙን ገፀባሕርያት የሚጫወቱት ተዋንያን ሌላ ደንቃራ ይፈጥራሉ:: እንደገና ሌላው ተመልካች ትያትሩን ያስቆምና የራሱን መፍትሔ ይሰጣል:: በአጠቃላይ በተዋንያኑና በተመልካቹ መካከል ያለ «ውድድር» ወይም «ክርክር» ነው:: ትያትራዊ «ክርክሩ» መሥመሩን እንዳይስት መድረኩን የሚመሩ «አጫዋቾች» (Jokers) አሉ:: በዚህ የሸንጐ ትያትር ውስጥ ለአንድ ችግር የተለያዩ መፍትሔዎች ይቀርባሉ:: ውጤቱ ታዲያ የልምድ፣ የዕውቀትና የብልሃት መናኸሪያ መድረክ መፍጠር ነው:: በአሁኑ ሰዓት የተለያየ ገጽታ በመያዝ በብዙ ሀገሮች ውስጥ በትምህርት ቤቶች፣ በፋብሪካዎች፣ በቀበሌዎች፣ የጐዳና ተዳዳሪዎች በሚረዱባቸው ድርጅቶች ወዘተ. እየተሠራ በራሳቸው ችግር ላይ ለውይይት ማነሣሣትና አማራጮችን እንዲፈልጉ ማድረግ በሌላ አነጋገር በራሳቸው ጉዳይ ራሳቸው «መሪ ተዋንያን» እንዲሆኑ ዕድል መስጠት ነው::

እስካሁን ጠቅለል ባለ መልክ የጠቃቀስናቸው የትያትር ዓይነቶች በዋነኛነት የሕዝቡን ባህላዊ ግንዛቤዎች እየተጠቀሙ ለሕዝብ ዕድገትና ወደፊት መራመድ የባሕርይና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ::

## 3. የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎች ለሥነ ሕዝብ ጠቀሜታ

መገናኛ ብዙኃን በሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ መልእክት ማስተላለፍ በመቻላቸው ጠቃሚነታቸውና ውጤታማነታቸው የሚያጠራጥር አይደለም:: የሕዝብ መገናኛ መሣሪያዎች የአንድ ሀገር የደም ሥር ከመሆናቸውም ሌላ የአንድን ኅብረተሰብ እድገትና ሥልጣኔ ከምንለካባቸው መሥፈርቶች ውስጥ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ:: ዛሬ የሰው ልጅ ከሥልጣኔው እድገት የተነሣ የመገናኛ እንቅፋቶችን በጥበቡ ውጤት ጥሶ፣ ከሚያውቀው አካባቢ ወደ እማያውቀው ለመድረስ ያደረገው ግሥጋሴ ዘመናዊ የመገናኛ መሣሪያዎችና የረቀቁ ዘዴዎችን ለማግኘት አስችሎታል:: የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች፣ በተለይም በኅትመት ጥበብ ከሚከናወኑት (ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ መጽሐፍ) ይልቅ በሬዲዮና በቴሌቪዥን አማካይነት የሚደረጉ ግንኙነቶች ቀድመው በመገስገስ ላይ በሚገኙበት በአሁኑ ወቅት፣ የቋንቋ የባህል፣ የኢኮኖሚና የመልክአምድር መሰናክሎችን ጥሰው ኅብረተሰቡን የሚያቀራርቡ በመሆናቸው፤ ማርሻል ማክሉሃን የተሰኘው የመገናኛ ብዙኃን ኤክስፐርት እንደሚለው «ዓለማችን ዛሬ የጠባብ መንደር ያህል ሆናለች»:: የእነዚህ ለዐይንና ለጆሮ የስሜት ሕዋሳቶቻችን ቅርብ የሆኑ መገናኛ ብዙኃን በዐይነትም ሆነ በጥራት መስፋፋት ከምንም ጊዜ በላይ የእይታ አድማሳችንን አስፍቶታል:: በትምህርትና በመገናኛ ብዙኃን መካከል ያለውን ሰንሰለት ይበለጥ አሳድጉታል::

የመረጃና የመልእክት ልውውጥ ማደግ፤ የሦስተኛውን ዓለም ሕዝቦች የአስተሳሰብ ግንዛቤ ለማዳበር ከመርዳቱም በላይ በተለይ በገጠር ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል የትምህርት ቤትን ያህል ዋጋ ያለው ነው፣ ለማለት ያስደፍራል:: የመገናኛ ብዙኃን ሚና በተለይ የትራንስፖርትና የመጓጓዣ እጥረት በሚታይባቸው መንደሮች፣ የገጠር ቀበሌዎችና የሠፈራ መንደሮች አስፈላጊነቱ እጅግ የጐላ ነው:: ይልቁንም በአሁኑ ጊዜ የአዳጊ ሀገሮች የሥነ ሕዝብ ባለሙያዎች መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም ማኅበራዊ ችግሮችን (የልማትን፣ የአባባቢን ብክለት፣ የግል ንፅህናን፣ የበሽታዎችን መስፋፋት፣ የጐልማሶችን ትምህርት፣ የሴቶችን መብትና ፍላጐት፣ የልጆች ምጣኔንና አስተዳደግ ወዘተ...) ለመቅረፍ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ::

በእነዚህ የመገናኛ ብዙኃን (ሬዲዮና ቴሌቪዥን) ለታዳሚዎች ከሚቀርቡት ዝግጅቶች መካከል የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎች ይገኙበታል:: በዚህም፤ ዕድሜ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ተደራስያንን ድራማ ለማየት ወደትያትር ቤት ከመሄድ ይልቅ የሚቀርብላቸውን የድራማ ዝግጅት በየቤታቸው ሆነው በሬዲዮና በቴሌቪዥን የመከታተል ዕድል አጐናጽፏቸዋል::

የትያትር ቤቶች ቁጥር በጣም ውሱን በሆነበትና፣ አብዛኛው ሕዝብ ቲያትር የማየት ዕድሉ እጅጉን በጠበባት ሀገራችን አዝናኝና አስተማሪ ድራማዎችን በማቅረቡ በኩል ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም። የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎች በእነዚህ የመገናኛ ብዙኃን ለሚቀርቡት ሌሎች ወቅታዊና ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ማጣፈጫ ቅመሞች ናቸው፣ ቢባል ከዕውነት መራቅ አይሆንም። ይህን ለማወቅ የተደራሲ ጥናት ማካሄድ ሳያስፈልግ ለሬዲዮና ለቴሌቪዥን ከሚላኩ የተደራስያን ደብዳቤዎችና የስልክ ጥሪ ብዛት ማረጋገጥ ይቻላል። በኢትዮጵያ ሬዲዮ በየሳምንቱ እሑድ ጠዋት የሚቀርበውን ተከታታይ የሬዲዮ ድራማ ፕሮግራም፣ በየሳምንቱ ቅዳሜ በወጣቶችና በመዝናኛ ፕሮግራም የሚቀርቡትን ድራማዎች፣ «በሕይወት ዙሪያ» በተሰኘው ሳምንታዊ ፕሮግራም የሚተላለፉትን ድራማዎችና በየሳምንቱ ረቡዕና እሑድ በ«120» ፕሮግራም የሚቀርቡትን የቴሌቪዥን ድራማዎች ተደራስያኑ ምን ያህል በጉጉት እንደሚጠብቋቸው የተገነዘብኩት እዚህ አዲስ አበባ ሆኜ ብቻ ሳይሆን ለሥራ ጉዳይ በየክፍለሀገሩ በተንቀሳቀስኩባቸው ወቅቶችም ጭምር ነው። ይህም መሆኑ ያለ ምክንያት አይደለም። ድራማ በባሕርዩ የሰው ልጅ የሳለፈውን የኑሮ ውጣ ውረድ፣ ያካበተውን የሕይወት ልምድ፣ ተስፋውንና ምኞቱን በገፀባሕርያት ንግግርና ድርጊት አማካይነት በማቅረት የተደራስዩን ስሜት ቆንጥጦ የመያዝ ዐቅሙ፤ ተደራሲው የቀረበለትን ድራማ ከራሱ የሕይወት ልምድም ሆነ፣ በቅርብ ከሚያውቀው ሌላ ሰው ገጠመኝ ጋር እያገናዘበ እየተዝናና ትምህርት የሚቀስምበት በመሆኑም ጭምር ነው። በመሆኑም ከደረቅ ዘገባና ሰበካ ይልቅ ድራማ ተመልካቹንም ሆነ አድማጩን የማሳወቅ፣ የማስተማር፣ የሚተላለፈውም መልእክት ውጤታማ እንዲሆን የማድረግ ብቃቱ ከፍተኛ ስለሆነ፤ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን ለሕዝብ ለማቅረብ ጠቃሚ የመገናኛ ዘዴ ነው።

በሁለቱ የመገናኛ ዘርፎች የሚቀርቡ ድራማዎችን ጠቃሚነት ባይካድም ድራማዎቹን በመጻፍ፣ በማዘጋጀት፣ በመተወን የሚሳተፉ ባለሙያዎች ኃላፊነት ግን ቀላል አይደለም። ስለሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይና ጭብጥ በሚገባ ማወቅ፣ ስለተደራሲው ማኅበረ ሰባዊ ዳራ በቂ ዕውቀት መጨበጥ፣ ስለሬዲዮና ቴሌቪዥን ድራማዎች የአጻጻፍ፣ የአዘገጃጀትና የመተወን ጥበባዊ ክሂሎቶችን ማዳበር በጣም አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን እያንዳንዳቸውን መተንተን በዚህች አነስተኛ የጥናት ወረቀት ስለሚያስቸግር ለግንዛቤ ያህል በመጠኑ እንቃኛቸው:-

## 3.1 ስለሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይና ጭብጥ መረዳት

በሥነ ሕዝብ ችግሮች ላይ ተመሥርተው የሚጻፉ ድራማዎች ትኩረታቸው ለአንድ ሀገር ሁለ ገብ ልማትና እድገት እንቅፋት በሆኑ ኋላ ቀርና ዘልማዳዊ አመለካከቶች፣ ባሕርዮችና ተግባሮች ላይ በመሆኑ፤ የእነዚህን ምንነትና በልማት ላይ የሚያደርሱትን

ተፅዕኖ በሚገባ ለማወቅ ጥናት ማድረግ ከደራሲው ይጠበቃል። ስለአንድ ሀገር የእድገት ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርበታል። ለመሆኑ ሕዝቡ በድህነት ይማቅቃል ወይ? የድህነቱ ምንጮች ምንድን ናቸው? እነዚህን ምንጮች ለመድፈንና ችግሩን ለመቅረፍ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ምንድ ነው? አበረታች ነው ወይስ የተሳሳተ አቅጣጫ የተከተለ? ሥራ አጥነትስ ምን ያህል አሳሳቢ ነው? በሴቶች ላይ የሚንፀባረቅ ኋላቀር አመለካት አለ? በምርቱ ሂደት ምን ያህል ተሳታፊ ናቸው? ሕዝቡ በመሠረተ ትምህርት፣ በጤና፣ በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት፣ በመኖሪያ ቤት፣ በብድር አገልግሎት ምን ያህል ተጠቃሚ ነው? ተጠቃሚ ካልሆነስ ለምን? የመሳሰሉትን፣ የማኅበራዊ ለውጥና ለአጠቃላይ ዕድገት ቁልፍ የሆኑ ጥያቄዎች መጠየቅና በዚህ ላይ የተጻፉ ጥናታዊ ወረቀቶችን ማገላበጥ በጣም ጠቃሚ ነው። የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ፖሊሲን ዓላማና ግቦች፣ የአፈጻጸማቸውንም መርሐ ግብሮች በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። እንዲህ ማድረግ ለተቀባዩ ክፍል (ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ) ትክክለኛ መረጃዎችን በድራማ በማስተላለፍ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ምርጫ እንዲያደርግ ዕድል መስጠት ነው። በሌላ አቅጣጫም ጥናቱ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳናስጨብጥና የማይሆን ተስፋና ምኞት በተደራሲዎቻችን ላይ እንዳንፈጥር ይረዳናል።

## 3.2 ስለተደራሲው ጻራ ማጥናት

የተደራሲን ልቦና በአግባቡ ለመጨበጥ የድራማ ደራስያን የመልእክቱን ተቀባዮች ፍላጐት፣ አስተሳሰብ፣ ልምድና ዝንባሌ በቅጡ ማጥናትና መመርመር ይገባቸዋል። ጥናቱ ውል ባለው ሁኔታ ከተካሄደ ከተደራሲ ጋር ያቀራርባቸዋል። የድራማ ተደራስያን የሚተላለፈው መልእክት ምኞታቸውን፣ ፍላጐታቸውን ብሎም ግባቸውን የሚመለከትና ከእነርሱ ስሜት የሚጣጣም ከሆነ በምንም ዓይነት በመገናኛ ብዙኃን ለሚቀርበው ድራማ ጆሮባቸውን ሊሰጡ አይችሉም። እናም መልዕክቱ የታለመለት ተደራሲ ጉዳዬ ብሎ ድራማችንን እንዲከታተል የእርሱን ውስጣዊ ፍላጐትና ዝንባሌ ከማጤን ውጭ አማራጭ የለም። ካለተደራሲ ባሕርይ ጥናት አንድ ፀሐፊ የመልዕክቱን ጠቃሚነት ብቻ አጢኖ መጀመር የለበትም። ስለተመልካች ባህርይ መረጃ መሰብሰብን በተመለከተ ካተሪንና ጃን ጆንሰን (1996) አራት ቴክኒኮችን ይጠቁማሉ። አንዱን ቴክኒክ ብቻ ነጥለን በመውሰድ የተሟላ መረጃ ማግኘቱ አስቸጋሪ ስለሚሆን እንደአመቺነቱ ቴክኒኮቹን ቀላቅለን መጠ ቀም ይኖርብናል።

3.2.1 ማሰላሰል (Cogitation):- የድራማ ደራስያን ጊዜ ወስደው ስለተደራስያን ማሰብና ማሰላሰል አለባቸው። ልክ ሩቅ ቦታ ላለ ለምንወደው ጓደኞችን ስንጽፍ እንደምናደርገው ቆም ብለን «ከእኔ ሕይወት ውስጥ የትኛው ይበልጥ ስሜት ይሰጠዋል? የትኛው

ያስቀዋል? በበለጠ ማወቅ የሚፈልገው ምንድን ነው ብሎ ራስን መጠየቅ አንዱ የተደራሲ ጥናት ማካሄጃ መንገድ ነው::

3.2.2 የቤተ መጻሕፍት ጥናት (LIbrary research):- የድራማ ደራስያን ከቤተ መጻሕፍትና ከዕለታዊ ጋዜጦችና መጽሔቶች ስለተደራስያን በርካታ ቁምነገሮችን ሊጨብጡ ይችላሉ:: በሥራ ላይ የተሠማሩ ሴቶች ያለባቸውን ችግር በተመለከተ፣ ድራማ ለመጻፍ የሚፈልግ ደራሲ በዚህ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ማገላበጡ በቂ መረጃ እንዲያገኝ ይረዳዋል:: በሴትኛ አዳሪዎችም ላይ ቢሆን ዝም ብሎ በዘፈቀደና በግምት ከመጻፍ በዚህ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ማየቱ ይጠቅማል::

3.2.3 መደበኛና ኢመደበኛ አጠቃላይ ጥናቶች ወይም ቅኝቶች (Formal and informal surveys):- ይህ ደግሞ ሳይንሳዊ መንገድ የተከተለና ከተለያዩ የተደራስያን አባላት በጥያቄ የሚሰበሰብ መረጃ ነው::

በኢመደበኛ አጠቃላይ የመረጃ ጥናት፣ ጸሐፊው ከዕለት ተዕለት ሕይወቱ ጋር በማቀናጀት ለተለያዩ የማኅበረሰቡን አባሎች ቃለመጠይቅ በማቅረብ መረጃ ይሰበስባል:: የተለያዩ ሰዎችን (በሥራም ሆነ በግል ሕይወታቸው) የአኗኗር ዘይቤ በቅርብ ሆኖ መመልከት ለጸሐፊው፣ ለአዘጋጁም ሆነ ለተዋናዩ ተጨማሪ ዕውቀት ያስጨብጣል:: ስለሕዝቡ ትውፊታዊ ሀብትና ታሪክ በማጥናትና በመመርመር ስለሥነ ልቡናዊ አመለካከቱም ሆነ የሕይወት ግንዛቤው መረዳት ይቻላል:: ይህን በተመለከተ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ /1988/ ስለሥነቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ ባቀረቡት ጥናት እንዲህ ብለው ነበር:-

> *የሰው ልጅ በያለበት አካባቢ ከጥንት ጀምሮ ላጋጠሙት ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት እየሞከረ ነው የኖረው.... ከጠቡና ከፍቅሩ፣ ከጦርነቱና ከሰላሙ፣ ከድሉና ከሽንፈቱ እያጠቀሰ የሕይወት ሥርዓት አበጅቷል:: ከዚህ የሕይወት ሥርዓት ጋር የተያያዘ የልማት እሳቤ፣ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊ ኑሮና የሒሳብ መለዋወጫ እቅድና ሥርዓት አዳብሯል:: /ገጽ 18-19/*

የሬዲዮና የቴሌቪዥን ድራማ ሙያተኞች ይህን «የሕይወት ሥርዓት «እና» የልማት እሳቤ» ከተረቶቻቸው፣ ከዘፈኖቻቸው፣ ከአፈ ታሪኮቻቸው፣ ከእንቆቅልሾችና ተረትና ምሣሌዎች ውስጥ መፈለግና ማግኘት አለባቸው:: በአጠቃላይ የሕዝቡ ማኅበራዊ ሕይወት በሚገለጽባቸው ቦታዎች፣ ማለትም በየገበያው፣ በየመንገዱ፣ በጠላ ቤትና በጠጅ ቤት፣ በየዕድሩ፣ በለቅሶ ቤትና በሠርግ ላይ ራሳቸውን በማሳተፍ ተደራሲዎቻቸውን

በውል ማጥናት አለባቸው:: በሌላ በኩልም በመደበኛ አጠቃላይ ጥናት ቴክኒክም ተደራሲውን የበለጠ ለመረዳት የሚጠቅሙ ጉዳዮች አሉ:: አንድ ዝግጅት ለተደራሲው ከቀረበ በኋላ የተደራሲውን ስሜት ለማወቅ የሚደረግ ጥናትና ተጨማሪ የድራማ ፕሮግራሞችን ለመጀመር በጋዜጠኞች የሚደረግ ጥናት ነው:: ሁለቱም የጥናት (መደበኛና ኢመደበኛ) ዓይነቶች፣ የድራማ ባለሙያዎች ስለተደራስያን የተሳሳተ ግምት ይዘው እንዳይነሡ ይረዳቸዋል:: ምናልባት በጸሐፊዎች በኩል አንድ አደጋ ቢኖር፣ ተደራሲ ሁሉ አንድ ዓይነት ነው፣ ብሎ መገመት ወይም እንደራሱ የሚያስቡ አድርጎ መገመቱ ነው:: ተደራስያን የተለያዩ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆናቸውንም ማጤን ያሻል::

3.2.4 ቡድንን ማጥናት ወይም በቡድን ላይ ያነጣጠረ ጥናት (Focus group survey):- የድራማ ደራሲው ተደራስያኑን በእምነት፣ በሙያ፣ በዕውቀት ደረጃ፣ በፆታ ወይም በዕድሜ በመለየት ከዚያ ውስጥ ከ7-10 ከሚሆኑ የቡድኑ አባላት ጋር በመወያየት የሚያካሂድባቸው ጥናት ይመለከታል:: ይህም ጥልቀት ያለው መረጃ ለማግኘት ጠቀሜታው የትየለሌ ነው:: ደራሲው ተግባቢና እነርሱን መስሎ መቅረብ ከቻለ ወትሮ ሊገልጹት የማይፈልጉትን ድብቅ ሕይወታቸውን የመረዳት ዕድል ይኖረዋል::

የመገናኛ ብዙኃን መልእክት የሚሠራጭለት በሚሊዮን የሚቆጠር የገጠርና የከተማ ብዙኃን ሕዝብ በሙያ ዘርፍና በተለያዩ ስታትስቲካዊ ቀመሮች (ፆታ፣ ዕድሜ፣ የዕውቀት ደረጃ፣ ወንደላጤ፣ ባለትዳር ወዘተ.) የተለያየ ነው:: ተደራሲን በእንዲህ ዓይነት ስብጥር ከፋፍሎ ማጥናት ደራስያንን ተፈላጊውን መልእክት ለታለመለት ተደራሲ እንዲያደርሱ ይረዳቸዋል:: ድራማቸው ለየትኛው ቡድን መሆኑን ለማወቅ አቋራጩ መንገድ ርእሰ ጉዳዮን በግልጽ ካስቀመጡ በኋላ «ማንን ይመለከታል?» ብሎ መጠየቅና ለጉዳዩ ቀረቤታ ያላቸውን ማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች በዝርዝር ማስቀመጥ ነው:: በምንሠራው ሥራ ሁሉ ተደራሲ ትልቅ ግምት ሊሰጠው ይገባል:: እናም ድራማዎቻችንን ስንጽፍም ሆነ ስናዘጋጅ በደመ ነፍስና በግምት ከመሥራት ይልቅ፣ ሙያዊና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ብይን በመስጠት የተደራሲን ቀልብና አትኩሮት እንድናገኝ ያስችለናል:: ደራሲው ከጊዜው ጋር ለመራመድም ሆነ (በየጊዜው በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚከሠቱትን ለውጦች ለማጤን) ቀድሞ ለመገኘት ሁልጊዜ ንቁና ጠያቂ፣ ገጠመኞቹን ባገኘው አጋጣሚ ለማስፋት ጥረት የሚያደርግ በዐውደጥናቶችና በሲምፖዚየሞች ላይ በመካፈል፣ ቲያትሮችንና ሲኒማዎችን በመመልከት፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር መዋልን ወዘተ. እና የማንበብ ፍቅርን ባህሉ ያደረገ መሆን አለበት::

## 3.3 የሬዲዮና ቴሌቪዥን ድራማ የአቀራረብ ቴክኒኮች

የቴሌቪዥንን፣ የሬዲዮንና የመድረክ ድራማዎችን ከሚያመሳስላቸው በርካታ መንገዶች አንዱ ሁሉም ፈጠራን መነሻ በማድረግ በገሀዱ ዓለም የሚታየውን የሰው ልጅ ሕይወት የሚቀጽሉ ወይም የሚከትቡና ለተመልካቹ አልያም ለአድማጬ የተለያየ የሕይወት ገጽታን በማቅረብ ስሜቱን የሚኮረኩሩ መሆናቸው ነው:: ድራማዎቹ የሚያቀርቡት ጭብጥ ወይም መልእክት ተደራሲው ከሚያየውና ከሚሰማው ነገር ተነሥቶ፣ ስለአለበት ሕይወት፣ ስለአካባቢውና ስለማኅበረሰቡ እንዲያስብና እንዲመራመር የሚጋብዙ ናቸው:: በተውኔት አወቃቀር ደረጃም ሮበርት ኤል ሂላርድ (1997) እንዳስቀመጠው «የተውኔት አጻጻፍ ደንቦችና መመሪያዎች ዓለም አቀፍ ናቸው:: ደንቦቹ ለመድረክ፣ ለፊልም፣ ለቴሌቪዥንም ሆነ ለሬዲዮ ተውኔት መዋቅር እኩል ያገለግላሉ »(ገጽ 384)

የቴሌቪዥንም ሆነ የሬዲዮ ድራማ ዕውቂያ፣ ግጭት፣ ትውስብ፣ ጡዘት፣ እናም አስፈላጊ መስሎ ከታየ፣ ልቀት ይኖራቸዋል:: ሁለቱም የተውኔት መሠረታዊ አላባውያን የሆኑትን መቼት፣ ገጸባሕርይ፣ ቃለ ምልልስና ሴራ ይይዛሉ:: የሚለያዩቸው የሚቀርቡበት የመገናኛ ዘዴ ባሕርይና የአቀራረብ መንገድ ነው::

### 3.3.1 የሬዲዮ ድራማ

- በሬዲዮ ድራማ ታሪክ አመራረጥ ዓላማ (purpose) እና አታሪኩ ለተደራሲው ያለው ቅርበት (familiarity) ወሳኝ ነጥቦች ናቸው:: ዓላማው የተለያየ የኅብረሰብ ክፍል ወገን ለሆኑት አድማጮች የሚስማማ ነገር ማቅረብ ሲሆን ቅርበቱ ደግሞ ኅብረተሰቡ ሊቀበለው የሚችለውን ነገር መንገር ነው::

- የሬዲዮ ድራማ በድምፅ ለአድማጭ የሚቀርብ ታሪክ እንደ ቴሌቪዥንና እንደ መድረክ ተደራስያን ለሚታዩ ድርጊቶች የታደሉ አይደሉም:: በመሆኑም ታሪኩ የተመጠነ፣ የማያሰለችና የተደራስያኑን ስሜት ቆንጥጦ የሚይዝ መሆን አለበት::

- ገጸ ባሕርያቱ ከስድስት መብለጥ የለባቸውም:: አድማጩ የሚለያቸው በድምፅ ብቻ ስለሆነ ገጸባሕርያቱ ከበዙ መደናገርን ይፈጥራል:: ገጸባሕርያቱ በአካላዊ፣ በማኅበራዊ፣ በሥነልቡናዊና እንዲሁም በሞራላዊ የአቀራረጽ ደረጃዎች ፍጹም የተለያዩ ሆነው መገኘት አለባቸው:: ሁሉም የየራሳቸው የአነጋገር፣ የቃላት አገላለጽ፣ የድምፅ አወጣጥና ቃና እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: ተውኔቱ

አድማጭን ሳለማደናገር ትኩረት ሰጥቶ ማጠንጠን ያለበት በዋናው ገፀ ባሕርይ ላይ ነው።

- ቃለ ተውኔት የሬዲዮ ድራማ የመሠረት ድንጋይ ነው። በሬዲዮ ድራማ ሁሉን ነገር የምናስተላልፈው በቃለ ተውኔት ነው። በመሆኑም ደራሲው በተደራሲው ምናብ ውስጥ ምስል የሚጭሩ፣ በመሳጭና ገላጭ ቃላት መጠቀም አለበት። ረዝሞ እንዳያሰለች ቁጥብና ግልጽ መሆን አለበት። ቃለ ተውኔቱ ለመቼቱ መታወቅ፣ ለተውኔቱ ሴራ ፈጣን እድገት፣ ለገጸባሕርያቱ ግጭትና ለአጠቃላይ ድባቡ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ የሬዲዮ ድራማ ደራስያን በዚህ በኩል ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

- መቼት በሬዲዮ ተውኔት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ አለው። ይሁንና የሬዲዮ ተውኔት እንደመድረክ ተውኔት ለጊዜና ለቦታ የሚጨነቅ አይደለም። በግብአተ ድምፅ አማካይነት ከአንዱ ወደ አንዱ በቀላሉ መሸጋገር ይቻላል። ይህም ስለተባለ ጊዜና ቦታ ያለቅጥ በዝተው አድማጪን ማደናገር የለባቸውም። መቼቱን ለመግለጽ በተራኪ፣ በቃለ ተውኔት፣ በግብአተ ድምፅና በሙዚቃ መጠቀም ይቻላል።

- ትረካ፣ ሙዚቃና ግብአተ ድምፅ በአዘጋጁ የሚታቀዱና የሚካተቱ በመሆናቸው አጠቃቀማቸው በተቻለ መጠን ግልጽ፣ ተስማሚና የትዕይንቱን ድባብ የሚገልጹ መሆን አለባቸው።

- በትወና በኩል ተዋናዩ ጥሩ የድምፅ አወጣጥ ያለውና ድምፁን እንደልብ ለመቀያየር

የሚችል ቢሆን ይመረጣል። በቀረጻ ጊዜ ግብአተ ድምፅ ጠብቆ በመናገር፣ ባሕሪ ውስጥ ገብቶ በመናገር፣ የፋታ አወሳሰድ፣ ድምጽን እንደአስፈላጊነቱ ከፍና ዝቅ በማድረግ አተዋወን የተካነ መሆን አለበት።

3.3.2 የቴሌቪዥን ድራማ

- በታሪክ አመራረጥና በሴራ አገነባብ ልክ የሬዲዮ ድራማን ዓይነት ባሕርይ የያዘ ነው። ዓላማና ለተደራሽ ቅርበት ተፈላጊ ነው።

- የቴሌቪዥን ድራማ ጸሐፊ ታሪኩን ሲያዋቅርና ቃለ ተውኔት ሲጽፍ በዐይነ ኅሊናው እንዴት ሁለቱ በካሜራ ወደተንቀሳቃሽ ምስል እንደሚለወጡ ማየት አለበት የቴሌቪዥን ድራማ የምስል፣ የድምፅና የብርሃን ቅንብር ውጤት ነውና።
- የቴሌቪዥን ድራማ ለሚታዩ ድርጊቶች (Visual action) የታደለ ስለሆነ እንደሬዲዮና እንደመድረክ ብዙ ቃለ ተውኔት አያሻውም። በምስልና በእንቅስቃሴ መግለጽ ሳይቻል ሲቀር፤ ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ ቢባል ቃበለ ተውኔት መጠ ቀም ግድ ይሆናል።
- ቋንቋው ፍልስፍና ያልበዛበት፣ ከባድ ቃላትና ከሙያ ጋር በተያያዙ አስቸጋሪ ቃላት መጠቀም ተመልካችን ማደናገርና በጥሞና እንዳይከታተሉ ማድረግ ነው። የተምሳሌታዊ አባባሎችና አገላለጾች መታከል ለድራማው ቋንቋው ውበት ይሰዋል።
- በሙዚቃም ሆነ የንግግር የድምጽ አጠቃቀም ወይም ግብአተ ድምፆች ለድራማው ውጤታማነት ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው።
- በቴሌቪዥን ድራማ ጊዜ ምስል ቀረፃዎች አሰልቺ እንዳይሆኑ ከተወሰኑ ሰኮንዶች (8 – 10) ሳይበልጡ ቢቀያየሩ ጥሩ ነው። የምስል ቀረፃ የሚቀያየረው ያደረጉት ለተመልከቹ ከተለያየ ማዕዘን የማየት ነፃነት ለመስጠት፣ ስሜትን አጥብቆ ለመያዝ፣ ምስልን በማነፃፀር ድራማዊ ሞገዶችን (effects) ለመፍጠር ነው።
- መቼቱን ለተመልካች ለማስተዋወቅ በረዥም እይታ (Long shot) እንጠቀማለን። ከዚያ በተረፈ ግን የቴሌቪዥን መስኮት (ስክሪን) ጠባብ በመሆኑና ተዋናዮቹ ከተመልካች ጋር የበለጠ ቀረቤታ እንዲኖራቸው በብዛት የቅርብ እይታ (Close up) እና የመካከለኛ እይታ (Medium shot) ቀረፃን እንጠቀማለን። ሌሎቹንም ቀረፃዎች ከጐን ወደጐን (Panning)፣ ወደላይና ወደታች (Tilting)፣ ወደተዋናዩ በመጠጋትና በመራቅ (Dollying, Tracking) ስልቶች በመጠቀም የተመልካቹን አትኩሮት መሳብ፣ ማዝናናት፣ የሚጠበቁ ድርጊቶችን አስወግዶ ግርምትን ለመፍጠር፣ ተመሳሳይ እይታዎችን ለማስቀረት እንችላለን።
- የብርሃን፣ የገጸ–ቅብ ሁኔታ መታሰብ አለበት። ገጸ–ቅብ ከተጠቀምን በጣም የማያስታውቅ ሊሆን ይገባል። ተዋናዮችም የተጋነነ አተዋወን ትተው የዕውነተኛ ሕይወትን እንቅስቃሴ ተከትለው ሊሠሩ ይገባል።

ለማጠቃለል፣ የሥነ ሕዝብ ችግሮችን ለመቅረፍ በተከታታይ የሚቀርቡ ድራማዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው። የሕዝብን ልማዳዊ አመለካከት ለመቀየርም ሆነ ዘላቂ የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት የምንችለው በተለያዩ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ቀጣይነትና ዘላቂነት ያለው ሥራ መሥራት ሲቻል ነው። ከስንት አንድ ጊዜ ብቅ የሚሉ ድራማዎች ብዙም ውጤት አያስገኙልንም። ሌላው፣ በድራማዎቻችን ውስጥ የሕዝቡን ትውፊታዊ ሀብቶች (ዘፈኑን፣

ተረቱን፣ ተረትና ምሳሌውን) በማስገባት የተደራሲውን ሥነ ልቦና ለመያዝ ጥረት ማድረግ አለብን። ሃገራችን የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች ሀገር እንደመሆኗ ሕዝቡም እንደየእምነቱ ለምኞቱ ምሉዕነት፣ ለሕልሙ ተፈቺነት፣ ለፍላጐቱ ስኬታማነት በሀይማኖቱ የታዘዘውን ያደርጋል። ፈጽም፣ የተባለውን ይፈጽማል። የተወገዙትን፣ የተኮነኑትን ድርጊቶች ያወቅግዛል። ይኮንናል። እንግዲህ ሀይማኖት በአንድ ማኅበረሰብ ባህል ላይ ያለው ተጽእኖ ጠንካራ ስለሆነ በተለያዩ ያገራችን ሃይማኖቶች ስለልጆች ብዛት፣ ስለቤተሰብ ስፋትና ስለሴቶች ሁኔታ ያለውን አመለካከት እያጠናን ገጸባሕርዮቻችንን ስንቀርጽ ከተለያዩ ሃይማኖቶች የተወከሉ ቢሆኑና ከላይ የተጠቀሱትን አመለካከቶች ደካማና ጠንካራ ጐኖቻቸውን እያነሡ ቢፋጩበት የተደራሲውን አመለካከትና ግንዛቤ ማስፋት ይሆናል። በቤተሰብ ምጣኔና ዕቅድ ላይም ሆነ ሴቶችን በልጅነታቸው ለጋብቻ መስጠት በኩል በአብዛኛው ወሳኙ (ወላጅ/አሳዳጊ) ወንድ ስለሆነ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በወንዱ በኩል ሊኖር ለሚገባው የአመለካከትና የባሕርይ ለውጥ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

# ዋቢ መጻሕፍቶች


ፍቃደ አዘዘ፣ የሥነ ቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ በኢትዮጵያ፣ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለስምንተኛው ሴሚናር የቀረበ፤ ታኅሣሥ 10–11፣ 1988

Grebenik, E & AL. (ed.) Population Studies: A Journal of demography. July 1988 V. 42 No. 2

Hillard, L. Robert. 1997. Writing for Television and Radio. 6th edition. Wadsworth Publishing Company

Macbride, Sean (ed.). 1980. Many Voices, one World. The Camelot Press Ltd.

Mcadams, C. Katherine & Jan Johnson. 1996. Reaching Audiences. Boston: Allyn & Bacon.

Mlama, P. Munando. 1991. Culture and Development: The Popular Theatre Approach in Africa. Nordiska Afrikain Stitutet, Uppsala.

National Workshop on Integrating Population and Development Planning (IPDP). 5-7 May 1994 Workshop proceedings.

Nwunel, E. Onuora (ed.). 1985. Mass Communication in Nigeria. Fourth Dimension Publishers.

Obera, A.S. 1993. Population Growth, Employment & Poverty in the third-world. Mega cities. St. Martine's Press.

Plotrow, T. Phyllis & Al. 1997. Health Communications: Lessons from Family Planning and Reproductive Health. London; John Hopkins School of Public Health.

# ኪነ ጥበብና ማኅበራዊ ጠቀሜታው

በልጅወንድሜ ሳዕከማርያም
ሀበሻ ቴአትርና ሙዚቃ ኢንተርፕራይዝ

## መግቢያ

የሰው ልጅ በነባራዊ ዓለም በተክለሰውነት ምልዓት ከተከሰተ ጀምሮ ፍላጎቱን ለማርካትና መንፈሱን በሃሴት ለማትነን የሚያደርጋቸው ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች በማኅበራዊ ሕይወቱ እየጎሉ፣ እየገዘፉ እና የራሳቸውን ስልት ይዘው በመፍሰስ ዛሬ የደረሰበት ድረስ እያንሳፈፉ ያመጡት ባለውለታው የመሆናቸውን ሐቅ ወደኋላ አርቆ ከማየት ባሻገር ያን ያህልም ማመሳጠር የሚሻው አይደለም:: ኑሮውን እየዘወሩ በችግርና በደስታ እያላተሙ የሚንጡትን አጋጣሚዎች የሚገልጽባቸውና ለመፍትሔ ውልድ የሚበቃበት ጥበባዊ ትውፊቶች ሳይንሳዊ ቅርጽ አግኝተው በሙያው ሥርዓት ከመበጃጀታቸው በስተቀር ካለመኖር ወደመኖር የመጡ እንግዶቹ አይደሉም ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ስለዚህም ነው ጥበብ ለሰው ልጅ ማኅበራዊ ሕይወት በየመስኩ ልቆ መገኘት ተፈጥሮአዊ መሣሪያው በመሆን በጊዜና አጋጣሚዎች ለተከሰቱ እውነቶች የተገለገለበት መሆኑን አስረግጠን የምንናገረው:: በዚህ መሠረት በተለይ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የዕድገት ደረጃችን ጨቅላ ለሆንነው ኢትዮጵያውያን ጥበብ ማለት ቅንጦት አይለም፤ ለቁሳዊና ለማኅበራዊ ሕይወታችን ፈውስ በመንፈሳዊ ፍቅር የተጎዳኘንው ቱፈጥሮአዊ ፅሴት ነው:: ከዚህ እውነታ በመነሳት ኪነጥበብ ዛሬስ ለተከሰቱ ማኅበራዊ ችግሮቻችን መወገድ ምን አስተዋጽኦ አበርክቷል ምንስ እያበረከተ ነው በሚለው አነጋጋሪ ጉዳይ ሀሳቤን ለመሰንዘር እሞክራለሁ:: በዚህ ዙሪያ የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመቃኘት በርካታ ሰነዶችን አገላብጦ ሰፋ ያለ ቅኝት ማድረጉ አስፈላጊ እንደነበረ ባያጠያይቅም በዚህ ፀውደ ጥናት ላይ ግን ብዙም ወደኋላ ባልራቀ፣ ለጆሮአችንና ለዕይታችን ባዕዳን ባልሆኑ እውነቶች ዙሪያ መታጠሩን መርጬዋለሁ:: ምክንያቱም:-

1. በሥነ ሕዝብ፣ በዘመናችን አስከፊ ጉዳት እያደረሰ በሚገኘው ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፣ በሴቶች ፆታዊ በደሎች፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና ሌሎችም ማኅበራዊ ችግሮቻችን ዙሪያ ኪነጥበብ ልታበረክት በምትችለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ትኩረታችንን ለማቅናት፣

2. ሀበሻ የቴአትርና ሙዚቃ ኢንተርፕራይዝ ማኅበራዊ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ ኪነጥበብን መሣሪያ በማድረግ ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች ከተሞክሮአችን ለማካፈል በፀውደ ጥናቱ አዘጋጆች ስተጠቆምኩ ነው::

በዚህ መሠረት በሚቀጥሉት ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ በማቀርባቸው ነጥቦች ላይ አፅንዖት እንዲሰጣቸው በሚደጋገሙ ሀሳቦች ቅር እንዳትሰኙ ከወዲሁ አሳስባለሁ::

## ዐበይት ማህበራዊ ችግሮቻችን ምንድናቸው?

- ከጤና ችግርነቱ ባሻገር ማህበራዊ ቀውስ እየፈጠረብን ያለው የኤች አይቪ ኤድስ ጠንቅ ለበርካታ ዜጎች በተለይም አምራች ለሆነው የሕበረተሰብ ክፍል እልቂትና ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሕፃናት ወላጅ አልባ ማድረጉ፣

- በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሳቢያ የሚደርሱ አካላዊና ሥነልቡናዊ ችግሮች፣

- ስለሴቶች ባለን ኋላቀር አመለካከት በሴቶች የሚደርሱ ፆታዊ በደሎች መባባስ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያችንና በማህበራዊ ዕድገታችን እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ፣በተለይም የሴቶች የሥራ ጫና፣የጤናና የትምህርት ዕድል መነፈግ፣ በባህላዊና ወግ ልማዶች መታፈን፣ መገለል እና የሕፃናት ተገዶ መደፈር፣

በሥነሕዝብ ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች፡-

- የቤተሰብ ምጣኔ እና የሥነ ተዋልዶ ትምሕርት በበቂ ሁኔታ አለመሰጠት፣

- የጤና ተቋማት ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር የተመጣጠነ ሆኖ አለመገኘትና በሕፃናትና በሴቶች ላይ ያለው የሕመምና የሞት መጠን ከፍተኛ ከሚባልባቸው አገሮች ውስጥ መገኘታችን፣

- የትምህርት ተቋማት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት የዜጎችን በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ውስን ማድረግ፣

- የሕፃናትና የአረጋውያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅምን መገንባትና መንከባከብ አለመቻል፣

- በአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ ችግር የሚከሰቱ የጎርፍ፣ የድርቅና የአፈር መሸርሸር አደጋ፣

- የሥራ አጥ ቁጥር ንሮ መታየትና በዚህም ሳቢያ በተለይ ወጣቶች በአደገኛ ዕፅ ሱስ የመበከል እና ለወጣት አጥፊነት መገፋፋት፣

- እጅግ እየጨመረ በመጣው የሕዝብ ቁጥር እና ዝቅተኛ በሆነው የኢኮኖሚ ምርታማነት መካከል ያለው ልዩነት መስፋት፣

• በገጠርና በከተሞች መካከል ያልተመጣጠነ ዕድገት በመኖሩ የተነሳ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣው ከገጠር ወደ ከተማ የሕዝቦች ፍልሰት፣

• የጎዳና ተዳዳሪ፣ ለምኖ አዳሪ እና ዝሙት ተዳዳሪዎች ቁጥር መጨመር ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው::

ምንም እንኳ በማህበራዊ ችግርነታቸው የተገለፁት በሙያ መስኩ ምሁራን በቂ ትንታኔ ቢሰጥባቸው የሚገባ ቢሆንም የችግሮቹ አንዱ ከአንዱ የመሰናሰል ሁኔታ ችግሩን ምን ያህል ከቁጥጥራችን ውጪ ሊያደርገው እንደሚችል አይተን ኪነጥበብን መሣሪያ በማድረግ እንደምን ልንቋቋመው እንደሚገባ ለማነሳቸው ነጥቦች ማጠናከሪያ ነውና ጥቂት ብዬ ወደተመደንኩበት ርዕስ ጉዳይ እገሰግሳለሁ::

ስለኤድስ ስናነሳ በዋነኝነት ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነትን እንደ ዐቢይ ምክንያት እንጠቅሳለን፣ በእርግጥም የሴቶችና የህፃናት መብት በማይጠበቅበት ሁኔታ ከሚፈጠሩት ፆታዊ በደሎች በዋነኝነት የሚጠቀሰው በሕፃናትና ሴቶች ላይ የሚፈጸም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው:: በዚህም የተነሳ ለአላስፈላጊ እርግዝና፣ ዝሙት ተዳዳሪነት፣ ጎዳና ተዳዳሪነት እና ብሎም የኤድስ ሰለባ ይሆናሉ፣በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም ቢሆን ግንባር ቀደም ተጠቂዎቹ ሴቶች በመሆናቸው ከላይ ላነሳናቸው ችግሮች ይዳረጋሉ:: የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት አለመስፋፋታቸውና ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ጋር አለመጣጣም በተለይም የገጠሮችና የከተሞች ዕድገት የተራራቀ መሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ለሕዝቦች ፍልሰት ምክንያት ይሆናል:: ይህም በተለይ በሴቶች ላይ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናን ስለሚፈጥር ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች እንዲሰማሩ፣ ለዝሙትና ጎዳና ተዳዳሪነት ችግር ይጋለጣሉ፤ በዚህ የተነሳ ለተለያዩ በሽታዎችና በተለይም ለኤድስ ይዳረጋሉ::

ከላይ ጥቂቶቹን ሰንጥረን በማውጣት እንዳየነው አንደኛው ችግር ሌላውን ችግር እየወለደ አንዱ በአንዱ እየተደገፈ ለመፍትሄ ውልድ እንዳንበቃ ችግሮቹን በማወሳሰብ ይበልጥ በማህበራዊ ጠንቅ ተጠቂ ያደርገናል:: እንደአገራችን አባባል "ዘጠኝ መስኮቶች ያለው ቤት ቢኖረንና ስምንቱን ዘግተን አንዱን ብንረሳ እነሆ በሌባ ከመዘረፍ እንድናለን?" የሚለውን ብሂል ያስታውሰኛል::እንደዚሁ ከላይ የዘረዘርናቸው ችግሮች ሁሉ ካለተወገዱና ለዚህም ጠንክረን ካልሠራን ባንዱ ክፍተት የገባው ችግር ሌላውን ያናጋብናል::

## 3. የማህበራዊ ችግሮቻችን መንስዔ

የሰው ልጅ ማህበራዊ ሕይወቱ ደርጅቶ፣ በዙሪያ ገባ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱ ተሳክቶለት በግዘፈ - ፍጡርነቱ ልቆ አካባቢውን ለመቆጣጠር በሚያስችለው ብቃት የመገኘቱ ዕውነት ትናንትን ቅጠል አገልድሞ ፍራፍሬ እየለቀመ ከእንስሳት እየተባረረ ሆዱን እየሞላ በዕለታዊ ኑሮ ከመባተል ተነስቶ በሥልጣኔና በጥበብ እየረቀቀ ዛሬ ከደረሰበት ለመድረስ የቻለ ታላቅ ፍጡርነቱ ሕያው ምስክር ነው። ሌሎች ፍጥረታት በራሳቸው የዕድገትና የለውጥ ስሌት እየሰሉ በአዳዲስ ግብዓቶች የመለዋወጣቸው ምስጢር የሰውን ልጅ ነገሮች ሁሉ ከዕይታው ውጪ እና ከመቆጣጠር አቅሙ እንዳይዘሉ ለማድረግ ባለው ጽኑ ፍላጎት ይበልጥ በዕውቀት እየረቀቀ፣ በጥበብ እየመጠቀና በብልጠት የመብለጥ ክሂሎቱ ሽቅብ እንዲገሰግስ ምክንያት ሆኖታል። ስለዚህ በማህበራዊ ጉዳይ እንቅስቃሴው የአርቆ ማሰብ፣ ሁኔታዎችን በአስተውሎት የመመርመርና አካባቢውን አጉርጦ የማየት ንቃትን እንዲያዳብር አስችሎታል።

ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደጊዜ የአዳዲስ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ድንገተኛና አደገኛ አመጣጥና የሁኔታዎች ቶሎ ቶሎ መለዋወጥ፤ ለመለዋወጡም በሰው ልጅ በራሱ የአሳዋቂ እርምጃዎቹ መደገፍ ነገሮችን ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ብቃቱንና አቅሙን እንደፈታተኑት፣ ለችግርና ለአደጋ እንዲጋለጥ ዳርገውታል።

ሰዎች ባላቸው ተፈጥሮአዊ ብቃት እርስ በእርስ ተቻችለው እና ከተፈጥሮ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት በሥርዓት ሊኖሩ እንደሚገባ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ይመክራሉ። በሁሉም ወገን በስርዓት የመኖሩ ማህበራዊ ዑደት ሲፋለስ በማንነታችን እና ለመማንታችን የደረጁ ማህበራዊ ዕሴቶች ይፈራርሳሉ። አጉርጦ ባሻገር የሚያየው ዐይነ-ህሊናችን ባለማመዛዘን፣ ባለማስተዋልና በአለማወቅ ግርዶሽ ይከለላል፣ ስለራሳችንና ስለዐለማችን ያለን ግንዛቤ ይጠ ባል፣ ነገሮችን መልክ ለማስያዝ አቅማችን ይሰንፋል፣ የማህበራዊ ግንኙነት ዕሳቤያችን ይዘበራረቃል፣ ሰው በሰውነቱ ተወስኖ ከመኖር አምልጦ በአውሬነቱ ይመርናል።

ዛሬ በማህበራዊ ጠንቅነታቸው የምናውቃቸው ችግሮቻችን እየከፉና እየተባባሱ ለከፍተኛ ጉዳት የዳረጉን፣ ችግር በእኛነታችን ይሰለጥን ዘንድ የቻለው ከአውሬነታችን ወጥተን በሕገ አዕምሮና ሕገልቦና ተፈጥሮአችን ቆም ብሎ በማሰብ በራሳችን ላይ የመወሰን አቅም በማጣታችን አይደል? አነጋጋሪው ቁም ነገርም ይኸው ይመስለኛል። ሁላችንም ዙሪያችንን ከበው የሚፈታተኑንን ማህበራዊ ጠንቆች እናውቃቸዋለን። ስለዚህ ዛሬ ችግራችን ምንድነው ሳይሆን ምን መሆናቸውን የምናውቃቸው እነኚህ ችግሮቻችንን በመግታት የማህበራዊ ኑሮ

ዕድገታችንን እንደምን እንከባከበው ነው የሚያነጋገረን፣ ያጣነውን አቅም እንደምን እንገንባ? እንደምንስ በራሳችን ላይ የባህርይ ለውጥ እናምጣ? ነው ፍሬ ነገሩ።

ስለዚህ ሰፊ ግንዛቤና ዕይታ በሚያስፈልገው የማህበራዊ ጉዳዮቻችን ዙሪያ የሚጠበቅብንን ሁሉ ለማበርከት ስንነሳ አልሰሩም ወይም አልተናገሩም እንዳንባል ያህል የምንሰነዝራቸው መልዕክቶች ስንኩል ሆነው ሌላውን እንዳያስናክሉ፣ ሰንፈው እንዳያሰንፉ፣ ባላዋቂነታቸው እንዳያታልሉ ጥንቃቄ ልንወስድ ይገባል። መልዕክቶቻችን በቁም ነገር ደርጅተው በጊዜ፣ በቦታ እና በተመልካቾቻችን ወይም አድማጫችን አቅም ሊወሰኑና ተገቢ መልዕክት የሚያስተላልፉ መሆን ይገባቸዋል። ለምሳሌ አብሮ ስለመኖርና በፍቅር ጥሩ ግንኙነት ስለመመስረት ማህበራዊ ግንኙነት ልጆቻችንን ስናስተምራቸው እንዴት፣ ለምን፣ከማን እና ምን ዓይነት ጤናማ ግንኙነት ማዳበር እንደሚገባቸው በጥልቅ የማስረዳት ሀላፊነት ይጠበቅብናል። አሊያ ባለአስፈላጊ ግንኙነት ከማንም እንዳይገጥሙና አልፎ አልፎም ከተቃራኒ ፆታ ጋር በሚመሰርቱት ግንኙነት ለወሲብ እንዳይገፋፉ ይህም የሚያደርሰውን ጉዳትና ጥቅም ለይተው እንዲያውቁ ማስረዳት አለብን። እግራችንን አነባብረን በኩራት ሳሎናችን ውስጥ ተቀምጠን "ና ማሙሽ ሂድና እናትህን እስካሁን ምናባሽ እየሠራሽ ነበር ቶሎ ራት አቅርቢ በላት" በማለት ልጃችንን ስንልክ በአንድ ቀን ራት መዘዝ ልጃችንን ምን እያስተማርነው እንደሆነ እና ዛሬ በአዕምሮው የተከልናት ዘር እየተመዘዘች ስነምግባሩን የምትፈታተን እሾክ ልትሆንበት እንደምትችል የምናስተውል ስንቶቻችን ነን? ወይም ውሎአችንን በቁጭት በምሬትና በዘለፋ "ሰራሁለት - አረኩለት" እያልን ከጓደኛ ወይም ከሚስት ጋር ልጆች በተሰበሰቡበት ስሜታችንን ስንገልፅ በልጆቻችን የምናሳድረው ተፅዕኖ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚገባን ስንቶቻችን ነን? -ውሎ አድሮስ ልጅ በአካል እየጠነከረ በዕድሜ እየገሰገሰ ሂዶ ቀድሞ ባሳደርንበት ተፅዕኖ በሚያደርጋቸው አጓጉል ድርጊቶች የማንራገምስ - ለልጅ ባለመታደላችን የማናማርር - ማንኛችን እንሆን?

ልጆቻችን ፊት እንደአልባሌ የምንወረውራቸው ቀልዱ-ቀልዶች፣ አፈታሪኮች፣ ተረቶችና ሌሎችም ቀስ በቀስ በማንነታቸው እየሰረፀ አጋጣሚ ሲያመቸው እያታለለ በማህበራዊ ህይወታቸው ያሰንፋቸዋል። የአበጀን መስሎን ቤታችን ግድግዳ ላይ ባማረ ኀብረ ቀለምና ዕይታ በሚስብ ፊደል አጣጣል አጽፈን - ፅፈን ወይም የተገፈን ጥቅስ/ዛሬማ በማርከር ጥቅሶችን አሳምረው እየፃፉ ባደባባይ ደርድሮ መሸጥ እንደገቢ ምንጭስ መታየት ከጀመረ ውሎ አድሮ የለ። በተለይ ቆም ብላችሁ እንደኔ ታዝባችሁ ከሆነ ከተደረደሩት ውስጥ ከመቶ አንድ እንኳ "ተስፋን" የሚፈጥር ጥቅስ የለም። ሰውም የሚገዛው ልብ የሚሰብሩ፣ ተስፋ የሚያስቆርጡ፣ የሰውን ግብዝነት፣ ያለምን ከንቱነት የሚገልፀውን ነው/እናም ይህን ገዝተን ሰቅለን እኛም ሆነን ልጆቻችን ነጋ ጠባ ነገሬ ሳይሉ እያዩት ከቀልባቸው እንዲሸነቱ ስናደርግ

መልዕክቱ ውሎ አድሮ በእኛም ሆነ በልጆቻችን የሚያሳድረውን የባህርይ ግሽበት፣ የሥነ ምግባር ጉድለት እና የሥነ ልቡና ችግር አጢነንው እናውቅ ይሆን?

ብዙዎቻችን ስለባልና ሚስት፣ ስለውሽማ፣ስለፍቅረኛ ወንድና ሴቶች እና በመሃላቸው ስለሚኖረው ግንኙነትም ጭምር አምሮና ጣፍጦ የሰማነው ገና በጠዋቱ ሳይሆን እንዳልቀረ እገምታለሁ፤ ከዚሁ ጋር ስለምቀኝነት፣ አሉባልታ፣ሃሜት፣ስለመገዳደል እና ሌሎችም ሁሉ የሰማነው በዚያው ወቅት ሲሆን የሚገርመው ስለበጎ ነገሮችም በዚያን ግዜ ሰምተናል:: በልጅነት አእምሮአችን ስናስበው የሚቀለንና ስንናገረው የሚጣፍጠን ነገር ግን ቋንቋችን ሆኖ አድጓል:: ቀስ በቀስም ባህርያችን በዚያው አግባብ ሊቀረፅ የሚችልበት አጋጣሚ ይሰፋል:: "ምስጢርህን ለባዳ ለምን አዋየህው፣ ወንፊት ውሃ ይዞ መቼ ሲሄድ አዋየህው" የመሳሰሉትን ጥቅሶች እያነበበ ያደገ ብላቴና ለሰው ያለው ግምት ቢያንስ፣ ድብቅና ከሰው የማይገጥም ተጠራጣሪ ሆኖ ማህበራዊ ግንኙነቱ በእንከን ቢታጠር የዚህ ሁሉ ችግር መዘዝ እየተመዘዘ ሥሩ ከዚች ስነቃል ላይ የመሆኑን ምስጢር እንደምን አስቦት ራሱን ለመለወጥ ይዳዳዋል:: ዛሬም ቢሆን የተዘበራረቀና ጥንቃቄ የጎደላቸው መልዕክቶች ይዘው የሚወጡ ዘፈኖች፣ ቲአትሮች፣ ፊልሞች፣ የስዕል ውጤቶችና ሌሎችም ሁኔታዎች የልጆችንም ሆነ የሕብረተሰቡን አስተሳሰብ በመስረቅ ለውድቀቱ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የከፋ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል:: አባት ዘወትር የሚቀናውና በትንሽ በትልቁ ጓደኞቹን ሚስቱንና ልጆቹን የሚገስጸው "አንተ ውሻ፣አንተ ሌባ፣ ዱርዬ፣ ወዘተ..." ከሆነ ልጅም እንደምን ዋልክ አቡ ሲባል "አንተ ውሻ" ቢል ምን ይደንቃል? አንድ ሰው ስለልጁ ያጫወተኝ ነገር ዘወትር በትግርምት ያስደምመኛል:: እንዲህ ነው :-አባት ከሥራ ከገባ በኋላ ወንድ ልጅ አፉ ውሃ ውሃ ማለት የለበትም እያለ ማምሻው ላይ በአቅራቢያው ወዳለ መጠጥ ቤት አንድ ሁለት ብሎ መለስ ማለትን ያዘውትራል:: አልፎ አልፎ ልጁን ወግ ያሣየ መስሎት አንድ ሁለት ቀን እዛው ይዞት ሄዷል:: አንድ ቀን ሊያዝናናው ወደኬክ ቤት ይወስደውና ወንበር ይዘው ይቀመጣሉ፤ አስተናጋጅ ቀረብ ብላ ማሙሽዬ ምን ላምጣልህ ስትለው "ድራፍት" ይላታል እየተኮላተፈ:: አስተናጋጅ ደንገጥ ብላ ሳቅ ትልና "ማሙሽዬ ምን አልክ?" ስትለው "የወንድ ልጅ አፍ ውሃ ውሃ ማለት የለበትም" ይላታል:: - አባት እጅግ ማፈሩን በዚህ መልክ ነበር የገለጸልኝ:: እንደዚህ ዓይነት ድርጊቶች የልጆችን ሥነምግባር በእጅጉ የሚጎዱ መሆኑን በማስተዋል ልጆቻችንን ለማዝናናትና ለማስደሰት የምንመርጥላቸው ሁኔታዎች በጥንቃቄ ሊጠኑ ሊጠኑ ይገባቸዋል::

በዚህ ዙሪያ በርካታ ጉዳዮችን አንስተን መነጋገር ብንችልም ይህን ያህል ካልኩ ይህንን በዚሁ ቆም ላርገውና ሰው በዕውቀት በልፅጎ ተኮትኩቶ በሚያድግባቸው ወይም ተብሎ በሚታሰብባቸው ትምህርት ቤቶች ዙሪያ ጥቂት ነጥቦች ላንሳ:: ልጆች በበጎ አስተዳደግ

አድገው መጀመሪያ ከቤት የሚወጡበት ሰበብ ትምህርት በመሆኑ ሌላው ቤታቸው ትምህርት ቤት ነው - የት/ቤቱ ማህበረሰብም ቤተሰባቸው ይሆናል። ስለዚህ ቤተሰብ ለልጆቹ በጥሩ ሥነምግባር ተኮትኩተው እንዲያድጉ የሚያደርገው ጥረት ልጆቹ ወደትምህርት ቤት ምልልስ በሚጀምሩበት ወቅት አብዛኛዉን ሰዓት የሚያሳልፉበት ሥፍራ በመሆኑ ቤተሰብ ልጆቹን በጥሩ ባህርይ ለመቅረፅ የሚኖረው ድርሻ ከመቶ እጅ በእጅጉ ያነሰ ይሆናል። የት/ቤቶቹ ድርሻ ደግሞ ይጨምራል። ስለዚህ ትምህርት ቤቶች ልጆችንና ወጣቶችን በትምህርትና በጥሩ ስነምግባር ለመቅረፅ የሚያስችሉአቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ሰብዓዊና ማህበራዊ ሃላፊነት የሚሰማቸውን ልጆችና ወጣቶች ለመፍጠር መቻል ይኖርባቸዋል። በአጋጣሚዎች ለሚከሰቱ ችግሮች የሚፈታ ሳይሆን በሥርዓት ሊኖር የሚችል ትውልድ ማምጣትም በእጅጉ ይጠበቅባቸዋል።

ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን እንደምንረዳው ሰዎች ባለተፈለገና አደገኛ በሆነ አቅጣጫ ጨፍነው ሲጓዙ የምናገኛቸውና ላልተፈለገ ችግር የሚዳረጉት እህቶችና ወንድሞች ሲባክኑ የምናያቸው በሥነ ዜጋ ትምህርት ያለመታነፅ ወይም ግልፅነት በጎደለው አስተሳሰብ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የአለመቻል ውጤቶች ናቸው። ሰው በአጋጣሚዎችና በሁኔታዎች ሲፈተን በዕውኑ ቀርቶ በህልሙ የማያስበውን ስህተት ይፈፅማል። ለጥቅሙ ጓጉቶ በስሜታዊነት ይጨፍናል-ክብሩን ይጥላል። እንግዲህ ነገሬን ላሳጥረውና ከነዚህ መሰሉ ሁነቶች የተሰናሰለው ሂደት ነው ለማናስበው ማህበራዊ ጠንቅ ሰለባ የሚያደርገን። ሰዎች በስርዓት ሊኖሩ ይችሉ ዘንድ ከጠዋቱ በሥነዜጋ ትምህርት ሊታነፁ ይገባል። ረፈድ ያለብንም ብንሆን የባህርይ ለውጥ ለማምጣት አካላዊና ሥነልቦናዊ ዝግጅት ማድረግ ይገባናል።

ከዚህ በተጨማሪ የማህበራዊ ችግር መንስዔ ተደርጎ ሊታሰብበት የሚገባ ሌላም ሁኔታ አለ። ሰዎች በሥርዓት ሊኖሩ የአለመቻላቸው ሌላው ገጽታ ኑሮን በአቅማቸው ለመኖር ባለማቀድ የተዘበራረቀ ሕይወት ለመኖር በሚገደዱበት ሁኔታ ውስጥ የመገኘታቸው ነው። ይኸውም መጥኖ በአለመውለድ ልጆችን በአግባቡ ተከታትሎና ተንከባክቦ ለማሳደግ የአለመቻል የአገራችን ተጨባጭ ችግር ነው። ለምሳሌ አቅሙ ሁለት ልጆችን ብቻ በአግባቡ ተንከባክቦ ለማሳደግ የሚቸል የወር፣ የሳምንት ወይም የቀን ገቢ ያለው ሰው በማንኛውም ስሌት ተሰልቶ አቅሙ የሚሆነው ሁለት ልጆች ማሳደግ ነው። በቃ። ምናልባት ይወለድና እነአባዬ ጋ ልኬው ገጠር ከብት ይጠብቃል - ወይም ወንድሜ ጋ ሄዶ ራሱን እየረዳ /እያገለገለ/ ይማራል - ወይም ለአጎቴ እሰጠዋለሁ በሚል <u>በእንሸካከም</u> አጓጉል ስሌት ካላሰላን በስተቀር ወደ ፍሬ ነገሩ እንመለስና ብቻ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወይም በማናቸውም አጋጣሚ ሦስት እና ከዚያ በላይ ልጆች ቢወለዱ አንዱ ቅድም በገለጽኩት መንገድ ወይም በራሱ

ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት ሁለት ልጆች የማሳደግ አቅሙን በማመናመን አኗኗሩን ስርዓት-አልባ ያደርጉበታል። የሁለት ልጆች ድርሻ የነበረው ለሌሎችም ልጆች ጭምር ይከፋፈልና የሁሉም ድርሻ ጎደሎ - ከባሰ ትንሽ እና ከከፋም ደግሞ ምንም ሊሆን ይችላል። በዚህን ወቅት ወላጅ በልጆቹ ከሚደሰት ይልቅ ያዝናል -ያማርራል - ከሚከብር ይልቅ ይከስራል፤ ዕድሜያቸው በዘለገ ቁጥር ፍላጎታቸው ይጨምራል፤ ሁኔታው ጫን እያለ ሲሄድ ዕድሜያቸው ከሚፈቅድላቸው አኗኗር ውጪ ለመኖር ይገደዳሉ፤ በህፃናት ለሚደርሱ በርካታ አእምሮአዊና አካላዊ የጉልበት ብዝበዛዎች ይደረጋሉ፤ በትምሕርት ተኮትኩተው ሊያድጉ በሚገባቸው ዕድሜ የራሳቸውን የገቢ ምንጭ ፈጥረው፣ አሊያም ዘርፈው ወይም ሰው ተጠ ግተው፣ ለምነው፣ ተለማምጠውና ቀላውጠው ሕይወትን ሊኖርዋት ግድ ይሆንባቸዋል። አልፎ አልፎም ቤተሰብን የማስተዳደር ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በእነርሱ ትክሻ ይወድቃል። በዕውነቱ ላይ የተመሠረተ ገጠመኝ ላካፍላችሁ። ነገሩ እንዲህ ነው:-

በላይ በላዩ ልጆች የሚወልዱ አንዲት ገና ለመወለድ ያላቸው ጉጉት በእጅጉ ያስገረመው ሰው ሴትዮዋን መውለድ ቢያቆሙ የተወለዱትን በአግባቡ ለማሳደግና ኑሮአቸውን በስርዓት ለማኖር የተሻለ መሆኑን ማስረዳት ሲጀምር በአላዊቅነቱ ሳቅ ብለው "አይ በእግዜር ስራ ገብቶ መዘባረቅ?" - ምን ልጅ ቢበዛ እኮ ሞኝ ወጥቶለት፣ከፉ ወጥቶለት፣ ዱርዬው ተቀንሶለት፣ ሂያጁም ወዳሻው ሄዶለት፣ ሞት ወስዶለት የተረፈው ነው ለእናት አባት የሚቀረው " እንዳሉት አጫወተኝ። ኑሮን በሥርዓት ለመምራት በሚያስችሉ በቤተሰብ ምጣኔ፣ በስነተዋልዶ እና በመሳሰሉት ሳይንሳዊ ስልቶች እየታገዙ ሕይወትን አጣፍጦና አስተካክሎ ለመኖር መቻል በእግዜር ሥራ እንደመግባትም የሚያስቆጥር አይመስለኝም። ነገሩን ያመጣሁት በውስጡ አላዊቅነት፣ የዋህነት፣ ስስት፣ስጋት እና አጉል ብልጠትም ያለው ስለመሰለኝ ነው። ገበሬ በወጉ ሊያርሰውና አለስልሶ ጥሩ ዘር ሊዘራበት - አርሞ - አጭዶ ወቅቶ ከጎተራ ሊከተው የሚችለውን ማሳ ካረሰ በፍሬው የመክበሩን ያህል በስስት ሰፊ ማሳ ይዞ ቢማስን እርሻውን ሳይጨርስ የዘር ጊዜው ያልፋል - ጥቂትም አምርቶ ሳይሰበስብ ባዶ እጁን ይቀራል። ዛሬ በአገራችን በሕዘብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ሳቢያም የሚያነጋግረን በቦታ ጥበት የመጨናነቅ አሳሳቢ ችግር ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነው የኢኮኖሚ አቅም በበቂ ሁኔታ የአለመኖር ችግር ሲሆን ይህም የሥራ አጥ ቁጥር መብዛቱና ችግሩን ከቁጥጥር ውጪ ወደሚሆን እንዲያመራ ስለሚገፋፋው ነው።

አባትና እናት በአላስፈላጊ የልጆች ቁጥር መብዛትና ምክንያት የልጆቻቸውን ፍላጎት ማሟላትና መንከባከብ አለመቻላቸው ቃላቸው እንዳይሰማ፣ ትዕዛዛቸው እንዳይከበር እና ልጆቻቸውን በሥርዓት የማስተዳደር መብት እንዲያጡ ከማደረጉ ባሻገር ቤተሰባዊ ፍቅር

ቀዝቅዞ ልጆች በራሳቸው ፈቃድ፣ ባሻቸውና በመሰላቸው መንገድ ለመኖር ከቤተሰብ ፈቃድ ውጪ ይሆናሉ፣ ወደጎዳና ይወጣሉ።

በአጠቃላይ ማህበራዊ ችግሮቻችን በቁጥር የበዙ፣ በመጠንም የሰፉና የገዘፉ እንደመሆናቸው መንስኤያቸውም የዚያኑ ያህል የበዛና የሰፋ ነው። በዚህ ጽሑፍ ላይ ለማንሳት የሞከርኩት አንድም ማህበራዊ ኑሮአችን፣ ልማዳችን፣ አስተሳሰባችንና አስተዳደጋችን በቤተሰብም ሆነ በት/ቤት ደረጃ በተፈለገው መንገድ ሊያድግና ሊዳብር ባለመቻሉ፣ አንድም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገታችን በመጫጫቱና የህዝብ ቁጥራችን ግን እያደገ በመምጣቱ እየተወሳሰቡ የመጡ ችግሮቻችን የማህበራዊ ኑሮ ዕድገታችንን የሚያፋልሱና ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዳይኖረን የሚፈታተኑ ከስነህዝብ ሳይንሳዊ ግንዛቤዎች ጋር ተፃራሪ የሆኑ ጠንቆች ናቸው። ለዚህም በዋነኛነት ኪነጥበብ በጥበብነትዋ የሰውን አስተሳሰብ የመለወጥ ብቃትዋን በአግባቡ ልንጠቀምበትና የሙያው ባለቤቶች ሰብአዊና ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የግድ ይሆናል።

## 4. ኪነጥበብና ማህበራዊ ጉዳዮቻችን

ኪነጥበብ ከዕለት ዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ተፀንሶ በነባራዊው ዐለም ዕውነት ተጋግሞ የሚጎለብትና በሕሊና ሞግዚትነት በቅዱስ ልብ ተረግዞ የሚወለድ ሀብት ነው። ይልቁንም ግዙፍ በሆነው ዓለም ላይ ሰልጥኖ ለፍጥረታት ገዢ የሆነው የሰው ልጅ ሕይወቱን ከነባራዊው ዓለም ጋር አቆራኝቶ በሚያደርጋቸው ውጣ ውረዶች ዳብሮ፣ በምስጢር ታጭቆ፣ በቁም ነገር ደርጅቶ፣ በቅድስና ገዝፎ ፍቅሩን፣ ሐዘኑን፣ ደስታውን፣ ጥላቻውንና አድናቆታዊ ትግርምቱን፣ድህነቱን፣ጥቃቱንና ችግሩን የሚገልጽበት መሣሪያው ነው። በተለይም ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ኪነጥበብ ስሜታችንን በመግለፅ ዕሮይታ የምንቀዳጅበት እና መፍትሄ ጠ ቋሚ አንቴና በመሆን ለውጤት የምንበቃበት የፀጋ ስጦታችን ነው። ስለዚህ በእኛ አእምሮ ኪነ ጥበብ ሁለንተናችንን የሚገዛውና ስብዕናችንን የሚዘውረው ምታሃታዊ ጥበብ ነው።

በዚህ መሠረት በማህበራዊ ሕይወታችን የተለያዩ ጉዳቶች ለሚደርስብን እኛ ኢትዮጵያውያን ጥበብ በመግቢያዬ እንደገለጽኩት - ለማህበራዊ ሕይወታችን ፈውስ ሊሆነን ገንዘባችን ያደረግነው መንፈሳዊ እሴታችን ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው በማህበራዊ ችግሮቻችን ዙሪያ ለተከሰቱ በርካታ ችግሮች መንግሥት ሕግ ይቀርፃል፣ የነበረውን ያሻሽላል፣አዋጆችንና ፖሊሲዎችን ያወጣል። ከነዚህም ውስጥ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ፣ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ የሥነሕዝብ ፖሊሲ፣ የትምህርት ፖሊሲ፣ የጤና ፖሊሲ፣ በቅርቡ የወጣው የኤድስ ፖሊሲ ወዘተ......ከብዙ በጥቂቱ ናቸው። ይህ እርምጃ ችግራችንን ለመፍታት ቁልፍ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ ነው። ነገር ግን ሕጎችና ፖሊሲዎች ሁሉ ባማረ ጥራዝ ተከሽነው በየቢሮው

በየቤቱ እንዲያውም እንደእምነት ድርሳናት እንደክታብ ብናንጠለጥላቸው መልዕክቱ የሚያስገኘውን ጥቅም፣ ለማህበራዊ ሕይወታችን የሚያደርልንን ጥበቃ እና ቁምነገር ተረድተን ካልተገበርነው ፋይዳ አይኖረውም:: ከልምድ እንደሚታወቀው ሕጎችና ፖሊሲዎች ሲወጡ የአለመቀበል ችግር የለብንም፤ እንኳንስ ብዙ መከረን ዘክረን ሃሳብ ሰጥተን የወጡ ሕጎችን ይቅርና ባልነበርንበት ዘመን ሃሳብ ባልሰጠንበት ሁኔታ በነቢያትና በቅዱሳን አማካይነት የወረዱ መንፈሳዊ ሕግጋትንና ትዕዛዛትን በሙሉ ልብ ለመቀበል ብዙዎቻችን አናንገራግርም:: ችግሩ መተግበሩ ላይ ነው - ይህ ደግሞ ተፈጥሮአዊ በሆኑ ሰብዓዊ ባህርያቶቻችን ይታገዛል - ስለዚህ ነው የባህርይ ለውጥን ደጋግመን የምናነሳው:: ለዚህ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን እና የኪነጥበብ ባለሙያዎች ተገቢውን ለውጥ ለማምጣት መሣሪያዎቻችን ናቸው:: ወደተሰጠኝ ርዕስ ልምጣና በተለይ የኪነጥበብ አካል የሆኑት የቴያትርና ሙዚቃ ዝግጅቶች በአግባቡና በቦታው ከተጠቀምንባቸው ጥረታችን ውጤታማ ይሆናል:: ይሁን እንጂ የጥበቡ አዘገጃጀትና አቀራረብ በእጅጉ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው::

ለዕይታ የሚቀርቡ ድራማዎች እና ለጆሮአችን የሚደመጡ የሬድዮ ድራማዎችም ሆኑ ሙዚቃዎች እታለመው ሕብረተሰብ ዘንድ ደርሰው ተገቢውን ግንዛቤ ሊያስጨብጡ የሚችሉት ወግና ደርዝ ኖሮአቸው ጥበባዊ ምልዓታቸው በሚስብ መልክ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው:: ይህ ካልሆነ ከሚያለሙት የሚያጠፉት ጎልቶ ማህበራዊ ችግራችንን ለማስፋፋት አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል:: ብዙ ትምህርታዊ ትያትሮችና ሙዚቃዎችን አዳምጠን ብዙ የተጠቀምንባቸውን ያህል አልፎ አልፎ ለማሳቅ የታሰበው አሳስቅ ሲለን፣ በአሳዛኝነቱ ሊያስለቅስ ታስቦ ተዋናይዋ ወይም ተዋናዩ ጧ ብሎ በማልቀስ ሊሸነግለን ሲባትል እንኳን ሊያስለቀሰን ከእኛነታችን ተላኮ በሃዘን ሊቧጭረን የአለመቻሉ፣ በትግርምት ሊያስደምሙን የታሰቡት እንኳን ለዚያ ሊበቁ በተዘበራረቁ መልዕክቶችና ውል የለሽ አቀራረብ ሲያሰለቹን የተስተዋለበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: ይህም ከጊዜ ጌዜ እንደመለያየቱና የሰው ልጅ ዕሳቤያዊ ምጥቀት እየጨመረ የመሄዱን ተፈጥሯዊ ክስተት ተከትሎ የጥበቡ ዕድገት ደረጃውን አለመጠበቅ ወይም የጥበቡ ባለቤት ባልተጠናና - በቂ ግንዛቤ ባልጨበጠበት ርዕስ ጉዳይ ጥንቃቄ በጎደለው ስሜታዊነት የአዘጋጀው እንደሆነ ነው::

"ኪነጥበብና ኤድስ" በሚል ርዕስ በሀበሻ የቲአትርና ሙዚቃ ኢንተርፕራይዝ በተዘጋጀው ዐውደጥናት ላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተጋበዙት ምሁር ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሑፍ "ለዕድገት በሕብረት ዘመቻ አዋጅ፣ ለአረንጓዴው ዘመቻ፣ ለአኢወማ፣ለአኢሴማ፣ለኢሰፓ ወዘተ.....ከሚወጡ መመሪያዎችና አዋጆች ጋር ግጥሞችና ተውኔቶች ባንድ ሌሊት ይፈበረኩ ነበር:: አንድ በሩቁ የማውቀው ፀሐፊ የተውኔቱን ዲያሎግ የሚያገኘውና የሚገለብጠው ከጋዜጦቹና ከፖለቲካ ስብሰባዎች እንደወረደ በሚባል

ዓይነት እንደነበር እርሱን በቅርበት የሚያውቅ ሰው አጫውቶኝ ነበር። እንደ ቶሎ ፎቶ እና ሻይ በቶሎ ቲያትር የታወቀ ነበር ይባላል። ነገር ግን አንድ ፀሐፊ አንድ ውል ያለው ቁምነገር እውስጡ ሳይገባና ስሜት አዕምሮውን ሳይነካው ለፖለቲካ ሥልጣን - ለእወደድ ባይነት - ከመምጣቱ መሂዱ ለሚፈጥን ዝና እና ገንዘብ ተስገብግቦ ቢፅፍ ፅሑፉ ተደማጭ ተመልካችና ተነባቢ ልብና አእምሮ መተንኮስና ማነቃቃት ይሳነዋል። ስለዚህም በድርቀቱ ተሸመድምዶ ያሽመደምዳል" በማለት ነበር አንዳንድ ኃላፊነት የጎደላቸውን ፀሐፊዎች የገለጿቸው።

ምሁሩ እንደገለፁት በተለይ ማህበራዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት የምናቀርባቸው ትያትሮችና ፅሁፎች ከግል ፍላጎታችን ውጪ ከተደራሲው ጋር ባለን ልባዊ ቁርኝት ስሜቱን ተጋርተን፣ ይህም ብቻ ባለመሆኑ መነሻ ሃሳባችንን በጠለቀው የጉዳዩ ዕውቀት ላይ መሥርተን ፍፁም ዕውነት በሆነ ሙያዊ ቴክኒክ በለዛ አጣፍጠን ራሳችንን ለሙያው ቅድስና አስገዝተን በተመስጦ ልንሰራው ይገባል። ስለኤድስ፣ ስለሥነ ሕዝብ፣ ስለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ስለ ፆታ በደሎችና ጥቃቶች ወዘተ.....ልንፅፍ ስንነሳሳ ሳይንሳዊ ትንተናውንና ፍልስፍናውን በመጠኑም ቢሆን ካላወቅን በርካታ ጥፋቶችን እናደርሳለን። ለሰው ስሜትና እይታ ያስደመጥነውንና ያሳየነውን ትርዒት ዕርምት ለመስጠት ዕድሉ ጠባብ ከመሆኑ ባሻገር የሚጠይቀው መስዋዕትነት ቀላል አይደለም። ለምሳሌ ስለኤድስ ስርጭትና አስከፊ ገፅታ በጥሩ ዝግጅትና ትወና የሚቀርቡ ትያትሮች በሌላ በኩል ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖቻችንን ሰብዓዊ መብት፣ ክብርና ሞራላቸውን የሚደፈጥጥና የመኖር ተስፋቸውን የሚያላሽቅ ይልቁንም ቫይረሱ ባለበትና በሌለበት የህብረተሰብ ክፍል መካከል ጥላቻን የሚያጭርና ለብቀላ የሚገፋፋ መሆኑን ከጉዳዩ ባለቤቶች አንደበት የሰማችሁ ይመስለኛል። በተለያየ አጋጣሚ ሆነ ሲባል የምንሰማውና የምናየው ስለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ምንነትና መተላለፊያ መንገዶች ባለመረዳት ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝባቸው ወገኖች ጋር አብሮ መብላት፣መጠጣት፣ መጨባበጥና አንድ ልብስ በአንድ መስቀያ እንኳ ለመስቀል በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ፍራቻና ጭንቀት ጎልቶ ሊታይ የቻለው በአላዋቂዎች ወይም የሙያውን ሥነምግባር ተከትለው በማይፅፉ የኪነጥበብ ሰዎች ያፋተላለፉት የተሳሳተ መልእክት ያሣደረው አሉታዊ ተጽእኖ የበኩሉ ድርሻ እንዳለዉ ነው። ስለሥነሕዝብ፣ስለሴቶችና ስለሌሎችም በሚጽፉ ሰዎች የሚከሰተው ችግር ተመሳሳይ ነው። አንድ ጽሑፍ ሲፃፍ ከጠለቀ ግንዛቤና ዕውቀት ሳይመነጭ ተለባብሶ ቢቀርብ አቀራረቡን ለመረዳትና ለማገናዘብ ዕድል ባላቸው ውስን የህብረተሰብ ክፍሎች ጥላቻን ከማትረፍና በሌላ ወገን ደግሞ መልዕክቱን እንዳለ የሚቀበለው አብዛኛው ክፍል ተገቢውን የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ ሳይሆን አውሬያዊ ባህርያትን እንዲያባብስ ከመገፋፋት ውጪ የታሰበው ውጤት አቅም

በፍጹም ሊኖረው አይችልም። ይህም ማህበራዊ ችግሮቻችንን መነሻ በማድረግ በሚቀርቡ አብዛኛው ትያትሮችና ሙዚቃ ዝግጅቶች የሚታይ ነው።

በሥራ አጋጣሚ እንደተረዳሁት ለምሳሌ በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ጥቃቶች አንዱ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው። ከ4 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እስከ አዛውንት  እናቶች ድረስ ድርጊቱ ይፈጸምባቸዋል። በተለይ ሕፃናት በሚዘገንን ሁኔታ ይጠቃሉ። በአብዛኛው ደግሞ በቅርብ ዘመድ፣በእንጀራ አባት፣በወላጅ አባትና በወንድማቸው ይደፈራሉ። ከመብት አንፃር ጉዳዩ እጅግ ከፍተኛ ወንጀል በመሆኑና ሌሎቹን ሕፃናት ወላጆች ጥበቃ እንዲያደርጉ ለማትጋት እና ሌላውንም የሕብረተሰብ ክፍል በአካባቢውና በቤቱ ድርጊቱን መዋጋት እንዲችል በትምህርታዊነቱ በመገናኛ ብዙሀን ፕሮግራሞች ለአድማጭ እንዲቀርብ ቢደረግ፣ በትያትርና በሙዚቃ መልክ ቢቀርብ ሊያስከትል የሚችላቸው ሌሎች በርካታ ጠንቆችና አደጋዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ማጤን የተገባ ነው። በጐዳና ተዳደሪነትና ሥራ አጥነት ወይም ሰው ሊሠራ ከፈለገ የማሠራው እንዴት ያጣል ከተባለም ሥራ ፈት ወጣቶች በየቦታው ምን እንስራ እያሉ እንደሚታዩ እየታወቀ፣ በርካታ የሥነምግባር ችግር የሚታይባቸው ወጣቶች በሚገኙበት ሁኔታ "ለካ ከህፃናትም ጋር ወሲብ መፈፀም ይቻላል" የሚለውን ርዕስ በሥራ ፈት አእምሮው እንዲያብሰለስል እና ትኩረት እንዲያደርግ ማንቃት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ነገርን ብቅ እንዳለ አንቆ ያበደ ዜና ከማውጣት፣ ያበደ ትያትርና ሙዚቃ አዘጋጅቶ ለታዳሚ ከማቅረብ ብዙ ማሰላሰልና ሁኔታዎችን ማጥናት ይበጃል። ሊከሰቱ ከሚችሉ ችግሮችም ይሰውራልና!!

ወደጥንተ ነገሬ ልመለስና እንደኔ ወይም- እንደመስከ ባለሙያዎች ዕምነት ጭምር በማህበራዊ ችግሮቻችን ዙሪያ ለሚሰሩ ቲያትሮችና ሙዚቃዎች በታላላቅ መደረኮች፣ በቴሌቭዥን መስኮቶች እና በሬድዮ የምናውቃቸው የጥበብ ሰዎችን ብቻ አስተዋጽኦ ከመጠ በቅ ይልቅ(Falk Media) ን በመጠቀም ሕብረተሰቡ በየውሎውና ማምሻው ከራሱ የግንዛቤ ደረጃ፣ ፈሊጥና ቋንቋው ጋር በስልት እያስማሙ በእንጉርጉሮው፣ በሽለላው፣ በቀረርቱውና ከነባር እንቅስቃሴዎቹ በማጣመር  ትያትሮችንና ሙዚቃዎችን እያዘጋጁ እርስ በርስ እንዲማማር ቢደረግ ውጤቱ ከጠበቅነው በላይ ይሆናል። በተለይም የትያትሩ ፍሬ ነገር የዚያንው ማህበረሰብ ችግር መሠረት አድርጎ በአካባቢው ባዳበራ ቸው ግለ- ጠባዩ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ስለሚሆኑ በወጉ ይደመጠዋል፤ በአስተውሎ ህሊና ያየዋል። በውል ይገነዛባል አለያ እናቅልሃለን ተብለው የሚሰሩ ሙዚቃዎችና ቴአትሮች እንኳንስ ወደ ማህበራዊ ችግሩ ዘልቀው ሥነልቦናውን እያስታመሙ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ ሊያግዙት ቀርቶ በአንድ የቲያትርና ሙዚቃ ቡድን፣ ድርጅት፣ ክበብና የቲያትር ቤት ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ኪነጥበባዊ የባህል ትርዒት እንኳ ምናልባት በአካባቢው ተወላጅ ስሜት ምን

ትርጉም እንዳለው ሲነገር አዳምጣችሁ ከሆነ ዕውነታቸውን ትረዱታላችሁ፡፡ እንደየአካባቢው ባህልና ወግ እንዲህ ሲሉ ይሰማል፡፡ "አሁን የምንጃር ጭፈራ እንዲህ ነው?- የጎንደር-የጎጃም-የወሎው-የትግሬ-የጉራጌ-የሲዳማ-የወላይታ የኦሮሞ ወዘተ...እስክስታ -ጭፈራና ዝላይ?" በማለት በተወላጆቹ አቃቂር እየወጣለት ብሽቀታቸውን የሚገልፁ ስንቶቹ ናቸው? በትያትሩም ቢሆን ሁኔታው ተመሣሣይ ነው፡፡ ታዲያ "ያገሩን መሬት ባገሩ በሬ" እንደሚባለው የራሱን ማህበራዊ ችግር በራሱ ዘዬ-ልማድ - ወግና እምነት በቋንቋው ከራሱ በተውጣጡ አባላት እንዲቀርብ የሚጠበቅብንን ድጋፍ እየሰጠን ሕብረተሰቡ በራሱ እንዲማማር ቢደረግ የሚተላለፈው ቁምነገር በመልዕክቱ ውጤት የማስገኘት አቅሙ የበረታ ይሆናል፡፡

| 36 | ጌትነት እሸቱ (አቶ)<br>የሬዲዮ ፕሮግራም አስተባባሪ | የጎንደር የትምህርት<br>ሬዲዮ ማሠራጫ ጣቢያ |
| 37 | ግርማይ ከበደ (አቶ)<br>ዘጋቢ | ሬዲዮ ፋና |
| 38 | ኃይሉ ነጋሳ (ዶ/ር)<br>ቡድን መሪ | ኤፒደሞሎጂና ኤድስ<br>መከላከያ መምሪያ(ጤና ጥበቃ<br>ሚኒስቴር) |
| 39 | ኃይሉ ጽጌ<br>አዘጋጅ | ኢትዮጵያን ሄራልድ<br>ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት |
| 40 | ጎሩይ ምትኩ (አቶ)<br>የኢንፎርሜሽን፣የትምህርትና የኮሙኒኬሽን<br>መምሪያ ኃላፊ | ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 41 | ጆኒ ቦና (አቶ)<br>የመገናኛ ብዙኃን አስተባባሪ | ዲኬቲ ኢትዮጵያ |
| 42 | ኩራባቸው ደነቀ (አቶ)<br>የኪነ ጥበባት አገልግሎት ኃላፊ | ራስ ቴአትር |
| 43 | ልጅ ወንድሚ ለአከማርያም (አቶ)<br>ሥራ አስኪያጅ | ሀበሻ የቲአትርና ሙዚቃ<br>ኢንተርፕራይዝ |
| 44 | ሉላ አህመድ (ወ/ት)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |
| 45 | ማኅሌት ታደሰ (ወ/ት)<br>የትምህርት ቤት ዲሬክተር | ቤተፍቅር<br>ትምህርት ቤት |
| 46 | ማርታ ተስፋዬ (ወ/ት)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |
| 47 | መኰንን ናና (አቶ)<br>የኢንፎርሜሽን፣የትምህርትና<br>የኮሙኒኬሽን ቡድን መሪ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 48 | መልካሙ አሰፋ (አቶ)<br>የሬዲዮ ፕሮግራም ንኡስ ቡድን መሪ | የደሴ ትምህርት ሬዲዮ<br>ማሠራጫ ጣቢያ |
| 49 | መሪማ መሐመድ (ወ/ሮ)<br>አዘጋጅ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |
| 50 | መስፍን አሰፋ (ወ/ሮ)<br>አዘጋጅ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |
| 51 | ምትኩ ወርቅነህ (አቶ)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን |
| 52 | መሐመድ ገልማ (አቶ)<br>ፕሮግራም አስተባባሪ | ኦሮሞ ልማት<br>ማኅበር |

| ተራ ቁጥር | ስምና | ድርጅት |
|---|---|---|
| 53 | ነቢዩ ተካልኝ (አቶ)<br>የኢንፎርሜሽን መምሪያ ኃላፊ | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር<br>ባህልና ኢንፎርሜሽን ቢሮ |
| 54 | ሙሉ በርሄ (ወ/ት)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |
| 55 | ንጉሤ ታደሰ (አቶ)<br>የምናባዊ ፈጠራ ጥበባት<br>ቡድን አስተባባሪ | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር<br>ባህልና ኢንፎርሜሽን ቢሮ |
| 56 | ነሚ ነጋሳ (አቶ)<br>የተዋልዶ ጤና ቡድን መሪ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 57 | ሸዋዬ ለገሠ (ወ/ት)<br>የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ | ሬዲዮ ፋና |
| 58 | ሲሣይ ወርቁ<br>የፕላን ዝግጅት፣ የሥልጠና፣ የክትትልና<br>ግምገማ ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 59 | ሰሎሞን አላዩ(አቶ)<br>የፕላን ዝግጅት፣የግምገማና ክትትል<br>ቡድን መሪ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 60 | ሰሎሞን ዓለሙ (አቶ)<br>ተዋናይና ጸሐፊ ተውኔት | አፍለኛው ጥበባት<br>ኢንተርፕራዝ |
| 61 | ሰሎሞን በላይነህ (አቶ)<br>የሥነሕዝብ ቤተሰብ ኑሮ<br>ትምህርት አስተባባሪ | የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣<br>ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት |
| 62 | ሰለሞን ተስፋዬ (አቶ)<br>አዘጋጅ | አዲስ ዘመን ጋዜጣ<br>ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት |
| 63 | ታደሰ ያዳ (አቶ)<br>የሴቶችና የመጣቶች ተዋልዶ<br>ጤና ቡድን መሪ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ<br>ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 64 | ታሪኩ ቶለዋቅ (አቶ)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ሬዲዮ |

| ተራ ቁጥር | ስምና ደረጃ | ድርጅት |
|---|---|---|
| 65 | ታየ አበራ (አቶ)<br>የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ | የሰንዳፋ የትምህርት ሬዲዮ ማሠራጫ ጣቢያ |
| 66 | ተመስገን ያለው (አቶ)<br>ተዋናይ | ራስ ቴአትር |
| 67 | ተናኘ ቀለሙ (ወ/ት)<br>የሴቶችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ኤክስፐርት | ብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 68 | ቴዎድሮስ ተስፋዬ (አቶ)<br>ተዋናይ | ብሔራዊ ቴአትር |
| 69 | ጥላሁን ዘውገ (አቶ) | በግል |
| 70 | ጺጋዬ ኃይሉ<br>የኢንፎርሜሽን፣ የትምህርትና የኮሙኒኬሽን ከፍተኛ ኤክስፐርት | ብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 71 | ውብሸት ታምራት (አቶ)<br>የኢንፎርሜሽን፣ የትምህርትና የኮሙኒኬሽን ኤክስፐርት | አማራ ብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 72 | ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን | ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን |
| 73 | የምሥራች ሰሎሞን (ወ/ት)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን |
| 74 | የትምወርቅ ሐሰን (ወ/ሮ)<br>ዘጋቢ | ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት |
| 75 | ይገዙ ሰሎሞን (አቶ)<br>የኢንፎርሜሽን፣ የትምህርትና የኮሙኒኬሽን ኤክስፐርት | ሶማሊ ክልል ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 76 | ደርጉ ቶላ(አቶ)<br>የክልሎች ሥነሕዝብና የአካባቢ ጉዳይ ቡድን መሪ | ብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት |
| 77 | ዘሪሁን ከበደ (ዶ/ር)<br>ረዳት ከፍተኛ መምህር | መገናኛ ብዙኃን ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት |

**ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት «ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን» (Population and the Media)**
**በሚል ርእስ ለጋዜጠኞችና ለሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በቀይ መስቀል ማሠልጠኛ ማእከል**
**ከየካቲት 7–9 ቀን 1992 ዓ.ም. የተካሄደው ዐውደጥናት መርሐግብር – አዲስ አበባ**

**የካቲት 7 ቀን 1992**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2:20–3:00 | ም ዝ ገ ባ | | |
| 3:00–3:10 | የመግቢያ ንግግር | አቶ ጎሩይ ምትኩ፣ የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ የትምህርትና የኮሙኒኬሽን ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ | |
| 3:10–3:30 | የመክፈቻ ንግግር | ክብርት ወ/ሮ ብሥራት ጋሻውጠና ፣ የማስታወቂያና ባህል ም/ሚኒስትርና ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ፣ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ | |
| 3:30–4:00 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |

| ሰዓት | ርዕስ | አወያይ | ጽሑፍ አቅራቢ |
|---|---|---|---|
| 4:00–4:30 | ሥነሕዝብ፣ ልማትና የአካባቢ ሁኔታ | ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ | አቶ ሢሣይ ወርቁ |
| 4:30–5:15 | ውይይት | » » » | » » |
| 5:15–5:45 | ሥነ ሕዝብና ኮሙኒኬሽን | » » » | አቶ አስረስ ከበደ |
| 5:45–6:30 | ውይይት | » » » | » » |
| 6:30–8:00 | ምሳ | | |
| 8:00–8:30 | የጤና ፕሮግራሞችና የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት | አቶ ጌታቸው ሚናስ | አቶ ገብረመድህን ኪዳነማርያም |
| 8:30–9:15 | ውይይት | » » » | » » » |
| 9:15–9:45 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |
| 9:45–10:15 | የወጣቶችና ተዋልዶ ጤና | ወ/ሮ ቦጋለች ዓለሙ | ወ/ሮ ገነት መንግሥቱ |
| 10:15–11:00 | ውይይት | » » » | » » » |

**የካቲት** 8 **ቀን** 1992 **ዓ.ም.**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3:00–3:30 | ያገራችን የሴቶችና የጐጂ ባህሎች ሁኔታ | ወ/ሮ አባይነሽ ብሩ | ወ/ሮ ቦጋለች ዓለሙ |
| 3:30–4:15 | ውይይት | | |
| 4:15–4:45 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |
| 4:45–5:15 | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሚዲያ | አቶ አስረስ ከበደ | ዶ/ር ኃይሉ ነጋሳ |
| 5:15–6:30 | ውይይት | » » | » » |
| 6:30–8:00 | ምሳ | | |
| 8:00–8:30 | ማኅበራዊ ግብይትና የሚዲያ ሚና | አቶ ጎሩይ ምትኩ | አቶ ደምሰው በቀለ |
| 8:30–9:15 | ውይይት | » » | » » |
| 9:15–9:45 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |
| 9:45–10:15 | በመገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ድራማዎች ለሥነ ሕዝብ ጠቀሜታ | አቶ አስታጥቃቸው ይሁን | አቶ በላይነህ አቡኔ |
| 10:15–11 | ውይይት | » » | » » |

**የካቲት** 9 **ቀን** 1992 **ዓ.ም.**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3:00–3:30 | ኪነጥበብና ማኅበራዊ ጠቀሜታው | አቶ ይገረም ረታ | አቶ ልጅ ወንድም ለአከማርያም |
| 3:30–4:30 | ውይይት | » » | » » |
| 4:30–5:00 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |
| 5:00–6:30 | የቡድኖች ውይይት (3 ቡድን)* | | |
| 6:30–8:00 | ምሳ | | |
| 8:00–9:30 | የቡድኖች ውይይት ይቀጥላል | | |
| 9:30–10:00 | የቡና/የሻይ ዕረፍት | | |
| 10:00–11 | አጠቃላይ የቡድን ውይይት ሪፖርትና መዝጊያ | | |

*3ቱ ቡድን ከተሳታፊዎች መካከል:–

1. ከኅትመት መገናኛ ብዙኃን (ከፕሬስና ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትና ሌሎች የኅትመት ሚዲያዎች)
2. ከኤሌክትሮኒክ ሚዲያ (ከተለያዩ ሬዲዮ ጣቢያዎችና ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን)
3. የቲያትር ጥበባትና የሥነጽሑፍ ባለሙያዎች

## በብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ለ3 ቀናት (የካቲት 15-17/1992 ዓ.ም) በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ማሠልጠኛ ማእከል «ሥነ ሕዝብና መገናኛ ብዙኃን (Population and the Media) በሚል ርእስ ባካሄደው ዐውደጥናት መዝጊያ ሥነ ሥርዓት ላይ ኃላፊው ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ ያደረጉት ንግግር

ክቡራን የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች፣

በዐውደጥናቱ መክፈቻ ዕለት እንደገለጽኩት ይህን ዐውደጥናት ስናዘጋጅ ሦስትና አራት ዓላማዎች ነበሩን:-

የመጀመሪያው፣ ጋዜጠኞቻችንና የኪነት ባለሙያዎቻችን ከሥነ ሕዝብ አኳያ ተገቢውን ግንዛቤ የሚያገኙበትን መድረክ ማዘጋጀት የሚል ነበር።

ከዚህ አኳያ ጥናታዊ ጽሑፍ ያዘጋጁልን ባለሙያዎች ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም። በተናገሩባቸው ርእሶች ላይ ከፍተኛ ግንዛቤ ለመጨበጥ ችለናል። ስለሆነም የመጀመሪያው ዓላማችን ከሞላ ጐደል ግቡን መቷል።

ሁለተኛው ዓላማችን፣ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር እስካሁን የተጓዝንበት ሕዝቡን የማስተማርና ግንዛቤ የመፍጠር ተግባራችን ምን ያህል የተሳካ ነበር? የሚል፣ ተገቢውን ግምገማ ማካሄጃ መድረክ መፍጠር ነበር። ይህም ካደረግናቸው ሰፊ ውይይቶች አኳያ ግቡን መቷል ማለት እንችላለን።

ሦስተኛው ዓላማ፣ ከምናደርጋቸው ውይይቶችና ግምገማዎች ተነሥተን መሠረታዊ ችግሮቻችን የትኞቹ መሆናውን በውል ለይተን መወጣት፣ የሚል ነበር። ከዚህም አኳያ ግልጽ አድርገን የተወያየንባቸው ችግሮቻችን ለመፍትሔ ፍለጋው መሠረት በመሆናቸው ሐሳባችን ተሳክቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዘው የተደረጉት የቡድን ውይይቶች፣ በመጨረሻም የተዘረዘሩት ችግሮችና የተጠቆሙት የመፍትሔ ሐሳቦች ያዘጋጀነው ዐውደጥናት ፍሬያማ መሆኑን አረጋግጠውልናል። ይህን ዐውደ ጥናት ከዚህ ደረጃ ማድረስ የብዙዎችን ትብብር ጠይቋል።

በተለይም ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎቹ በሰጠናቸው አጭር ጊዜ ይህን ሁሉ ማቅረብ በመቻላቸው በእናንተ በተሳታፊዎቹና በራሴም ስም ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

በጥናታዊ ጽሑፎቹ የቀረቡትን ሐሳቦች በውይይቱ ወቅት ለማዳበርና አስባስቦ ለወደፊቱ ተግባራችንና ዓላማችን ነጥረው እንዲወጡ በማድረግ የረዳው በመካከላችን የተገኛችሁት ባለሙያዎች ከፍተኛ ዕውቀት፣ ግንዛቤና ልምድ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ወትሮ አንድ ላይ ተሰባስባችሁ ማግኘት የሚገደንን ብዙዎቻችሁን እዚህ ተገናኝታችሁ በተነሡት የሥነ ሕዝብና የመገናኛ ብዙኃን ጉዳዮች ላይ ሐሳብና አስተያየቶቻችሁን ሁሉ ለማግኘት ይህ ዐውደጥናት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልናል፡፡

በሰነዘራችኋቸው የውሳኔ ሐሳቦች ውስጥ የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤትን የሚመለከቱና ከእኛም አልፈው የሚሄዱ ብዙ ሐሳቦች ተካተዋል፡፡ እነኚህ የውሳኔ ሐሳቦች ሥራችንን ለማስተካከል እንደሚረዱንና እኛም በዚሁ መሠረት መልክ ያለው ሥራ ለመሥራት በሚቻለን ሁሉ ጥረት እንደምናደርግ አረጋግጥላችኋለሁ፡፡ ከእናንተም ጋር የምንሠራበትን መንገድ ሁሉ እንደምናመቻችም ቃል እንገባለን፡፡

ባለፉት ስድስትና ሰባት ዓመታት ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን ለማስተዋወቅ ባደረግነው ጥረት ሁሉ ጋዜጠኞችና የቲያትር ጥበባት ባለሙያዎች ያደረጉትን ከፍተኛ ተሳትፎ በአድናቆት በመጥቀስ ሁላችሁንም በዚህ አጋጣሚ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

አሁንም ደግሜ አመሰግናለሁ፡፡

# ክፍል ሁለት

*ብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣*
*ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ*
*ማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናት*

## ስንኝቶች (Proceeding)

ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት

*ግዮን ሆቴል*
*መጋቢት 26 ቀን 1992 ዓ.ም.*
*አዲስ አበባ*

# ማውጫ


ገጽ

ሀ. የአማርኛ ስንኝቶች

1. መግቢያ .................... 182
   - የዓውደ ጥናቱ ዓላማ .................... 183
   - ዝርዝር ዓላማዎች .................... 183
   - ተሳታፊዎች .................... 183
   - የዓውደ ጥናቱ መርሃ-ግብር .................... 183

2. የዓውደ ጥናቱ ሂደት **(Proceeding)**.................... 184
   - የመክፈቻ ንግግሮች ዐበይት ነጥቦች

3. በሐራዊ የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሚኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ መነሻ ይዘት.................... 189

4. በሐራዊ የሥነ ሕዝብ ኢትኮ/አድቮኬሲ ተግባራትና የአፍሪካ ተሞክሮዎች .................... 192

5. በቀረቡት ሁለት ጽሑፎች ላይ የተነሱ ነጥቦችና አስተያየቶች .................... 192

6. የቡድን ውይይት .................... 194

7. በፌዴራል የሚቋቋመው ማዕከላዊ ኮሚቴ .................... 196

8. ስለ ዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት አስተያየት .................... 197

ለ. የእንግሊዝኛ ስንኝቶች .................... 199

1. **Sessions**
   - Opening .................... 200
   - Session1.................... 207
   - Session 2 .................... 211
   - Discussion .................... 216
   - Group Works .................... 221
   - Closing Session.................... 226

2. **Annexes**
   - Speeches.................... 277
   - Time Table.................... 237
   - List of Participants.................... 238

## 1. <u>መግቢያ</u>

በኢትዮጵያ ሆነ በየትኛውም የዓለም አካባቢ በርካታ የሥነሕዝብ ልማት መርሃግብሮች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገራችን ሥነሕዝብና ልማትን የሚያግዙ ሁኔታዎች በመመቻቸታቸው የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ተቀርጾ ዛሬ ለተግባር መሣሪያነት እንዲያገለግል ይፋ ለመሆን በቅቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በ1993/እ.ኤ.አ/ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ፖሊሲን ከማውጣቱም ባሻገር የጤና ፖሊሲ የብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲና ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች ሥራ ላይ በመዋላቸው የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽንን አስፈላጊነትና ዋና ሚናን ሊያጎሉት ችለዋል። ከዚህ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ የሥነሕዝብና ልማት ጉባኤዎች የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንን እንደአንድ ፕሮግራም ሆኖ እንዲያገለግል አድርገውታል።

የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ፕሮግራም ለሥነሕዝብ ፕሮግራሞች መሳካት አቢይ መሣሪያ እንደሆነ ሁሉ የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ስትራቴጂም ለጥሩ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ፕሮግራም የመሠረት ድንጋይ ነው። በሚገባ የተጠናና የተቀረጸ ስትራቴጂ ዋና ዋና ጉዳዮችን ለመለየት፣ የባህርይ ለውጥ ለማምጣትና ታዳሚን ለመምረጥ፣ የተሳካ መልዕክት ለመቅረጽ፣ተስማሚ የመገናኛ ዘዴ ለመወሰንና የተገኘውንም ለውጥ ለመገምገም ያስችላል።

የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ስትራቴጂ ዋና ዓላማም ቁልፍ የሆኑ የሥነሕዝብ ጉዳዮችን በመለየት ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ሥራ ለሚሠሩ መመሪያ በመሆን ተቀባይነት ያለው የንድፈ ሀሳብም ሆነ የተግባር መሣሪያ ሆኖ የሥነሕዝብ ፕሮግራሞች ክንውን፣ አደረጃጀት፣ ክትትልና ግምገማ ስልቶችን በማሳየት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲን ሥራ ውጤታማ ያደርጋል።

በዚህ መሠረት የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሰ ስትራቴጂ ይፋ ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል የአንድ ቀን የማስተዋወቂያ ዐውደጥናት መጋቢት 26/1992 በግዮን ሆቴል በማካሄድ የስትራቴጂውን ጠቀሜታና አጠቃላይ ገጽታ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ተሳታፊዎች አስተዋውቋል።

## የዓውደጥናቱ ዓላማ

የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢትኮ/ አድቮኬሲ ስትራቴጂ የማስተዋወቂያ ዐውደጥናት ዓላማ በሥነሕዝብ ልማት ጉዳዮች የሚያገባቸው አካላት (Stakeholders)ስትራተጅውን ተገንዝበው በሥራ ላይ በማዋል ሥነሕዝብ ኢትኮ/ አድቮኬሲ ሥራ ሥርዓት ባለው መንገድ ለመምራት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

## ዝርዝር ዓላማዎች፣

- የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢትኮ/ አድቮኬሰ ስትራቴጂ ሠነድ በሥራ ላይ እንዲውል በመንግሥት በኩል ይፋ መሆኑን ለማሰተዋወቅ፣
- ሥነሕዝብ ኢትኮ/ አድቮኬሲ ስትራቴጂ ሠነድ መነሻ ይዘት ለተሳታፊዎቹ በማሰተዋወቅ ግንዛቤ መፍጠር፣
- የሚመለከታቸው አካላት (Stakeholders) የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢትኮ/ አድቮኬሲ ስትራቴጂን በሥራ ላይ እንዲያውሉት ማነሳሳት።

## ተሳታፊዎች፣

ብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂን ወደ ተግባር መሸጋገር በሚያስተዋውቀው ዓውደጥናት ላይ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ምክትል ምኒስትር፣ በተባበሩት መንግሥታት ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት (UNFPA) የኢትዮጵያ ተወካዮች የተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤት ማለትም የግብርና፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር ተወካዮች፣ የክልል ሥነሕዝብ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የተለያዩ መንግሥታዊና ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና ሥነሕዝብ ፕሮግራም ላይ የሚመለከታቸው ከ61 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።

## የዓወደጥናቱ መርሃግብር፣

ለአንድ ቀን የተካሄደው የማስተዋወቂያ ዓውደጥናት መርሃ-ግብር የእንኳን ደህና መጣችሁ የመክፈቻ ንግግር አካቷል። በመርሃግብሩ መሠረት የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢትኮ/አድቮኬሲ ስትራቴጅ ሠነድ መነሻ ይዘት የሚያብራራ ጽሑፍ ቀርቧል። በብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢትኮ/አድቮኬሲ ስትራቴጅ ላይ የአፍሪካ ሀገሮችን ልምድ የሚዳስሰው ጽሑፍም መግለጫ ተሰጥቶበታል። በቀረቡት ሁለት ጽሑፎች ላይ ውይይት

ተካሂዷል። የሥነሕዝብ ኢትኮ/አድቮኬሲ ስትራቴጅ የቅንጅት ስልት ምን መምሰል እንዳለበት የቡድን ውይይት ተካሂዶ በብሔራዊ ሥነሕዝብ ጽ/ቤት የሚመራ አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ በመመሥረት የዓውደ ጥናቱ መርሃግብር ተጠናቋል።

## 2. *<u>የዓውደ ጥናቱ ሂደት /Proceeding/</u>*

### *<u>የመክፈቻ ንግግሮች ዐበይት ነጥቦች</u>*

በብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ወደ ተግባር መሸጋገሩን በሚያስተዋውቀው አውደ ጥናት ላይ የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን፣ የተባበሩት መንግሥታት የሥነ ሕዝብ ፈንድ ጽ/ቤት ተወካዮችና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ትምህርት ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ንግግር አድርገዋል።

አቶ ኅሩይ ምትኩ የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና መገናኛ ብዙሃን ጉዳይ ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ የማስተዋወቂያ ንግግር ያደረጉ ሲሆን የስትራቴጂው ወደተግባር መሸጋገር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ዘርዝረዋል። አቶ ኅሩይ ስትራቴጂው በተዋልዶ ጤና፣ በሥነ ሕዝብና ልማት መጣጣም ረገድ ለሚከናወኑ ተግባራት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ አስገንዝበው የሕዝብን አስተሳሰብ፣ ዕምነት፣ እሴትና ባህርይ ለመለወጥና በፖሊስዎች፣ በስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ላይ ተጽእኖ ለማሳደርና በተጨማሪም በተወሰኑ ጉዳዮች የግለሰቦችንና የህብረተሰቡን ድጋፍና ተቆርቋሪነት ለማትረፍ የተፈለገውን ለውጥ ለማስገኘት ስትራቴጂው አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ብለዋል። የዚህ ዓውደጥናት ዓላማም የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከሚመለከታቸው አካላት በማቋቋም የስትራቴጂውን ተግባራዊነት መከታተል እንደሚሆን አቶ ኅሩይ ለተሳታፊዎች አስገንዝበዋል።

ወ/ሮ ገነት መንግሥቱ የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ተ/ኃላፊ ሁሉንም በጋራ በሚመለከተው በሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ወደ ተግባር መሸጋገር ዓውደ ጥናት ላይ ጥሪውን አክብረው በመገኘታቸው ተሳታፊዎችን በጽ/ቤቱና በራሳቸው ስም አመስግነዋል።

ወ/ሮ ገነት የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ባለፉት ዓመታት በተለያዩ የሥነ ሕዝብ ፕሮጄክቶች ታቅፈው ፕሮግራሙን ያስፈጽሙ የነበሩትን የተለያዩ ድርጅቶችን በማስተባበር በፖሊሲው ላይ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ጥረት

ማደረጉን አስገንዝበው ዛሬ በሚካሄደው በሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ እስትራቴጂ ሥራ ላይ ለመዋል የሚወያየው ዐውደ ጥናትም የቅንጅት ሥራውን ለመጀመር የሚያስችል መንገድ የሚፈጥር በመሆኑ ወደፊት ለሚጠ ብቀን የአፈጻጸም ተግባር አመቺ መንገድ የሚቀይስ እንደሚሆን ገልጸዋል።

የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቬኬሲ ስትራቴጂ ዶኩመንት በተዋልዶ ጤናና በሥነ ሕዝብና ልማት ሥር የሚነሡ ዋና ዋና ጉዳዮችን ትኩረት በመስጠት ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጨባጭ በሆነና በተከታታይ መልኩ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ተገቢውን አቅጣጫ የሚጠቁም መሆኑን ወ/ሮ ገነት አብራርተው በሥነ ሕዝብ ዙሪያ የተዋልዶ ጤናን ጨምሮ በሚነሡት አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ትምህርት ከግንዛቤ ባሻገር የአስተሳሰብና የባሕርይ ለውጥ የሚያስገኝ ሆኖ እንዲከናወን የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አስረድተዋል።

ይህንን ስትራቴጂ በማዘጋጀት የተባበሩትን ሁሉ ወ/ሮ ገነት አመስግነው ክቡር አቶ መኩንን ማንያዘዋል፣ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ለስትራቴጂው ዶኩመንት ተግባራዊነት መነሻ የሚሆን የቅንጅት አሠራር ስልት ለመፍጠር የተጠራውን ዐውደጥናት በንግግር እንዲከፍቱ ጋብዘዋል።

ክቡር ም/ሚኒስትሩ በንግግራቸው እንዳስገነዘቡት መንግሥት ገና ከመነሻው የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ፖሊሲን አውጥቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው የሕዝብ ቁጥር ከኢኮኖሚው እድገት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ከሚያስችሉ ተግባራት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የተዋልዶ ጤና፣ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ የሥነ ሕዝብ መረጃ አሰባሰብ ትንተናና ስርጭትን በማጠናከር፣ የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ሥራን በስፋትና በጥራት በማካሄድና በሥነ ሕዝብና ልማት አስፈላጊውን ዐቅም በመፍጠሩ ረገድ ሰፊ ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን አስገንዝበዋል።

ፖሊሲው ይፋ ከሆነ ወዲህ የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ክንዋኔ ሲገመገም ለሥራው ሂደት የሚያግዙ በቅድሚያ መደረግ ለሚገባቸው ተግባራት ትኩረት መስጠቱና የፕሮግራሙ አስፈጻሚ የሆኑ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ሙያውን በተመለከተ በተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲሳተፉ በመደረጉ የሥነ ሕዝብ ፕሮግራም ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲጓዝ እገዛ ማድረጉን ክቡር ም/ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤትን በሰው ኃይል የማጠናከሩ ተግባር እየተከናወነ በመሆኑ ሥራውን በማእከልና በክልል ለመከታተል አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን የጠቀሱት የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ምክትል ሚኒስትር በመደበኛው ትምህርት ዘርፍም የሥነ ሕዝብና የቤተሰብ ኑሮ ዘዴ ትምህርቶችን /POP/FLE/ ለማዳረስ በተደረገው ጥረት በሥርዓተ ትምህርቱ የሥነ ሕዝብ ዋና ዋና ጉዳዮችን በማካተትና የተለያዩ የማስተማሪያ መጻሕፍትንም በማዘጋጀት ተማሪውንና የት/ቤቱን ማኅበረሰብ ግንዛቤ ለማዳበር የተደረገው ጥረት አመርቂ ነው ብለዋል።

በሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ስርጭት በኩል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በማተኮር የግንዛቤ አድማሱን ለማስፋት የሚያስችል ትምህርት በመስጠቱ በአሁኑ ጊዜ በዐቅም መጥኖና አራርቆ የመውለድን ጠቀሜታና ሌሎችንም በሥነ ሕዝብ ጉዳይ የሚነሡ ችግሮችን የተረዳው የኅብረተሰብ ክፍል ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ጥናቶች እንደሚጠቁሙ ያስረዱት አቶ መኰንን በሥነ ሕዝብ አንገብጋቢ ችግሮች ላይ ግንዛቤ ማሳደሩ የትምህርቱ ሂደት የመጀመሪያው ምዕራፍ መሆኑንና ወደምንፈልገው የመጨረሻ ግባችን ለመድረስ ገና ብዙ እንደሚቀረን ለዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አስገንዝበዋል።

ቀሪ ተግባራችንን ለማሳካት ዛሬ በዚህ ዐውደጥናት የተገኙትና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወደፊት የጋራ የሆነ ስፊና ተከታታይ የቅንጅት ሥራ እንደሚጠ ብቃቸው አሳስበው የዐውደ ጥናቱ ዋና ዓላማም የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ዝግጅት ተጠናቆ በመንግሥት በኩል ወደ ተግባር መሸጋገሩ እንዲታወቅና ቀጣዩን የአድቮኬሲ ተግባራት አፈጻጸም ስልት በጋራ በመንደፍ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ማበርከት እንድትችሉ ነው ብለዋል።

ዛሬ በዐውደጥናቱ የቀረበው የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ እስትራቴጂ ሠነድ ለወደፊቱ የሥነ ሕዝብ ትምህርት ስርጭት የመጀመሪያ የሆነ የጋራ መመሪያ መሆኑንና ሠነዱ ሲዘጋጅ የሚመለከታችሁ ሁሉ ጠ ቃሚ አስተዋጽኦ በማበርከት የጋራ ሠነድ እንዲሆን እንዳደረጋችሁት ሁሉ የወደፊት አፈጻጸሙን በተመለከተ በቡድን ውይይት የጋራ ስልት ቀይሳችሁ በቅንጅት መሥራት ይጠበቅባችኋል በማለት ያሳሰቡት አቶ መኰንን ሥራውን በተጠናከረ መንገድ ለማከናወን ከማእከል እስከ ክልል የሚገኙትን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ የሆኑም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መ/ቤቶች ተቀናጅተው በመንቀሳቀስ ውሱን የሆኑትን ባለሙያዎችና ብ ቃት ያላቸውን ተቋማት በጋራ በመጠቀም ድግግሞሽን በማስወገድ በአነስተኛ ወጪ የሚፈለገውን አጥጋቢ ውጤት ማስገኘት እንደሚቻል አስገንዝበዋል።

ተቀናጅተን ከሠራን ውጤታማ የማንሆንበት ምክንያት የለም፣ ያሉት ምክትል ሚኒስትሩ ቅንጅታዊ የአፈጻጸም ስልት መንደፍ ብቻውን በቂ አለመሆኑንና ይልቁንም ወሳኙ በሥራ ድርሻችን ስልቱን በመጠቀም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማፋጠን ይኖርብናል፣ በማለት ለዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች በአንክሮ አሳስበዋል።

በተባበሩት መንግሥታት የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኢትዮጵያ ተወካይ ሚስተር ቤንሰን ሞራ ለዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ባሰሙት ንግግር የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ልዩ ልዩ የዝግጅት ሂደቱን አጠናቆ ዛሬ በሥራ ላይ እንዲውል ይፋ ሲደረግ የተሰማኝ ደስታ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

በዚህ ሰነድ ዝግጅት የተባበሩት መንግሥታት የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት /UNFPA/ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ድርሻውን እንደተወጣ ያስገነዘቡት ሚስተር ቤንሰን በስትራቴጂ ሰነዱ ዝግጅት ከማዕከል እስከ ክልል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ጥልቅ ውይይትና ሰፊ ምክክር አድርገውበት ይህን ከፍተኛ ተቀባይነት ያለውን የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ አስገኝተዋል በማለት አስረድተዋል።

ይህ ሰነድ በአግባቡ ሥራ ላይ ሲውል የታለመውን ግብ እንደሚመታ እተማመናለሁ ያሉት ሚስተር ቤንሰን ሞራ ስትራቴጂው በተዋልዶ ጤና፣ በሥነ ሕዝብና ልማት ቁልፍ የሆኑ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን ለሕዝብ ለማዳረስ የሚያስችል መመሪያ ከመሆኑም በላይ ትርጉም ያለው የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን በመጠቀም የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል ብለዋል። በተጨማሪም የሥነ ሕዝብ ፕሮግራሞችን አፈጻጸም፣ ማኔጅመንት እንዲሁም አደረጃጀት ለመከታተልና ለመገምገም ስትራቴጂው ከፍተኛ መሣሪያ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

አግባብ ያላቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች፣ ለጋሾች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በሥነ ሕዝብ መስክ የተሰማሩ አካላት የስትራቴጂውን ሰነድ ይዘት ጠንቅቀው በማወቅ ለኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ሥራቸው በመመሪያነት እንደሚገለገሉበት አምናለሁ ሲሉ ሚስተር ቤንሰን ሞራ አብራርተዋል።

በመጨረሻም ለተባበሩት መንግሥታት የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ግለሰቦች፣ በተጨማሪም አለም አቀፍ ድርጅቶች /USAID/፣ ጆን ሆፒከንስ ዩንቨርስቲ /Johon Hopkins University/ እና ኮርኔል ዩንቨርስቲ /Cornell University/ የኮሙኒኬሽን መምሪያ፤ የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣

ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂን ከቀረጻው እስከ ፍጻሜው ለማድረስ የረዱትን ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

አቶ ገ/መድህን ኪዳነማርያም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ትምህርት ማዕከል ዋና ሥራ አስኪያጅ በዓውደጥናቱ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ዝግጅት ከመጀመሪያው ጀምሮ ሲካፈልበት የቆየ መሆኑን አውስተው ዛሬ ስትራቴጂው በሥራ ላይ እንዲውል ይፋ መደረጉ በጣም አስደስቶኛል ብለዋል፡፡

በተለይ በተዋልዶ ጤና ተግባራት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ሰነድ በመጠቀም አይነተኛ ውጤት እንደምናስገኝ እናምናለን ያሉት የጤና ትምህርት ማዕከሉ ኃላፊ ሥራችንን በተቀናጀ መንገድ ለመምራት ስትራቴጂውን በመመሪያነት በመጠቀም ከሁሉም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ለመሥራት ተዘጋጅተናል ካሉ በኋላ ስትራቴጂው ሁሉም የሥራው ባለቤቶች በጋራ እንዲንቀሳቀሱ የሚጋብዝ በመሆኑ በሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ በጋራ ከሠራን መ/ቤታችን ከዚህ ብዙ እንደሚጠቀም ዕምነቴ የፀና ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

## 3. ብሔራዊ የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ መነሻ ይዘት፡-

*አቶ አስረስ ከበደ በብሔራዊ ሥነሕዝብ ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ አማካሪ*

### የቀረበው ጽሑፍ ጥቅል ሀሳብ

አቶ አስረስ በአቀረቡት ጽሑፍ የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ የሥነሕዝብ ፕሮግራሞችን ለማከናወን የመሠረት ድንጋይ በመሆኑ የሥነሕዝብ ጉዳዮችን ለይቶ ለማወቅ፣ የባህርይ ለውጥ ለማስገኘት፣ አቅምን ለመገንባት፣ ሊደርስበት የሚገባን ታዳሚ ለይቶ ከማውጣትና ለማነሳሳት፣ ሊተላለፍ የሚገባውን የተመረጠ መልዕክት ለማዘጋጀትና ሥራውን ለመከታተልና የተገኘውንም ለውጥ ለመገመገም የሚያስችሉ ስልቶችን ለተጠቃሚዎች እንደሚናሳይ አስረድተዋል።

የስትራቴጂውን ቀረጻ ሂደት በተመለከተ በ1995/እ.አ.አ/ በብሔራዊ ደረጃ የኢትኮ/ አድቮኬሲ ግብረሃይል በብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት በኢንፎርሜሽን ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽን ማስተባበርያ ሥር ተቋቁሞ ሥራውን እንደጀመረና ግብረሃይሉ በአማካሪዎች፣ በተባበሩት መንግሥታት ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ እንዲሁም የሀገር አቀፍ ፕሮግራሙን ከሚደግፉ ልዩ ልዩ ቡድኖችና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ጥናቶችን መርምሯል፤ ለስትራተጂው ቀረጻ የሚያገለግሉ ሁኔታዎችን በጥልቀት ተንትኗል። ሦስት አጋዥ የሆኑ ጥናቶችን በመፈተሽ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ዝግጅት የሚረዱ ሁኔታዎችን በመገምገም ምቹ ሁኔታዎችንና እጥረቶችን ለመለየት መቻሉን አስገንዝበዋል። በተደረገው ትንተናም የሚከተሉት የኢትኮ/አድቮኬሲ ሁኔታዎችን ለመለየት/ለማወቅ ተችሏል።

- የሥነሕዝብ ፖሊሲ መውጣት ለኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ሥራ መስፋፋት/መስፈርት/የሚያመች መሆኑ፣
- የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽንን ሥራ ለማቀናጀት የተደረገው ጥረት በጅምር ላይ መሆኑ፣
- የኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ሥራ ስትራቴጅካዊ አቀራረብ የሌለው መሆኑ፣ ይኸውም ጉዳዮችን ለይቶ በማወቅ፣ ዓላማና ግብን በመወሰን፣ ታዳሚን በመለየት፣ መልዕክትንና ማስተላለፊያ ዘዴዎችን

በመምረጥ እንዲሁም በክትትልና ግምገማ ስትራቴጅካዊ አቀራረብ ያልነበረ መሆኑ፣

- በቂ ጥናትና ምርምር አለመካሄድ፣
- ሥራውን ለመሥራት ደካማ መዋቅርና አደራጃጀት መኖር ይህም የሚያስተባብሩ፣ የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጡ፣ ሥራውን በቀጥታ የሚሠሩ አካላት መካከል ግልጽ የሆነ የሥራ ዝርዝር (ድርሻ) አለመኖር፣
- ብቁ የሆነ የሰለጠነ የሰው ሃይል፣ ቁሳቁስና ገንዘብ አለመኖር፣
- ከፕሮግራሙ ጋር ተሳስሮ ያለመሄድ፣
- የመገናኛ መሠረተ ልማቶች ተስፋፍተው አለመገኘት
- በሁሉም ቋንቋዎችና ባህሎች ግንኙነት ለመፍጠር አለመቻል
- ሴቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘትና ለፆታ ጉዳዮች በቂ ትኩረት አለመስጠት፣
- ያልተማከለ የአስተዳደር መዋቅር መኖርና የክልሎች መፈጠር የኢትኮን ሥራ ለህዝብ ለማድረስ ምቹ መሆኑን::

በ1996 /እ.አ.አ/ የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርት ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲን ስትራቴጂ ለመቅረጽ በግዮን ሆቴል የተካሄደው ዓውደ ጥናት ጉዳዩ የሚያገባቸውን አካላት በሙሉ በመጋበዝ የስትራቴጂውን ቁልፍ ነጥቦችን በጋራ ውይይት በማዳበር የጋራ ሀሳብ እንደሆኑ ለማድረግ መቻሉን አቶ አስረስ አስረድተዋል::

የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ በሁለት ዓቢይ ዓላማዎች ላይ ያተኮረ መሆኑን የገለጹት አቶ አስረስ ዋና ዋናዎቹ:–

1ኛ/ የተዋልዶ ጤና፣

2ኛ/ የሥነሕዝብና ልማት መሆናቸውን በዝርዝር አብራርተዋል::

የተዋልዶ ጤና የሚያተኩርባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ:: ዋናዋናዎቹ ጤናማ እናትነት፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታዎች HIV/AIDs ጨምሮ፣ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ የፆታ ጉዳዮች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መሆናቸውንና እነዚህን ጉዳዮች ለሕዝብ ለማድረስ ስትራቴጂው የነደፋቸውን ስልቶች ከተጠቀምን የባህርይ ለውጥ ለማምጣት ያስችለናል ሲሉ አስገንዝበዋል::

ሥነሕዝብና ልማት የሚመለከታቸው ጉዳዮች ፈጣን የሕዝብ ዕድገት፣ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ፖሊሲን መተግበር፣ የታና ልማት፣ ጥናትና ምርምር፣ የሥነሕዝብ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ማሰራጨትና ወጣቶች ልማትና ሌሎች የሥነሕዝብ ጉዳዮችን እንደሚያካትትና የኢ.ትኮ/አድቮኬሲ ሥራን ለመሥራት የምንከተላቸውን የአሠራር መርሆዎች ስትራቴጂው በሚገባ አመልክቷል።

የኢ.ትኮ/ አድቮኬሲ ስትራቴጂ መሠረታዊ መርሆችና የትኩረት መስኮቹ፣ በባህርይ ለውጥ ላይ ማተኮር የኢ.ትኮን ተግባራት ከአገልግሎት ጋር ማጣመር፣ ብዙውን ታዳሚ ለመድረስ መጣር፣ በክልሎችና በህብረተሰቡ ላይ ማተኮር፣ ለሥራው መመዘኛና ደረጃ እንዲኖረው ማድረግ፣ የሥራ ጥራትና ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚሆን አቶ አስረስ በአቀረቡት ጽሑፍ አስገንዝበዋል።

## 4. *የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ኢትኮ/አድቮኬሲ ተግባራትና የአፍሪካ ተሞክሮዎች*

*«ሚስተር ዱዋ አሚሉ ሰንፎሬ በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ሥነ ሕዝብ ፈንድ ጽ/ቤት (UNFPA) ምክትል ኃላፊ (Deputy representative)»*

ሚስተር ዱዋ በአቀረቡት ጽሑፍ የዓለም የሥነ ሕዝብ ልማት ጉባኤ (ICPD) የሕዝብ ቁጥር መቀነስ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ በመለወጥ የሥነ ሕዝብና ልማትን ተያያዥነት በመገንዘብ ሥነ ሕዝብና ልማትን ማጣጣም በሚል አብይ መርህ ተመርኩዞ ፕሮግራሞችን ማካሄድ መጀመሩን ጠቅሰው ለውጥ በራሱ ብዙ ውጣውረድ ያለውና ውስብስብ መሆኑን አስረድተዋል።

ለውጥ ሲባል ግልሰቦች፣ ማኅበረሰቡ አጠቃላይ አገርና ድርጅቶች ይከተሉት የነበረውን የአሠራር ሥርዓት መቀየርን፣ በተዋልዶ ጤና መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የነበራቸውን ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ድርጊቶችን መለወጥን፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ማወያየት፣ በተፈለገው ለውጥ ላይ ፅኑ እምነት ያላቸው አካላት መፍጠርና ለለውጡ ግንባር ቀደም ተሰላፊ እንዲሆኑ ማድረግን ያጠቃላል ብለዋል።

በዚህ ረገድ የአፍሪካ ተሞክሮዎች የሚያመለክቱትን የኬንያ ወጣቶች ለአካባቢ እንክብካቤ የሚያሳዩት ተቆርቋሪነት፣ በተዋልዶ ጤና በተለይ በሴት ልጅ ግርዛት በጋና ፖሊሲና መመሪያ መውጣቱ፣ በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ስርጭት መስፋፋት በዚምባብዌና ሌሎችም እንደ ዩጋንዳ የመሳሰሉት ሀገሮች በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ለውጦች ያሳዩ በመሆናቸው ብዙ ልንማርባቸው እንደምንችል ሚስተር ዱዋ አብራርተዋል።

### *አድቮኬሲ ምንድን ነው?*

የሥነ ሕዝብ አድቮኬሲ የድርጊቶች ስብስብ ሲሆን እምነት ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች የጋራ ድጋፍ በማስገኘት በፖሊሲዎች በስትራቴጂዎችና በፕሮግራሞች ላይ አወንታዊ ለውጦች (ተፅእኖዎች) በማድረግ ሕዝቡ እንዲተገብራቸውና እንዲደግፋቸው ተስማሚ ድባብ (ሁኔታ) መፍጠር መሆኑን የገለጹት ሚስተር ዱዋ፣ የሥነ ሕዝብ አድቮኬሲ ዋና ዓላማ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን በማሻሻልና በማስተካከል የሥነ ሕዝብና የተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞች ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ሕብረተሰቦችን በማነሳሳትና በማስተባበር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስቻል ነው ብለዋል።

በሥነ ሕዝብ አድቮኬሲ ውስጥ ሁኔታዎችን በመተንተንና ጥናትና ምርምር በማድረግ በብሔራዊ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ ያለው ፖሊሲ ከሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ጋር ያለውን ትስስር ማጤን ተገቢ ይሆናል። የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን ወይም ችግሮችን ለማቃለል በፖሊሲዎችና ሕጐች ላይ ሊኖር የሚገባውን አወንታዊ ለውጥም ማየት ተገቢ ነው። ምን አይነት የፖሊሲ፣ የሕግና የማህበረሰብ ድርጊቶች ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው መታሰብ አለበት። በሥነ ሕዝብ ጉዳዮች (ችግሮች) ዙሪያ የሚመለከታቸው አካላት እነማን እንደሆኑ በመለየት፣ ደጋፊዎችን፣ ተቃዋሚዎችንና ኟሪዎችን (gatekeepers) እንዲሁም ውሳኔ ሰጪ አካላትን አበጥሮ ማወቅ ይጠይቋል፡፡ ውሳኔዎች እንዴት እንደሚተላለፉና የሚተላለፉት ውሳኔዎች በውሳኔ ሰጪዎች፣ በፓርላማ አባላት፣ በሕብረተሰቡና በባሕላዊ መሪዎች የሚፈጠሩትን የአመለካከት ለውጥ ማመዛዘን ይኖርብናል። መልዕክቱ የሚተላለፍባቸውን ዘዴዎች በመምረጥ ለውሳኔ ሰጪዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ለአድቮኬሲ ሥራ የምንከተላቸው ሂደቶች መሆን አለባቸው ሲሉ ሚስተር ዱዋ አስገንዝበዋል።

የአድቮኬሲ ስትራቴጂ ግልጽ የሆነ መንገድኖሮት የተፈለገውን ዓላማ ለማስገኘት የሚያስችል ስልት ነው። ስትራቴጂው የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን ለመተግበር የአደረጃጀት መካኒዝም ምን መሆን እንዳለበት ያሳያል። ይኸውም የሚያስተባብሩ ድርጅቶች እነማን ይሁኑ? የሚተገብሩ የተለያዩ ድርጅቶችስ እነማን ናቸው? ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶችስ? የሚሉትን ጉዳዮች በመለየት ሥራዎች ከተገቢው አካል ጋር እንዲፈጸሙ በግልጽ ያሳያል። ለተፈለገው ታዳሚ የሚሆኑ ተግባራትን ማቀድ ለዕቅዱ ማስፈጸሚያ የተግባር መርሐግብርና በጀት ማዘጋጀት፣ መልዕክቶች አግባቢ ቅልብጭ ያሉና ስሜትን የሚነኩ እንዲሆኑ አድርጐ ማዘጋጀት፣ የማስተላለፊያ ዘዴዎች በርካታ እንዲሆኑ (milti media approach) እንዲኖራቸው ማድረግና የተገኘውንም ለውጥ ለመከታተልና ለመመዘን የሚያስችል እንዲሆን በማድረግ ድጋፍን በማስገኘት ሊኖር የሚገባውን የፖሊሲና የሕግ ለውጥ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት እስትራቴጂው ያተኮረባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

የኢትዮ/አድቮኬሲን ስትራቴጂ ለመተግባር ሊኖር የሚገባውን ትብብር በተመለከተ የተግባር መርሐ ግብሩ ዕቅድ ሁኔታዎችን የሚያመለክት የተፈለገውን ታዳሚና ተግባሮችን ለይቶ በማሳየት የሚፈጸምበትን ጊዜና ለክትትልና ግምገማ የሚያስፈልጉ መለኪያዎችን የሚያስቀምጥ ሆኖ ተዘጋጅቷል። ለሚተባበሩ አካላት ኃላፊነትና ሥልጣን ማከፋፈል ያስፈልጋል። የጋራ ጥረታቸውን ለማጠናከር የሚያስችል ትስስር (Network) መፈጠር አለበት። የአድቮኬሲ ሥልጠናና ተግባሮችን

ማደረጃት፣ ቁልፍ መረጃዎችን ለይቶ በመስጠት ዓላማውን እንዲደግፍ ማድረግ፣ ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር የራስን አቋምና አላማ ማስተሳሰር፣ የሰዎችን ፍላጐትና ጥቅም በመልዕክታችን ውስጥ ማካተት፣ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ምን ያህል አንገብጋቢና ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሚያስገነዝቡ ዜናዎች በመገናኛ ብዙኃን በማሰራጨት መረጃዎችን በተገቢውና በትክክለኛው ሰው እንዲገለጽ በማድረግ ሕብረተሰቡ እንዲደግፋቸው ማስተባበር በእስትራቴጂው መብራራቱን አስገንዝበዋል፡፡

ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ሥራ ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ በየጊዜው ክትትል በማድረግ አስተያየታቸውንም ሆነ የተ ቋው ሞ ሀሳብ ከአላቸው ተገንዝቦ በአግባቡ መፍታት፤ በዕቅዱ መሠረት ተግባሮችን በወጣላቸው መርሐግብር መሠረት እንዲያከናውኑ ማግባባት ግንኙነት መፍጠር፣ መሰብሰብና መረዳዳት ያስፈልጋል፡፡ በሥራው የተባበሩ አካላትን ስለሥራውና ስለተገኘው ውጤት መረጃ መለዋወጥ፣ የመገናኛ ብዙኃን ድጋፍ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የሚነሱ አጨ ቃጫቂ ጉዳዮችን አለመፍራትና ተገቢውን ውጤት እንዲያስገኝ ማድረግ፣ ሕገወጥና ከሥነ ምግባር ውጪ የሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮችን አለማስተናገድ፣ ፖሊሲ አውጪዎች ለገቡት ቃል ኪዳን ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የተገኙ አመርቂ ውጤቶችንም ሆነ ውድቀቶች መመዝገብ፣ ሕብረተሰቡ በተገኙት አወንታዊ ለውጦች ላይ ያለውን አስተያየት መከታተል፣ ፖሊሲ አውጪዎችንም ሆነ በጉዳዩ የተባበሩ አካላትን ለፈጸሙት ተግባር ምስጋና ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተብራርቷል፡፡

የተገኘውን ውጤት ለመከታተልና ለመገምገም መሣሪያዎች ያስፈልጉናል ያሉት ሚስተር ዱዋ በመጀመሪያ ሥራውን በመከናወን ላይ እያለ የሂደት አመልካቾችን በማዘጋጀት አንድን ተግባር በመገምገም የተገኘውን ውጤትና ያለውን ክፍተት በመተንተን ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል፡፡ በሥነ ሕዝብ ጉዳዮች የተደራጁ አካላት ብዛት፣ የተደራጁ የሕብረሰብ ክፍሎች ብዛት፣ ዕኑ እምነት ኖሯቸው ለጉዳዩ ጊዜያቸውን በመስጠት የሚሳተፉ የፖሊሲ አውጪዎች ቁጥር፣ የተለወጡ ሕጐችና ባህላዊ ድርጊቶች፣ በጉዳዩ ላይ የተገኘ ተጨማሪ ሀብት መለኪያዎች ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ሲሆን የተገኘውን ውጤት ከመለኪያዎች ጋር በማነጻጸር መገምገም የሚቻል መሆኑን ሚስተር ዱዋ አስረድተው ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በየጊዜው የሥነ ሕዝብ አድቮኬሲ ሂደትን በመገምገም ስትራቴጂውን ማሻሻልና ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

## *5. በቀረቡት ሁለት ጽሑፎች ላይ የተነሱ ነጥቦችና አስተያየቶች*

- የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ የወጣው የ4ኛው አገር አቀፍ ፕሮግራም ከተጀመረ በኋላ ነው ይህን እንዴት ማጣጣም ይቻላል?

- ይህን ስትራቴጂ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገን ገንዘብ መጠን ይታወቋል?

- በምዕራብ አፍሪካና በደቡብ አፍሪካ ሀገሮች የኢትኮ/አድቮኬሲ ትግበራ ላይ ያለው ተሞክሮ ምን ይመስላል?

- በሠነዱ ላይ የፆታ ጉዳዮች ተንፀባርቀዋል፣ ያለዕድሜ ጋብቻ ለምን ትኩረት አልተሰጠውም?

- የሥነሕዝብ ጉዳዮችን በተመለከተ መሪዎች የሚመለከታቸው አካላት በመነናኛ ብዙሃን ተናግረው ያውቋሉ ወይ?

- "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" የሚለው አባባል ከአድቮኬሲው አንፃር እንዴት ሊሠራ ታስቧል?

ከላይ በተነሱት ነጥቦች አቅራቢዎችና ባለሙያዎች በቂ ማብራሪያ ስጠውበታል፡፡ በዚህ መሠረት የብሔራዊ ሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርት ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራተጂ ለአገር አቀፍ ፕሮግራም አፈጻጸም እንደመመሪያ ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ለስትራተጂው የሚያስፈልገውን ገንዘብ በተመለከተም ቅንጅት ከሰራን የገንዘብ ችግር የማይገጥመን መሆኑን በተሳታፊዎች አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

ስትራተጅውን በመተግበር የምዕራብ አፍሪካና የደቡብ አፍሪካ ልምዶችን ብንመለከት በፓርላማው ውስጥም ውይይት ለመፍጠር በመቻሉ የጋብቻ ዕድሜ ለውጥ ተደርጎበታል፡፡ ለምሳሌ በጋና የጋብቻ ዕድሜ ወደ 16 ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ በዚንባብዌ የኮንዶም ስርጭትና አጠቃ ምን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ተችሏል፡፡ የተዋልዶ ጤና ማስተባበሪያ ኮሚቴ በማቋቋም ሥራውን በማቀላጠፍ ላይ ይገኛል፡፡

የስልጠናና የድራማ ቡድኖች በስፋት በመቋቋማቸው የሥነሕዝብ ጉዳዮች በቀላሉ ለህዝብ በማድረስ የህዝቡን ግንዛቤ በማሳደግ ላይ ይገኛሉ በማለት ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በኢትኮ/አድቮኬሲ ሰነድ የፆታ ጉዳዮች ሰፊ ናቸው፡፡ ያለዕድሜ ጋብቻ የመሳሰሉት ከዚሁ ጋር የሚታዩ በመሆናቸው በዝርዝር አልቀረቡም፡፡ ይሁን እንጂ ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አንጻር ያለዕድሜ ጋብቻም ተካቶ ሊቀርብ የሚችል ጉዳይ ነው የሚል አስተያየት ቀርቧል፡፡

በተለይ ከኢትኮ/አድቮኬሲ አንጻር መሪዎች የሀገር አቀፍና የክልል ዕቅድ አውጭዎች የሥነሕዝብ ጉዳዮችን ቦታ ሰጥተው ከልማት ሥራ ጋር አስተሳስረው መመልከት ይኖርባቸዋል፡፡ የምናካሂደው የልማት ተግባር ከህዝብ ቁጥር ጋር

ካልተጣጣመ ዕድገት ሊታይ አይችልም፡፡ በመሆኑም የሥነሕዝብ ጉዳዮችን ለህዝብ በማድረስ ህዝብን ያሳተፈ መፍትሄ እንዲገኝ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ በውይይቱ ተብራርቷል፡፡

አንዳንድ ኃላፊዎች የሥነሕዝብ ጉዳዮችን አውቀው ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠታቸው፡፡ "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" በሚል ማለፍ ተገቢ አይሆንም፡፡ በእኛም በኩልም ቢሆን የአቀሳቀስ ስልታችን በቂ አይደለም፡፡ ስለዚህ ሊተላለፍ የሚገባው መልዕክት ምን ይሁን? በምን ዘዴ እናስተላልፈው? ለማን እናስተላልፈው የሚሉትን አበይት ጥያቄዎች ስትራተጂው መልስ የሰጠው ስለሆነ በኢትኮ/አድቮኬሲ ስትራቴጂ እየተመራን የባህርይ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማደረግ አለብን በማለት መልስ ተሰጥቶበታል፡፡

## 6. *የቡድን ውይይት*

በአውደ ጥናቱ ላይ የተገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥነሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርት፣ ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቲጂ ትውውቅ ዓውደ ጥናት ተሳታፊዎች ቅንጅቱን ለመፍጠር ማዕከላዊ (ኮር) ኮሚቴውን ለማቋቋም በሦስት ቡድኖች በመደራጀት ውይይት አካሂደዋል፡፡ በውይይታቸውም የማዕከላዊ ኮሚቴውን መቋቋም አስፈላጊነትና ሊኖረው የሚገባ የሥራ ድርሻ በተመለከተ ረዘም ላለ ጊዜ በመወያየት የኮሚቴው አባላት ሊሆኑ የሚገባቸውን ድርጅቶች መሥፈርት በማውጣት ለመምረጥ ችለዋል፡፡

### *መሥፈርቶች*

- በቀጥታ የኢትኮ/አድቦኬሲን ሥራ በሰፋት የሚሠሩ
- ከታች ከህዝብ ለመድረስ ያላቸው የመዋቅር ጥንካሬ
- የድርጅቶች አቅም/በሰው ሃይል፣ በመሣሪያ፣ በገንዘብ ወዘተ.../

## 7. *በፌደራል የሚቋቋመው ማዕከላዊ ኮሚቴ*

ሦስቱም ቡድኖች ማዕከላዊ ኮሚቴ በፌዴራል ደረጃ እንዲቋቋም ተስማምተዋል፡፡ ተመሳሳይ ኮሚቴዎች በክልል ደረጃ ተቋቁመው የኢትኮ/አድቮኬሲን ስትራቴጂ በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ታምኖበታል፡፡ በሦስቱም ቡድኖች የኮሚቴ አባላት የሚሆኑ ድርጅቶች ተጠቁመው ውይይት ከተካሄደባቸው በኋላ በጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ድርጅቶች የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት እንደሆኑ ተወስኗል፡፡

1. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
2. የግብርና ሚኒስቴር
3. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (የጤና ትምህርት ማዕከል)
4. በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት
5. በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
6. በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ላይ የተሠማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማኅበር (ኮፍፐ)
7. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት

*__የስብሰባ ጊዜ፡-__*

ኮሚቴው በየሦስት ወሩ ጠቅላላ ጉባዔው ደግሞ በዓመት አንድ ጊዜ እየተገናኘ ሥራውን እንዲከታተል የተወሰነ ሲሆን የብሔራዊ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የኮሚቴው ሰብሳቢ በመሆን እንዲያስተባብር በጉባዔው ተሰይሟል፡፡

*__የማዕከላዊ ኮሚቴው የሥራ ድርሻ፡-__*

ኮሚቴው የራሱን የሥራ ድርሻ በዝርዝር ማውጣት እንደሚችል የታመነበት ሲሆን ለመወያያ የቀረበው የሥራ ድርሻ እንዳለ ተቀብሎታል፡፡ በዚህ መሠረት፡-

1. የኢትኮ/አድቮኬሲ ስትራተጂ በሁሉም የአስፈጻሚ አካላት ዘንድ በመቀናጀት የሰው ኃይል፣ የማቴሪያልና፣ የገንዘብ ብክንት በማይኖርበት ሁኔታ ተፈጻሚ እንደሆነ ያደርጋል፡፡

2. በማዕከልና በክልል ደረጃ ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት መረጃዎችን ይሰጣል፣ ቴክኒካዊና ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3. በኢትኮ/አድቮኬሲ ፕሮጀክት አፈጻጸምን በሚመለከት በሚደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ይተባበራል፡፡

4. በየክልሉ የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ሥራቸውን በትክክል እያከናወኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

5. የኢትኮ/አድቮኬሲ ተግባር ተፈላጊ ታዳሚዎችን፣ ማቴሪያሎችንና ተስማሚ የመገናኛ ብዙሃን አጠ ቃቅምን በመለየቱ ሂደት ይሳተፋል፡፡

6. በየወቅቱ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ ሥራውን ይገመግማል፣

7. ለብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 8. *ስለዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት፡-*

- ማዕከላዊ ኮሚቴውን የማቋቋም ሥራ የዓውደ ጥናቱ ከፍተኛ ውጤት መሆኑን፣
- የተቋቋመው ኮሚቴ በአስቸኳይ ይፋ ሆኖ ሥራ እንዲጀምር
- ኮሚቴው የተቋቋመው በተሳታፊዎች ሙሉ ዕምነት በመሆኑ የሚያስደስት መሆኑ፣
- ዓውደ ጥናቱ የተሳካና የታለመለት ግብ የመታ መሆኑን በአስተያየታቸው ገልጸውታል፡፡

ወ/ሮ ገነት መንግሥቱ የብሔራዊ ሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ተ/ኃላፊ ዓውደ ጥናቱን ሲዘጉ ባሰሙት ንግግር ሁሉም ተሳታፊዎች ጊዜያቸውን በመውሰድ በዓውደ ጥናቱ መሳተፋቸውና የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን ኮሚቴ በማዋቀራቸው አመስግነዋል፡፡ የማዕላዊ ኮሚቴውን ማቋቋም ብቻ በቂ ባለመሆኑ ሁሉም ለተግባራዊ ተሳትፎው በመተባበር ዛሬ ህብረተሰቡና ልዩ ልዩ አካላት የደረሱበትን የግንዛቤ ደረጃ በማስፋት ወደ ሙሉ የባህርይ ለውጥ ማሸጋገር ይጠበቅብናል በማለት አሳስበዋል፡፡

# PROCEEDINGS OF ORIENTATION WORKSHOP ON THE NATIONAL POPULATION IEC

## AND

## ADVOCACY STRATEGY

# NATIONAL OFFICE OF POPULATION

**Ghion Hotel**
**April 4, 2002**
**Addis Ababa**

## Opening Address

The IEC and Advocacy Orientation workshop was opened by the speech of Ato Mekonnen Manyazewal, Vice Minister of the Ministry of Economic Development and Cooperation (MEDaC). In his speech he made in Amharic, Ato Mekonnen recalled the importance that the Federal Government of Ethiopia has given to the inextricable union between population and development through its population and other socio - economic policies from the very outset. He underscored that population education is the single most important activity included in the National Population Policy enabling people understand serious population issues and make decisions in all measures they take along this line. The MEDaC official pointed out that the establishment of Regional Offices of Population would enable population education reach the majority of our people in the rural areas. Ato Mekonnen lauded the population activities undertaken to implement the policy particularly in the areas of human and institutional capacity building both at the Federal and the Regional levels.

Appreciating what has been done so far in creating awareness among the people, the Vice Minister called on the workshop participants to devise a mechanism which will enable them implement the National Population IEC and Advocacy Strategy jointly in a coordinated manner in a momentum similar to that they applied to the development of their common guideline during their group discussions. He concluded his speech by thanking all those who have helped in making the IEC and Advocacy Strategy a reality.

## Welcome speech

In her welcome address to invited guests and workshop participants earlier, in Amharic, Acting Head of the National Office of Population, W/O Genet Mengistu, refreshed the memories of her audience by recalling the fact that her Office has been doing basic coordination of population activities, previously carried out in a disorganized or fragmented manner by different concerned organizations, since the launching of the National Population Policy. She brought to the attention of her audience that her Office has been trying in the last few years to implement the purposes listed out in the policy document. According to the Acting NOP Head, Population Offices established in all Regions and Administrative councils of the country are discharging their duties of coordinating population activities in their respective areas. She added that they are also involved in the implementation of the UNFPA Fourth Country Programme Projects.

The Acting NOP Head expressed hope that the workshop will devise a mechanism that will facilitate the implementation of the Country Programme lying ahead using the Strategy document as a guideline or as a framework to action.

She made specific reference to issues of major concern in population activities on which the Strategy document has focussed as being Reproductive Health and, Population and Development. It was mentioned in the welcome speech that the implementation of the strategy document will take Ethiopia's population IEC & Advocacy activity one step foreword by a shift in population education from sensitization and awareness creation to attitudenal and behavioural change.

The NOP Official told her audience that the strategy document which is a general framework for systematic and sustained IEC & Advocacy work in population education is subject to revision that incorporates feed backs expected to be received and experiences to be gained over the coming years of its application.

Ethiopia's current major health concern, HIV/AIDS is singled out in the welcome address as one of the main population issues in the field of Reproductive Health included in the strategy document.

The Acting Head of the NOP acknowledged that different implementing organizations have actively participated in a workshop previously conducted at this same venue to develop the strategy document to be launched by this very workshop and made substantial contributions by giving constructive and fruitful suggestions on different occasions. W/O Genet also acknowledged the contribution made by UNFPA in availing its professionals to play pivotal roles in the preparation of the document as members of the National Population IEC & Advocacy Strategy development task force, in addition to financial support. The NOP Official gave recognition to the contribution of the National Professional Project Personnel at her Office noting their major effort in making the document a reality. She wound up her welcome address by taking the opportunity to thank all of those mentioned above and all others who had roles in the development of the document. W/O Genet then called upon His Excellency the Vice Minister of the Ministry of Economic Development and Cooperation to open the orientation workshop.

A brief introductory speech was earlier made by Ato Hiruy Mitiku, IEC/Advocacy Department Head of NOP. He lauded the workshop participants by breaking them the news that the National Population IEC & Advocacy Strategy document in whose design and development they have greatly participated has been finalized at long last and that they should feel proud and honored that the effort they have exerted has beared fruit.

After telling participants the goals of the strategy document's two components - IEC & Advocacy and their complementary roles in supporting the implementation of Reproductive Health, and Population and Development interventions, he added that the strategy shows how the two components support the two thematic areas.

The department head promoted the fact that the details of the strategy document will be discussed by two population professionals at this workshop.

Ato Hiruy at last disclosed the purpose of the workshop to be the formation of an IEC & advocacy Coordination Committee, composed of stakeholders, whose task would be overseeing the effective implementation of the strategy.

He then invited the Acting Head of the National Office of Population to welcome invited guests and workshop participants as reported above.

## Remark of UNFPA Representative
## Dr. Benson Morah

The UNFPA official started his remark by describing the orientation workshop "as the culmination of a rather long process of formulating, reviewing, finalizing and (now) launching of the National Population IEC and Advocacy Strategy." After substantiating his statement by going into the background s'ory of the document Dr. Morah expressed his satisfaction that the "very important exercise" has finally come to the conclusion. He added that he is pleased also because his organization was able to provide to the Ethiopian government the required financial and technical expertise to make the conclusion of the long breath-taking endeavour possible. He underscored the importance UNFPA attaches to the development and implementation of such documents.

Dr. Morah particularly commended every step of the process adopted in the formulation of the document.

The UNFPA official expressed confidence that the contents of the document will serve the purposes for which they have been developed: providing a framework for implementing IEC and Advocacy interventions addressing key issues in Reproductive Health as well as Population and Development. He added that the contents of the document would also provide a sound basis for conducting IEC and Advocacy activities as well as to address key issues in programme implementation.

Continuing his remark the population professional attested that the contents of the document are the basis for many of the intervantintions in projects included in the Fourth Country Programme.

Dr. Morah expressed hope that the provisions of the document will help in redressing weaknesses in RH/IEC encountered in the implementation of the Health Sector Development Programme. He also expressed hope that awareness and use of this document by all concerned government departments, donors, NGOs and other actors in the area of population will make constructive

contributions in the transition from awareness creation to making lasting attitudinal, behavioural as well as policy and programme changes.

The UNFPA Country Representative to Ethiopia concluded his remark by extending his appreciation to all who participated in the formulation of the strategy document.

Following the remark W/O Genet Mengistu thanked the UNFPA official and called on the General Manager of the Health Education Centre of the Ministry of Health, Ato Gebre Medhin Kidane Mariam to make an opening remark.

# Remark by the Head of the Health Education Centre of the Ministry of Health Ato Gebre Medhin Kidane Mariam

The last person to give his remark on the opening ceremony of the National Population IEC and Advocacy Strategy Orientation workshop was Ato Gebre Medhin Kidane Mariam, Head of the Health Education Centre of the Ministry of Health. In his remark the health official said that the strategy document, taken as a guiding principle has been developed to enhance an effective and quality Reproductive Health service in Ethiopia. He disclosed to the participants of the workshop and guests that his ministry has fully participated in the preparation and final development of the document cognisant of the need to have a National Population IEC and Advocacy Strategy.

Referring from the strategy document itself Ato Gebre Medhin said that the main objective of the strategy is to help enable the public to make use of all available Reproductive Health services and finally own it. He expressed belief that his ministry will fully benefit from the document in all its Reproductive Health services at all levels. The Health Education Centre head assured his audience that his department would use the document through its institutional arrangement as a guideline for smooth coordination with all stakeholders to develop and produce relevant educational materials.

Ato Gebre Medhin brought his remark to conclusion by reassuring the fact that his ministry will receive the invitation to all actors in population issues to work in harmony in the common cause of the implementation of the National Population IEC and Advocacy Strategy.

W/O Genet Mengistu, Acting Head of National Office of Population thanked the General Manager and requested participants to go out for coffee break.

## Session 1

The first session of the one-day workshop was covered by the presentation of Ato Asres Kebede, NOP - IEC & Advocacy consultant. The topic of the presentation was "The National Population IEC and Advocacy Strategy Document: Background and Content."

Aided by transparencies, the National POP/IEC and Advocacy consultant at the National Office of Population (NOP), has outlined the strategy document within thirty minutes.

In his outline he said that a comprehensive IEC and Advocacy strategy is a cornerstone in the implementation of population programmes because it provides the basis for the identification of issues, setting behavioural change and institution building objectives, selection of audience, motivating messages and setting the criteria for the evaluation of impact.

Going into the background of the development of the Ethiopian National POP - IEC and Advocacy strategy document he said that it was the result of several internal and external events in population and development. He listed the adoption of four social policies including the National Population Policy to be among the historic events.

Proceeding into the process of the development Ato Asres mentioned the formation of a National IEC & Advocacy Strategy Development taskforce under the IEC department of NOP to carryout the drafting of the document with the participation of consultants and the UNFPA staff in Ethiopia.

He recalled that the taskforce had to review a number of studies and material including three background papers.

The consultant said that as a result of work and review of a number of commissioned and non commissioned studies and other relevant material the

task force identified opportunities and constraints some of which were concerning constraints:

- An IEC coordination mechanism at an early stage of development;
- Lack of a strategic approach in the identification of population IEC/Advocacy issues, in the setting goals and objectives, in the identification and segmentation of audiences, in the selection of messages and media, as well as in monitoring and evaluation;
- Lack of a clear demarcation of functions among coordinating, implementing and technical support institutions, as well as lack of adequate integration of IEC interventions with the mainstream of activities of implementing organizations;
- Inadequacies in human power, material and financial resources, linkage to progammes, as well as research;
- Low status of women and lack of appreciation of gender issues;
- Problems of physical access to communication infrastructure and were singled out;
- Weak institutional arrangements;

With regard to opportunities:

- Policy consensus supporting broad based IEC;
- Regionalization and decentralization; and
- Cultural and ethnic diversity were identified.

Ato Asres reiterated that a consensus was reached on the orientation and key elements of the strategy by all stakeholders who met in a population IEC and Advocacy Strategy Development workshop conducted at the Ghion Hotel in October 1996.

The other major sub-topics treated by the consultant were some of the purposes of the strategy as well as components of the two thematic areas or sub-programmes: Reproductive Health (RH) and Population and Development. He said the purposes of the strategy are, among others, to give a framework for implementing interventions in IEC and Advocacy concerning key issues; providing a sound theoretical, practical and effective methods for conducting IEC & Advocacy activities and finally addressing key issues in programme implementation and management encompassing institutional arrangements, supervision, monitoring and evaluation.

Listed in the presentation, as components of RH are safe motherhood, family planning, STIs including HIV/AIDS, access and quality of RH services and care, gender issues and harmful traditional practices.

The components of Population and Development thematic area mentioned are rapid population growths, implementation of the National Population Policy, Gender and Development, research/data collection and dissemination, youth and development as well as other population policy priorities.

According to Ato Asres, the strategic planning framework for the IEC and Advocacy programme is a six-point structure. As outlined by the presenter the first three of the points are issues, programme goals, IEC and Advocacy objectives. The fourth framework includes IEC activities among primary and secondary audiences, advocacy activities among beneficiaries, partners, adversaries and decision makers; IEC messages to primary and secondary audiences, advocacy messages to beneficiaries, partners, adversaries and decision makers as well as the selection and use of media to the concerned segment of the population or the target audience. The fifth framework as referred by Ato Asres is research, monitoring and evaluation of indicators and methodologies. The last in the list of framework are implementing institutions which are line ministries and implementing partners accommodating NGOs.

The NOP consultant concluded his presentation after listing out the concepts and principles underlining the strategy. These, he said, are focus on behaviour change, regions and the community; linking IEC and advocacy with services; reaching ultimate or primary audiences; going to scale (joining hands by sharing cost in the production of materials and/or provision of services to be mutually cost effective) and finally, quality control and assurance.

## Session 2

The second presenter/facilitator Mr. Duah Owusu Sarfo took off by illustrating the meaning of advocacy with a short story. Narrating his story the UNFPA Deputy Country Representative had the following to say:

I have a very short story to tell.

There was this man who was married to an illiterate. And the couple were invited to a party. Before they started eating, the man saw that his wife had the knife in her left hand and the fork in her right hand.

The man felt there was problem in that sort of arrangement. Very quickly he shouted to everybody in the room that in his culture, before one eats it was very important to pray. And for them to pray before they start eating. And then he convinced them to abide by it. It was a trick. He just then asked them to bow their heads. They all did that. In the process, he whispered to the wife to change the cutlery - put the fork from her right to her left and the knife from her left to her right hand. After the wife had done that, he told them to raise their heads and start eating.

The lesson to be learnt from this short story is that the man realized the problem. The man also realized that he needed some partners to agree with him on a certain cause. So through that he was able to solve the problem of the wife. This is some form of what you call advocacy. This man firstly, identified the problem. Secondly, he was able to convince people in the room to agree with him, to reach a consensus with him. This is a form of advocacy. So I want you to conceptrialize what advocacy is.

The theme of his presentation was "The National IEC and Advocacy Strategy. Implementation and the African Experience".

Mr. Duah presented his paper with the aid of transparencies mounted on an overhead projector.

